ታማኝ ሁን

የ1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ፥ የቲቶና የፊሊሞና መልእክቶች

እንዴት አድርገን ለቃሉ፥ ለሥራችንና እርዳታችንን ለሚሹ ታማኝ እንደምንሆን

ጽሑፍ፡- በዋረን ዌርዝቢ
ትርጉም፡- በመስፍን ታዬ
እርማት፡- በግርማዊና በፍቃዱ ገብሬ

Copyright © 2000 by SIM Ethiopia. Originally published in English under the title of BE FAITHFUL, copyright © 1981 by SP Publications, Inc. ChariotVictor Publishing, 4050 Lee Vance View, Colorado Springs, Colorado 80918 U.S.A.
All rights reserved.

ማውጫ

መቅድም ገጽ

የ1ኛ ጢሞቴዎስ አስተዋጽኦ

1. በሥራው ላይ መቆየት (1ኛ ጢሞ. 1) 1
2. አገልግሎት ወይስ የመድረክ ትዕይንት (1ኛ ጢሞ. 2) 13
3. መሪዎችን ተከተል (1ኛ ጢሞ. 3) 26
4. የእግዚአብሔር ሰው መሆን እንዴት እንደሚቻል (1ኛ ጢሞ. 4) 39
5. የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት (1ኛ ጢሞ. 5) . . 52
6. ከበላይ አካላት የሚተላለፉ ትእዛዛት (1ኛ ጢሞ. 6) 65

የቲቶ መልእክት አስተዋጽኦ

7. የኛ ሰው በቀርጤስ (ቲቶ 1) 79
8. ጤናማ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊኖረን እንደሚችል (ቲቶ 2-3) 90

የ2ኛ ጢሞቴዎስ አስተዋጽኦ

9. የበረቱ ክርስቲያኖች (2ኛ ጢሞ.1) . . . 104
10. ሁኔታውን ማወቅ (2ኛ ጢሞ. 2) 117
11. ከማለቁ በፊት ምን ማድረግ እንደሚገባ (2ኛ ጢሞ. 3) 129
12. የመሰነባበቻ ቃላት (2ኛ ጢሞ. 4) 141

የፊሊሞና መልእክት አስተዋጽኦ

13. የሁለት ከተሞች ታሪክ 154

መቅድም

ጢሞቴዎስ በኤፌሶን ውስጥ ባለችው ቤተ ክርስቲያኑ በጣም ደስተኛ አልነበረም። እንዲሁም ቲቶ በቀርጤስ ደሴት ላይ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነበረ። ጳውሎስ ለሁለቱም ሰዎች እንዲህ አላቸው፡- «ታማኝ ሁኑ! ምን ጊዜም ግቡ ሳይደርስ ተስፋ ቆርጦ ሩጫውን መተው አይገባም።»

ጳውሎስ ዛሬም ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ይህን መልእክት እንዲሰሙና በአንክሮ እንዲያስቡበት ይፈልጋል። እባካችሁ እነዚህ የመጋቢነት መልእክቶች ለመጋቢዎችና ለሌሎች «የሙሉ ጊዜ ክርስቲያን አገልጋዮች» ብቻ ናቸው ብላችሁ አታስቡ። እነዚህ ሦስት ደብዳቤዎች ለሁሉም ክርስቲያንና ለእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል የተጻፉ ናቸው።

ጳውሎስ በግሪክ ቃል «ፒስጦስ» ወይም «ታማኝ» የሚለውን ቃል በእነዚህ ሦስት ደብዳቤዎች ውስጥ ቢያንስ አሥራ ሰባት ጊዜ ያህል ተጠቅሞአል። ይህ አቢይ አሳብ በየምዕራፉ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ይቀጥላል። ለቃሉ ታማኝ ሁን፤ ለምትሠራው ሥራ ታማኝ ሁን፤ ለምታገለግላቸው ሰዎች ታማኝ ሁን። እግዚአብሔር ታማኝ ነውና።

በፊሊሞና መጽሐፍ ላይ አንድ ተጨማሪ ምዕራፍ አክያለሁ። ምንም እንኳ ፊሊሞና መጋቢ ባይሆንም፥ ጳውሎስ ለእርሱ የጻፈው መልእክት ከዚህ መጽሐፍ ዋና አሳብ ጋር በትክክል ይዛመዳል። ፊሊሞና በኮበለለው ባሪያው በአናሲሞስ የተነሣ ከችግር ላይ ወድቆ ነበር። ስለዚህም የጳውሎስ ምክር ፊሊሞና ያንን ችግር በመፍታት ለጌታ ታማኝ እንዲሆን አበረታታው። ይህ ደብዳቤ፥ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ያደረገውን ነገር በሥዕላዊ መግለጫ የሚያቀርብ ግሩም ታሪክ ነው።

የዊተን ኮሌጅ ፕሬዚዳንት የነበሩት ዶክተር ሬይሞንድ ኤድማን ክርስቲያኖችን እንዲህ ብለው ያሳስቡ ነበር። «ምን ጊዜም ግቡ ሳይደርስ ተስፋ ቆርጦ ሩጫውን መተው አይገባም»። እውነታቸውን ነበር። የርሳቸውን ምክር ለመከተል የደፈርነውም ሰዎች፥ እግዚአብሔር መቆየት የምንችልበትን ኃይል እንደሚሰጠን ለማወቅ በቅተናል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሁለት አበይት አላማዎችን እንድታከናውኑ እፈልጋለሁ፡- 1ኛ) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ለመረዳት እንድትችሉ እና 2ኛ) ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ ጋር የጠበቀ ኅብረት

እንዲኖራችሁ ለማበረታታት ነው። እኔና እናንተ እግዚአብሔር ለሰጠን ሥራ ታማኞች ከሆንን፥ የእርሱ ሥራ በስኬታማነት ይከናወናል፤ ስሙም ይከበራል። ከዚህ የበለጠ ምን መጠየቅ እንችላለን?

ዋረን ዌርዝቢ

የጳውሎስን የሕይወት ታሪክ ቅደም ተከተል በተመለከተ አጭር ልዩ ማስታወሻ

በ57 ዓ.ም. አካባቢ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ታስሮ ነበር። እንዲሁም ለሁለት ዓመታት ያህል በቂሳርያ በእስር ቤት ይጠበቅ ነበረ (የሐዋ. 21፡19-26፡32 ተመልከቱ)። በቄሳር ፊት ቆሞ መልስ ለመስጠት ጳውሎስ ሮም የሄደበት ጉዞ የተጀመረው በመስከረም 59 ዓ.ም. ነበረ። መርከብ ተሰብሮ ማልታ በምትባለው ደሴት የሦስት ወራት ቆይታ ካደረገ በኋላ፥ በ60 ዓ.ም. በየካቲት ወር ሮም ደረሰ (ሐዋ. 27-28 ተመልከቱ)። ከዚያም ራሱ በተከራየው ቤት ለማገልገል ነጻነት አግኝቶ ኖረ።

ጳውሎስ ከተከሰሰበት ክስ ነጻ በመሆን ለተከታዮቹ ለሁለት ዓመታት በተለያዩ ቦታዎች ከማገልገሉም በተጨማሪ፥ 1ኛ ጢሞቴዎስንና ቲቶን ጻፈ።

በ65 ዓ.ም. አካባቢ እንደገና ታሰረ። በዚህም ጊዜ በጨለማ ክፍል ውስጥ እንዲቀመጥ ተበየነበት። የመጨረሻ ደብዳቤው የሆነውን 2ኛ ጢሞቴዎስ የጻፈው ከዚያ በኋላ ነበር።

ኤፌሶን፥ ፊልጵስዩስ፥ ቆላስይስ፥ እንዲሁም ፊሊሞና የተጻፉት መጀመሪያ ሮም ውስጥ ታስሮ ሳለ ነበር።

የ1ኛ ጢሞቴዎስ አስተዋጽኦ

ዋና አሳብ፡- የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት እንዴት ማስተዳደር እንደሚቻል (3፡15)

1. ቤተ ክርስቲያንና መልእክቷ፡- ምዕራፍ 1

   1፡1 ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት ማስተማር (1፡1-11)

   1፡2 ወንጌልን ማሰራጨት (1፡12-17)

   1፡3 እምነትን ከጥቃት መከላከል (1፡18-20)

2. ቤተ ክርስቲያንና አባሎችዋ፡- ምዕራፍ 2-3

   2፡1 የሚጸልዩ ወንድሞች (2፡1-8)

   2፡2 የሚታዘዙ እህቶች (2፡9-15)

   2፡3 ብቁ የሆኑ መጋቢዎች (3፡1-7)

   2፡4 ብቁ የሆኑ ዲያቆናት (3፡8-13)

2:5 ሰናይ ምግባር የተላበሱ ምዕመናን (3:14-16)
3. ቤተ ክርስቲያንና አገልጋይዋ:- ምዕራፍ 4
3:1 ቃሉን የሚሰብክ መልካም አገልጋይ (4:1-6)
3:2 በቃሉ የሚኖር ፈሪሃ-እግዝኢአብሔር ያደረበት አገልጋይ (4:7-12)
3:3 በቃሉ የሚያድግ አገልጋይ (4:13-16)
4. ቤተ ክርስቲያንና አገልግሎቷ - ምዕራፍ 5-6
4:1 በዕድሜ የገፉ አባሎች (5:1-2)
4:2 በዕድሜ የገፉ ባልቴቶች (5:3-10)
4:3 ለወጣት ባልቴቶች (5:11-16)
4:4 ለቤተ ክርስቲያን ሹማምንት (5:17-25)
4:5 ለአገልጋዮች (ባሪያዎች) (6:1-2)
4:6 ለሐሰተኛ አስተማሪዎች (6:3-10)
4:7 ለመጋቢው (6:11-16፤ 20-21)
4:8 ለሐብታሞች (6:17-19)

በሥራው ላይ መቆየት

1ኛ ጢሞቴዎስ 1

«ለትንሽ ደመወዝ፥ ለሚሸነቁጥ ብርድ፥ ለረኽም የጨለማ ወራት፥ ለማያቋርጥ አደጋ፥ በኋላም መመለስ አጠራጣሪ ለሆነበት አደገኛ ጉዞ ወንዶች ይፈለጋሉ። በዚህም ሁሉ ስኬታማ ሆነው ካለፉም ክብርና ዝና ያገኛቸዋል»።

ይህ ማስታወቂያ በለንደን ከተማ በአንድ ጋዜጣ ላይ ወጥቶ ብዙ ሺህ ወንዶች አመልክተው ነበር። ማስታወቂያው ተፈርሞበት የነበረው፥ በሰር አርነስት ሻክለተን በተባሉ ታዋቂ የሰሜን ዋልታ አሳሽ ስለነበረ ማስታወቂያውን ልዩ አደረገው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሠራተኞች ማስታወቂያ አውጥቶ ቢሆን ኖሮ፥ ማስታወቂያው ከዚህ በታች የቀረበውን ሊመስል ይችል ነበር፡-

«ለቤተ ክርስቲያኔ ግንባታ ሥራ አስቸጋሪ የእገዛ ተግባር ለማከናወን የሚችሉ ወንዶችና ሴቶች ይፈለጋሉ። ብዙ ጊዜ አብረዋችሁ የሚሠሩት እንኳ ሳይቀሩ አይረዷችሁም። ከማይታይ ጠላት የማያቋርጥ ውጊያ ይገጥማችኋል። ምናልባት የድካማችሁን ዋጋ አታዩም ይሆናል። ሥራችሁ በሙሉ እስካልተጠናቀቀ ድረስ ሙሉ ሽልማታችሁንም አታገኙም። ይህ ሥራ ምናልባት ቤታችሁን፥ ፍላጎታችሁን፥ ሕይወታችሁን ሳይቀር ያስከፍላችሁ ይሆናል።»

ከእነዚህም የመመዘኛ ነጥቦች ባሻገር፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለንተናቸውን በደስታ ለእርሱ የሚሰጡትን የብዙ ሰዎች «ማመልከቻ» ይቀበላል። እርሱ በእርግጥ ማንም ሰው ሊሠራለት የሚችል ከሁሉም በላይ የላቀ ጌታ ነው። ቤተ ክርስቲያንን የመገንባቱ ሥራም አንድ አማኝ ሕይወቱን ሊሰጥ የሚችልበት ከሁሉም የላቀና ወደር የማይገኝለት ተግባር ነው።

ጢሞቴዎስ፥ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ ግንባታ ሥራ የበኩሉን እገዛ እንዲያደርግ ላቀረበለት ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ የሰጠ አንድ ወጣት ነበር። እርሱ ከሐዋርያው ጳውሎስ ልዩ ረዳቶች አንዱ ነበር። ከቲቶ ጋራ በመሆን፥ ጢሞቴዎስ ጳውሎስ በመሠረታቸው አቢያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለአንዳንድ አስቸጋሪ ጉዳዮች መፍትሔ ሸቷል። ጢሞቴዎስ

ያደገው ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ በሚካሄድበት ቤተሰብ ውስጥ ሲሆን (2ኛ ጢሞ. 1፡5)፥ በክርስቶስ ወዳለው እምነት የመጣውም በራሱ ጳውሎስ ምስክርነት ነበር። ይህ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለምን፡- «በእምነት እውነተኛ ልጄ» እንዳለው ያስረዳል (1ኛ ጢሞ. 1፡2)።

ጢሞቴዎስ የተወለደው ከሁለት የተለያዩ ዘሮች ነበር። እናቱ አይሁዳዊት ስትሆን፥ አባቱ ግሪካዊ ነበር። ለክርስቶስ በጣም የተሰጠ ስለነበረ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ መሪዎች ለጳውሎስ ነገሩለት። ጳውሎስም ለሚስዮናዊ አገልግሎቱ ተጨማሪ ሠራተኛ አድርጎ ተቀበለው (የሐዋ. 16፡1-5)። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለዚህ አገልግሎቱ እንደተመረጠ ብዙ ጊዜ ያስታውሰው ነበር (1ኛ ጢሞ. 1፡18፤ 4፡14)። ጢሞቴዎስ ለጌታ ታማኝ ነበረ (1ኛ ቆሮ. 4፡17)። እንዲሁም ለእግዚአብሔር ሕዝብ በቅንነት የሚጨነቅ ሰው ነበረ (ፊሊ. 2፡20-22)።

ነገር ግን ከተቀበለው ጥሪ፥ ከጳውሎስ ጋር ከነበረው ጥብቅ ግንኙነትና ከተሰጡት መንፈሳዊ ስጦታዎች ባሻገር፥ ጢሞቴዎስ በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጥ ሰው ነበር። ጳውሎስ ከጢሞቴዎስ ጋር ሊሰነባበት በደረሰ ጊዜ፥ በኤፌሶን እንዲቆይና ሥራውን እንዲጨርስ አበራቶት ነበረ (1ኛ ጢሞ. 1፡3)። በግልጽ እንደሚታየው፥ ጢሞቴዎስ የጤና ችግሮችና (1ኛ ጢሞ. 5፡23) ተስፋ የቆረጠባቸው ጊዜያት ነበሩት። ስለዚህም የተወሰኑ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን መጋቢያቸውን እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ አድርገው በመቁጠር ተገቢውን አክብሮት እንዳልሰጡት ለመመልከት ይቻላል (1ኛ ጢሞ. 4፡12፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡6-8)።

ኤፌሶን አንድን ቤተ ክርስቲያን በመጋቢነት ለማገልገል ቀላል ቦታ አልነበረችም። («ቀላል ቦታዎች» ይኖራሉን? መኖራቸውን እጠራጠራለሁ)። ከተማይቱ ዲያና በተባለች የዝሙት ጣዖት አምልኮ የተሞላች ነበረች። የወሲብ ፍላጎት የሚቀሰቅሰው ምስሏ ማንኛውንም ዓይነት የዝሙት ተግባር ለማከናወን ረድቷል (የሐዋ. 19 ተመልከት)። ጳውሎስ በሦስት ዓመት አገልግሎቱ በኤፌሶን ትልቅ ሥራ ስላከናወነ፥ በእስያ የኖሩት ሁሉ የጌታ ኢየሱስን ቃል ሰሙ (የሐዋ 19፡10)። እንደ ጳውሎስ ያለውን ሰው ለመከተል ለጢሞቴዎስ ቀላል አልነበረም! መንፈሳዊ በር በተከፈተበት ቦታ ሁሉ ሰይጣናዊ እንቅፋቶች ስላሉ (1ኛ ቆሮ. 16፡8-9)፥ በእርግጥ በከተማይቱ ውስጥ ሰይጣን የራሱ ሠራተኞች ነበሩት።

ጳውሎስ የመጀመሪያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ የምንለውን ደብዳቤ የጻፈው፥ ጢሞቴዎስን ለማበረታታት፥ አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደምትተዳደር ለማብራራትና እንደ እግዚአብሔር አገልጋይነቱ የራሱን ሥልጣን ለመግለጽ ነው። በመጀመሪያው ምዕራፍ፥ ጳውሎስ በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ መጋቢና ሕዝቡ ያላቸውን 3 ኃላፊነቶች አስረድቷል።

1. ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት አስተምር

(1ኛ ጢሞ. 1፡1-11)

ጳውሎስ በደብዳቤው የሰላምታ ክፍል ውስጥ እንኳን፥ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ እንደ መሆኑ መጠን የነበረውን ስልጣን ያረጋግጣል። የጳውሎስ ሥልጣን ከእግዚአብሔር የተሰጠ በመሆኑ፥ በጢሞቴዎስ ላይ ችግር ይፈጥሩ የነበሩ ሰዎች መጋቢያቸው እዚያ የተገኘው እግዚአብሔር በዚያ ስላስቀመጠው እንደሆነ ማስታወስ ነበረባቸው። ጳውሎስ እግዚአብሔር በልዩ ተልዕኮ የላከው «ሐዋርያ» ነበረ። ሐዋርያነቱ በኢየሱስ ክርስቶስ «ትእዛዝ» የመጣ ነው። ይህ ቃል «ንጉሣዊ ተልዕኮ» ማለት ነው። በመሆኑም ጳውሎስና ጢሞቴዎስ ሁለቱም በነገሥታት ንጉሥ የተላኩ ነበሩ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ብቻ ሳይሆን፥ በመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ አሥር ጊዜ እንደተጠቀሰው «አዳኛችን»ም ነው (1ኛ ጢሞ. 1፡1፤ 2፡3፤ 4፡10፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡10፤ ቲቶ 1፡3-4፤ 2፡10፥ 13፤ 3፡4፥ 6)። ተስፋ ለቆረጠው ጢሞቴዎስ «ተስፋችን» (1ኛ ጢሞ. 1፡1) የሚለው አባባል እውነተኛ መመኪያ ነበረ። ጳውሎስ ለቲቶም ተመሳሳይ ማበረታቻ ጽፎ ነበረ (1፡2፤ 2፡13፤ 3፡7)። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚመጣልን ማወቅ፥ በታማኝነት እንድናገለግለው ያበረታታናል።

ክርስቲያን አገልጋዮች በሥራው መጽናት ከሚኖርባቸው ምክንያቶች አንዱ፥ የሐሰት አስተማሪዎች ክርስቲያኖችን ለማጥመድ ስለሚሯሯጡ ነው። በዚህ ዘመን እንዳሉት ሁሉ በጳውሎስም ጊዜ ሐሰተኛ ትምህርት የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ነበሩ። ስለዚህ ቸል ልንላቸው አይገባም። እነዚህ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ለጠፉት ኃጢአተኞች መልካም ዜና የላቸውም። እንደውም ክርስቲያኖችን ወደ ጥፋት ከመምራታቸውም ሌላ ለራሳቸው ዓላማዎች ያጠምዱዋቸዋል።

ጳውሎስ ጢሞቴዎስና አብረውት የሚሠሩ ሰዎች የችግሩን አሳሳቢነት እንዲገነዘቡ ለመርዳት በወታደራዊ ቋንቋ ተጠቅሟል (1ኛ

ጢሞ. 1፡3)። «ትእዛዝ» ማለት ከፍ ካለ ባለ ሥልጣን የሚሰጥ ጠንካራ መመሪያ ነው። ጳውሎስ ይህንን ቃል ለጢሞቴዎስ በጻፋቸው በሁለቱ መልእክቶቹ ውስጥ ስምንት ጊዜ ያህል ተጠቅሞበታል (1ኛ ጢሞ. 1፡3፥ 5፥ 18፤ 4፡11፤ 5፡7፥ 6፡13፥ 17፥ 2ኛ ጢሞ. 4፡1)። የሚከተለውን አሳብ ነበር የሚያስተላልፈው፡- «ጢሞቴዎስ አንተ በአስቸጋሪ ከተማ ውስጥ ያለች የአንዲት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ብቻ ሳትሆን፥ ከንጉሡ ዘንድ በሚመጡ ትእዛዛት ሥር የምትተዳደር ክርስቲያን፥ ወታደርም ነህ። አሁንም እነዚህን ትእዛዛት በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ለሚገኙ ወታደሮች አስተላልፍ!»

ትእዛዙ ምን ነበረ? ጳውሎስ ካስተማራቸው የተለዩ ትምህርቶች አታስተምሩ!። በመጀመሪያ መጽሐፍ ውስጥ በሚገኙ ሦስት የመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ፥ «ትምህርት» «አስተምር» «አስተማሪ፥» «ያስተምራል» እና «ማስተማር» ለሚሉት ቃላት ሠላሳ ሁለት ማጣቀሻዎች አሉ። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ አማኞች የእግዚአብሔር ቃልና መሠረታዊ የክርስትና ትምህርቶችን ትርጉም ይማሩ ነበር። ዛሬ በብዙ አቢያተ ክርስቲያናት፥ መድረኩ የመንፈሳዊ መገለጥና የሙላት ሳይሆን፥ የመዝናኛ ቦታ ነው።

እግዚአብሔር የቃሉን እውነት ለጳውሎስ ሰጥቶ ነበር (1ኛ ጢሞ. 1፡11)። ጳውሎስ ደግሞ ለጢሞቴዎስ ሰጠው (6፡20)። እምነቱን መጠበቅ (2ኛ ጢሞ. 1፡14) እና ለታመኑ ሰዎች አደራ መስጠት (2፡2) የጢሞቴዎስ ኃላፊነት ነበር።

ሐሰተኛ ትምህርትን ጳውሎስ «ተረትና መጨረሻ የሌለው የትውልዶች አፈ ታሪክ» አድርጎ ያቀርባል (1ኛ ጢሞ. 1፡4)። ቲቶም ተመሳሳይ የሆነ ሐሰተኛ ትምህርት በቀርጤስ አጋጥሞት ነበር (ቲቶ 1፡14፤ 3፡9)። ሐሰተኛ አስተማሪዎች የብሉይ ኪዳንን ሕግ፥ በተለይም የትውልዶችን ታሪክ ሁሉንም ዓይነት ልብ ወለድ ታሪክ ለመፍጠር ይጠቀሙበት ነበረ። እነዚህ አዳዲስ ትምህርቶች ሕዝቡን ወደ ስሕተት ይመሩ ነበር። የሐሰት አስተማሪዎቹ ጥያቄዎችን ያነሳሉ እንጂ ምላሾችን አያቀርቡም ነበር። እነዚህ ሰዎች ሕዝቡን ከእውነት የሚያርቁ እንጂ፥ «በእምነት ለሚደረገው ለእግዚአብሔር [የማዳን] ሥራ» (1ኛ ጢሞ. 1፡4) የሚፈርዱ አልነበሩም። እነዚህ የፈጠራ ትምህርቶች ፍቅርን፥ ንጽሕናን፥ በጎ ሕሊናንና ቀና እምነትን ከመፍጠር ይልቅ፥ መለያየትን ግብዝነትንና ሁሉንም ዓይነት ችግሮች እየፈጠሩ ነበር።

ጳውሎስ «ሕሊና» የሚለውን ቃል ሃያ አንድ ጊዜ በመልእክቶቹ ውስጥ ተጠቅሞአል። ከእነዚህም ውስጥ ስድስቱ የሚገኙት በመጋቢነት መልእክቶቹ ውስጥ ነው (1ኛ ጢሞ. 1፡5፥19፤ 3፡9፤ 4፡2፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡3፤ ቲቶ 1፡15)። «ሕሊና» የሚለው ቃል «ማወቂያ» ማለት ነው። ሕሊና ስንሳሳት የሚወቅሰንና በትክክል ስንሠራ ትክክለኛነታችንን የሚያረጋግጥልን ውስጣዊ ፈራጅ ነው (ሮሜ 2፡14-15)። የሕሊናን ሕግ በመተላለፍ ኃጢአት መሥራት ይቻላል፥ ይህም ሲሆን ሕሊናችን ይረክሳል (ቲቶ 1፡15)። የተደጋገመ ኃጢአት ሕሊናን ስለሚያደነድነው፥ በሰውነት ላይ እንደ ተቃጠለ ጠባሳ ሆኖ ይቀራል (1ኛ ጢሞ. 4፡2)።

ክርስቲያኖች «ጤናማ ትምህርት» (1ኛ ጢሞ. 1፡10) በመቃወም ሲሳሳቱ ማየት አሳዛኝ ነው። እንዲሁም ጳውሎስ «እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚስማማ ትምህርት» (6፡3)፥ «ጤናማ ቃል» (2ኛ ጢሞ. 1፡13)፥ «ሕይወት የሚገኝበት ትምህርት» (4፡3፤ ቲቶ 1፡9፤ 2፡1)፤ «እምነት» (1፡13፤ 2፡2) እና «የማይነቀፍ ንግግር» (2፡8) በማለት ይጠራዋል፤ ዳሩ ግን ብዙዎች በሰዎች ሕይወት ውስጥ ቅድስና የሚያስገኘውን የእግዚአብሔርን ንጹሕ ቃል ትተው፥ የልብ ወለድ ፈጣሪዎች የሚያስተምሩትን «ከንቱ ንግግር» ይመርጣሉ (1ኛ ጢሞ. 1፡6)። ዛሬ «ከንቱ ንግግር» በስብከትና በትምህርት ብቻ ሳይወሰን፥ በመዝሙርም ውስጥ መኖሩ የሚያሳዝን ነው። በጣም ብዙ መዝሙሮች ምንም ትምህርት አለማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን፥ የስሕተት ትምህርትም ያስተምራሉ። አንድ አስተማሪ ውሸት ለማስተማር መብት እንደሌለው ሁሉ ዘማሪውም ውሸት ለመዘመር መብት የለውም።

ለዚህ ሐሰተኛ ትምህርት ምክንያቱ የብሉይ ኪዳንን ሕግ አለአግባብ መጠቀም ነው። እነዚህ ሐሰተኛ አስተማሪዎች የእግዚአብሔርን ሕግ ይዘትም ሆነ ዓላማ አልተረዱም ነበር። አማኞችን ከጸጋ ነጻነት (ገላትያ 5፡1) ወደ ሕግ ባርነት እየመሩ ነበሩ። ይህ ዛሬም የሚታይ አሳዛኝ ድርጊት ነው። ሕግና ሥርዓት አንድን ሰው የልብ ለውጥ ሳይኖረው ቅዱስ መስሎ እንዲታይ ስለሚያስችል፥ ሥጋ (አሮጌው ተፈጥሮአችን) በሥርዓት የታሰረ ኃይማኖታዊነትን ይወዳል።

ጳውሎስ በሕግ ርግማን ሥር የሚገኙትን አሥራ አራት ዓይነት ሰዎች ዘርዝሯል (1ኛ ጢሞ. 1፡9-10)። ይህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ካሉ በርካታ ተመሳሳይ ዝርዝሮች አንዱ ነው (ማርቆስ 7፡20-23፤ ሮሜ 1፡18-32፤ ገላትያ 5፡19-21 ን ተመልከት)። የአሮጌው ሕግ ሕጋዊ

ጠቀሜታ፥ ሕጋዊ ያልሆነውን ለማጋለጥ፥ ለማገድና ለመውቀስ ነው። ሕጉ አዳኝ እንደሚያስፈልጋቸው ከመግለጽ ባሻገር፥ የጠፉትን ኃጢአተኞች ለማዳን አይችልም (ገላትያ 2፡21፤ 3፡21-29)። አንድ ኃጢአተኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ባመነ ጊዜ ከሕግ እርግማን ነጻ ይሆናል (ገላ. 3፡10-14)፤ እንዲሁም አማኝ ራሱን ለእግዚአብሔር ሲሰጥ፥ በውስጡ በሚያድረው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት፥ ተገቢዎቹ የሕግ ትእዛዛት ይሟላሉ (ሮሜ 8፡1-4)።

ጳውሎስ በዘጸአት 20 ላይ ከተጠቀሱት አስርቱ ትእዛዛት ውስጥ በተለይ በአምስቱ ላይ አትኩሯል (1ኛ ጢሞ. 1፡9-10)።

ተራ ቁ. 5 - «አባትህንና እናትህን አክብር»

«አባትንና እናትን የሚገድሉ ነፍሰ ገደዮች»

ተራ ቁ. 6 - «አትግደል»

«አባትንና እናትን፥ ሌሎችንም የሚገድሉ ነፍሰ ገዳዮች»

ተራ ቁ. 7 - «አታመንዝር»

«ሴሰኞች፥ ከወንድ ጋር በመተኛት ራሳቸውን የሚያረክሱ (ግብረ-ሰዶማውያን)»

ተራ ቁ. 8 - «አትስረቅ»

«ሰው የሚሰርቁ (አፋኞች)»

ተራ ቁ. 9 - «በሐሰት አትመስክር»

«ውሸተኞች - በሐሰት የሚምሉ»

የጠፉትን ኃጢአተኞች የሚያድነው «የከበረው ወንጌል» ነው። ጳውሎስ የወንጌልን ኃይል ተለማምዶ የነበረና (ሮሜ 1፡16)፤ እንዲሁም የወንጌል አገልግሎት አደራ የተሰጠው ነበረ (1ኛ ተሰ. 2፡4)። ሕግና ወንጌል ጎን ለጎን የሚሄዱ ነገሮች ናቸው፤ ምክንያቱም ሕግ ያለ ወንጌል አንድን በሽተኛ መርምሮ ውጤቱን ካወቁ በኋላ፥ በሽታውን የሚያስታግስለትን መድኃኒት አለመስጠት ማለት ነው። ነገር ግን ወንጌል ያለ ሕግ፥ የፍርድን ክፉ ዜና ስላልሰሙ የመዳን መልካም ዜና ያስፈልገናል ብለው ለማያስቡ ሰዎች ማቅረብ እንደማለት ነው። ሕጉ ወንጌል አይደለም፤ ወንጌሉ ግን ሕግ አልባ አይደለም (ሮሜ 3፡20-31)።

2. ወንጌሉን አውጅ (1ኛ ጢሞ. 1፡12-17)

«የብሩክ እግዚአብሔር የክብር ወንጌል» (ቀጥተኛ ትርጉም 1፡11) ተብሎ የተጠቀሰው ቃል፥ ጳውሎስ የግል ሕይወቱን ምስክርነት እንዲያካፍል ገፋፋው። የእግዚአብሔር የጸጋ ወንጌል በእርግጥ እንደሚሠራ ለማረጋገጥ እርሱ ራሱ ዋና ማስረጃ ነበር። የጳውሎስን ምስክርነት ስታነብ፥ አስደናቂውን የእግዚአብሔር ጸጋና የማዳኑን ኃይል መረዳት ትጀምራለህ (የሐዋ. 9፡1-22፤ 22፡1-21፤ 26፡9-18 ተመልከት)።

ሀ) ጳውሎስ ምን ዓይነት ሰው እንደነበረ (1ኛ ጢሞ. 1፡13)፡- የክርስቶስን አምላክነት ስለካደና ሌሎችም እንዲክዱ ያስገድድ የነበረ፥ ተሳዳቢ ነበር። ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ጉልበቱን የተማመነና የተጠቀመ አሳዳጅ ነበረ። «የግድያ ዛቻዎች» የሕይወቱ ዓላማ ነበሩ። (የሐዋ. 9፡1)። የክርስቲያኖችን ቤተ ክርስቲያን ያሳደደ ነበረ (1ኛ ቆሮ. 15፡9)። ከዚያ በኋላም እጁን እያነሳ ያለው በመሢሑ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንደ ነበር ተረዳ (የሐዋ 9፡4)። በዚህ የሕይወቱ ክፍለ ጊዜ፥ ጳውሎስ እስጢፋኖስ በድንጋይ እንዲወገር የተስማማና በቤተ ክርሲትያን ላይ ስደት እንዲነሳ ያደረገ ነበረ (የሐዋ 8፡1-4)።

ጳውሎስ የሚያንገላታ ማለትም ትዕቢተኛና አዋራጅ ነበረ። ምናልባት በዘመናችን ይህን ቃል የሚተካው «ጀብደኛነት» የሚለው ይሆናል። በየቦታው በጠብ ፈላጊነት እየዞረ ኃይሉን ለማሳየት የሚሞክር ጉረኛ ሰውን ይመስላል፤ ዳሩ ግን ፈሪሃ-እግዚአብሔር ለራቀው ባሕርዩ መሠረታዊ ምክንያቶች አለማወቅና አለማመን ናቸው። ምንም እንኳን የተርሴሱ ሳውል ብሩህ አእምሮ የነበረውና የተማረ ሰው ቢሆንም (የሐዋ 22፡3፤ ገላ. 1፡13-14)፥ አእምሮው ለእውነት የታወረ ነበረ (1ኛ ቆሮ. 2፡14፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡3-4)። ሃይማኖታዊ ሰው ቢሆንም፥ ወደ መንግሥተ ሰማይ እያመራ አልነበረም። እምነቱን በኢየሱስ ክርስቶስ እስኪያደርግ ድረስ አልዳነም ነበረ (ፊል. 3፡1-11)።

ለ) ጳውሎስ እንዴት እንደ ዳነ (1ኛ ጢሞ. 1፡13-15)፡- ቅዱሱ እግዚአብሔር እንዲህ ራሱን ያጸደቀውን ኃጢአተኛ እንዴት ሊያድንና ይቅር ሊል ይችላል? ቁልፍ የሆኑት ቃላት «ምሕረት» እና «ጸጋ» ናቸው። እግዚአብሔር በምሕረቱ ለጳውሎስ የሚገባውን አልሰጠውም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በጸጋው ለጳውሎስ

የማይገባውን ሰጠው። ጸጋና ምሕረት የእግዚአብሔር ፍቅር በተግባር የሚታይባቸው መንገዶች ናቸው። የእግዚአብሔር ፍቅር የጠፉትን ኃጢአተኞች ለማዳን ዋጋ ሲከፍል እንመለከታለን። እግዚአብሔር ዓለሙን በሙሉ ስለሚወድ (ዮሐ. 3:16)፥ የሚያድነን የእግዚአብሔር ፍቅር ብቻ አይደለም (ኤፌሶን 2:8-9)። እግዚአብሔር በምሕረትና (2:4) በጸጋ (2:7) የተሞላ ስለሆነ፥ የዳንነው በጸጋ ነው።

የጳውሎስ «አለማወቅ» ከመዳኑ ጋር ምን ግንኙነት ነበረው? አለማወቅ በእግዚአብሔር ፊት ምክንያት ነውን? በእርግጥ አይደለም! የአለማወቁ ምክንያት ልዩ ከሆነ ከአይሁድ ሕግ ጋር የተያያዘ ነው (ዘሌ. 5:15-19፤ ዘኁ 15:22-31)። በእስራኤል አንድ ሰው እያወቀ ኃጢአትን በድፍረት ቢሠራ፥ ከሕዝቡ ተለይቶ ይጠፋ ነበር፤ ነገር ግን ባለማወቅ ኃጢአትን ቢያደርግ፥ ለኃጢአቱ ማስተሰሪያ አስፈላጊውን መስዋዕት እንዲያቀርብ ይፈቀድለታል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» (ሉቃስ 23:34) ብሎ የጸለየው ይህንን መመሪያ በማሰብ ነበር። የክርስቶስ ጸሎትም ሆነ የራሳቸው አለማወቅ አላዳናቸውም ነበረ፤ ነገር ግን የሁለቱ ነገሮች መጣመር፥ የመዳንን ዕድል በመስጠት፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ አዘግይቶታል።

ጳውሎስ እርሱን ለማዳን «እጅግ የበዛ» ጸጋ እንዳስፈለገ ገልጿል። ጳውሎስ በግሪኩ «ሁፐር» ማለትም «እጅግ የበዛ መጠን» የሚለውን ቃል መጠቀም ስለሚወድ፥ ብዙውን ጊዜ በመልእክቶቹ ውስጥ ከሚገኙ ቃላት ጋር ያያይዘዋል። ከእነዚህ ጥቂቶቹን «እጅግ የሚያድግ እምነት» (2ኛ ተሰ. 1:3)፥ «ከሁሉ የሚበልጥ ኃይል» (ኤፌ. 1:9)፥ «ከአሸናፊዎች የሚበልጥ አሸናፊ» (ሮሜ 8:37) ብለን መተርጎም እንችላለን።

ጳውሎስ ይህ ደኅንነት ለእርሱ ብቻ ሳይሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ለሚቀበሉ ሁሉ እንደሆነ በግልጽ ይናገራል (1ኛ ጢሞ. 1:15)። ኢየሱስ የኃጢአተኞች ዋና የነበረውን የተርሴሱን ሳውል ለማዳን ከቻለ፥ ማንንም ሊያድን ይችላል! የጳውሎስን ትሕትና እናደንቃለን። እንዲሁም ራሱን «ከሐዋርያት ሁሉ የሚያንስ» ና (1ኛ ቆሮ. 15:9) «ከቅዱሳን ሁሉ የሚያንስ» (ኤፌሶን 3:8) አድርጎ እንደቆጠረ እናስተውላለን። ጳውሎስ ከሁሉ «ዋና የነበርሁትን» ሳይሆን፥ ከሁሉ «ዋና የሆንሁትን» እንዳለ አስተውል።

ሐ. ጳውሎስ ምን ዓይነት ሰው ሊሆን እንደ በቃ (1ኛ ጢሞ. 1፡12፥ 16)፡- የእግዚአብሔር ጸጋ አሳዳጁን ሰው ወደ ሰባኪነት፥ እንዲሁም ነፍሰ-ገዳዩን ወደ አገልጋይነትና የወንጌል መልእክት አብሳሪነት ለወጠው። በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ለግታለል የተደረገ ጥረት እንደሆነ በመጠራጠር፥ እርሱን ለመቀበል ተቸግራ ነበር (የሐዋ 9፡26-31)። እግዚአብሔር ለጳውሎስ አገልግሎቱን ሰጠው እንጂ፥ ከጴጥሮስ ወይም ከሌሎች ሐዋርያት አልተቀበለም (ገላ. 1፡11-24)። የተጠራውና የተላከው፥ ከሙታን ተነሥቶ በሰማይ በአባቱ ቀኝ ባለው በክርስቶስ ነበር።

እግዚአብሔር የጳውሎስን ታማኝነት በመመልከት፥ የወንጌሉን አደራ ሰጠው። የማያምንና ወንጌሉን የማያውቅ የአይሁድ መሪ በነበረበት ጊዜ እንኳን፥ ጳውሎስ በጎ ሕሊና የነበረውና ለተረዳው ነገር በሚገባ የኖረ ሰው ነበረ፤ ስለዚህ ብዙውን ጊዜ በጣም ተሳስተው የጠፉ ኃጢአተኞች፥ ጠንካራና እውነተኛ ክርስቲያኖች ይሆናሉ። እንዲሁም ነፍሳትን ለመማረክ እግዚአብሔር በኃይል ይጠቀምባቸዋል። እግዚአብሔር ለጳውሎስ የወንጌል አደራ ብቻ ሳይሆን፥ ያንን ወንጌል ለማገልገል የሚችልበትን ኃይል ጭምር ሰጠው (ፊሊ. 4፡13፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡10)። አንድ ሰው ለእግዚአብሔር የአገልግሎት ጥሪ ሲታዘዝ፥ ሁልጊዜም እግዚአብሔር ያንን ሰው ያስታጥቀዋል፤ ኃይልንም ይሰጠዋል።

ሆኖም ጳውሎስ አገልጋይ ብቻ ሳይሆን፥ ምሳሌም ሆኗል (1ኛ ጢሞ. 1፡16)። ጳውሎስ በክርስቶስ ለሚያምኑ የጠፉ ኃጢአተኞች ምሳሌ የሚሆነው እንዴት ነው? ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ባለፈበት ልምምድ ውስጥ ማናችንም አላለፍንም (የሐዋ. 9)። ብርሃን በዙሪያችን ሲያንጸባርቅ አላየንም፤ በምድር ላይ አልወደቅንም፤ እንዲሁም ኢየሱስ ከሰማይ ሲናገር አልሰማንም፤ ነገር ግን ጳውሎስ የኃጢአተኞች ዋና ስለነበረ፥ ለጠፉት ኃጢአተኞች ሁሉ እንደምሳሌ ነው። ጳውሎስ የእግዚአብሔር ጸጋ ማንንም ኃጢአተኛ ሊለውጥ እንደሚችል የሚያሳይ ማረጋገጫ ነው።

ነገር ግን ይህ፥ ጳውሎስ በተለየ ሁኔታ ያስብላቸው ለነበሩና የአገሩ ሰዎች ለሆኑት ለዛሬዎቹ የእስራኤል ሕዝቦች፥ የተለየ ተዛምዶ አለው (ሮሜ 9፡1-5፤ 10፡1-3)። እንዳልተለወጠው የጠርሴሱ ጳውሎስ፥ የእስራኤል ሕዝቦች ሃይማኖተኞች፥ ራሳቸውን የሚያጸድቁ፥ ለገዛ ሕጋቸውና ሕጉ ስለመጪሉ ለሚያስተላልፈው መልእክት የታወሩና

ለማመን ፈቃደኞች ያልሆኑ ናቸው። አንድ ቀን ጳውሎስ እንዳየው እስራኤል ኢየሱስ ክርስቶስን ታያለች። ሕዝቡም ይድናል። «ወደ እርሱም ወደወጉት ይመለከታሉ» (ዘካ. 12፡10)። ጳውሎስ «ሞንጋፍ ለምሆን ለእኔ» (1ኛ ቆሮ. 15፡8) እንዲል ያደረገው አንዱ ምክንያት ይህ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን በማየት ልምምድ ውስጥ ያለፈው በዚህ በቤተ ክርስቲያን ዘመን መጀመሪያ እንጂ፥ በመጨረሻው ስላልሆነ ነው (ማቴ. 24፡29-31)።

3. ስለ እምነት መቆም (1ኛ ጢሞ. 1፡18-20)

ጳውሎስ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት ከማስተማርና ወንጌልን ከማወጅ በተጨማሪ ልታሟላ የሚገባትን ሦስተኛ ኃላፊነት ሰጥቷል።

ደግሞም በዚህ ክፍል «ትእዛዝ» (1፡18) የሚለው ቃል ከከፍተኛ ባለሥልጣን የወጣ አስቸኳይ ትእዛዝ የሚል ትርጉም ስላለው (1፡3) ጳውሎስ አሳቡን ለመግለጥ ወታደራዊ ቋንቋ ተጠቅሟል። ጳውሎስ በተጨማሪም እግዚአብሔር ጢሞቴዎስን ለአገልግሎት እንደመረጠው ያስታውሰዋል። በአጥቢያ ግጎበራት ውስጥ ከሚገኙ ነቢያት ውስጥ አንዳንዶቹ ጢሞቴዎስን ለአገልግሎት ለመምረጥ በመንፈስ ተመርተው የተንቀሳቀሱ ይመስላል። (ለዚሁ ሂደት ምሳሌነት የሐዋ. 13፡1-3 ተመልከት።)

በአረማዊቷ ኤፌሶን ውስጥ እግዚአብሔርን ማገልገል ቀላል አልነበረም፤ ነገር ግን ጢሞቴዎስ ትእዛዝ የደረሰው ሰው ስለ ነበር መታዘዝ ነበረበት። የወታደር ሥራ ራሱን ማስደሰት ሳይሆን «ለጦር ያስከተተውን ደስ ማሰኘት» ነው (2ኛ ጢሞ. 2፡4)። በተጨማሪም ጢሞቴዎስ እዚያ የነበረው በመለኮታዊ ሹመት ስለተሾመ ነው። እግዚአብሔር መርጦታል፤ ልኮታልም። በአስቸጋሪ ጊዜያት ውስጥ ዋስትና ሊሰጥ የሚችለው ይኸው እውነታ ነበር። አንተ በመንፈስ ቅዱስ ተጠርተህ ለፈቃዱ የምትገዛ የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሆንክ፥ «ልትጸናና» ሥራውን ልትፈጽም ትችላለህ። እነዚህ ዋስትናዎች ጢሞቴዎስ መልካሙን ጦርነት እንዲዋጋ አስችለውታል።

ጳውሎስ ምሳሌውን ከጦር ሠራዊት ወደ ባህር ኃይል ይለውጠዋል (1ኛ ጢሞ. 1፡19) «እምነትንና በጎ ኅሊናን» አጥብቆ መያዝ ለስኬታማነት ብቸኛ መንገድ እንደሆነ በመግለጽ ያስጠነቅቀዋል። እምነትን በከንፈራችን ማወጅ ብቻ በቂ አይደለም። በዕለት ተዕለት ኑሮአችን እምነትን መለማመድ አለብን። አንድ ሰው ግብዝ ስለነበረው

መጋቢ እንዲህ ብሏል፡- «በጣም ጎበዝ ሰባኪ ስለሆነ ከመድረክ መውረድ የለበትም። ነገር ግን በጣም ደካማ ክርስቲያን ስለሆነ መድረክ ላይ መውጣት የለበትም»።

በጎ ሕሊና ለመልካም ጦርነትና ለመልካም አገልግሎት አስፈላጊ ነው። ኤች ኤል ሜንኩን የተባሉ የአንድ መጽሔት አዘጋጅ ስለ ሕሊና፡- «ውስጣዊ ድምፅ አንድ ሰው እንደሚያየን ያስጠነቅቀናል» ብለው ተርጉመውታል፤ ነገር ግን በጎ ሕሊና ያለው ሰው፥ ማንም ቢያየው ወይም ሰዎች የፈለጉትን ቢሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመፈጸም ወደ ኋላ አይልም። እንደ ማርቲን ሉተር «በዚህ ስፍራ ቆሜያለሁ፤ ሌላ የማደርገው ስለሌለኝ፥ እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ!!» ይላል።

የተሰበረ መርከብ እንደሚሰምጥ፥ በእምነት ነገር የጠፉ አስመሳይ ክርስቲያኖች ይህንን የሚያደርጉት የሕሊናቸውን ወቀሳ ተላልፈው ኃጢአት በመሥራት ነው። መጥፎ ትምህርት ብዙውን ጊዜ በመጥፎ ጠባይ እና በተደበቀ ኃጢአት ይጀመራል። ሄሜኔዎስና እስክንድሮስ ፈሪሃ-እግዚአብሔር የራቀውን ሕይወታቸውን ለመከላከል መልካም ሕሊናቸውን ሆን ብለው ገፍተዋል። ጳውሎስ ኃጢአታቸው በሆነ መንገድ «ሰድብ» ን እንደሚጨምር ከመናገር በስተቀር፥ በትክክል ምን እንዳደረጉ አልገለጸም። ሄሜኔዎስ ትንሣኤ ከአሁን በፊት ሆኗል ብሏል (2ኛ ጢሞ. 2፡16-18) እስክንድሮስ የሚለው ስም በዚያን ዘመን ታዋቂ ስለነበር፥ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በላከው ሁለተኛ መልእክቱ ላይ (2ኛ ጢሞ. 4፡14) የጠቀሰው ሰው ያ ሰው ለመሆኑ እርግጠኞች ልንሆን አንችልም። ከሆነ ግን ሐሰተኛ ትምህርት በማስተማር ጳውሎስን እንደተቃወመው ጥርጥር የለውም።

«ለሰይጣን አሳልፌ የሰጠኋቸው» (1ኛ ጢሞ. 1፡20) የሚለው ዐረፍተ ነገር ሐዋርያዊ የሥነ-ሥርዓት እርምጃንና (1ኛ ቆሮ. 5፡5ን ተመልከት) ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መለየትን ያመለክታል። «ይግሩ ዘንድ» (1ኛ ጢሞ. 1፡20) ማለት «በሥነ-ሥርዓት እርምጃ መማር» ማለት ነው። አንድ ክርስቲያን ንስሐ ለመግባት ሳይፈልግ ሲቀር፥ ጎብረቱ ከተከለለበት የቅዱሳን ጎብረት በማግለልና ለሰይጣን ጥቃት በማጋለጥ፥ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ መውሰድ አለበት። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጎብረት፥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዝ፥ ለአማኙ መንፈሳዊ ከለላ ይሰጠዋል። ሰይጣን አማኝን ለማጥቃት፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅ አለበት (ኢዮብ 1-2፤ ሉቃ. 22፡31-34 ተመልከት)።

ለማመን ፈቃደኞች ያልሆኑ ናቸው። አንድ ቀን ጳውሎስ እንዳየው እስራኤል ኢየሱስ ክርስቶስን ታያለች። ሕዝቡም ይድናል። «ወደ እርሱም ወደወጉት ይመለከታሉ» (ዘካ. 12፡10)። ጳውሎስ «ሞንጋፍ ለምሆን ለእኔ» (1ኛ ቆሮ. 15፡8) እንዲል ያደረገው አንዱ ምክንያት ይህ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን በማየት ልምምድ ውስጥ ያለፈው በዚህ በቤተ ክርስቲያን ዘመን መጀመሪያ እንጂ፥ በመጨረሻው ስላልሆነ ነው (ማቴ. 24፡29-31)።

3. ስለ እምነት መቆም (1ኛ ጢሞ. 1፡18-20)

ጳውሎስ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት ከማስተማርና ወንጌልን ከማወጅ በተጨማሪ ልታሚላ የሚገባትን ሦስተኛ ኃላፊነት ሰጥቷል።

ደግሞም በዚህ ክፍል «ትእዛዝ» (1፡18) የሚለው ቃል ከከፍተኛ ባለሥልጣን የወጣ አስቸኳይ ትእዛዝ የሚል ትርጉም ስላለው (1፡3) ጳውሎስ አሳቡን ለመግለጥ ወታደራዊ ቋንቋ ተጠቅሟል። ጳውሎስ በተጨማሪም እግዚአብሔር ጢሞቴዎስን ለአገልግሎት እንደመረጠው ያስታውሰዋል። በአጥቢያ ማኅበራት ውስጥ ከሚገኙ ነቢያት ውስጥ አንዳንዶቹ ጢሞቴዎስን ለአገልግሎት ለመምረጥ በመንፈስ ተመርተው የተንቀሳቀሱ ይመስላል። (ለዚሁ ሂደት ምሳሌነት የሐዋ. 13፡1-3 ተመልከት።)

በአረማዊቷ ኤፌሶን ውስጥ እግዚአብሔርን ማገልገል ቀላል አልነበረም፤ ነገር ግን ጢሞቴዎስ ትእዛዝ የደረሰው ሰው ስለ ነበር መታዘዝ ነበረበት። የወታደር ሥራ ራሱን ማስደሰት ሳይሆን «ለጦር ያስከተተውን ደስ ማሰኘት» ነው (2ኛ ጢሞ. 2፡4)። በተጨማሪም ጢሞቴዎስ እዚያ የነበረው በመለኮታዊ ሹመት ስለተሾመ ነው። እግዚአብሔር መርጦታል፤ ልኮታልም። በአስቸጋሪ ጊዜያት ውስጥ ዋስትና ሊሰጥ የሚችለው ይኸው እውነታ ነበር። አንተ በመንፈስ ቅዱስ ተጠርተህ ለፈቃዱ የምትገዛ የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሆንክ፥ «ልትጸናና» ሥራውን ልትፈጽም ትችላለህ። እነዚህ ዋስትናዎች ጢሞቴዎስ መልካሙን ጦርነት እንዲዋጋ አስችለውታል።

ጳውሎስ ምሳሌውን ከጦር ሠራዊት ወደ ባህር ኃይል ይለውጠዋል (1ኛ ጢሞ. 1፡19) «እምነትንና በጎ ኅሊናን» አጥብቆ መያዝ ለስኬታማነት ብቸኛ መንገድ እንደሆነ በመግለጽ ያስጠነቅቀዋል። እምነትን በከንፈራችን ማወጅ ብቻ በቂ አይደለም። በዕለት ተዕለት ኑሮአችን እምነትን መለማመድ አለብን። አንድ ሰው ግብዝ ስለነበረው

መጋቢ እንዲህ ብሏል፡- «በጣም ጎበዝ ሰባኪ ስለሆነ ከመድረክ መውረድ የለበትም። ነገር ግን በጣም ደካማ ክርስቲያን ስለሆነ መድረክ ላይ መውጣት የለበትም»።

በጎ ሕሊና ለመልካም ጦርነትና ለመልካም አገልግሎት አስፈላጊ ነው። ኤች ኤል ሜንኪን የተባሉ የአንድ መጽሔት አዘጋጅ ስለ ሕሊና፡- «ውስጣዊ ድምፅ አንድ ሰው እንደሚያየን ያስጠነቅቀናል» ብለው ተርጉመውታል፤ ነገር ግን በጎ ሕሊና ያለው ሰው፥ ማንም ቢያየው ወይም ሰዎች የፈለጉትን ቢሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመፈጸም ወደ ኋላ አይልም። እንደ ማርቲን ሉተር «በዚህ ስፍራ ቆሜያለሁ፤ ሌላ የማደርገው ስለሌለኝ፥ እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ!!» ይላል።

የተሰበረ መርከብ እንደሚሰምጥ፥ በእምነት ነገር የጠፉ አስመሳይ ክርስቲያኖች ይህንን የሚያደርጉት የሕሊናቸውን ወቀሳ ተላልፈው ኃጢአት በመሥራት ነው። መጥፎ ትምህርት ብዙውን ጊዜ በመጥፎ ጠባይ እና በተደበቀ ኃጢአት ይጀመራል። ሄሜኔዎስና እስክንድሮስ ፈሪሃ-እግዚአብሔር የራቀውን ሕይወታቸውን ለመከላከል መልካም ሕሊናቸውን ሆን ብለው ገፍተዋል። ጳውሎስ ኃጢአታቸው በሆነ መንገድ «ስድብ» ን እንደሚጨምር ከመናገር በስተቀር፥ በትክክል ምን እንዳደረጉ አልገለጸም። ሄሜኔዎስ ትንሣኤ ከአሁን በፊት ሆኗል ብሏል (2ኛ ጢሞ. 2፡16-18) እስክንድሮስ የሚለው ስም በዚያን ዘመን ታዋቂ ስለነበር፥ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በላከው ሁለተኛ መልእክቱ ላይ (2ኛ ጢሞ. 4፡14) የጠቀሰው ሰው ያ ሰው ለመሆኑ እርግጠኞች ልንሆን አንችልም። ከሆነ ግን ሐሰተኛ ትምህርት በማስተማር ጳውሎስን እንደተቃወመው ጥርጥር የለውም።

«ለሰይጣን አሳልፌ የሰጠኋቸው» (1ኛ ጢሞ. 1፡20) የሚለው ዐረፍተ ነገር ሐዋርያዊ የሥነ-ሥርዓት እርምጃንና (1ኛ ቆሮ. 5፡5ን ተመልከት) ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መለየትን ያመለክታል። «ይማሩ ዘንድ» (1ኛ ጢሞ. 1፡20) ማለት «በሥነ-ሥርዓት እርምጃ መማር» ማለት ነው። አንድ ክርስቲያን ንስሐ ለመግባት ሳይፈልግ ሲቀር፥ ጎብረቱ ከተከለለበት የቅዱሳን ጎብረት በግልለና ለሰይጣን ጥቃት በግጋለጥ፥ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ መውሰድ አለበት። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጎብረት፥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዝ፥ ለአማኙ መንፈሳዊ ከለላ ይሰጠዋል። ሰይጣን አማኝን ለማጥቃት፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅ አለበት (ኢዮብ 1-2፤ ሉቃ. 22፡31-34 ተመልከት)።

እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የክፉውን ኃይላት ለመቋቋም በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ ነው። ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ አስተማሪዎች፥ እንዲሁም ሐሰተኛ ክርስቶሶች አሉ። ሰይጣን ከመጀመሪያው ሐሰተኛ ስለነበረ (ዮሐ. 8፡44)፥ የሐሰት ትምህርቶች አፍላቂ ነው። አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛውን ትምህርት ማስተማርና ወንጌሉን ማሰራጨት ብቻ ሳይሆን፥ ሐሰቶችን በመግለጥና የአጋንንትን ትምህርት ቦመቃወም (1ኛ ጢሞ. 4፡1)፥ እምነትን መጠበቅ አለባት።

አገልግሎታችን ሚዛናዊ እንዲሆን ያስፈልጋል። አንዳንድ አቢያተ ክርስቲያናት ወንጌልን ብቻ እየሰበኩ፥ ለምእመናኑ የክርስትና ሕይወት እውነቶችን ከማስተማር ይታቀባሉ። ቢያደርጉትም እንኳን አልፎ አልፎ ብቻ ይሆናል። ሌሎች አቢያተ ክርስቲያናት ደግሞ ሐሰተኛ ትምህርቶችን በመቃወም ላይ ብቻ ስለሚያተኩሩ፥ ተገቢውን አገልግሎት ለማበርከት አልቻሉም። የጤናማ ትምህርት (ሕይወት የሚገኝበት ትምህርት» 1ኛ ጢሞ. 1፡10) አስተማሪዎች መሆን አለብን። ይህ ካልሆነ ግን ምእመናኑ አያድጉም። ወንጌሉን እየሰበክን፥ የጠፉትን ለክርስቶስ በመማረክ መቀጠል አለብን። እንዲሁም በሐሰተኛ ትምህርትና ፈሪሃ-እግዚአብሔር በሌለው አኗኗር ቤተ ክርስቲያንን ከሚበክሉ ሰዎች እምነታችንን መከላከል አለብን። ነገሩ የሚያቋርጥ ጦርነት ቢሆንም፥ እስከ ፍጻሜ ድረስ መታገል ያሻል።

ጢሞቴዎስ ይህንን የጳውሎስ መልእክት የመጀመሪያ ክፍል ሲያነብ፥ ብዙ ሳይጠቀምና ሳይበረታታ አልቀረም። እግዚአብሔር ጢሞቴዎስን በመጥራት አስታጠቀው። ከዚያም በአገልግሎቱ ቦታ አስቀመጠው። የጢሞቴዎስ ሥራ በብዙ እንቅስቃሴዎች በመጠመድ በኤፌሶን ከተማ ሁሉ መሯሯጥ አልነበረም። የእርሱ ሥራ የጠፉትን በማዳን፥ የዳኑትን በማስተማርና እምነትን በመጠበቅ፥ ቤተ ክርስቲያንን መንከባከብ ነበረ። ከእነዚህ አገልግሎቶች ጋር ያልተያያዘ ሥራ ሁሉ መቅረት ነበረበት። አንዳንድ አጥቢያ አቢያተ ክርስቲያናት ከሚቸገሩባቸው ምክንያቶች አንዱ፥ መጋቢዎችና መንፈሳውያን መሪዎች ከዋና ተግባራቸው ውጭ በበዙ በርካታ ጉዳዮች መጠመዳቸውና እግዚአብሔር እንዲሠሩት የጠራቸውን ሥራ ብቻ አለማከናወናቸው ነው።

ምናልባት ለአቢያተ ክርስቲያኖቻችን መንፈሳዊ የአገልግሎት ግምገማ ማካሄድ ጥሩ አሳብ ይሆን ይሆናል።

አገልግሎት ወይስ የመድረክ ትዕይንት

1ኛ ጢሞቴዎስ 2

«ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን» (1ኛ ቆሮ. 14፡40) የሚለው ለቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ሥርዓት መሠረታዊ መመሪያ ነው። በግልጽ እንደሚታየው፥ ወጣቱ ጢሞቴዎስ በኤፌሶን ማኅበረ ምእመናን መካከል ይህንን መመሪያ ተግባራዊ በማድረጉ ረገድ ችግር ገጥሞት ነበር። የቤተ ክርስቲያኒቱ ወንዶችና ሴቶች አባላት ለእግዚአብሔር ቃል የማይታዘዙ ስለነበሩ የጉባኤዎቻቸው የአምልኮ ጊዜያት ሥርዓታቸውን በማጣት፥ ውጤት-አልባ እየሆኑ ነበሩ።

አንድ መጋቢ «ቤተ ክርስቲያን የአማኞች ጎብረት ናት፤ ስለዚህ በአደረጃጀት ላይ በጣም መጫን የለብንም። ለመንፈስ ቅዱስ ነጻነት መስጠት አለብን» ብሎ ተናገረኝ። እኔም በፍጥነት እንዲህ ስል አስገነዘብኩት፡- «ነገር ግን አንድ የአማኞች ጎብረት ሥርዓቱ ከፈራረሰ ይሞታል። አዎን፥ መንፈስ ቅዱስ ነጻነት እንዲኖረው ልንፈቅድለት ይገባል፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ እንኳን የእግዚአብሔርን ቃል ለመተላለፍ ነጻ አይደለም»።

ብዙውን ጊዜ «የመንፈስ ነጻነት» ብለን የምናስባቸው፥ በመንፈስ የማይመላለሱ የአንዳንድ ክርስቲያኖች ሥጋዊ አሳቦች ናቸው። በመጨረሻም ይህ «ነጻነት» ሥርዓት አልበኝነት ይሆንና ቤተ ክርስቲያን ቀስ በቀስ ከእግዚአብሔር ቃል መለኪያዎች እየራቀች ስትሄድ መንፈስ ቅዱስ ያዝናል።

ይህንን ዝንባሌ ለመግታት ጳውሎስ የቤተ ክርሲትያኒቱን ወንዶችና ሴቶች አጥብቆ ይመክራል። ደግሞም የተሰጧቸውን መንፈሳዊ ኃላፊነቶች ያስታውሳቸዋል።

1. የሚጸልዩ ወንዶች፡- (1ኛ ጢሞ. 2፡1-8)

ሀ. የጸሎት ቀዳሚነት (1ኛ ጢሞ. 2፡1)፡- «ከሁሉ በፊት» የሚለው ጸሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚደረገው አምልኮ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል። በብዙ አቢያተ ክርስቲያናት ውስጥ ጸሎት ምን ያህል ተፈላጊነት እንዳጣ ማየቱ የሚያሳዝን ነው። አንድ መጋቢ «ግብዣ እንዳለ ባስታውቅ ሰዎች ከየአቅጣጫው ተነሥተው

ይመጣሉ። ነገር ግን የጸሎት ጊዜ እንዳለ ባስታውቅ፥ አስተናጋጆች እንኳ ብቅ ቢሉ እድለኛ ነኝ» ብሏል። አስፈላጊነታቸውን ያጡት በብዙ አቢያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚደረጉ ልዩ የጸሎት ስብሰባዎች ብቻ ሳይሆኑ፥ በጉባኤ የአምልኮ ጊዜያት የሚደረገው ጸሎት እንኳን በጣም ቀንሷል። ብዙ መጋቢዎች ከጸሎት ይልቅ፥ ማስታወቂያዎችን በመናገር ብዙ ጊዜ ያሳልፋሉ።

ጥሩ ጓደኛዬ የነበሩትና የስላቪክ ወንጌል ማስፋፊያ ድርጅትን ያቋቋሙት የቀድሞው ፒተር ዴይኔካ፡- ብዙ ጊዜ «ብዙ ጸሎት ካለ፥ ብዙ ኃይል አለ! ጸሎት ከሌለ ኃይል የለም!» ይሉኝ ነበረ። ጸሎት፥ ቃሉን የመስበክን ያህል የሐዋርያዊ አገልግሎት አንዱ አካል ነበር (የሐዋ. 6፡4)። ሆኖም ብዙ መጋቢዎች ስብከታቸውን በማዘጋጀት ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ እንጂ፥ የጉባኤ ጸሎቶችን ፈጽሞ አያዘጋጁም። ከዚህም የተነሣ ጸሎቶቻቸው የተለመዱና ድግግሞሽ የበዛባቸው ናቸው። መጋቢው እያንዳንዱን ቃላት ጽፎ ያንብበው ማለቴ አይደለም፤ ነገር ግን ስለ ምን መጸለይ እንዳለበት ሊያስብበት ይገባል። ይህም «የመጋቢነቱን ጸሎት» ባለፈው ሳምንት «የተጸለየውን» ከመድገምና የጸሎትን ሕይወት ከማዳከም ይጠብቀዋል።

ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን አባላትም ለጸሎት መዘጋጀት ይገባቸዋል። ልባችን ከእግዚአብሔር ጋርና እርስ በርሳችን ለምናደርገው ግንኙነት የተስተካከለ መሆን አለበት። ሰዎችን ለማስደሰት (ፈሪሳውያን እንዳደረጉት፥ ማቴ. 6፡5)፥ ወይም ሃይማኖታዊ ተግባር ለመፈጸም ሳይሆን፥ በእውነት ለመጸለይ መፈለግ አለብን። አንዲት ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ላይ መደገፍ ስታቆም፥ እግዚአብሔርም አገልግሎቷን መባረክ ያቆማል።

ለ. የጸሎት ዓይነቶች (1ኛ ጢሞ. 2፡1)፡- «ጸሎት» የሚለው ቃል በግሪክ ቢያንስ ሰባት የተለያዩ ስሞች አሉት። ከእነዚህም አራቱ ከዚህ ቀጥሎ ተጠቅሰዋል። «ልመና»፥ «ተፈላጊ ነው ተብሎ ለታሰበ ነገር ጥያቄ ማቅረብ» የሚለውን አሳብ ይይዛል።

«ጸሎት» ለዚህ ተግባር በጣም የተለመደ ስያሜ ሲሆን፥ የጸሎትን ቅዱስነት ያጎላል። የምንጸልየው፥ ወደ እግዚአብሔር ነው፤ ጸሎት የአምልኮ ተግባር እንጂ፥ ፍላጎታችንና መሻታችንን የምንገልጽበት ብቻ አይደለም። ወደ እግዚአብሔር ስንጸልይ፥ በልባችን ራስን ዝቅ የማድረግ ትህትናና አክብሮት መኖር አለበት።

«ምልጃ»፡- ጥርት ያለው ትርጉሙ ማመልከቻን ወይም ጥያቄን ማቅረብ ነው። ይኸው ቃል በ1ኛ ጢሞ. 4፡5 ላይ የምንበላውን ምግብ መባረክን በማስመልከት «ጸሎት» ተብሎ ተተርጉሟል። (በዚህ ቃል የተለመደ አጠቃቀም፥ ለምግባችን እንደማንማልድ ግልጽ ነው)። መሠረታዊ ትርጉሙ «ወደ አንድ ሰው መጠጋትና በመተማመን መነጋገር» ነው። ይህ ስንጸልይ በእግዚአብሔር ተማምነን ከእርሱ ጋር ባለን ኅብረት እንደምንደሰት ያሳየናል።

«ምስጋና» በትክክል የአምልኮና የጸሎት ክፍል ነው። ምስጋናን የምንሰጠው ጸሎት ስለተመለሰልን ብቻ ሳይሆን፥ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና በጸጋው ለእኛ ስላደረገው ነገር ነው። ራስ ወዳድነት በሞላው የጸሎት መንፈስ ሆነን፥ የራሳችንን የምስጋና ጸሎት ዝም ብለን ማከል የለብንም። ምስጋና በጸሎታችን ጊዜ ሁሉ አንደኛው አስፈላጊ አካል ሆኖ መቅረብ አለበት። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ የዳዊትን የጸሎት ልምምድ ምሳሌ በመከተል ምንም ዓይነት ልመና ሳንጨምር ለእግዚአብሔር ምስጋና ብቻ ልናቀርብለት ያስፈልገናል [መዝሙር (103) ተመልከት]።

«ጸሎትና ምልጃ ከምስጋና ጋር»፥ በልባችን ውስጥ የእግዚአብሔር ሰላም እንዲኖር ጳውሎስ በተለማችው ዕቅዶች ውስጥ ይካተታሉ (ፊል. 4፡6)። ታላቁ የጸሎት ተጋዳይ ዳንኤል ይህንን ዓይነት ጸሎት ተለማምዶ እንደነበረ ማስተዋል ዋጋ ያለው ነገር ነው (ዳን. 6፡10-11)።

ሐ. ጸሎት የሚጸለይላቸው ሰዎች (1ኛ ጢሞ. 2፡1-2)፡- «ሰዎች ሁሉ» የሚለው በምድር ላይ ማንም ሰው የእምነት ጸሎት ከሚያስከትለው ተጽዕኖ ውጪ እንዳልሆነ ግልጽ ያደርጋል። (ለሞቱት ሰዎች እንድንጸልይ የሚመክሩን ምሳሌዎች የሉም። ለሞቱት መጸለይ ቢኖርብን ኖሮ፥ ጳውሎስ በዚህኛው የደብዳቤው ክፍል ሊነግረን የሚችልበት ጥሩ ዕድል ነበረው።) ይህ ማለት ላልዳኑትና ለዳኑት፥ አጠገባችን ላሉትና ከእኛ ርቀው ለሚኖሩ ሰዎች፥ ለጠላቶቻችን እንዲሁም ለወዳጆቻችን መጸለይ አለብን ማለት ነው። የሚያሳዝነው፥ ፈሪሳውያን ቀዳሚ ትኩረታቸውን በእስራኤል ላይ ስለሚያሳርፉ፥ በጸሎታቸው የዚህ ዓይነት አጠቃላይ አመለካከት አልነበራቸውም።

ጳውሎስ፥ ቤተ ክርስቲያን በተለይም በሥልጣን ላይ ላሉት እንድትጸልይ አጥብቆ ይመክራል። በዚያን ዘመን እግዚአብሔርን

የግያውቅ ንጉሥ ኔሮ በዙፋን ላይ ነበረ። እንዲህም ሆኖ አማኞች ለእርሱ መጸለይ ይጠበቅባቸው ነበረ። በሥልጣን ላይ ያሉትን ወንዶችና ሴቶች ለማክበር በማንችልበት ጊዜ እንኳን፥ ኃላፊነታቸውን አክብረን ልንጸልይላቸው ይገባል። እንዲያውም ይህንን የምናደርገው ለእኛ መልካም እንዲሆንልን ነው፡- «እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር» (2፡2)። ቀደምቷ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ ለተቃውሞና ለስደት የተጋፈጠች ስለነበረች፥ በሥልጣን ላይ ላሉት መጸለይ ብልህነት ነበረ። «በጸጥታ» የሚለው በአካባቢያችን ያሉትን ሁኔታዎች ሲያመለክት፥ «በሰላም» የሚለው በውስጣችን ያለውን የረጋ ሁኔታ ያመለክታል። የእነዚህም ውጤት የተቀደሰ የተከበረ ሕይወት ይሆናል።

እርግጠኛ ለመሆን፥ ጳውሎስ ልንጸልይላቸው የምንችለውንና የሚገባንን የሰዎች ስም አልዘረዘረም፥ ምክንያቱም «ሰዎች ሁሉ» የሚለው ቃል ሁሉን ነገር ስለሚጠቀልል ነው። በዓለም ዙሪያ ያሉትን በየስማቸው እየጠራን መጸለይ አንችልም። ነገር ግን ለምናውቃቸውና ስለ እነርሱ ለምናውቀው ሰዎች መጸለይ አለብን። ለምን? ምክንያቱም ይህን ለማድረግ መልካምና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ስለሆነ ነው።

መ. የምንጸልይባቸው ምክንያቶች (1ኛ ጢሞ. 2፡3-4)፡- በጳውሎስ የመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ «መልካም» የሚለው ቃል ቁልፍ ቃል ነው (1፡8፥ 18፤ 2፡3፤ 3፡1፥ 7፥ 13፤ 4፡4፥ 6፤ 5፡4፥ 10፥25፤ 6፡12-13፥ 18-19፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡14፤ 2፡3፤ 4፡7፤ ቲቶ 2፡7፥ 14፤ 3፡8፥ 14)። የግሪኩ ቃል አንድ ነገር በውጤቱ ብቻ ሳይሆን፥ በተፈጥሮአዊ ባሕርዩ መልካም በመሆኑ አሳብ ላይ ያተኩራል።

በተጨማሪም ጸሎት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነው። ልጆቹ እርሱ እንዳዘዛቸው ሲጸልዩ፥ አብን ደስ ያሰኘዋል። ፈሪሳውያን በሰዎች ለመመስገን (ማቴ. 6፡5)፥ ወይም ሌሎችን አምላኪዎች ወደ ራሳቸው ለመማረክ ይጸልዩ ነበረ (ሉቃ. 18፡9-14)። እውነተኛ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ይጸልያሉ። ይህ እንግዲህ በእግዚአብሔር ፈቃድ መጸለይ እንዳለብን ያሳየናል። ምክንያቱም በራስ ወዳድነት ስንጸልይ አብን ደስ ስለማያሰኘው ነው (ያዕ. 4፡1-10፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡14-15)። ብዙውን ጊዜ የጸሎት ዓላማ የሰው ፈቃድ በሰማይ ተፈጻሚነት እንዲያገኝ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር ለመፈጸም እንደሆነ ይነገራል።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድን ነው? በአንደኛ ደረጃ የጠፉትን ነፍሳት ለማዳን ነው። «ሰዎች ሁሉ» በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ወደሚገኝ የደኅንነት እውቀት እንዲመጡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ፥ «ለሰዎች ሁሉ» መጸለይ እንችላለን። እግዚአብሔር ዓለምን ስለ ወደደ (ዮሐ. 3፡16)፥ ክርስቶስ ለዓለም ሁሉ ሞቷል (1ኛ ዮሐ. 2፡2፥ 4፡14)። ኢየሱስ «ሰዎችን ሁሉ» ወደ ደኅንነት ያመጣ ዘንድ በመስቀል ላይ ሞተ (ዮሐ. 12፡32)። ይህ ማንም ሳይቀር ሰዎችን ሁሉ ማለት አይደለም። ምክንያቱም ዓለም ሁሉ እንደማይድን የተረጋገጠ ስለሆነ ነው፤ ነገር ግን ሰዎችን ሁሉ ማለት ካለምንም ልዩነት አይሁድና፥ አህዛብ፥ ሀብታምና ድሀ፥ ሃይማኖተኛና ሃይማኖት የሌለው ሳይባል ማለት ነው።

እግዚአብሔር ማንም እንዳይጠፋ ከፈለገ፥ ብዙዎች የሚጠፉት ለምንድን ነው? እግዚአብሔር ፍርዱን ያዘገየው የጠፉ ኃጢአተኞች ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ በመታገሡ ነው (2ኛ ጴጥሮስ 3፡9)፤ ነገር ግን ደኅንነት «እውነትን በማወቅ» ላይ የተመሠረተ ነው (1ኛ ጢሞ. 2፡4)። ሁሉም ሰው የወንጌልን እውነት አልሰማም። ከሰሙትም ብዙዎቹ ወደ ጎን ጥለውታል። የእግዚአብሔርን ሉዐላዊነት ምስጢር እና የሰውን ኃላፊነት ልናብራራው አንችልም (ዮሐ. 6፡37 ተመልከት)፤ ነገር ግን ሁለቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጹና በእግዚአብሔር ታላቅ የማዳን ዕቅድ ውስጥ ተጣምረው እንደሚገኙ እንረዳለን። ጸሎት እግዚአብሔር የጠፋውን ዓለም ለመድረስ በወጠነው ዕቅድ ውስጥ አስፈላጊ ሚና እንዳለው እናውቃለን። ለጠፉ ነፍሳት የመጸለይና (ሮሜ 10፡1)፥ ወንጌልን ለሌሎች ለማካፈል ራሳችንን የማዘጋጀት ኃላፊነት አለብን።

ሠ. የጸሎት መሠረት (1ኛ ጢሞ. 2፡5-7)፡- ብዙ አማኞች ጸሎት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አዳኝና መካከለኛ (አማላጅ) ሆኖ በሠራው ሥራ ላይ እንደሚመሠረት አያስተውሉም። እንደ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱሱ እግዚአብሔርና በደካሞች ልጆቹ መካከል ፍጹም የሆነ አማላጅ ነው። ኢዮብ በማጉረምረም ከጠየቃቸው ጥያቄዎች መካከል አንዱ መልእክቱን ወደ እግዚአብሔር ዙፋን የሚወስድለት አማላጅ ከማጣቱ ጋር የተያያዘ ነበረ። «እጁን በሁለታችን ላይ የሚያኖር ዳኛ በመካከላችን ምነው በተገኘ!» (ኢዮብ 9፡33)።

አንድ እግዚአብሔር ብቻ ስላለ፥ የሚያስፈልገው አንድ አማላጅ ብቻ ነው። ያም አማላጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሌላ ማንም ሰው ይህንን ተግባር ለማከናወን ብቁ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክም ሰውም ስለሆነ፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል «ዳኛ» መሆን ይችላል። ፍጹም በሆነው ሕይወቱና በሰዎች ቦታ ተተክቶ በመሞቱ፥ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕግ የሚጠይቃቸውን የጽድቅ ግዴታዎች አሟላ። «እርሱ ለሁሉ ቤዛ» ነበረ። «ቤዛ» የሚለው ቃል «አንድን ባሪያ ነጻ ለማውጣት የሚከፈል ዋጋ» ማለት ነው። የሞተውም «በሁሉም ሰው ፈንታ» ነበር። የክርስቶስ ሞት ለሚታመኑበት ብቻ የሚሠራ ቢሆንም፥ ለዓለም ሁሉ ኃጢአት በቂ ነው። ኢየሱስ «ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ» እንደመጣ ተናግሯል (ማቴ. 20፡28)።

ክርስቶስ «ለሰዎች ሁሉ» ስለ ሞተ፥ እግዚአብሔር «ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ» ፈቃዱ ነው። ይህ መልካም ዜና ወደ ኃጢአተኛው ዓለም የሚደርሰው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ወንጌልን ወደ ጠፉ ኃጢአተኞች የሚያደርሱትን መልእክተኞች ይጠራል፤ ይሾማልም። ጳውሎስ እንዲህ ያለ መልእክተኛ ነበረ። ሰባኪ (የንጉሡ አዋጅ ነጋሪ)፥ ሐዋርያ (ለልዩ ተልዕኮ የተላከ)፥ አስተማሪም ነበረ። ፍጻሜውን (የጠፉትን የማዳን ሥራ) ያዘጋጀው እግዚአብሔር፥ ለፍጻሜው የሚረዳውን መንገድ ያዘጋጀል። ይህም ጳውሎትና ቃሉን መስበክ ነው። ይህ መልካም ዜና ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን፥ ለአሕዛብም ጭምር ነው።

በመስቀል ላይ የተደረገው የክርስቶስ ኢየሱስ የመሥዋዕትነት ሥራ ለጳውሎት መሠረት ከሆነ፥ ጳውሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጣም አስፈላጊ ተግባር ነው ማለት ነው። አለመጸለይ መስቀሉን ማቃለል ነው! ለራሳችን ብቻ መጸለይ የመስቀሉን ዓለም አቀፋዊነት መካድ ማለት ነው። የጠፉትን ነፍሳት ችላ ማለት መስቀሉን ወደ ዳር መግፋት ነው። «ሰዎች ሁሉ» ለዚህ አንቀጽ ቁልፍ ነው። ክርስቶስ «ለሁሉም» ስለሞተና «ሁሉም» እንዲድኑ የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ፥ «ለሁሉም» እንጸልያለን። ጊዜው ሳያልፍ እግዚአብሔር ሰዎችን ለመድረስ ያዘጋጀው ዓለም አቀፍ መርሐ ግብር አካል ለመሆን ራሳችንን ለእግዚአብሔር መስጠት አለብን።

ረ. በጸሎት ውስጥ የሚኖረን አስተሳሰብ (1ኛ ጢሞ. 2፡8)፡- ጳውሎስ ወንዶች በማኅበር እንዲጸልዩ በግልጽ አስቀምጦታል። በቀደምቷ ቤተ ክርስቲያን ወንዶችም ሴቶችም ይጸልዩ ነበር (1ኛ ቆሮ. 11፡4-5)፤ ነገር ግን በዚህ ስፍራ ትኩረት የተደረገው በወንዶች ላይ

ነው። የሴቶችን የጸሎት ስብሰባዎች ማግኘት የተለመደ ነው፤ ነገር ግን የወንዶችን የጸሎት ስብሰባዎች ብዙ ጊዜ አናገኝም። ወንዶቹ ካልጸለዩ፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ስለ አገልግሎቷ ግድ የሚላቸውና ራሳቸውን የሰጡ መሪዎች አይኖሯትም።

ለአይሁድ ወንዶች እጃቸውን በማንሳትና ወደ ሰማይ በመዘርጋት መጸለይ የተለመደ ነበረ። ራሳችንን ዝቅ አድርገን፥ እጆቻችንን አጣጥፈንና ዓይኖቻችንን ጨፍነን የምንቀርብበት የጸሎት ልማዳችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየትም ቦታ አይገኝም ወይም አልታዘዘም። እርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ የጸሎት አደራረግ አቋሞች ይገኛሉ፡- እጆችን ዘርግቶ መቆም (1ኛ ነገ. 8፡22)፥ መንበርከክ (ዳን. 6፡10)፥ መቆም (ሉቃስ 18፡11)፥ መቀመጥ (2ኛ ሳሙ. 7፡18)፥ ራስን ዝቅ ማድረግ (ዘፍጥረት 24፡26)፥ ዓይኖችን ማንሳት (ዮሐ. 17፡1)፥ በመሬት ላይ መውደቅ (ዘፍ. 17፡3)። አስፈላጊው ነገር የሰውነት አቋም ሳይሆን፥ የልብ አቋም ነው።

ጳውሎስ ለውጤታማ ጸሎት 3 አስፈላጊ ነገሮችን ገልጿል። የመጀመሪያው «የተቀደሱ እጆች» ነበር። ይህ የተቀደሰ ሕይወት ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው። «ንጹሕ እጆች» የሚለው ነቀፋ የሌለበት ሕይወት ምሳሌ ነው (2ኛ ሳሙ. 22፡21፥ መዝ. (24)፡4)። በሕይወታችን ውስጥ ኃጢአት ካለ ለመጸለይም ሆነ እግዚአብሔር መልስ እንደሚሰጠን ለመጠበቅ አንችልም [መዝ. (66)፡18]።

«አለ ቁጣ» ሁለተኛው አስፈላጊ ነገር ሲሆን፥ እርስ በርሳችን በጥሩ ሁኔታ እንድንኖር ይፈልግብናል። ከሌሎች አማኞች ጋር በተደጋጋሚ ችግር ያለበትና ሰላምን ከመፍጠር ይልቅ ችግርን የሚፈጥር ሰው ለመጸለይና ከእግዚአብሔርም ዘንድ የጸሎት መልሶችን ለማግኘት አይችልም።

«ክፉ አሳብ» የሚለው በእምነት መጸለይ እንዳለብን ያሳያል። ግን በትክክል ቃሉ «ግሮት» ማለት ነው። በልባችን ቁጣ ሲኖር፥ ከሌሎች ጋር ብዙ ጊዜ ግልጽ አለመግባባቶች ይኖሩናል። ክርስቲያናች ተግባቢዎች ሆነው፥ አለመስማማትን መማር አለባቸው። «ሳናንገራጉር ክፉም ሳናስብ ሁሉን ማድረግ» መቻል አለብን (ፊሊ. 2፡14)።

ስለዚህ ውጤታማ ጸሎት፥ ማለት «የተቀደሱትን እጆች በማንሳት» ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ማድረግ፥ በተጨማሪ ደግሞ «አለ ቁጣና አለ ክፉ አሳብ» ከአማኞች ጋር ትክክለኛ ኅብረት እንዲኖር ያስፈልጋል። ኢየሱስ ይህንኑ ተመሳሳይ እውነት

አስተምሯል (ማር. 11፡24-26)። ለመጸለይ በመዘጋጀትና በእግዚአብሔር ፊት ልባችንን በማስተካከል የበለጠ ጊዜ ካሳለፍን፥ ጸሎታችን የበለጠ ውጤታማ ይሆናል።

2. የሴቶች መገዛት፡- (1ኛ ጢሞ. 2፡9-15)

በዚህ «የሴቶች ነጻነት» እና ሌሎች የሴቶች እንቅስቃሴዎች ባሉበት ዘመን «መገዛት» የሚለው ቃል አንዳንድ ሰዎችን ያስቆጣቸዋል። አንዳንድ የታወቁ ጸሐፊዎች እንኳን ጳውሎስ «ፀረ-አንስታይ» አቋም የያዘ «ጨቋኝ ያረጀ ወንደላጤ» እንደሆነ በመግለጽ ከሰውታል። በእግዚአብሔር ቃል መለኮታዊነትና ባለሥልጣንነት የምንታመን ሰዎች፥ የጳውሎስ ትምህርቶች ከራሱ ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር እንደመጡ እናውቃለን። መጽሐፍ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚገኙ ሴቶች በሚለው ነገር ላይ ችግር ካለብን፥ ጉዳዩ ቃሉን ከሰጠው ከእግዚአብሔር ጋር እንጂ ከጳውሎስ ጋር (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17)፥ ወይም ከጴጥሮስ ጋር (1ኛ ጴጥ. 3፡1-7) አይደለም።

በ1ኛ ጢሞ. 2፡11 ላይ «መገዛት» የሚለው ቃል፥ በኤፌሶን 5፡21-22 እና ቆላስይስ 3፡18 ላይ «መታዘዝ» ተብሎ ተተርጉሞአል። በቀጥታ ስንወስደው «በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆን» ማለት ነው። በጦር ኃይሎች ውስጥ ያገለገለ ማንም ሰው፥ «ደረጃ» የሚለው በትእዛዝ ከሥልጣን ጋር የተያያዘ እንጂ ከተፈላጊነትና ከችሎታ ጋር የተያያዘ እንዳልሆነ ያውቃል። ኮሎኔል ከተራ ወታደር በደረጃ ከፍ ያለ ነው፤ ነገር ግን ይህ ማለት ኮሎኔሉ የግድ ከተራ ወታደሩ የተሻለ ሰው ነው ማለት አይደለም። ይህ ኮሎኔሉ ከፍ ባለ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ፥ የበለጠ ሥልጣን አለው ማለት ነው።

«ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን» (1ኛ ቆሮ. 14፡40) የሚለው እግዚአብሔር በፍጥረቱ ውስጥ የሚከተለው መመሪያ ነው። አንድ ሠራዊት የሥልጣን ተዋረዶች ባይኖሩት ግራ እንደሚጋባና እንደሚተራመስ ሁሉ፥ በሕብረተሰብም አንዱ ለአንዱ መገዛት ከሌለ ቀውስ ያጋጥመዋል። እግዚአብሔር ልጆቹን እንዲያሠለጥኑና በፍቅር እንዲቀጧቸው ለወላጆች ሥልጣንን ስለ ሰጠ፥ ልጆች ለወላጆቻቸው መገዛት አለባቸው። ሠራተኞች ለአሠሪዎቻቸው መገዛት አለባቸው። (ኤፌ. 6፡58 የዚህ ጥቅስ ቀጥተኛ ማነጣጠሪያ ለቤት ውስጥ ባሪያዎች ቢሆንም፥ በዛሬው ዘመን ለሚገኙ ሠራተኞችም መሆን ይችላል።) ዜጎች ባለሥልጣኖቹ ክርስቲያኖች ባይሆኑም እንኳን፥

ለመንግሥት ባለስልጣናት ሊገዙ ይገባቸዋል (ሮሜ 13፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡13-20)።

መገዛት የበታች መሆን አይደለም። መገዛት እግዚአብሔር በቤተሰብና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሰጠው የግንኙነት ደረጃ ማወቅና በደስታ መታዘዝ ነው። አንዲት ክርስቲያን ሚስት ለጌታና ለባለቤቷ በደስታ ስትገዛ፥ ይህ በርስዋ ሕይወት ውስጥ ከሁሉም የላቀ ውጤት ማስከተል አለበት። (ይህ እንዲሆን፥ ባልየው ሚስቱን መውደድ አለበት፤ በባልና በሚስት በኩል ከእግዚአብሔር የተሰጠውን የግንኙነት ደረጃ በመጠቀም እንዲጣሉበት ሳይሆን እንዲታነጹበት የሚያደርጉት መሣርያ ሊሆን ይገባል። ኤፌ. 5፡18-33)። መገዛት ለመንፈሳዊ ዕድገትና አገልግሎት ቁልፍ ነው፡- ባሎች ለጌታ መገዛት አለባቸው፤ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው አንዱ ለሌላው መታዘዝ አለባቸው (ኤፌ. 5፡21)። ደግሞም ሚስቶች ለጌታና ለባሎቻቸው መገዛት አለባቸው።

በዚህ ክፍል (1ኛ ጢሞ. 2፡9-15) ውስጥ ትኩረት የተደረገው ሴቶች በቤተ ክርስቲያን በሚኖራቸው ቦታ ላይ ነው። ጳውሎስ እነዚህን አማኝ ሴቶች መገዛታቸውን በብዙ መንገዶች እንዲያሳዩ ያበረታታል።

ሀ) ተገቢ አለባበስ (1ኛ ጢሞ. 2፡9)፡- በዚህ ስፍራ የተመለከተው፥ በዓለማዊው ሰው ሠራሽ ብልጭልጭታ እና ፈሪሃ-እግዚአብሔር ባለበት እውነተኛ ውበት መካከል ያለው ልዩነት ነው። ጳውሎስ ጌጦችንና ጥሩ ጥሩ ልብሶችን አልከለከለም፤ ነገር ግን እርሱ የሚቃወመው፥ የዋህና ረጋ ያለ መንፈስ (1ኛ ጴጥ. 3፡1-6 ተመልከት) ያለበት እውነተኛ ውበት እንዲህን ነገሮች ከሚገባው በላይ በመጠቀም ስለተተካ ነው። በውጪ ባለው ነገር ላይ ብቻ የምትደገፍ ሴት ብዙም ሳይቆይ ድርጊቷን ለመከላከል የምትጠቀምባቸው ማመካኛዎችዋ ይከዷታል። የሰውን አሳብ ልትስብ ትችል ይሆናል፤ ነገር ግን ዘላቂ ፍቅር ለማግኘት አትችልም። ምናልባት የጊዜው ዘመናዊው ፋሽን በኤፌሶን ባለችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን ሴቶች እየፈተነ ስለሆነ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሴቶቹ እንዳይጠመዱ እንዲያስጠነቅቃቸው ማስታወስ ነበረበት።

«የሚገባ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል (1ኛ ጢሞ. 2፡9) «አግባብና ሥርዓት ያለው» ማለት ነው። በእንግሊዝኛ «ኮዝሞቲክ» (ሴቶች ለማማር የሚጠቀሙት የገላ መዋቢያ) የሚለውን ቃል ካገኘንበት የግሪክ ቃል ጋር የተዛመደ ነው። የሴት አለባበስ ተገቢ፥ ሥርዓት ያለውና

መልካም መዓዛ የሚሰጥ መሆን አለበት። «እፍረት» ማለት በቀጥታ ሲተረጎም «አግባብ፥ ከመጠን ያለፉትን ነገሮች ማስወገድ» ማለት ነው። ይህንን ጠባይ የያዘች ሴት ተገቢና ትክክለኛ ከሆነው ነገር ለማለፍ ታፍራለች። «ጭምት» የሚለው ቃል «አስተዋይ አእምሮና ጥሩ ስሜት» ተብሎ ከሚተረጎም የግሪክ ቃል የመጣ ነው። ውስጣዊ ራስ መግዛትን የሚገልጽና ለአንድ ሰው መልካምና ተገቢ የሆነውን ነገር የሚናገር መንፈሳዊ የአቅጣጫ ጠቋሚ ነው።

ኤፌሶን ሀብታም የንግድ ከተማ ስለነበረች፥ አንዳንድ ሴቶች የሰዎችን ትኩረት ለመሳብና ለመታወቅ እርስ በርሳቸው ይወዳደሩ ነበር። በዚያን ጊዜ ውድ የፀጉር አሠራሮች ብዙ ዋጋ ከሚያወጡ ጌጣ ጌጦች ጋር ተዳምረው፥ በሕብረተሰቡ ውስጥ የበላይነቱን ለመቀዳጀት የሚያስችሉ መንገዶች ነበሩ። ጳውሎስ ክርስቲያኖቹን ሴቶች ክርስቶስ ብቻ ሊሰጥ በሚችለው እውነተኛ ውበት ማለትም «ውስጣዊ ሰው» ላይ እንዲያተኩሩ ያበረታታል። መልካም አለባበስንና ጌጣጌጦችን አልከለከለም። በአግባብነትና በቅዱስ ባሕርይ ላይ የበለጠ በማተኮር፥ በሚዛናዊነትና ቅድሚያ በመስጠቱ ጉዳይ ላይ ጥንቃቄ እንድናደርግ ያሳስባል።

በአንድ የበጋ ወራት አንዲት የቤተ ክርስቲያን አባል «ለክርስቲያን ሴት ትክክለኛውን ዓይነት ልብስ ማግኘት ከባድ እየሆነ እየመጣ ነው» ብላ ነገረችኝ። «የሚሸጧቸውን የዋና ልብሶች የሚመስሉትን ለመልበስ አልፈለግሁም። በጭራሽ ወደ ዋናም አልሄድም። ለመሆኑ የድሮ ዘመኑን ጨዋነት የበላው ምን ይሆን?»

ለ) በጎ ምግባራት (1ኛ ጢሞ. 2፡10)፡- ጳውሎስ መልካም ሥራዎች አለባበስን ይተካሉ አላለም፤ ነገር ግን የውድ ልብሶችንና ጌጣጌጦችን «ዋጋቢስነት» ከመልካም ባሕርይና ከክርስቲያናዊ አገልግሎት ጋር እያነጻጸረ ነበረ። በጳውሎስ የመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ «እግዚአብሔርን መምሰል» ሌላው ቁልፍ ቃል ነው (2፡2፥ 10፤ 3፡16፤ 4፡7-8፤ 6፡3፥ 5-6፥ 11፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡5፤ ቲቶ 1፡1)። ብልጭልጭ ነገር በከፊል በውጪው አካል ላይ እንዲኖር ማድረግ ይቻላላል፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን መምሰል ከውስጥ መምጣት አለበት።

መልካም ሴቶች በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ የተጫወቱትን ሚና በፍጹም ዝቅ አድርገን መገመት የለብንም። የወንጌል መልእክት በእነርሱ ላይ ያመጣው አስደናቂ ለውጥ ነበረው፤ ምክንያቱም

በእግዚአብሔር ፊት ያላቸውን ዋጋና በክርስቶስ አካል ውስጥ ያላቸውን እኩልነት አረጋግጦ ስለነበረ ነው (ገላትያ 3፡28)። በሮማውያን ዓለም ሴቶች ዝቅ ያለ ቦታ ነበራቸው፥ ወንጌል ግን ያንን ለወጠ።

በምድር ላይ በነበረው የአገልግሎት ጊዜ ኢየሱስን ለማገልገል ራሳቸውን የሰጡ ሴቶች ነበሩ (ሉቃ. 8፡1-3)። ሲሰቀልና ሲቀበር በቦታው ነበሩ። ደግሞም የትንሣኤውን አስደናቂ ዜና በመጀመሪያ ያወጀችው ሴት ነበረች። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ዶርቃን (የሐዋ. 9፡36-43)፥ ልድያን (16፡14-15)፥ ጵርስቅላንና (18፡1-3) በቤርያና በተሰሎንቄ አብያተ ክርስቲያናት የነበሩትን መልካም ሴቶች (17፡4፥12) እናገኛለን። ጳውሎስ በሮሜ 16 ቢያንስ 8 ሴቶችን ሰላም ብሏል። የሮሜን መልእክት ወደ ሮሜ ቤተ ክርስቲያን የወሰደችው ፌቤን በቤተ ክርስቲያኒቷ ዲያቆን ነበረች (ሮሜ 16፡1)። ብዙ አማኝ ሴቶች ባሎቻቸውን ለጌታ በመማረክ፥ ቤታቸውን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ክፍት አድርገዋል።

ሐ. በጥሞና መማር (1ኛ ጢሞ. 2፡11) «ዝምታ» የሚለው አማኝ ሴቶች በማጎበር በፍጹም አፋቸውን መክፈት እንደሌለባቸው የሚከለክል ስሜት ስለሚሰጥ፥ ጥሩ ትርጉም አይደለም። ይህ በቁጥር ሁለት ላይ «ጭምትነት» ተብሎ ከተተረጎመው ጋር አንድ ዓይነት ቃል ነው። አንዳንድ ሴቶች በክርስቶስ ያገኙትን አዲስ ነጻነት በአግባቡ ባለመጠቀም፥ በስብሰባዎች ላይ ጣልቃ በመግባት ረብሻዎችን ይፈጥሩ ጀመር። ጳውሎስ በዚህ ግሣጼ ውስጥ የገለጸው ይህን ነበር። ሴቶች በነጻነታቸው «ለመደሰት» በመሞከር ቤተ ክርስቲያንን ለማሳዘን ለሚችሉበት አደጋ እንደተጋለጡ ያሳያል። ይህንን ዓይነት ግሣጼ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንም ጽፎ ነበረ (1ኛ ቆሮ. 14፡34)፤ በእርግጥ ያን ጊዜ በይበልጥ ያተኮረው በልሳን መናገርን በተመለከተ ነበር።

መ. ባለሥልጣንን ማክበር (1ኛ ጢሞ. 2፡12-15)፡- ሴቶች እንዲያስተምሩ ተፈቅዶላቸዋል። ትልልቅ ሴቶች ወጣቶቹን ሴቶች ማስተማር አለባቸው (ቲቶ 2፡3-4)። ጢሞቴዎስ በቤቱ በእናቱና በአያቱ የተማረ ነበረ (2ኛ ጢሞ. 1፡5፤ 3፡15)፤ ነገር ግን በማስተማር አገልግሎታቸው በወንዶች ላይ «መጫን» የለባቸውም። መልካም ሴት አንድን ወንድ በግል ብተመከረው ምንም ችግር የለበትም (የሐዋ. 18፡24-28)። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥልጣን እንዳላት በመገመት፥ የወንድን ቦታ ለመውሰድ መሞከር

የለባትም። «ዝምተኝነትን» መለማመድና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስነ ሥርዓት እንዲኖር ማገዝ አለባት።

ጳውሎስ ክርስቲያን ወንዶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ መሪዎች መሆን አለባቸው የሚለውን ምክር ለመደገፍ ብዙ ምክንያቶችን አቅርቧል። የመጀመሪያው ምክንያት ከፍጥረት ነው፡- አዳም ቀድሞ ተፈጥሯል፥ ከዚያም ሔዋን ተፈጠረች (1ኛ ጢሞ. 2፡12-13)። (ጳውሎስ ይህንኑ ተመሳሳይ ምክንያት በ1ኛ ቆሮ. 11፡1-10 ተጠቅሞአል።) ቅድሚያ ማግኘት ማለት መብለጥ ማለት እንዳልሆነ ልብ ማለት አለብን። ወንድና ሴት ሁለቱም የተፈጠሩት በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር አምሳል ነበር። ጉዳዩ ከሥልጣን ጋር የተያያዘ ነው። ወንድ በመጀመሪያ ተፈጥሯል።

ሁለተኛው ምክንያት ከሰው በኃጢአት ውስጥ ከመውደቅ ጋር የተያያዘ ነው። ሰይጣን ሴቷን ኃጢአት እንድታደርግ አታለላት (2ኛ ቆሮ. 11፡3፤ ዘፍ. 3፡1-8)። ወንዱ ዓይኖቹ እያዩ ኃጢአትን ሠራ። ምክንያቱም አዳም ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ትእዛዝ ወደ ጎን በመተው ሚስቱን ሰማ፤ እግዚአብሔርንም አልታዘዘም፤ ስለዚህ ኃጢአትንና ሞትን ወደ ዓለም አመጣ። የሚስቶች ለገዛ ባሎቻቸው መገዛት በመጀመሪያው የፍጥረት ታሪክ ውስጥ የተገለጠ ነበር። ዛሬ በጎብረተሰብ ውስጥ የምንመለከተው ፈር የለቀቀ ሁኔታ ያንን ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ትእዛዝ ከመተላለፍ የመነጨ ነው።

ጳውሎስ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ሞኞች በመሆናቸው በቀላሉ ይታለላሉ ማለቱ አይመስለኝም። ምክንያቱም ልምምዳችን ወንዶችም ሴቶችም በሰይጣን እንደሚታለሉ ስለሚያረጋግጥልን ነው። በአንድ ወቅት፥ አብርሃም ሚስቱን ሰማና ችግር ውስጥ ገባ (ዘፍ. 16)። በኋላም መከረችውና እግዚአብሔርም እንዲሰማት ነገረው (ዘፍ. 21)። በመጋቢነት አገልግሎቴ እግዚአብሔርን ከሚፈሩ ሴቶች ከማገኘው ማበረታቻና ምክር ብዙ ተጠቅሜአለሁ፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥልጣንን አላግባብ እንዳይይዙ ለማድረግ ሞክሬአለሁ። በእርግጥ የማውቃቸው እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሴቶች፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነገሮችን ለማካሄድ ፍላጎት የላቸውም።

ሴትን በዝቅተኛ ቦታ የማስቀመጥ ምክንያቶች፥ የሰው ልጆች አፈጣጠርና አወዳደቃቸው ይመስላሉ፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣት አገልግሎት አለ (1ኛ ጢሞ 2፡15)። ምናልባት በዚህ ስፍራ እርሱ በጠቀሰውና «ከሴት የተወለደ» አዳኝ እንደሚመጣ ሙሴ በዘፍ.

3፡16 በጻፈው መካከል በጳውሎስ አእምሮ ውስጥ የጠበቀ ግንኙነት ሳይኖር አይቀርም። አዳኙ ወደ ዓለም የሚመጣው በሴት በኩል ነበረ። (ኢየሱስ ምድራዊ እናት እንደነበረውና ነገር ግን ምድራዊ አባት እንዳልነበረው አስታውስ (ሉቃ. 1፡34-35፥ ማቴ. 1፡18-21)።

ነገር ግን ጳውሎስ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ትምህርት ያስተምራል (1ኛ ጢሞ. 2፡15)። «ሁለቱም» ባልና ሚስት በእውነተኛ መሰጠት ለጌታ ከኖሩ፥ ሴቷ «በመውለድ ትድናለች» በማለት ጳውሎስ ቃል ይገባል።

ይህ ማለት ክርስቲያን እናቶች ልጅ በመውለድ ጊዜ አይሞቱም ማለት ነውን? ታሪክና ልምምድ እንደሚሞቱ ይነግሩናል። እግዚአብሔር የራሱ ዓላማዎች አሉት። መንገዱ ደግሞ ከአሳባችን ከፍ ያለ ነው (ኢሳ. 55፡8-9)። ጳውሎስ በዚያን ጊዜ የነበሩትን አማኝ ሴቶች የሚያበረታታ አጠቃላይ መመሪያ ሰጥቶ ነበረ። አገልግሎታቸው ቤተ ክርስቲያንን «መምራት» ሳይሆን፥ ለቤታቸው መጠንቀቅና ልጆችን ለእግዚአብሔር ክብር መውለድና ማሳደግ ነበር (1ኛ ጢሞ. 5፡14)። በቤታቸው የሚያደርጉዋቸው ስብሰባዎች ቃሉን ለማስተማርና ቅዱሳንን ለማገልገል እንዲችሉ ብዙ ዕድሎችን ይሰጧቸዋል (ሮሜ 16፡1-6 ተመልከት)።

በመጋቢነት ስሜት ቃሉን ለማስተማር የተጠሩ ባይሆኑም እንኳን፥ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሴቶች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ አገልግሎት አላቸው። ሁሉም ነገር «በአግባብና፥ በሥርዓት» ከተሠራ እግዚአብሔር ይባርከዋል።

መሪዎችን ተከተል

1ኛ ጢሞቴዎስ 3

በቤተሰብም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ ሁሉም ነገር የሚነሳው ወይም የሚወድቀው በአመራር ምክንያት ነው። መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግሉ ስጦታዎችን ይሰጣል። ከእነዚህ ስጦታዎች ውስጥ «መጋቢዎችና አስተማሪዎች» (ኤፌ. 4፡11)፥ «ዕርዳታና» «አገዛዝ» (አስተዳደር 1ኛ ቆሮ. 12፡28) ይገኙባቸዋል። አስቀድመን እንዳየነው፥ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሕያው የሆነ የአማኞች ጎብረት ብትሆንም፥ በሚገባ በሥርዓት ካልተመራች ትሞታለች። አመራር የመንፈሳዊ አደረጃጀት አንዱ አካል ነው።

በዚህ ክፍል ጳውሎስ ጳጳስን፥ ዲያቆንንና ቤተ ክርስቲያን ራሷን ገልጿል። እነዚህን ሦስት ገለጻዎች በመረዳት፥ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተሻለ አመራር ለመስጠት እንችላለን።

1. መጋቢው (1ኛ ጢሞ. 3፡1-7)

እንደ አዲስ ኪዳን አገላለጽ፥ ኤጲስ ቆጶስ፥ «መጋቢ» እና «ሽማግሌ» የሚሉት ቃላት ተመሳሳይ ናቸው። «ጳጳስ» ማለት ከላይ ሆኖ በኃላፊነት «የሚቆጣጠር» ነው። ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያንን ሥራ የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው 1ኛ ጴጥ. 5፡1-3፥ የሐዋ. 20፡17፥ 28)። «ሽማግሌ» በግሪክ «ፕሬስብዩትስ» የሚል ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙም «ያረጀ ሰው» ማለት ነው። ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞ. 4፡14 «ፕሬስቢተሪ» የሚለውን ቃል አንድን ቤተ ክርስቲያን /ዲኖሚኔሽን/ ሳይሆን፥ ጢሞቴዎስን የሾመውን «የሽምግልና» ማህበር ለማሳየት ተጠቅሟል። ሽማግሌዎችና ኤጲስ ቆጶሳት (ለአንድ ሥራ የተሰጡ ሁለት ስሞች፤ ቲቶ 1፡5፥ 7) በመንፈሳዊ ጥበብና ልምድ የበሰሉ ሰዎች ነበሩ። በመጨረሻም «መጋቢ» ማለት «እረኛ» ማለት ሲሆን፥ የእግዚአብሔርን መንጋ የሚመራና የሚጠብቅ ማለት ነው።

ከዚህ ቦታ ለኤጲስ ቆጶሳት የተሰጡትን መስፈርቶችና በቲቶ 1፡5-9 ለሽማግሌዎች የተሰጡትን ስታወዳድር፥ በሁለቱም ወገን አንድ ዓይነት ሥራ እንዳለ ታያለህ። በሐዋርያት ዘመን የቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት በጣም ቀላል ነበር፡- መጋቢዎች (ሽማግሌዎች፥ ኤጲስ ቆጶሳት) እና ዲያቆናት ነበሩ (ፊልጵ. 1፡1)። አንዳንዶቹ በመምራት

(አደረጃጀትና አስተዳደር)፥ ሌሎች ደግሞ በማስተማር የአያንዳንዱን ቤተ ክርስቲያን ሥራ በመቆጣጠር ላይ የተሰማሩ በርካታ ሽማግሌዎች ሳይኖሩ አይቀሩም (1ኛ ጢሞ. 5፡17)።

ነገር ግን እነዚህ ሰዎች የሠለጠኑ መሆን ነበረባቸው። አንድ አዲስ አማኝ ኤጲስ ቆጶስነት ቢፈልግ ጥሩ ነበር። ነገር ግን ይህንን ለማግኘት የሚሻለው መንገድ የክርስቲያናዊ ባሕርይን ማሳደግና የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ነበር፡- በቀደምቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ (ኤጲስ ቆጶስ) መሆን በቀላሉ የሚታይ ሳይሆን፥ ከባድና ቆራጥ ውሳኔ ነበረ። ጳውሎስ አንድ ሰው በሽምግልና በኤጲስ ቆጶስነት ወይም በመጋቢነት ለማገልገል ከፈለገ፥ 16 መስፈርቶችን እንዲያሟላ አቅርቧል፡-

ሀ. የማይነቀፍ (1ኛ ጢሞ. 3፡2) ፡- ይህ ቃል በቀጥታ ሲተረጎም «እንከን የሚሆን ምንም ነገር ሳይኖር» ማለት ነው። ይህም፥ ሰይጣን ወይም ያልዳኑት ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን ለመኮነን ወይም ለማጥቃት የሚያላክኩበት አንዳችም ምክንያት በሕይወቱ መኖር የለበትም ማለት ነው። ሕያው ሰው ሆኖ ኃጢአት የሌለበት ማንም የለም። ነገር ግን ያለነቀፋ ወይም «ከነቀፋ ውጪ» ሆነን ለመገኘት መጣር አለብን።

ለ. የአንዲት ሚስት ባል (1ኛ ጢሞ. 3፡2)፡- በዚህ ምዕራፍ ሁሉም ገላጭ ቅጽሎች በተባዕታይ ፆታ የተጠቀሱ ናቸው። በማኅበር ለሴቶች አገልግሎት የሰፋ ቦታ ሲኖር፥ የሽምግልና ሥራ ግን ለሴቶች አልተሰጠም። ሆኖም የመጋቢው የቤት ውስጥ ሕይወት፥ በተለይም የጋብቻ ሁኔታው በጣም አስፈላጊ ነው። (በቁ. 12 መሠረት ይኸው ተመሳሳይ መስፈርት ለዲያቆናትም ይሆናል)። ይህም አንድ መጋቢ የተፋታና በድጋሚ ያገባ መሆን የለበትም ማለት ነው። አንድ መጋቢ ቀርቶ የቤተ ክርስቲያን አባል እንኳን ከአንድ በላይ ሚስት ካለው ተቀባይነት ስለማያገኝ፥ ጳውሎስ የሚናገረው ብዙ ሚስቶችን ስለማግባት አይደለም። ደግሞም ከሚስት ሞት በኋላ እንደገና ማግባትንም አይደለም የሚጠቅሰው። ምክንያቱም በዘፍ. 2፡18 እና በ1ኛ ጢሞ. 4፡3 መሠረት አንድ መጋቢ እንደገና ለማግባት ለምን ይከለከላል? የትዳር ጓደኞቻቸውን ያጡ የቤተ ክርስቲያን አባላት ያለ ጥርጥር በድጋሚ ማግባት ይችላሉ። ታዲያ ለምን መጋቢው ይቀጣል?

የአንድ ሰው ትዳሩንና ቤቱን የማስተዳደር ችሎታው፥ ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ያለውን ችሎታ እንደሚያሳይ ግልጽ ነው (1ኛ

ጢሞ. 3፡4-5)። የፈታ መጋቢ ራሱንና ቤተ ክርስቲያንን ከውጪ ሰዎች ለሚመጣ ነቀፌታ ከማጋለጡም በላይ፥ የጋብቻ ችግሮች ያሉባቸው ሰዎች የራሱን ትዳር አስተካክሎ ካልጠበቀ ሰው ምክር ፍለጋ ይመጣሉ ተብሎ አይገመትም። ፈትተው ሌላ ያገቡና ለጌታ የተሰጡ ክርስቲያኖች በሌሎች አገልግሎቶች ውስጥ ሊያገለግሉ የማይችሉበት ምክንያት አይታየኝም። ነገር ግን ሽማግሌዎችና ዲያቆናት ለመሆን አይችሉም።

ሐ. ልከኛ (1ኛ ጢሞ. 3፡2)፡- ይህ ማለት፥ ራሱን የሚቆጣጠርና የሚገዛ ማለት ነው። «ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ» (2ኛ ጢሞ 4፡5 ቀጥተኛ ትርጉም) ወይም «አንተ ግን በሁሉ ነገር ራስህን ተቆጣጠር»። አንድ መጋቢ በሁሉ ነገር በማስተዋል የሚያመዛዝነውን ነገር በሥራ የሚተረጉም መሆን አለበት።

መ. ራሱን የሚገዛ (1ኛ ጢሞ. 3፡2)፡- ቆራጥ አመለካከት ያለውና በሥራው ትጉህ መሆን አለበት። ይህ ምንም ስሜት የሌለው፥ ወይም ሁልጊዜ ዝግትና ጭፍግግ ያለ ነው ማለት አይደለም። ነገር ግን የነገሮችን ዋጋ የሚያውቅና በማይገባ ባሕርይ አገልግሎቱን ወይም የወንጌልን መልእክት የማያቃልል ማለት ነው።

ሠ. እንደሚገባው የሚሠራ (1ኛ ጢሞ. 3፡2)፡- «ሥርዓት ያለው» የሚለው የተሻለ ትርጉም ይሆናል። መጋቢው በአስተሳሰቡና በኑሮው እንዲሁም በማስተማሩና በስብከቱ የተቀናጀ መሆን አለበት። ይህ ቃል የሴቶችን አለባበስ በሚመለከት በ1ኛ ጢሞ. 2፡9 «በሚገባ» ተብሎ ከተተረጎመው የግሪክ ቃል ጋር አንድ ነው።

ረ. እንግዳ ተቀባይ (1ኛ ጢሞ. 3፡2)፡- በቀጥታ ሲተረጎም «እንግዳን መውደድ» ማለት ነው። ተጓዥ አማኞች የሚያርፉባቸውን ቦታዎች ስለሚፈልጉ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን፥ ይህ አስፈላጊ አገልግሎት ነበር (ሮሜ 12፡13፥ ዕብ. 13፡2፤ 3ኛ ዮሐ. 5-8)። ዛሬም እንኳን እንግዳ ተቀባይ የሆኑ መጋቢና የመጋቢ ሚስት በቤተ ክርስቲያን ላለው ጎብረት ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ።

ሰ. ለማስተማር የበቃ (1ኛ ጢሞ. 3፡2)፡- ከሽማግሌ ዋና ዋና አገልግሎቶች ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር አንዱ ነው። እንዲያውም ብዙ ምሁራን በኤፌ. 4፡11 የተጠቀሱት «መጋቢዎችና አስተማሪዎች» አንድን ሰውና ሁለት ተግባራትን እንደሚያከናውን ያምናሉ። መጋቢ በቀጥታ አስተማሪ ነው (2ኛ ጢሞ. 2፡2፥ 24)። በ1800ዎቹ በአሜሪካ የታወቁት ጳጳስ ፊሊፕስ ብሩክስ «የማስተማር ብቃት፡- በአጋጣሚ የሚመጣ ወይም በቅንዓት

የሚያገኝ አይደለም» ብለዋል። አንድ መጋቢ የእግዚአብሔርን ቃልና እንዲሁም ያንን ቃል እንዲያውቅና እንዲያስተምር የሚረዳውን ነገር ሁሉ በጥንቃቄ የሚማር መሆን አለበት። በጥናቱ ሰነፍ የሆነ መጋቢ÷ በመድረክ ላይ አሳፋሪ ነው።

ሸ. የማይሰክር (1ኛ ጢሞ. 3፡3)፡- ቃሉ የሚገልጸው ብርሌውን ጨብጦ ለረዥም ጊዜ የሚቀመጠውንና ከዚያም የተነሣ ከሚገባው በላይ የሚጠጣውን ሰው ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለመድኃኒትነቱ ሲል ወይን ጠጅ እንዲጠቀም መምከሩ÷ (5፡23) አማኞች በፍጹም እንዳልተከለከሉ ያሳያል። በጣም የሚያሳዝነው ግን የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት በጌታ ራት ጊዜ ባለው የፍቅር ግብዣ ላይ እንኳን ጠጥተው ይሰክሩ ነበረ (1ኛ ቆሮ. 11፡21)። የአይሁድ ሕዝቦች ወይን ጠጁ ጠንካራ እንዳይሆን ከውኃ ጋር ይቀላቅሉት ነበረ። በዚያን ጊዜ ውኃ ንጹሕ እንዳልሆነ በደንብ ይታወቅ ነበረ። ስለዚህ በመጠን የተወሰደ ቀላል የወይን ጠጅ ለመጠጣት ጤናማ ይሆን ነበር።

ሆኖም ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን በነበረው የወይን ጠጅ ባሕላዊ አጠቃቀምና የዛሬውን የአልኮል ኢንዱስትሪ በመደገፍ መካከል ሰፊ ልዩነት አለ። በሮሜ 14 (በተለይም ቁጥር 21) ያለው የጳውሎስ ምክርና ምሳሌ ለዛሬው ዘመን በልዩ መንገድ ይጠቅማል። እግዚአብሔርን የሚፈራ መጋቢ ጥሩ ምሳሌ መሆን እንጂ÷ በአንድ ደካማ ወንድም ሕይወት ውስጥ ለሚኖር ኃጢአት ምክንያት መሆን አይፈልግም።

ቀ. የማይጨቃጨቅ (1ኛ ጢሞ. 3፡3) - «ተጋፊ ያልሆነ ጥልን የማይፈልግ»። ቻርለስ ስፐርጅን የመጋቢዎች ኮሌጅ በተባለው ትምህርት ቤት ለሚማሩት ተማሪዎች እንዲህ አሏቸው፡- «ለመደባደብ እጃችሁን ጨብጣችሁ÷ ከሱሪያችሁ ሥር በጭናችሁ ላይ ሥነ-መለኮታዊ ሽጉጥ አንግባችሁ ወደ ዓለም ዙሪያ አትሂዱ»

በ. ገንዘብን የማይወድ (1ኛ ጢሞ. 3፡3)፡- ጳውሎስ በ (6፡3-10) ስለ ገንዘብ ብዙ የሚለው ነገር አለው። አንድ ሰው ሕሊና ወይም ግብረ-ገባዊ ጨዋነት ከሌላው አገልግሎቱን በቀላሉ ገንዘብ የማግኛ መንገድ አድርጎ ሊጠቀምበት ይችላል። (በብዙ አብያተ ክርስቲያናት መጋቢዎች በሚገባ አይከፈላቸውም)። ገንዘብን የሚመኙ መጋቢዎች ሁልጊዜ ከቤተ ክርስቲያናቸው ውጪ «ጉዳዮች» አሉዋቸው። እነዚህ ጉዳዮች ባሕርያቸውን ያበላሻሉ ደግሞም አገልግሎታቸውን ያደናቅፋሉ። መጋቢዎች መጥፎውን ረብ በመመኘት (1ኛ ጴጥ. 5፡2) መሥራት የለባቸውም።

ተ. ገር የሆነ (1ኛ ጢሞ. 3፡3)፡- «ትሁት» የተሻለ ትርጓሜ ነው። መጋቢው ሰዎችን የሚሰማና ሳይከራከር ትችትን መቀበል የሚችል መሆን አለበት። ሌሎች በመጋቢው «ሳይጨቆኑ» በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ መፍቀድ አለበት።

ቸ. ሰላማዊ የሆነ (1ኛ ጢሞ. 3፡3) መጋቢዎች ጥልን የሚፈጥሩ ሳይሆኑ፥ ዕርቅን የሚያደርጉ መሆን አለባቸው። ይህ ማለት ባመኑበት ነገር ላይ መወላወል አለባቸው ማለት ሳይሆን፥ ነገር ግን ልዩነታቸውን በሰላማዊ መንገድ መግለጽ መቻል አለባቸው። ቶሎ የሚቆጣ ባሕርይ ለዘላቂ አገልግሎት አይበጅም።

ኀ. ስግብግብ ያልሆነ (1ኛ ጢሞ. 3፡3)፡- ከገንዘብ በተጨማሪ ብዙ ነገሮች መመኘት ትችላለህ። ለምሳሌ በሰዎች ዘንድ መወደድ፥ ታዋቂ የሚያደርግ ሰፊ አገልግሎት፥ የራስ ቤተ ክርስቲያንን ማስፋፋት ወዘተ ናቸው። ይህ ቃል በተለይ በገንዘብ ላይ ያተኩራል።

ነ. የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር (1ኛ ጢሞ. 3፡4-5)፡- ይህ አንድ መጋቢ ያገባ ወይም ካገባ ልጆች ያሉት መሆን አለበት ማለት አይደለም። ዳሩ ግን ጋብቻና የቤተሰብ ሕይወት ለብዙዎቹ መጋቢዎች የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን አይቀርም። የአንድ ሰው ልጆች ካልታዘዙትና ካላከበሩት፥ ቤተ ክርስቲያኑ የእርሱን አመራር ሊያከብርና ሊታዘዝ ይችላል ማለት አይቻልም። ለክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንና ቤት አንድ ናቸው። ሁለቱንም በፍቅር፥ በእውነትና በሥነ-ሥርዓት መቆጣጠር አለብን። መጋቢው በቤት አንድ ዓይነት በቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሌላ ዓይነት ሰው መሆን አይችልም። እንዲህ ከሆነ ግን ልጆቹ ያውቁበታል። ከዚያም ችግሮች ይከሰታሉ። በቁጥር 4 እና 5 ላይ «የሚያስተዳድር» እና «ማስተዳደር» ተብለው የተጠቀሱት ቃላት «በሥልጣን መግዛት፥ ማስተዳደር» የሚል ትርጉም ሲኖራቸው፥ መጋቢ የቤተ ክርስቲያኒቷን ሥራ የሚመራ መሆኑን ያሳዩናል። (ይህም የሚደረገው እንደ ጨቋኝ ሳይሆን፥ እንደ አፍቃሪ እረኛ ነው - 1ኛ ጴጥ. 5፡3)። በቁጥር 5 ላይ «ይጠብቃታል» ተብሎ የተተረጎመው ቃል ቤተ ክርስቲያኒቱን አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ሁሉ በግሉ የሚያገለግል እንደሆነ ያሳያል። ይህ ደጉ ሳምራዊ የቆሰለውን ሰው እንደተንከባከበው በሚገልጸው ምሳሌ ውስጥ የተጠቀሰ ቃል ነው (ሉቃ. 10፡34-35)።

ኘ. አዲስ ክርስቲያን ያልሆነ (1ኛ ጢሞ. 3፡6)፡- ይህ አዲስ የተተከለ እንደ ማለት ነው። ዕድሜ ለአንድ ሰው መብሰል ዋስትና አይደለም።

ነገር ግን አንድ ሰው ቤተ ክርስቲያንን የመምራት ኃላፊነት ከመቀበሉ በፊት ለጥናትና ለዕድገት እንዲሆነው ለራሱ ጊዜ ቢሰጥ መልካም ይሆንለታል። በእርግጥ አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች ፈጥነው በሳል ይሆናሉ። ሰይጣን አንድ ወጣት መጋቢ ሲሳካለት፥ ሲታበይና ከዚያም የተገነባውን ሁሉ ሲያፈርስ ማየት ደስ ይለዋል።

ኣ. በውጭ ባሉት ሰዎች ዘንድ መልካም ምስክርነት ያለው (1ኛ ጢሞ. 3፡7)፡- እንደ መብራትና ውኃ ወዘተ. መክፈል ያለበትን ዕዳ ይከፍላል? አብሮ በሚሠራባቸው ባልዳኑት ሰዎች አካባቢ መልካም ስም አለው? (ቆላ. 4፡5 ና 1ኛ ተሰ. 4፡12 ተመልከት) ማንም መጋቢ መሆን እንደሚገባኝ ሆኖለሁ ብሎ አያስብም፤ ስለዚህ ምዕመናኑ ባለማቋረጥ ለእርሱ መጸለይ አለባቸው። በመጋቢነት/በሽምግልና ማገልገል ቀላል አይደለም። ነገር ግን ባሕርይህ እግዚአብሔር እንደሚወደው ከሆነ አገልግሎትህ የቀለለ ሊሆንልህ ይችላል።

2. ዲያቆን (1ኛ ጢሞ. 3፡8-13)

ዲያቆን ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ዲያኮኖስ» ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን፥ ትርጉሙም «አገልጋይ» ማለት ነው። የዲቁና ሥራ በመጀመሪያ የተጀመረው በሐዋሪያት ሥራ 6 ላይ እንደተገለጸው ሳይሆን አይቀርም። የመጀመሪያዎቹ ዲያቆናት የሐዋርያት ረዳቶች እንዲሆኑ ተሾሙ። በዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች/ሽማግሌዎች በቃሉ፥ በጸሎትና በመንፈሳዊ እንክብካቤ ላይ እንዲያተኩሩ ዲያቆናት ሌሎች ሥራዎችን ያቃልሉላቸዋል።

ምንም እንኳን ዲያቆናት የሽማግሌዎች ሥልጣን ባይሰጣቸውም፥ የተወሰኑ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። ብዙ ታማኝ ዲያቆናት ራሳቸውን ካስፈተኑ በኋላ ሽማግሌዎች ሆነዋል።

ሀ. ጭምት (1ኛ ጢሞ. 3፡8)፡- አንድ ዲያቆን ተቀባይነት (ተሰሚነት) ያለው መሆን አለበት። ማለትም ሌሎች እርሱን ለመምሰል የሚጥሩበት የክርስቲያን ባሕርይ ያለው መሆን አለበት። ዲያቆን ኃላፊነቱን በጥንቃቄ የሚወጣ፥ ሥራውን በሚገባ የሚሠራና ለታይታ ብቻ የማይቀመጥ መሆን አለበት።

ለ. በሁለት ቃል የማይናገር (1ኛ ጢሞ. 3፡8)፡- ከቤት ወደ ቤት እየዞረ ተረትን አያወራም፤ ሐሜተኛ አይደለም። ለአንድ ምእመን አንድ ነገር፥ ለሌላው ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ከመጀመሪያው የሚቃረን ነገር አይናገርም። በሚናገረው ነገር ልትተማመን ትችላለህ።

ሐ. ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጎመጅ (1ኛ ጢሞ. 3፡8)፡- ይህንን በቁጥር 3 ላይ ተነጋግረንበታል።

መ. ነውረኛ ረብ የማይወድ (1ኛ ጢሞ. 3፡8)፡- ዲያቆናት መባዎችን በመያዝ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለተቸገሩ ሰዎች ያከፋፍላሉ። ገንዘብን ለመስረቅ ወይም ለግል ጥቅም ለማዋል የሚያስጎመዠ ሊሆን ይችላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ የገንዘብ ኮሚቴዎች ለገንዘብ መንፈሳዊ አመለካከት ሊኖራቸው ይገባል።

ሠ. የሃይማኖትን ምሥጢር የሚይዝ (1ኛ ጢሞ. 3፡9)፡- «ምሥጢር» የሚለው ቃል «በአንድ ወቅት ተሰውሮ የነበረና አሁን ግን በእግዚአብሔር የተገለጠ እውነት» ማለት ነው። የእምነት ታላላቅ ትምህርቶች ከእምነት ውጪ ላሉት የተሰወሩ ናቸው። ጌታን በሚያምኑ ዘንድ ግን የተገለጡ ናቸው። ዲያቆናት የክርስትናን ትምህርቶች መረዳትና በመልካም ሕሊና መታዘዝ አለባቸው። ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ስብሰባ ማካሄድና ሥራውን በተቀላጠፈ መንገድ እንዴት ማራመድ እንደሚቻል መወሰን ብቻ በቂ አይደለም። ውሳኔያቸውን በእግዚአብሔር ቃል ላይ መመስረትና በመልካም አኗኗራቸው ማሳየት አለባቸው።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእግዚአብሔር ቃል የበለጠ፥ የቤተ ክርስቲያናቸውን መተዳደሪያ ደንቦች እንደሚያውቁ አስተውያለሁ። ሥነ-ሥርዓትን ለመጠበቅ ሕጎችና ደንቦች መኖራቸው አስፈላጊ ቢሆንም፥ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳዮች በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመመስረት መምራት ተገቢ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት የቀደምቷ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ነበሩ! መጽሐፍ ቅዱስን የማያውቅ ዲያቆን ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት እንቅፋት ነው።

ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ አንድ መጋቢ ጓደኛዬ ከሌላ ቤተ ክርስቲያን የተገነጠለና እርስበርሱ ሁልጊዜ የሚጣላ ቤተ ክርስቲያን ማገልገል ጀመረ። እርሱ ከነገረኝ እንደተረዳሁት የሥራ ስብሰባቸው ጉድ የሚባልለት ነበረ። የቤተ ክርስቲያኒቱ መተዳደሪያ ደንብ የመጽሐፍ ቅዱስን ያህል የሚከበር ነበር። ሰዎቹ «አረንጓዴው መጽሐፍ» ብለው ይጠሩታል። ጓደኛዬ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ጀመረ። መንፈስ ቅዱስም የሰዎችን ሕይወት መለወጥ ጀመረ፤ ነገር ግን ጠላት ሥራውን ጀመረና አንዳንዶቹን መሪዎች በስብሰባ ላይ መጋቢያቸውን እንዲቃወሙ አነሳሳ።

«አረንጓዴውን መጽሐፍ እየተከተልክ አይደለም!» አሉት

ጓደኛዬ መጽሐፍ ቅዱሱን ከፍ አድርጎ አነሳና «የእግዚአብሔርን ቃል እንከተላለን ወይስ በሰዎች የተጻፈውን አረንጓዴ መጽሐፍ?» ብሎ ጠየቀ። ይህ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ወሳኝ ነጥብ ነበረ። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር አስደናቂ በሆነ ዕድገትና ኃይል ባረካቸው።

የእግዚአብሔርን ቃል የማያውቅ ዲያቆን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ሊያስተዳድር አይችልም። በእግዚአብሔር ቃል የማይኖር፥ ነገር ግን «ያልጸዳ ሕሊና» ያለው ዲያቆን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ሊያስተዳድር አይችልም። አንድ የቤተ ክርስቲያን አባል ታዋቂ፥ በሥራው የተሳካለት፥ ወይም በልግስና የሚሰጥ ስለሆነ ብቻ በዲቁና ለማገልገል ብቁ አይደለም።

ረ. የተፈተነ (1ኛ ጢሞ. 3፡10)፡- ይህ ሕይወታቸውን በመመርመር ራሳቸውን እንዴት እንደሚገዙ መረዳትን ያሳያል። በብዙ አብያተ ክርስቲያናት አዲስ አባል ወይም አዲስ ክርስቲያን በጉብኝት፥ በመስተንግዶ፥ በሰንበት ትምህርት ቤት በመርዳትና በሌሎች ብዙ መንገዶች እግዚአብሔርን ማገልገል ሊጀምር ይችላል። በማቴ. 25፡21 ያለው መመሪያ ይህ ነው፡- «በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ»።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ጥቂት መሪዎች በመጀመሪያ እንደ ባሪያ የተፈተኑ እንደነበረ ማስተዋል ጠቃሚ ነው። ዮሴፍ በሀገሪቱ ላይ ሁለተኛ መሪ ከመሆኑ በፊት፥ በግብፅ ለአሥራ ሦስት ዓመታት ባሪያ ነበረ። ሙሴ እግዚአብሔር ሳይጠራው በፊት፥ ለአርባ ዓመታት በጎችን ይጠብቅ ነበር። ኢያሱ የሙሴ ምትክ ከመሆኑ በፊት፥ የሙሴ አገልጋይ ነበረ። ዳዊት ሳሙኤል ለንጉሥነት ሊቀባው ከመጥራቱ በፊት፥ የአባቱን በጎች ይጠብቅ ነበረ። ጌታችን ኢየሱስ እንኳን በባሪያ መልክ መጥቶ በአናጺነት ሠርቷል። ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ ድንኳን ሰፊ ነበረ። በመጀመሪያ አገልጋይ ከዚያ ገዢ።

ሁልጊዜ ያልተፈተነን አባል የቤተ ክርስቲያን መሪ ማድረግ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኒቱን ምስክርነት ያዳክማል። «ምናልባት ዓለማየሁን ዲያቆን ብናደርገው አዘውትሮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመምጣት ይገፋፋል።» የሚለው ዐረፍተ ነገር የዓለማየሁን የእግዚአብሔርን ቃል አለማወቅ የሚያሳይ ነው። ያልተፈተነ ክርስቲያን ያልተዘጋጀ ክርስቲያን ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመሪነትን ሥራ ብንሰጠው ከግንባታ ይልቅ ብዙ ጥፋት ሊያስከትል ይችላል።

ሰ. የራሳቸውን ቤቶች በመልካም ሁኔታ የሚያስተዳድሩ (1ኛ ጢሞ. 3፡11-12)፡- እግዚአብሔርን መምሰል በቤት ውስጥ መጀመር ስላለበት፥ የዲያቆን ሚስት የአገልግሎቱ አንድ ክፍል ናት። ዲያቆናት የፈቱና መልሰው ሌላ ያገቡ ሰዎች መሆን የለባቸውም። ሚስቶቻቸው ክርስቲያኖች ማለትም ስለ አገልግሎት ግድ የሚላቸው፥ «ለሐሜት» ያልተሰጡና (በቀጥታ «ዲያብሎስ ያልሆኑ» ለማለት ነው፤ ምክንያቱም ዲያብሎስ የሚለው ቃል «በሐሰት የሚከስ፥ ሐሜተኛ» ስለሆነ ነው።) በሚሠሩት ሁሉ የታመኑ መሆን አለባቸው። የሽማግሌዎች ወይም የዲያቆናት ሚስቶች ሌሎችን ሲያሙና ሲሳደቡ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ማየት የሚያሳዝን ነው።

አንዳንድ ተማሪዎች ቁጥር 11 የሚናገረው ስለ ሌላ የአገልጋዮች ቡድን ማለትም የሴት ዲያቆናት ነው እንጂ ስለ ዲያቆናት ሚስቶች አይደለም ይላሉ። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በሴቶች ሥራ፥ በጥምቀት፥ በኅብረት ጊዜያት ወዘተ. የሚያግዙ ሴት ዲያቆናት አሏቸው። ፌቤን በክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ነበረች (በሮሜ 16፡1 ቃሉ በግሪክ «ዲያኮኖን» ነው)። ምናልባት በአንዳንድ አብያተ ክርሲትያናት የዲያቆናት ሚስቶች እንደ ሴት ዲያቆናት ያገለግሉ ይሆናል። የአመራር ቦታ ያዙም አልያዙም እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሴቶች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚያገለግሉት አገልግሎት እግዚአብሔርን እናመሰግናለን! አገልግሎት ለመስጠት ወይም ስጦታን ለመለማመድ የመሪነት ቦታ መያዝ የግድ አስፈላጊ አይደለም።

ሸ. ለመሥራት ፈቃደኛ መሆን (1ኛ ጢሞ. 3፡13)፡- ቦታውን ለመሙላት ብቻ ሳይሆን በቦታው ለመሥራት መቻል አለበት። «ማዕረግ» ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል «ደረጃ (በጦር ሠራዊት እንዳለው)፥ መነሻ መሠረት፥ ደረጃ፥ የመወጣጫ መሠላል» እንደማለት ነው። ይህ ለታማኝ ዲያቆን እንዴት ያለ ማበረታቻ ነው! እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ነገር «ያሳድገዋል»። ደግሞም በቅዱሳን መካከል ሞገስን ይሰጠዋል። ይህም የበለጠ የአገልግሎት በር ይከፍትለታል ማለት ነው። ታማኝ ዲያቆን በእግዚአብሔርና በሰው ፊት መልካም አቋም አለው፤ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት እግዚአብሔር ይጠቀምበታል። ለውጤታማ አገልግሎት የሚሆን መንፈሳዊ ድፍረት አለው።

በርግጥ የዚህ በረከት አንዱ አካል የ «መንፈሳዊ ዕድገት» ን ዕድል ሊያካትት ይችላል። ለአንድ መጋቢ ዲያቆናት ሽማግሌዎች ሲሆኑና አንዳንዶች ሽማግሌዎች ደግሞ ሙሉ ጊዜያቸውን በመስጠት ወደ መጋቢነት አገልግሎት ሲጠሩ ማየት እንዴት ያለ ደስታ ነው። (በአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎች ከራሳቸው አጥቢያ ጉባኤዎች የሚጠሩ መሆናቸው መታወስ አለበት። ከሌሎች ቦታዎች የሚመጡ አልነበሩም)።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ከባድ ሥራ ነው። ከእኛ እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር ጸጋ ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ልቡን መመርመር አለበት።

3. ምዕመናን (1ኛ ጢሞ. 3፡14-16)

ሽማግሌዎች፥ ዲያቆናትና የቤተ ክርስቲያን አባላት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ምንነት እንዲረዱ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ አጭር አንቀጽ ጳውሎስ ሦስት መግለጫዎችን ሰጥቷል።

ሀ. የእግዚአብሔር ቤት (1ኛ ጢሞ. 3፡15)፡- የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ቤተሰባዊ ይዘት ስላላት፥ «የቤተሰብ» የሚለው የተሻለ ትርጉም ሊሆን ይችላል። ከጳውሎስ ተወዳጅ ቃላት መካከል አንዱ «ወንድሞች» የሚለው ነው (4፡6ን ተመልከት)። አንድ ኃጢአተኛ በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ሲያምን፥ ወዲያውኑ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ዳግመኛ ይወለዳል (ዮሐ. 1፡11-13፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡22-25)። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑን አባላት ልክ የራሱን ቤተሰቦች እንደሚያይ አድርጎ እንዲንከባከብ መክሮታል (1ኛ ጢሞ. 5፡1-2)።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ስለሆነ፥ መመገብ አለበት። ደግሞም ሕዝቡን የሚያፋፋ ተመጣጣኝ ምግብ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ለእኛ እንጀራ (ማቴ. 4፡4)፥ ወተትና ሥጋ (1ኛ ቆሮ. 3፡1-2፤ ዕብ. 5፡12-14) እና ማር (መዝ. (119)፡ 103) ነው። አንድ መጋቢ ሌሎችን ለመመገብ እንዲችል ጊዜ ወስዶ ለራሱ መመገብ አለበት (1ኛ ጢሞ. 4፡6)። ቤተ ክርስቲያን የምታድገው በጭማሪ ሳይሆን በተመጣጠነ ምግብ ነው (ኤፌሶን 4፡14-16)። አንዳንድ መጋቢዎች ሳምንቱን ሙሉ ጊዜያቸውን (የቤተ ክርስቲያናቸውንም ጊዜ) አባክነው በማጥፋት፥ በጌታ ቀን ለሕዝቡ የሚሰጡት አልሚ ምግብ የሚያጡበትን ሁኔታ መመልከት አሳዛኝ ነው።

እንደ ቤተሰብ ቤተ ክርስቲያን በፍቅር የሚሰጥ ቅጣት ያስፈልጋታል። ያልተቀጡ ልጆች ዓመፀኞችና ጨካኞች ይሆናሉ። የማኅበሩ መንፈሳዊ መሪዎች ቅጣትን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው (1ኛ ቆሮ. 4፡18-5፡13፥ 2ኛ ቆሮ. 2፡6-11)። አንዳንድ ጊዜ ልጆች ተግሳጽ ያስፈልጋቸዋል። ሌላ ጊዜ ቅጣቱ የበለጠ ጠጠር ያለ መሆን አለበት።

በተጨማሪም ልጆች መበረታታትና ምሳሌያዊነት ያስፈልጋቸዋል (1ኛ ተሰ. 2፡7-12)። መንፈሳዊ መሪዎች የአሳዳጊ እናት ርኅራኄ እና የአፍቃሪ አባት ጥንካሬ ያስፈልጋቸዋል።

ለ. ማኅበሩ (1ኛ ጢሞ. 3፡15)፡- ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በግሪክ ኤክሌሲያ ማለትም ጉባኤ ማለት ነው። ይህም በታዋቂ ዜጎች ንግድ በሚካሄድባቸው በግሪክ ከተሞች (የሐዋ. 19፡29፥ 32) የነበሩትን የፖለቲካ ድርጅቶች ያሳያል፤ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ የምእመናን ማኅበራት የሆኑትን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለማሳየት ወደ 100 ጊዜ ተጠቅሷል። የግሪኩ ቃል «ተጠርተው የወጡ» ማለት ነው። (በሐዋ. 7፡38 የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ መውጣት ለመግለጽ ተጠቅሷል፤ ነገር ግን እስራኤል በአዲስ ኪዳን አስተሳሰብ ቤተ ክርስቲያን አልነበረችም)።

ጳውሎስ ወጣቱ ጢሞቴዎስ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማኅበር ውስጥ እንዴት እንደ መሪ ሆኖ መኖር እንደሚገባው እንዲያውቅ ፈልጎ ነበረ። የመጋቢነት መልእክቶች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ለማስተዳደር መመሪያ የሚሰጡ መጻሕፍት ናቸው። በቅርብ ዓመታት ውስጥ አንድን ቤተ ክርስቲያን እንዴት መጀመር፥ መገንባትና፥ ማሳደግ፥ እንደሚቻል የሚናገሩ ብዙ መጻሕፍት ታትመዋል። አንዳንዶቹም ጥሩ ምክርን የያዙ ናቸው፤ ነገር ግን አንድን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለማስተዳደር ከሁሉም በላይ ጠቃሚ የሆኑ ምክሮች በእነዚህ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በተጻፉት ሦስት ደብዳቤዎች ውስጥ ይገኛሉ። አዲስ በተመሠረተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት የጀመረ ወጣት፥ እንዲሁም በአገልግሎት ብዙ ልምድ ያካበተ መጋቢ፥ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ ባካፈላቸው ትምህርቶች ራሱን ማስታጠቅ አለበት።

በርካታ የተለያዩ ዓይነት «ማኅበራት» አሉ። ቤተ ክርስቲያን ግን የሕያው እግዚአብሔር መኖሪያ ናት። የእግዚአብሔር መኖሪያ ስለሆነች፥ እንዴት መተዳደር እንዳለባት ሊነግረን መብት አለው። ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ልጅ ደም የተገዛች ናት (የሐዋ. 20፡28)፤

ስለዚህ እንዴት እንደምንኖር መጠንቀቅ አለብን። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የራሳቸውን የስግብግብነት ዓላማ ለማርካት፥ ሕዝቡን በተሳሳተ መንገድ የሚመሩ ሃይማኖተኛ ፈላጭ ቆራጮች መሆን የለባቸውም። (1ኛ ጴጥ. 5፡3-5 እና 3ኛ ዮሐ. 9-12)።

ሐ. የእውነት ዓምድና መሠረት (1ኛ ጢሞ. 3፡15-16)፡- ይህ የሕንፃ ፕላን ንድፍ ምስል ሲሆን፥ በኤፌሶን ለነበረው ጢሞቴዎስ ትልቅ መልእክት ነበረው። ምክንያቱም የዲያና ታላቁ ቤተ መቅደስ 127 ዓመዶች ነበሩት። መሠረት የሚለው ቃል መጠጊያ ወይም መደገፊያ የሚል አሳብ ይሰጣል። ቤተ ክርስቲያን እውነት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተገነባች ናት (ዮሐ. 14፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 3፡9-15)፤ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ራሷ የእውነት ዓምድና ተገን ናት።

አንድ ሐውልት ለሁሉም ሰው ሊታይ በሚችልበት ሁኔታ ከፍ ባለ መሠረት ላይ እንደሚቀመጥ ሁሉ፥ የቤተ ክርስቲያን የዓምድነት የአገልግሎት ገጽታም በመጀመሪያ ደረጃ የቃሉን እውነት በግልጽ ከማሳየት ጋር የተያያዘ ነው። ዓለም እንዲያየው «የሕይወትን ቃል ማቅረብ» አለብን (ፊሊ. 2፡16)። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስን በታማኝ አባላቷ የክርስትና ሕይወት ልምምዳቸው አማካይነት ታሳያለች።

ቤተ ክርስቲያን እንደ ምሽግ እውነትን በመጠበቅ እንዳይወድቅ ጥረት ታደርጋለች። (በየትም ቦታ «እውነት በአደባባይ ላይ ወድቋልና ቅንነትም ሊገባ አልቻለምና» [ኢሳ 59፡14]።) አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ከእውነት ዘወር ሲሉና (1ኛ ጢሞ. 4፡1-3) በአገልግሎታቸው ሲወላውሉ ጠላት እርምጃውን ያፈጥናል። አንዳንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኃጢአትና በክህደት አሠራር ላይ ወታደራዊ አቋም መውሰድ አለባቸው። ይህ በሰው ዘንድ የሚኖራቸውን ተቀባይነት ሊቀንስ ቢችልም፥ እግዚአብሔርን ግን ደስ ያሰኘዋል።

ቤተ ክርስቲያን ምስክር ሆና ልትቆምለት የሚገባት ዋናው እውነት የኢየሱስ ክርስቶስ ስብዕናና ሥራ ነው (ምናልባት (3፡16) የተጠቀሰው ከጥንት የክርስቲያን መዝሙር ሊሆን ይችላል)። ኢየሱስ ክርስቶስ በልደቱ ብቻ ሳይሆን፥ በምድራዊ አገልግሎቱ ጊዜ ሁሉ በሥጋ የተገለጸ አምላክ ነበር (ዮሐ. 14፡1-9)። የገዛ ሕዝቦቹ ባይቀበሉትም እንኳ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ የተመሠከረለትና የጸደቀ ነበረ፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ተአምራትን እንዲሠራና ራሱን እንኳን ከሞት

እንዲያስነሣ በኃይል አስታጥቆት ነበረ (ሮሜ 1:4)። የመንፈስ ቅዱስ በዓለም ላይ መኖር ራሱ ለዓለም ፍርድ ነው (ዮሐ. 16:7-11)።

ለመላእክት የታየ የሚለው የተመረጡት መላእክት ከኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት ጋር ብዙ ጊዜ መተባበራቸውን ያሳያል። ወደ መላእክት የተተረጎመው በግሪክ «አንጀሉስ» የሚለው ቃል «መልእክተኞች» ማለትም ነው (ያዕ. 2:25 ተመልከት)። ጳውሎስ ምናልባት የክርስቶስን ትንሣኤ ለመመስከር የተመረጡትን መልእክተኞች ይሆናል የሚጠቅሰው። ሆኖም ክርስቶስ ለጠፉ ኃጢአተኞች እንጂ፥ ለመላእክት አልሞተም፤ ስለዚህ ለአህዛብ ተሰብኳል። ይህም ጌታን ዓለም እንዲያምንበት እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ወንጌልን እንድናደርስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ተልእኮ ያስታውሰናል። በዕርገት ጊዜ በክብር አርጓል (የሐዋ. 1:2፥ 22)፤ ደግሞም አንድ ቀን ቤተ ክርስቲያኑን ያንን ክብር እንድትካፈል ሊወስዳት ይመለሳል።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንህ በአገርህና በዓለም ዙሪያ ኢየሱስ ክርስቶስን ለጠፉ ኃጢአተኞች እንድትመሰክር፥ ይህ እንዴት ያለ አስደናቂ ግበረታቻ ነው!

የእግዚአብሔር ሰው መሆን እንዴት እንደሚቻል

1ኛ ጢሞቴዎስ 4

ለመጋቢህ የሥራ ዝርዝር የምትጽፍ ቢሆን ኖሮ፥ ጽሑፉ የሚያካትተው ምን ይሆን? እርሱ ከሚጽፈው ዝርዝር ጋር እንዴት ሊወዳደር ይችል ይሆን? አንድ መጋቢ በየጊዜው ይሰብካል፤ የጋብቻ ሥነ ሥርዓቶችንና ሌሎች ክርስቲያናዊ አገልግሎቶችን ያከናውናል፤ የታመሙትን ይጠይቃል፤ እንዲሁም የተጨነቁትን ያማክራል። ነገር ግን የእርሱ አገልግሎት ምንድን ነው? እንዲሁም ከእግዚአብሔር የተሰጠውን አገልግሎት በሚገባ ለመፈጸም ምን ዓይነት ሰው መሆን ይገባዋል?

ጳውሎስ በዚህ የደብዳቤው ክፍል ውስጥ የአገልጋዩን ባሕርይና ሥራ አትኩሮት ሰጥቶበታል። አገልጋይ በተሳካ ሁኔታ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ሊኖሩት የሚገባ ሦስት ዓይነተኛ ባሕርዮችን ዘርዝሯል።

1. ቃሉን የሚሰብክ መልካም አገልጋይ (1ኛ ጢሞ. 4፡1-6)

ጳውሎስ የኤፌሶንን ሽማግሌዎች የሐሰት አስተማሪዎች ወደ ቤተ ክስርስቲያን እንደሚገቡ አስጠንቅቆአቸው ነበረ (ሐዋ. 20፡28-31)፤ እነሆ አሁን ደርሰዋል። ስለ እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች መንፈስ ቅዱስ በዝርዝር ተናግሮ ነበረ። ትንቢቱም በጳውሎስ ዘመን መፈጸም ጀምሮ ነበር። በእርግጥ በኛም ጊዜ ተፈጽሟል። የሐሰት አስተማሪዎችን ጳውሎስ በዚህ አንቀጽ ውስጥ ባወጣው መግለጫ መሠረት ልናውቃቸው እንችላለን።

ሀ. በሰይጣን ኃይል የሚሠሩ ናቸው (1ኛ ጢሞ. 4፡1)፡- በመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ አጋንንት የተጠቀሱበት ብቸኛ ቦታ ይህ ነው። ክርስቶስን በሚመለከት «እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢር» እንዳለ ሁሉ (1ኛ ጢሞ. 3፡16)፥ እንዲሁም ሰይጣንንና ሥራውን የከበበ «የዓመፅ ምስጢር» አለ (2ኛ ተሰሎ. 2፡7)። ሰይጣን ኮራጅ ነው (2ኛ ቆሮ. 11፡13-15)፤ የራሱ የሆኑ አገልጋዮችና ትምህርቶች አሉት፤ በዚህም ዓይነት የእግዚአብሔርን ሰዎች ለማሳትና ከመንገድ ለማስወጣት ይፈልጋል (2ኛ ቆሮ. 11፡3)። የማንኛውም

ሃይማኖታዊ ትምህርት የመጀመሪያ መመዘኛ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገረው ትምህርት ነው (1ኛ ዮሐ. 4፡1-6)።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የታወቁና የተመሰከረላቸውን ክርስቲያኖች ሰይጣን የራሱን ሥራ ለመፈጸም ሲጠቀምባቸው መመልከት ለአንዳንድ ሰዎች አስደንጋጭ ነው፤ ነገር ግን አንድ ጊዜ ሰይጣን ጴጥሮስን ኢየሱስን በተሳሳተ መንገድ ለመምራት እንዲሞክር ተጠቅሞበት ነበረ (ማቴ. 16፡21-33)፤ እንዲሁም ሐናንያንና ሰጲራን በኢየሩሳሌም የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ለማታለል ተጠቅሞባቸው ነበረ (የሐዋ. 5)። ጳውሎስ የሐሰት አስተማሪዎች ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚነሱ አስጠንቅቆ ነበረ (የሐዋ. 20፡30)።

ለ. ሰዎችን ያስታሉ (1ኛ ጢሞ. 4፡1)፡- ግባቸው ሰዎች ከእምነት እንዲለዩ ማግባባት ነው። ይህ «ክህደት» የሚባል ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙም «በፈቃደኝነት ከክርስትና እምነት እውነታ መራቅ ነው»። እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት ወይም ሰዎች ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋራ ጥልቅ በሆነ ሁኔታ እንዲገናኙ ለማድረግ አይሞክሩም። በዚህ ፈንታ የሚከተሉዋቸው ደቀ መዛሙርት ለማግኘትና በቡድናቸው ውስጥ ተጨምረው ፕሮግራሞቻቸውን እንዲያስፋፉ ይፈልጋሉ። ይህ በእውነተኛ ቤተ ክርስቲያንና የሃይማኖት መልክ በያዘ የሐሰት ትምህርት መካከል የሚገኝ አንዱ ልዩነት ነው፡- እውነተኛዪቱ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ለመማረክና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለማነጽ ትፈልጋለች። በተቃራኒው የሐሰት አስተማሪዎች የሌላ ሃይማኖት አባላትን በማፍለስና በመስረቅ፥ የሐሰት ትምህርቱ መሪዎች አገልጋዮች (እንዲያውም ባሪያዎች) ያደርጓቸዋል። ሆኖም ክህደቶች ሁሉ የሚመጡት ከሐሰት አስተማሪዎች ብቻ አይደለም። አንዳንዶች የሐሰት ትምህርት የሚያስተምሩትና ሰዎችን ወደ ጥፋት የሚመሩት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኘው መድረክ ላይ ቆመው ነው።

ሐ. ግብዞች ናቸው (1ኛ ጢሞ. 4፡2)፡- «ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ» (ማቴ. 7፡15-20)። እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች አንድ ነገር ይሰብካሉ፤ ሌላ ነገር ይለማመዳሉ። ለደቀ መዛሙርቶቻቸው የሚያደርጉዋቸውን ነገሮች ይነግሩዋቸዋል፤ እነርሱ ግን አያደርጉትም። ሰይጣን «በግብዝነት ሐሰትን በሚናገሩ ውሸተኞች» (1ኛ ጢሞ. 4፡2) ይሠራል። የእግዚአብሔር እውነተኛ አገልጋይ ሁለቱ ምልክቶች ታማኝነቱና ግብረ-ገባዊ ምስጉንነቱ

ናቸው። የሰበከውን የሚኖር ነው። ይህ ማለት እርሱ ያለ ኃጢአት የሚኖር ፍጹም ነው ማለት ሳይሆን፥ ነገር ግን በእውነት የእግዚአብሔርን ቃል ለመታዘዝ ይፈልጋል ማለት ነው። እርሱ መልካም ሕሊና እንዲኖረው ይሞክራል (1፡5፥ 19 እና 3፡9 ተመልከት)።

«ደንዝዘው» የሚለው ቃል «መተኮስ» ማለት ነው። የአንድ ሰው ሥጋ በጋለ ብረት «ተተኩሶ» ጠንካራና ስሜት-አልባ እንደሚሆን ሁሉ፥ እንዲሁ የሰው ሕሊናም ሊደነዘዝ ይችላል። በኑሮአችን የምንከደውን ነገር (ሰዎች ቢያውቁትም ባያውቁትም) በአፋችን ብቻ በተናገርን ቁጥር ሕሊናችንን ትንሽ በትንሽ እያደነዘዝን እንሄዳለን። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በዕለት ኑሮአችን ማድረግ እንጂ፥ ሃይማኖታዊ ንግግር ወይም ተአምራትን መሥራት እንኳ ሰውን ለመንግስተ ሰማይ ብቁ እንደማያደርገው በግልጽ ተናግሯል (ማቴ. 7፡21-29)።

ከሃዲ የሆነ ሰው በሚያሰራጨው ትምህርት ብቻ ሳይሆን፥ በግብረገባዊ ሕይወቱም ቢሆን የተሳሳተ ነው። የሚከተለው ትምህርት ከመለወጡ በፊት፥ የግል ሕይወቱ የተበላሸ ይሆናል። እንዲያውም ትምህርቱን የለወጠው የኃጢአት ኑሮውን ለመቀጠልና ሕሊናውን ለማረጋጋት ሳይሆን አይቀርም። ማመንና ባመኑበት መኖር ሁልጊዜ አብረው የሚሄዱ ነገሮች ናቸው።

መ. የእግዚአብሔርን ቃል ይክዳሉ (1ኛ ጢሞ. 4፡3-5)፡- በኤፌሶን የሚገኙ የሐሰት አስተማሪዎች የአይሁድን ሕጋዊነት ከምሥራቃውያን የምንኩስና ሃይማኖታዊ ባህል ጋር ያዋህዱ ነበር። ስለዚሁ የሐሰት ትምህርት፥ ጳውሎስ ለቆላስይስ በጻፈው ደብዳቤው ላይ ሲናገር እንመለከታለን (በተለይ 2፡8-23)። አንዱ ነገር ሳያገቡ መኖር አግብቶ ከመኖር የተሻለ መንፈሳዊነት አለው ብለው የሚያስተምሩት ነበረ። ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተቃራኒ ነው። የእግዚአብሔር የራሱ ቃል እንዲህ ይላል፡- «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም» (ዘፍ. 2፡18)። ሁሉም ሰው እንደማያገባ ቢያመለክትም (19፡10-12) ኢየሱስ የጋብቻን አግባብነት በመደገፍ የራሱን ማኅተም አሳርፎበታል (ማቴ. 19፡1-9)። ጳውሎስም በዚህ ጉዳይ ላይ እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ መከተል እንዳለበት በማስተማር፥ ስለ ጋብቻ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መሠረት አጠናክሯል (1ኛ ቆሮ. 7፡1-24)።

በእግዚአብሔር የጋብቻ መሠረት ውስጥ ጣልቃ ከሚገባ ከማንኛውም ሃይማኖታዊ ትምህርት መጠንቀቅ አለብን። በእግዚአብሔር ፍጥረትም ውስጥ ጣልቃ ከሚገባ ትምህርት መጠንቀቅ አለብን። የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ሊመርዙ የነበሩት የሐሰት አስተማሪዎች አንዳንድ ምግቦች ርኩስ ስለሆኑ ከተመገባችኋቸው መንፈሳዊ አይደላችሁም ብለው ያስተምሩ ነበረ። እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ «መልካም» ነው የማለቱ እውነታ (ዘፍጥረት 1፡10፥ 12፥ 18፥ 21፥ 25) እነዚህን ሰዎች አላስደሰታቸውም ነበር። የአመጋገብ ሥርዓት የመቆጣጠር ሥልጣናቸው በለወጧቸው ሰዎች ላይ ኃይል ሰጣቸው።

«የሚያምኑና እውነትን የተረዱ» ሰዎች በሕግ-አጥባቂዎቹ የአድርግና አታድርግ ዝርዝሮች አይማረኩም። ጌታ ኢየሱስ ምግቦች ሁሉ ንጹሓን እንደሆኑ ተናግሯል (ማርቆስ 7፡14-23)። ይህንን ትምህርት እንደገና ለጴጥሮስ ከማስተማሩም በላይ (ሐዋ. 10)፥ በጳውሎስ በኩል እንደገና አረጋግጧል (1ኛ ቆሮ. 10፡23-33)። አንድ ሰው በጤንነቱ ምክንያት (ለምሳሌ ለሰውነቱ ባለመስማማቱ አንዳንድ ምግቦችን ላይመገብ ይችላል)፥ ነገር ግን መንፈሳዊ ሕይወትን ላለማርከስ ተብሎ የሚተው የምግብ ዓይነት አይኖርም። ይሁንና ለመብልና ለመጠጥ ያለንን ነጻነት ደካማ ክርስቲያኖችን ለማጥፋት መጠቀም የለብንም (ሮሜ 14፡13-23)። የምንበላው ምግብ በምንጸልይበትና ምስጋና በምናቀርብበት ጊዜ የተቀደሰ (የተለየ፥ ለእግዚአብሔር የተሰጠ) ነው፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃልና ጸሎት የተለመደውን ምግብ እንኳን ወደ መንፈሳዊ አገልግሎት ይለውጡታል። ይህም ለእግዚአብሔር ክብር እንዲውል ነው (1ኛ ቆሮ. 10፡31)።

አገልጋይ በሕይወቱ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ላይ ማተኮር አለበት (1ኛ ጢሞ. 4፡5)። ቤተ ክርስቲያን መጋቢዎችዋን በቤት ውስጥ ሥራዎች ስታዋክባቸውና ለእግዚአብሔር ቃልና ለጸሎት ጊዜ ሲያጡ መመልከት አሳዛኝ ነው (የሐዋ. 6፡1-7)። ጳውሎስ ወጣቱን ጢሞቴዎስ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን የማጥናት፥ የማስተማርና የመስበክ እንዲሁም ጊዜውን በጸሎት የማሳለፍ ትልቅ ኃላፊነት እንዳለበት አሳስቦታል። እንደ «መልካም አገልጋይ የእምነት ቃል የሚመገብ» መሆን አለበት (1ኛ ጢሞ. 4፡6)። ጢሞቴዎስ ይህን እየተስፋፋና እያደገ የመጣውን የክህደት ትምህርት በተመለከተ የተወሰኑ ኃላፊነቶች ነበሩት፡-

ሠ. ለቤተ ክርስቲያን እውነትን አስተምር (1ኛ ጢሞ. 4፡6)፡-
የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ ሐሰተኛ ትምህርትና ሃይማኖታዊ ኑፋቄ ማስጠንቀቂያ ያስፈልጋቸዋል። አንድ አገልጋይ «የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ» (የሐዋ. 20፡27) የማስተማር ግዴታ ስላለበት፥ በሐሰት ትምህርቶች ላይ ጊዜውን ማጥፋት የለበትም። ያም ሆኖ ግን በፍጹም ቸል ሊላቸው አይገባም። አንድ መጋቢ ሕዝቡ የሚያምኑትንና ወዴት እንደሚሄዱ እንዲያውቁ መልካም የሆነ ትምህርት ማስተማር አለበት። እንዲሁም ሕዝቡ እንዳይታለሉና ወደ ጥፋት እንዳይሄዱ ሐሰተኛ ትምህርትን ማጋለጥ አለበት።

ረ. ራሱን በእግዚአብሔር ቃል መመገብ አለበት (1ኛ ጢሞ. 4፡6)፡-
እርግጥ ነው ሁሉም ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ቃል በየዕለቱ መመገብ አለበት (ማቴ. 4፡4፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡2፤ ኤር. 15፡16)፤ ነገር ግን መጋቢው በእግዚአብሔር ቃል ማደጉ በተለየ ሁኔታ አስፈላጊ ነው። በጌታ ሊያድግና ቤተ ክርስቲያንን ሊመራ የሚችለው፥ በየዕለቱ መልካሙን ትምህርት በማጥናትና ቃሉን በማሰላሰል ነው።

«መልካሙ አገልጋይ» በየዕለቱ ለራሱ የሚመገበውን ቃል ይሰብካል፤ ነገር ግን ቃሉን መስበክ ብቻ በቂ አይደለም፤ በተግባርም ሊለማመደው ይገባል።

2. በቃሉ የሚኖር እግዚአብሔርን የሚመስል አገልጋይ (1ኛ ጢሞ. 4፡7-12)

ጳውሎስ በዚህ የደብዳቤው ክፍል ሩጫን በምሳሌነት ወደ መጠቀም ይተላለፋል። ልክ የግሪክ ወይም የሮማ ሯጭ የተወሰኑ ነገሮችን እምቢ ማለት፥ ትክክለኛውን ምግብ መመገብና ትክክለኛ ልምምዶችን ማድረግ እንዳለበት፥ እንዲሁ ክርስቲያንም መንፈሳዊ ልምምድ ማድረግ አለበት። አንድ ክርስቲያን አንድ ሯጭ ለጨዋታው የሚያውለውን ያህል ኃይልና ሥነ- ሥርዓትን ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ከተጠቀመ፥ ለራሱ ፈጣን ዕድገት ከማሳየቱም በላይ፥ ለጌታም ብዙ ሥራዎችን ይፈጽማል። ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ ሦስት የሕይወት ደረጃዎችን አብራርቷል፡-

ሀ. መጥፎው ደረጃ - «ለዚህ ዓለም ከሚመችና ከአሮጊቶች ተረት ራቅ » (1ኛ ጢሞ. 4፡7)፡- በእርግጥ እነዚህ የመናፍቃኑ የሐሰት ትምህርቶችና ልማዶች ናቸው። እነዚህ ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንም መሠረት የላቸውም። እንዲያውም የእግዚአብሔርን ቃል ይቃረናሉ። መጽሐፍ ቅዱስን በትጋት

የሚያጠኑ ሰዎች ሳይሆኑ፥ ሞኞች ሰዎች የሚነጋገሩባቸው ዓይነት ትምህርቶች ናቸው። እነዚህ ነገሮች በስም የተጠቀሱትን የሐሰት ትምህርቶች እንደሚጨምሩ ጥርጥር የለውም (4፡2-3)። ጳውሎስ ቲቶንም እንዲሁ ስለ «አይሁድ ተረቶች» አስጠንቅቆታል (ቲቶ 1፡14)። ጳውሎስ ስለነዚሁ «ተረቶች» በሁለተኛ መልእክቱ ጢሞቴዎስን አስጠንቅቆታል (2ኛ ጢሞ. 4፡4)።

አንድ አማኝ አዲስ ትምህርቶችን እንደገና ማግኘት አይችልም። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን «በተከተለው መልካም ትምህርት ቃል» (4፡6) በእውነተኛነት ጸንቶ እንዲኖር ያስጠነቅቀዋል። «ወደ ተረትና መጨረሻ ወደሌለው ወደ ትውልዶች ቆጠራ» እንዳይመለስ ያስጠነቅቀዋል (1፡4)። መጋቢው ጠላት ምን እንደሚያስተምር ማወቅ ቢኖርበትም፥ ዳሩ ግን በትምህርቱ መወሰድ የለበትም። አንድ ቀማሚ መርዞችን ሊይዝና ሊያጠና ቢችልም፥ ወደ አካሉ እንዲገቡ አይፈቅድላቸውም።

ለ. ጊዜያዊው ደረጃ «የሰውነት እንቅስቃሴ» (1ኛ ጢሞ. 4፡7-8)፡- በድጋሚ ይህም የሯጭ መግለጫ ነው። በትክክል ለሰውነታችን እንክብካቤ ማድረግ አለብን፤ እንቅስቃሴ የዚህ እንክብካቤ አካል ነው። ሰውነታችን ለክብሩ ሊውል የሚገባ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው (1ኛ ቆሮ. 6፡19-20)፤ እንዲሁም ለእርሱ አገልግሎት የሚውል የእርሱ መሣሪያ ነው (ሮሜ 12፡1-2)፤ ነገር ግን የሰውነት እንቅስቃሴ የሚጠቅመው ለዚህ ሕይወት ብቻ ነው። እግዚአብሔርን የመምሰል ልምምድ ግን ለአሁኑም ለዘለዓለማዊውም መንግሥት የሚተርፍ ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ከሁለቱ መካከል አንዱን እንዲመርጥ አልጠየቀውም፤ እግዚአብሔር ሁለቱንም እንድንለማመድ የሚጠብቅብን ይመስለኛል። ጤነኛ ሰውነት የእግዚአብሔር መጠቀሚያ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በቅድስና ላይ ማተኮር አለብን።

ሐ. ዘለዓለማዊው ደረጃ «እግዚአብሔርን መምሰል» (1ኛ ጢሞ. 4፡7-8)፡- ፊሊፕስ ብሩክስ የተባሉ ሰው እንዲህ አሉ፡- «የሕይወት ታላቁ ዓላማ የባሕርይ በእውነት መቀረፅ ነው»። ምንም እንኳ አንድ ሰው ሁለቱንም ሊያገኝ ቢችልም፥ እግዚአብሔርን የመምሰል ባሕርይ ከድል መታሰቢያ ዋንጫዎች ወይም የውድድር ነጥቦችን ከመመዝገብ የበለጠ ጠቀሜታ ያለው ነው። ጳውሎስ ጤሞቴዎስን አንድ ሯጭ ለስፖርቱ የሚያደርገውን ጥረት ያህል እግዚአብሔርን

ለመምሰል ራሱን እንዲሰጥ ይጠይቀዋል። የምንኖረውና የምንደክመው ለዘለዓለሙ መንግሥት ነው።

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ፥ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ለመኖር በሚያስፈልጉ ሥርዓቶች ላይ በማተኮር፥ ሁለት ተመሳሳይ የሩጫ መግለጫዎችን ተጠቅሟል (1ኛ ቆሮ. 9፡24-27)። አንድ ሯጭ ሰውነቱን መቆጣጠርና ሕግጋቱን መታዘዝ እንዳለበት ሁሉ፥ ክርስቲያንም ሰውነቱን ባሪያው እንጂ ጌታው ማድረግ የለበትም። በሞቃቱ የበጋ ፀሐይ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የእግር ኳስና የእጅ ኳስ ተጫዋቾች የሰውነት ማጠንከሪያ ሲሠሩ በማይበት ጊዜ እኔም ላከናውናቸው የሚገቡኝ መንፈሳዊ ልምምዶች እንዳሉ አስታውሳለሁ (ዕብ. 5፡14)። ጸሎት፥ ጥሞና፥ ራስን መመርመር፥ ጎብረት፥ አገልግሎት፥ መስዋዕት፥ ለሌሎች ፈቃድ መገዛት፥ ምስክርነት - እነዚህ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የበለጠ እግዚአብሔርን እንድመስል ሊረዱኝ ይችላሉ።

መንፈሳዊ ልምምድ ቀላል አይደለም፤ «መድከምና መሰደብ» (1ኛ ጢሞ. 4፡10) አለብን። በአዲሱ ትርጉም «የምንታገለውና በሥራ የምንደክመው ለዚሁ ነው» ይላል። «መታገል» የሚለው ቃል ስለ ሩጫ የተጠቀሰ ነው። ይህም አንድ ሯጭ ሲታገልና ለማሸነፍ የሚያስችለውን ጥረት ሁሉ ሲያደርግ የሚያሳየን ነው። ተሸሎ ለመገኘት የሚፈልግ ክርስቲያን በእውነት በእግዚአብሔር ጸጋና ለእግዚአብሔር ክብር ይህንን ማድረግ አለበት።

ነገር ግን ራሳችንን እግዚአብሔርን እየመሰሉ መኖርን ማለማመድ ጥቅሙ ለራሳችን ብቻ ሳይሆን፥ ለሌሎችም ጭምር ነው (4፡11-12)። ለሌሎች መልካም ምሳሌዎች እንድንሆን ስለሚያስችለን፥ ሌሎችን እናበረታታለን። ጳውሎስ እኔና እናንተ ምሳሌ ልንሆንባቸው የሚገቡንን በርካታ የሕይወት አቅጣጫዎችን ዘርዝሯል።

«በቃል» (4፡12) የሚለው የሚያሳየን ንግግራችን ሁልጊዜ በቅንነትና በፍቅር መሆን እንዳለበት ነው። «እውነትን በፍቅር እንናገር» (ኤፌ. 4፡15)።

«በኑሮ» ይህ ቃል የሚያሳስበን ኑሮአችን በእግዚአብሔር ቃል ቁጥጥር ሥር መሆን እንዳለበት ነው። ጳውሎስ ለቲቶ እንደገለጸለት ዓይነት ግብዞች ሰዎች መሆን የለብንም (ቲቶ 1፡16)፦ «እግዚአብሔርን እናውቃለን ይላሉ፤ በሥራቸው ግን ይክዱታል»።

«በፍቅር» - የሚያመለክተን ሕይወታችን ስለሚነሳሳበት ጉዳይ ነው። እግዚአብሔርን ሰዎች እንዲያዩን ብለን አንታዘዝም (ማቴ. 6፡1-2)፤ ነገር ግን እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ሰዎች ስለምንወድ ነው።

«በእምነት» የሚለው በእግዚአብሔር እንደምንታመንና ለእርሱ ታማኞች እንደሆንን ያመለክታል። እምነትና ፍቅር ብዙ ጊዜ ጎን ለጎን ይሄዳሉ (1ኛ ጢሞ. 1፡14፤ 2፡15፤ 6፡11፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡13፤ 2፡22)። እምነት ሁልጊዜ ወደ ታማኝነት ይመራል።

«በንጽሕና» በዚህ የከፋ ዓለም ውስጥ ስንኖር ሳለ፥ በንጽሕና መመላለስ አስፈላጊ ነው። ኤፌሶን ልቅ የግብረ ሥጋ ርኩሰት የሚካሄድባት ስፍራ ስለነበረች፥ ወጣቱ ጢሞቴዎስ ከፈተና ጋራ ፊት ለፊት ተፋጦ ነበረ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙ ሴቶች ጋራ ንጹሕ የሆነ ግንኙነት ሊኖረውና (1ኛ ጢሞ. 5፡2) አእምሮውን፥ ልቡን ሥጋውን በንጽሕና መጠበቅ ነበረበት።

ነገር ግን እግዚአብሔርን እየመሰሉ መኖር የሚረዳው እኛንና ሌሎች አማኞችን ብቻ አይደለም፤ በጠፉት ላይም ተጽዕኖ አለው። ጳውሎስ መጋቢ ጢሞቴዎስን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ እንደሆነ (4፡10) እና የምስራቹን ቃል ለጠፉት ማካፈል የአማኞች ኃላፊነት እንደሆነ አሳስቦታል። በመቀጠልም እንዲህ ሲል ጽፏል፡- «እኛ ክርስቲያኖች ተስፋችንን በሕያው እግዚአብሔር ላይ አድርገናል፤ ነገር ግን የጠፉት ተስፋ የላቸውም። ደግሞም ሕያው እግዚአብሔርን አያውቁም። አብዛኛዎቹ የሚያውቁዋቸው ነገሮች በሙሉ በፍጹም ሊያድኗቸው የማይችሉት ሙት ጣዖቶች ናቸው»

«የሁሉም ሰው አዳኝ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሁሉም ሰው አይድንም ለማለት ነው፥ ወይም እግዚአብሔር ለማዳን ከፈለገ እነርሱ ፈቃደኛ ባይሆኑም እንኳ በሕይወታቸው የደኅንነት ሥራ መፈጸሙ አይቀርም ለማለት አይደለም። ምክንያቱም ጳውሎስ ይሽንን የተናገረው «በተለይ ላመኑት ሰዎች ነው» ሲል ተናግሮዋል። የአንድን ሰው ነፍስ የሚያድነው እምነት ነው (ኤፌ. 2፡8-10)። እግዚአብሔር «ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ስለሚወድ» (1ኛ ጢሞ. 2፡4) እንዲሁም ክርስቶስ «ራሱን ቤዛ አድርጎ ለሁሉም ሰው ስለ ሰጠ» (2፡6)፥ ማንኛውም የጠፋ ኃጢአተኛ በክርስቶስ ሊታመንና ሊድን ይችላል። ክርስቶስ «የሁሉ ሰው አዳኝ» ነው፤ ስለዚህ ማንም ተስፋ ሊቆርጥ አይገባውም።

«ይህ አባባል የታምነና ሰው ሁሉ ሊቀበለው የሚገባ» (4፡9) ስለሆነ፥ ጢሞቴዎስ የእግዚአብሔርን ቃል ለመለማመድና በቤተ ክርስቲያንም ሕይወት ውስጥ በተግባር ለማዋል መፍራት የለበትም። እነዚህ የታመኑ አባባሎች ለመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የእውነት ማጠቃለያ አበጅተዋል። (1፡15፤ 3፡1፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡11፤ ቲቶ 3፡8 ተመልከት)። ጢሞቴዎስ ወጣት የመሆኑ እውነታ (በዚያን ጊዜ ወጣት የሚለው ቃል እስከ 40 ዓመት ለሚደርስ ሰው ያገለግል ነበር) ቃሉን ከመለማመድ ሊያግደው አይገባም። በእርግጥ እነዚህን ነገሮች «ማዘዝ» ነበረበት፤ ይህ ደግሞ ወታደራዊ «ግዳጅ»ን የሚያመለክት ቃል ነው (1ኛ ጢሞ. 1፡3)። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር መንፈሳዊ ሠራዊት ውስጥ እንደ አንድ ክፍለ ጦር ነች፤ መሪዎችዋም በሥልጣንና በጽኑ እምነት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለሕዝቡ ማስተላለፍ አለባቸው።

3. በቃሉ የሚያድግ አገልጋይ (1ኛ ጢሞ. 4፡13-16)

በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው ዋና አሳብ «ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ» (4፡15) የሚለው ነው። መሻሻል (ማደግ) የሚለው ቃል የግሪክ ወታደራዊ ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙም «ቀድሞ ወደፊት መግፋት» ማለት ነው። በመሆኑም ከጦሩ ቀድመው በመሄድ፥ መሰናክሎችን የሚያስወግዱትንና ሌሎች እንዲከተሉዋቸው አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩትን ወታደሮች ያመለክታል። እግዚአብሔርን እንደሚመስል መጋቢ፥ ጢሞቴዎስ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ማደግ ነበረበት። ስለዚህም በዚህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑ በሙሉ የእርሱን ዕድገት በመመልከት ሊመስሉት ይችሉ ነበር።

ማንም መጋቢ እርሱ ራሱ ወዳልደረሰበት ስፍራ ሕዝቡን ሊመራ አይችልም። የሕይወትና የአገልግሎት መሠረታዊ መመሪያ «ይህን ያለኝን እሰጥሃልሁ» የሚለው ነው (ሐዋ. 3፡6)። የማያድገው መጋቢ (የቤተ ክርስቲያን አባል) እንደ እውነቱ ከሆነ ወደ ኋላ እየተመለሰ ነው፤ ምክንያቱም በክርስትና ሕይወት በአንድ ቦታ ረግቶ መቆም አይቻልም። በኑሮው፥ በትምህርቱ፥ እናም በምሪቱ አገልጋዩ የመንፈሳዊ ዕድገቱን ማስረጃ ማሳየት አለበት። ነገር ግን ለመንፈሳዊ ዕድገት እገዛ የሚያደርጉ ነገሮች ምንድናቸው?

ሀ. ለእግዚአብሔር ቃል ትኩረት መስጠት (1ኛ ጢሞ. 4፡13)፡- «ትኩረት ስጥ» ማለት «ራስህን ስጥ፥ ተመሰጥ» ማለት ነው። ቃሉን ማገልገል ጢሞቴዎስ ሌሎችን ነገሮች ከፈጸመ በኋላ የሚያደርገው

አልነበረም፤ ዳሩ ግን እርሱ ከሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ዋንኛው መሆን ነበረበት። ማንበብ ማለት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሕዝብ በተሰበሰበበት ስፍራ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ ነው። የአይሁድ ሕዝብ ሁልጊዜ የሕግና የነቢያትን መጻሕፍት በምኩራቦቻቸው የማንበብ ልማድ ነበራቸው፤ ይህም ልምምድ ወደ ክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት ተላለፈ። ኢየሱስ በናዝሬት ቅዱሳት መጻሕፍትን በምኩራብ አንብቦ ነበር (ሉቃስ 4፡16-20)፤ እንዲሁም ጳውሎስ ምኩራቦችን በሚጎበኝበት ጊዜ ባመዛኙ የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርቶችን ያነብ ነበር (የሐዋ. 13፡15)።

ከቦታ ቦታ እየተዘዋወርሁ ሳገለግል ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሕዝብ በተሰበሰበበት ስፍራ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ መተዋቸውን ተመልክቼ አዝኛለሁ። «ለልዩ ሙዚቃ» እና መጨረሻ ለሌላቸው ማስታወቂያዎች ጊዜ ሲኖራቸው ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ጊዜ የላቸውም። መጋቢው ከመስበኩ በፊት አንድ ክፍል ያነብ ይሆናል፥ ነገር ግን ያ የተለየ ነገር ነው። እያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ሕዝብ በሚሳተፍባቸው ፕሮግራሞች የማንበቢያ ጊዜ ማዘጋጀት አለበት። የእግዚአብሔርን ቃል በጉባኤ እንድናነብ በመጽሐፍ ቅዱስ የታዘዘ ነው። (ቃሉን ሕዝብ በተሰበሰበበት የሚያነቡት ሰዎች ደጋግሞ ለማንበብ በግል መዘጋጀት እንዳለባቸው ማሳሰብ ሳያስፈልገኝ አይቀርም። ማንም ሰው ሳይዘጋጅ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነብ መጠየቅ የለበትም። እኛ ልንሰጥ ከምንችለው ነገሮች እጅግ የተሻለውን ለመጽሐፍ ቅዱስ ልናበረክት ይገባል)

«ለመምከር» (1ኛ ጢሞ. 4፡13) ይህ የሚያሳስበን የእግዚአብሔርን ቃል ከሰዎች ህይወት ጋር ማዛመድን ነው። መጋቢው ቃሉን ማንበብ፥ ማስረዳትና ከሕይወቱ ጋር ማዛመድ ነበረበት። «ማስተማር» የሚለው ቃል በመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል። በእነዚህ አሥራ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ ቢያንስ በሃያ ሁለት ቦታዎች «ማስተማር» ወይም «ትምህርት» የሚለው ቃል ተጠቅሷል።

«ለማስተማር መብቃት» ለአንድ አገልጋይ ከሚያስፈልጉ መሥፈርቶች አንዱ ነው። (1ኛ ጢሞ. 3፡2)፤ እንዲሁም «ለማስተማር መብቃት ለመማር መዘጋጀትን ያመለክታል» የሚለው እውነተኛ አባባል ነው። የሚያድግ አገልጋይ ወይም አንድ የቤተ ክርስቲያን አባል የቃሉ ተማሪ መሆን አለበት። ሌሎችን ከማስተማሩ በፊት፥ ራሱን ማስተማር

አለበት (ሮሜ 2፡21)። የእርሱ መንፈሳዊ ዕድገት ለመንጋው ምሳሌ ከመሆኑም በላይ ለሌሎች ማበረታቻ ነው።

ለ. መንፈሳዊ ስጦታህን ተጠቀም (1ኛ ጢሞ. 4፡14)፡- በቅርብ ዓመታት ውስጥ፥ የጸጋ ስጦታዎችን ልንረሳ እንደተቃረብን በማስመልከት፥ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ብዙ ተጽፏል (ገላትያ 5፡22-23)። ስጦታ የሚለው ቃል «ካሪዝማ» ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን፥ ትርጉሙም «ከእግዚአብሔር የተሰጠ የጸጋ ስጦታ» ማለት ነው። (ዓለም ይህን ካሪዝማ የሚለውን ቃል የሚስብ ስብዕናና እንዲሁም ባለ ግርማ ገፅታ ያለውን ሰው ለመግለጽ ትጠቀምበታለች)። እያንዳንዱ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አለው (ሮሜ 8፡9)፤ ይህም ክርስቲያን ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ቢያንስ አንድ ስጦታ አለው (1ኛ ቆሮ. 12፡1-11)። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታና ከመንፈስ ቅዱስ የሆኑ ስጦታዎች ሁሉ በመለወጥ ጊዜ ከእግዚአብሔር የሚሰጡ ናቸው (1ኛ ቆሮ. 12፡13-14 ተመልከት)።

ሆኖም እግዚአብሔር አንድን አማኝ ለተለየ የአገልግሎት ቦታ ሲጠራው፥ ለዚያ ሥራ የሚሆነውን መንፈሳዊ ስጦታ ሊሰጠው ይችላል። ጢሞቴዎስ በሽማግሌዎች ሲሾም፥ እጃቸውን በጫኑበት ጊዜ ለአገልግሎት የሚያበቃውን ስጦታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀብሎ ነበር፤ ነገር ግን በሆነ ምክንያት ጢሞቴዎስ ለመንፈሳዊ ዕድገቱና ለአገልግሎቱ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ይህን ስጦታ ወደ ጎን ገፋ አድርጎት ነበረ። በእርግጥ ጳውሎስ በሁለተኛው መልእክቱ ሲመክረው ነበረ፡- «እጆቼን በመጫኔ በአንተ ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሳሳው አሳስብሃለሁ» (2ኛ ጢሞ. 1፡6)።

የሚጠራን እግዚአብሔር፥ ሥራውን ለማከናወን እንደሚያዘጋጀን ማወቅ የሚያበረታታ ነው። እርሱን ለማገልገል የሚያስችለን ከራሳችን የሆነ ምንም ነገር የለንም። አገልግሎት በሙሉ ከእግዚአብሔር መምጣት አለበት (1ኛ ቆሮ. 15፡9-10፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡12፤ ፊሊጵ. 4፡13)። ሆኖም ዝም ብለን መቀመጥ የለብንም፤ የእግዚአብሔርን ስጦታዎች ልናዳብር፥ ልንጠቀምባቸው፥ እናም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና በአስቀመጠን ቦታ ሁሉ ልናሳድጋቸው ይገባል፡-

ሐ. ራስህን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ ስጥ (1ኛ ጢሞ. 4፡15)፡- «አሰላስል» የሚለው ቃል «በእነርሱ ውስጥ ሁን፥ ራስህን ሙሉ ለሙሉ ለእነርሱ ስጥ» የሚለውን አሳብ ይዟል። የጢሞቴዎስ

መንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት በሕይወቱ ውስጥ ማራኪና ወሳኝ ነገሮች እንጂ፥ አንዳንድ ጊዜ ብቻ የሚለማመዳቸው ተጓዳኝ ተግባራት አልነበሩም። ለሥራው ሙሉ ለሙሉ ራሱን እስካልሰጠ ድረስ፥ አንድ ሰው በአገልግሎቱ የሚገባውን ያህል ሊራመድ አይችልም። «ለሁለት ጌቶች መገዛት አይቻልም» (ማቴ. 6፡24)።

የሚነቅፉትን ሰዎች ለመምሰል ባልሻም፥ በርካታ መጋቢዎችና ክርስቲያን ሠራተኞች ጊዜያቸውንና ፍላጎታቸውን ለቤተ ክርስቲያንና ለተጓዳኝ የገንዘብ ማግኛ ሥራዎች ማካፈላቸው እንዳሳሰበኝ ለመግለጽ እፈልጋለሁ። ከመጋቢነት አገልግሎት ጋር በንግድ ጉዳይ፥ ፖለቲካ ነክ የሆነ ሥራ በመሥራትና በተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች በመሥራት እንኳ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን ሙሉ ለሙሉ ለመጋቢነት አገልግሎት ባለመስጠታቸው፥ የራሳቸውን መንፈሳዊ ሕይወትና ቤተ ክርስቲያናቸውን ይጎዳሉ። የጳውሎስን ስሜት የሚቆጣጠረው «ነገር ግን ይህን አንድ ነገር አደርጋለሁ» የሚለው ቃል ነበረ። ይህ የኛም ተግባር ሊሆን ይገባል (ፊሊ. 3፡13)። «ሁለት አሳብ ያለውና በመንገዱም የሚያወላውል ምንም አያገኝም» (ያዕቆብ 1፡8)።

መ. መንፈሳዊ ጉዞህን መርምር (1ኛ ጢሞ. 4፡16)፡- የራስህን ልብ በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን መርምር። ጳውሎስ «ራስህን» የሚለውን ከ «ትምህርት» እንዳስቀደመ አስተውል። ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች በመሰናበቻ መልእክቱ እንደዚህ ዓይነት ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ነበር፡- «ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» (ሐዋ. 20፡28)። አንድ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሌሎችን በመርዳት ባተሌ ይሆንና ራሱንና መንፈሳዊ ሕይወቱን ቸል ሊል ይችላል።

በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአሜሪካ ታላቅ ወንጌላዊ የነበሩት ቻርለስ ፊኔይ በዚህ ክፍል ላይ ይሰብኩ ነበረ። የስብከታቸውንም ርዕስ «ሰባኪ ሆይ፥ ራስህን አድን» ብለው ሰየሙት። ያ ስብከት ዛሬም ያስፈልገናል። ምክንያቱም ብዙ ሰዎች ሕይወታቸው ከሙያቸው ጋራ አብሮ ስላልሄደ፥ አገልግሎታቸውን ሲተዉ እየተመለከትን ነው። ሥነ-ምግባራዊ ችግሮች የጋብቻ መፍረስና ሌሎች አሳፋሪ ጠባዮች ብዙ የእግዚአብሔር አገልጋዮችን አጥፍትዋል። «ስለዚህ የቆመ የሚመስለው ሰው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» (1ኛ ቆሮ. 10፡12)።

የዳኑትን መገንባትና የጠፉትን መፈለግ ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆኑ የአገልግሎታችን ዓላማዎች ናቸው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በኛ በኩል አልፎ በሚገባ ከመሥራቱ በፊት፥ በውስጣችን መሥራት አለበት

(ፊሊ. 2፡12-13)። እንደ መልካም አገልጋይ፥ ቃሉን እንሰብካለን፤ እግዚአብሔርን እንደሚመስል አገልጋይ በቃሉ እንኖራለን፤ እንደሚያድጉ አገልጋዮች በቃሉ እናድጋለን።

የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት

1ኛ ጢሞ. 5

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የተጋፈጠችው የመጀመሪያ ችግር የዘመናዊቷም ቤተ ክርስቲያን ችግር ነበር። ከቤተ ክርስቲያን አባላት የተወሰኑ ቡድኖች በአገልጋዮች ተዘንግተው ነበረ (የሐዋ. 6)። አንድ ጊዜ ስለ አንድ መጋቢ እንደዚህ ሲባል ሰማሁ። «በሳምንት ውስጥ የቤተ ክርስቲያን አባላት መጋቢ የት እንዳለ አያስቡም፥ በእሑድ ቀን ግን ምእመናን ሁሉ ችግራቸውን ይዘው ይመጣሉ።» እንዲሁ ይህ መጋቢ ከሚያስተዳድረው ማኅበረ ምእመናን መካከል አንዱ ደግሞ ችላ እንደተባለ ይሰማዋው ነበር።

ከዚያም ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተወሰኑ ቡድኖችን እንዴት እንደሚያገለግል መመሪያ ሰጠው።

1. አረጋውያን አባላት (1ኛ ጢሞ. 5፡1-2)

ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ዓይነት ሰዎችን እንዲያገለግልና ልዩነት እንዳያሳይ መከረው (1ኛ ጢሞ. 5፡21)። ጢሞቴዎስ ወጣት ስለነበረ፥ አረጋውያን የሆኑትን አባሎች በመዘንጋት ሊፈተን ስለሚችል፥ ዕድሜን ሳይመለከት ሁሉንም ሰው እንዲወድድና እንዲያገለግል ጳውሎስ በብርቱ ይመክረዋል። ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ናት፤ ስለዚህ አረጋውያን የሆኑትን አባላት ልክ እንደ እናትና አባትህ፥ እንዲሁም ወጣት አባላትን እንደ ወንድሞችህና እህቶችህ አስተናግድ በማለት ያሳስበዋል።

2. ያረጁ መበለቶች (1ኛ ጢሞ. 5፡3-10)

ቤተ ክርስቲያን ከአገልግሎቷ መጀመሪያ ጀምሮ ለሚያምኑ መበለቶች ይገዳት ነበር (የሐዋ. 6፡1፤ 9፡39)። በእርግጥ የእስራኤል ሕዝብ ለመበለቶች እንክብካቤ ማድረግ ፈቃዳቸው ነበረ። እንዲሁም እነርሱን ስለ መንከባከብ እግዚአብሔር ልዩ ሕግ ሰጥቷቸዋል (ዘዳግም 10፡18፤ 24፡17፤ ኢሳ. 1፡17)። እግዚአብሔር ለመበለቶች የሚያደርገው እንክብካቤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተደጋጋሚ ርዕስ ነው (ዘዳግም 14፡29፤ መዝ. 94፡6፤ ሚል. 3፡5)። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለእነዚህ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች ርኅራኄ ማሳየቷ ትክክል ነው።

ሆኖም ቤተ ክርስቲያን ያላትን ሀብት በትክክል እርዳታ ለማያስፈልጋቸው ሰዎች በመስጠት እንዳታባክን መጠንቀቅ አለባት። ብንቀበለውም ባንቀበለውም፥ ለመሥራት ፈቃደኞች ሳይሆኑ፥ ወይም ያላቸውን ሀብት በጥበብ ሳይጠቀሙ ቤተ ክርስቲያንን የሚመጠሙ ግለሰቦችና ቤተሰቦች አሉ። ከቤተ ክርስቲያን ዕርዳታ እስካገኙ ድረስ፥ ለምን ብለው ወደ ሥራ ይሄዳሉ?

ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን መረዳት ያለባት መበለት ምን ዓይነት መሆን እንዳለባት መመዘኛዎች ዘርዝሯል።

ሀ. ረዳት የሌላት (1ኛ ጢሞ. 5፡5) «ብቻዋን የምትኖር»፡- አንዲት መበለት ዘመዶች ካሉዋት ቤተ ዘመዶችዋ ሊከባከቧት ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያንም ገንዘብዋን ምንም ረዳት የሌላቸው ሌሎች እንዲረዱበት ለማዋል ትችላለች። የራሷ ልጆች የሞቱባት እንደሆነ፥ የልጅ ልጆችዋ ኃላፊነቱን ሊወስዱ ይገባል። የዚያን ዘመን የሕብረተሰብ ሥርዓት ሁኔታን በምታስቡበት ጊዜ፥ እኛ አሁን እንዳሉን ዓይነት ተቋሞች አልነበሩም - የጡረታ አበል፥ ማህበራዊ ዋስትና፥ የማገገሚያ ቤቶች ወዘተ. አልነበሩም። የቤተሰብ እንክብካቤ ምን ያህል አስፈላጊ እንደነበረ ማየት ይችላል። በእርግጥ በአሁኑ ጊዜ የእንደነዚህ ዓይነት ድርጅቶች መኖር አንድን ቤተሰብ ከፍቅር ግዴታው ውጪ አያደርገውም። «አባትህንና እናትህን አክብር» የሚለው ቃል አሁንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ (ዘጸ. 20፡12፤ ኤፌሶን 6፡1-3)።

ምናልባት አንድ ሰው ወዳጁን ለመርዳት ፈቃደኛ ላይሆን ይችላል። ጳውሎስ የዚህ ዓይነቱን ሰው «ከማያምን ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው» ይለዋል (1ኛ ጢሞ. 5፡8 እንዲሁም ቁ. 16 ተመልከት)። አሁን ከጌታ ጋር ያለች የወንጌል አገልጋይ ጓደኛዬ የታመሙና ያረጁ ወላጆችዋን ለመርዳት ከመስክ ወደ ቤት ተመለሰች። ከዚህም የተነሣ ጓደኞችዋ አጥብቀው ተቃወሟት። እርሷ ግን እስከ መጨረሻው በታማኝነቷ ጸናች። ከዚያም እግዚአብሔርን እንደታዘዘች በመረዳት፥ ለፍሬያማ የአገልግሎት ዓመታት ወደ መስክ ተመለሰች። ለነገሩ እግዚአብሔርን የምንወደው የእርሱን ሰዎች በመውደድ ነው፤ እናም እርሱ ደግሞ በዕድሜ ለገፉት፥ ለባልቴቶችና አባትና እናት ለሌላቸው የተለየ ትኩረት አለው።

ለ. የታመነ ምስክርነት ያላት አማኝ (1ኛ ጢሞ. 5፡5)፡- ቤተ ክርስቲያን በከተማ ውስጥ ለሚገኙ መበለቶች ሁሉ እንክብካቤ ለማድረግ

አትችልም፤ ነገር ግን የጎብረቱ አባል ለሆኑት አማኞች መጠንቀቅ አለባት። «ለሰዎች ሁሉ ይልቁንም ለሚያምኑ ሰዎች መልካም ነገርን እናድርግ» (ገላ. 6፡10)። ቤተ ክርስቲያን የምትረዳት ሴት የራሷን ምኞት የምታሳድድ፥ ምኞት ፈላጊ ሳትሆን፥ እግዚአብሔርን የምትመስል፥ እግዚአብሔርን ተስፋ የምታደርግና የምልጃና የጸሎት አገልግሎት የምትሰጥ መሆን አለባት። እግዚአብሔርን የምትመስል ባልቴት ምሳሌ ከሉቃስ 2፡36-37 ተመልከት።

ባገለገልሁባቸው በሦስት የተለያዩ የመጋቢነት አገልግሎቶች እግዚአብሔርን የሚመስሉ ባልቴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ «የመንፈሳዊ ኃይል ጎተራዎች» እንደሆኑ ተለማምጃለሁኝ። የጸሎት ስብሰባዎች የጀርባ አጥንት ናቸው። ለጉብኝት ራሳቸውን ይሰጣሉ፤ በሰንበት ትምህርት ቤትም የአስተማሪዎችን ቁጥር ከፍ ያደርጋሉ። እንዲሁም ደግሞ መበለት እግዚአብሔርን የማትመስል ከሆነች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ችግር ልትፈጥር እንደምትችል አይቻለሁ። ትኩረት እንዲደርግላት ትፈልጋለች፤ ወጣቶች በሚያደርጉት ነገር ታማርራለች፤ እንዲሁም ብዙ ጊዜ «ስልክ ላይ ተጣብቃ» የሐሜት ዶፍ ታወርዳለች። እንደ እርስዋ አስተሳሰብ ይህ «ሐሜት» አይባልም። ወዳጆችዋ በነዚህ ጉዳዮች ላይ «በሚገባ ለመጸለይ እንዲችሉ» በሚል ሰበብ ብቻ ነው የምትሻው። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን የምትረዳቸው መበለቶች «ነቀፋ የሌለባቸው» እንከን የማይወጣላቸው እንዲሆኑ ግልጽ አድርጓል (1ኛ ጢሞ. 5፡7)።

ሐ. ቢያንስ ስልሳ ዓመት የሆናት (1ኛ ጢሞ. 5፡9)፡- ምንም እንኳ ዛሬ ስልሳ ዓመት እስከዚህም «አሮጊት» ባያሰኝም፥ በዚያን ጊዜ ይህን ያህል ዕድሜ ያላት ሴት የግባት ዕድል አልነበራትም። ምናልባት «በመዝገብ ብትጻፍ» የሚለው ግሥ ፍንጭ ይሰጠን ይሆናል። ይህም በቀጥታ ትርጉም «መመዝገብ፥ በዝርዝር ውስጥ ማካተት» ማለት ነው። ቃሉ ወታደሮችን ለመመዝገብ የሚጠቀሙበት ነበረ። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መመዘኛ ያሟሉ ባልቴቶች ሕጋዊ የሰም ዝርዝር ነበራት። እናም እነዚህ የተመዘገቡ ሴቶች ማኅበረ ምእመናኑን በተለያዩ መንገዶች እንደሚያገለግሉ ልንገነዘብ እንችላለን። (ዶርቃንና ሌሎች ባልቴት ጓደኞችዋን አስታውስ የሐዋ. 9፡36-43)። ጳውሎስ ምናልባት እነዚህ በግልጽ ለድቁና ተሹመው ቢሆን ኖሮ ይነግረን ነበር።

መ. መልካም የጋብቻ ታሪክ ያላት (1ኛ ጢሞ. 5፡9)፡- ይህንኑ ተመሳሳይ መመዘኛ ቀደም ብሎ ለጳጳሳትና (3፡2) ለዲያቆናት (3፡12) በተገለጸው ውስጥ ተመልክተናል። ይህ የሚያመለክተው፥ ባልቴቷ ፈት የሆነች ሴት እንዳልሆነች ነው። ወጣት መበለቶች እንደገና እንዲያገቡ ስለተመከሩ (5፡14)፥ እንዲህ ዓይነቱ ገለጻ ባሏ ከሞተ በኋላ ሁለተኛ ጋብቻ የፈጸመችውን ሴት ሊያመለክት አይችልም። ለጋብቻ የገቡትን ቃል ኪዳን በታማኝነት መጠበቅ በእግዚአብሔር ዓይን ፈት በጣም አስፈላጊ ነው።

ሠ. በመልካም ሥራ የተመሰከረላት (1ኛ ጢሞ. 5፡10)፡- አንድ ሰው እግዚአብሔርን በታማኝነት የሚያገለግል ከሆነ፥ ብርሃኑ ያበራል፥ ሌሎችም አይተው እግዚአብሔርን ያከብራሉ (ማቴ. 5፡16)። «ልጆችን በሚገባ ማሳደግ» የሚለው የሚያመለክተው የመበለቲቱን ልጆች ወይም እናትና አባት የሌላቸውን መጠለያ ፈላጊ ልጆች ይሆናል። የራሷን ልጆች የሚመለከት ከሆነ፥ ልጆችዋ ሞተው ይሆናል ማለት ነው። አለዚያ ቤተ ክርስቲያን ልትረዳት አትችልም። ይህ ጥቅስ የሚያመለክተን የተጣሉትን ልጆች በመታደግና ጌታን በሚያውቁበት መንገድ የማሳደጉን ተግባር ሳይሆን አይቀርም።

እንግዳ ተቀባይነት ሌላው አስፈላጊ ነጥብ ነው፥ ከቦታ ወደ ቦታ መጓዝ አደገኛ በሆነበትና በሰላም ለመተኛት የሚቻልባቸው ስፍራዎች እጥረት በነበረበት በዚያን ጊዜ ይህ አገልግሎት በጣም አስፈላጊ ነበረ። እግር ማጠብ የሚያመለክተው የተለየ ሥርዓትን አይደለም፤ ነገር ግን አንድ እንግዳ በሚመጣበት ጊዜ እቤት ሲደርስ የሚደረግ የተለመደውን ልምምድ ነው (ሉቃስ 7፡44)። ራሱን ዝቅ የሚያደርገውን አገልጋይ ተግባር መወጣት የዚህችን ሴትዮ ክብር አይቀንሰውም።

«የተቸገሩትን መርዳት» ለችግርተኛ ሰው የሚደረጉትን በርካታ አገልግሎቶች ሊያጠቃልል ይችላል፤ የተራቡትን ማብላት፥ የታመሙትን መንከባከብ፥ ያዘኑትን ማጽናናት፥ ወዘተ...። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ ቁሳዊና ሥጋዊ ጉድለቶች የበኩላቸውን እገዛ ለሚያደርጉ እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ሴቶች ሁሉም መጋቢ ምስጋናውን ያቀርባል። እነዚህ መበለቶች ቤተ ክርስቲያን ስትንከባከባቸው ነበር፤ ነገር ግን እነርሱም በበኩላቸው ለቤተ ክርስቲያን እንክብካቤ በማድረግ ይረዱ ነበር።

3. ወጣት መበለቶች (1ኛ ጢሞ. 5፡11-16)

ከክፍሉ እንደምንረዳው ወጣት መበለቶች ማለት ከስልሳ ዓመት በታች የሆኑትን ማለት ነው። ነገር ግን ጳውሎስ ከዚያ በብዙ ዓመታት የሚያንሱ ወጣት ሴቶችን እያሰበ መሆኑ አያጠራጥርም። የአምሳ ዘጠኝ ዓመት አሮጊት ሴት እንደገና ብታገባ «ልጆች ትወልዳለች» ማለት አይቻልም (5፡14)። በጉዞ ላይ የሚያጋጥሙ አደጋዎች፥ የበሽታ ጠንቅ፥ ጦርነት፥ እንዲሁም ሌሎች በርካታ ነገሮች ከአንዲት ወጣት ሚስት ባሏን ሊነጥቁባት ይችላሉ። ነገር ግን ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ወጣት መበለቶችን በቤተ ክርስቲያን እንክብካቤ ዝርዝር ውስጥ እንዳያደርግ ይከለክለዋል።

ሀ. እነርሱን ያልተቀበለባቸው ምክንያቶች (1ኛ ጢሞ. 5፡11-14)፡-
በዕድሜያቸው ምክንያት ወጣት ሴቶች ባመዛኙ በወንዶች ስለሚሳቡ፥ እንደገና ለማግባት ይፈልጋሉ። ይህ ታዲያ ምን ክፋት አለበት? ጳውሎስ (5፡12) በመዝገብ ውስጥ የተጻፈች መበለት፥ መበለት ሆና በመቆየት ጌታን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል ቃል እንደገባች ለማመልከት የሚፈልግ ይመስላል። ቃል መግባቱ «የሴተ ላጤነት ስለት» ተደርጎ መተርጎም የለበትም፤ ወይም እነዚህን አገልጋይ መበለቶች «የተለዩ የመነኩሳት ቡድን» እንደሆኑ አድርገን ማየት የለብንም። በመበለቶቹ እና በቤተ ክርስቲያን መሐከል መበለት ሆነው እንደሚቆዩ ስምምነት ሳይደረግ አይቀርም።

ሌላም ሊሆን የሚችል አተረጓጎም አለ፡- እነዚህ ወጣት መበለቶች በቤተ ክርስቲያን የተረዱ እንደሆነ፥ በዕርዳታው በመሞላቀቅ ሌሎችን በተለይም የማያምኑትን ሰዎች የማግባት ዕድል ይኖራቸው ነበር። የማያምኑ ሰዎች በማግባት የመጀመሪያ እምነታቸውን ይተዋሉ። ሆኖም እኔ የመጀመሪያውን ገለጻ እመርጣለሁ።

ጳውሎስ ወጣት መበለቶች በቤተ ክርስቲያን እንክብካቤ የሚደረግላቸው ከሆነ፥ ጊዜ ይተርፋቸውና በኃጢአት እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊዎች እንደሚሆኑ ግልጽ አድርጎታል (5፡13)። ለሥራ ጠቃሚ በመሆን ፈንታ፥ ሥራ ፈት የመሆን ባህርይ ይኖራቸዋል። በየሰዉ ቤት እየዞሩና በሰው ነገር እየገቡ የሚያሙ ይሆናሉ። በሥራ ፈትነትና በኃጢአት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት አለ።

ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የቤተ ክርስቲያንን የእርዳታ አገልግሎት ሰዎች ሥራ ፈት እንዲሆኑ ለማድረግ እንዳይጠቀምበት

አስጠንቅቆታል። ቤተ ክርስቲያን እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን በእርግጥ መርዳት አለባት፤ ነገር ግን ኃጢአትን ለሚያበረታታ ነገር መስጠት የለባትም። መጋቢ እንደመሆኔ መጠን፥ በእንደነዚህ ዓይነት ጉዳዮች ላይ መወሰን ነበረብኝ፤ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ቀላል አይደለም።

ለ. ከወጣት መበለቶች የሚፈለጉ መመዘኛዎች (1ኛ ጢሞ. 5፡14-16)፡-

ከአሉታዊው አነጋገር በመለስ፥ ጳውሎስ ወጣት መበለቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀባይነትና ድጋፍ ለማግኘት ማድረግ የሚገቧቸውን አዎንታዊ ነገሮች ይዘረዝራል። ወጣት መበለቶች እንዲያገቡና ቤተሰብ እንዲኖራቸው ይፈልጋል። ሁሉም ሰው ያገባል ተብሎ ባይገመትም፥ ጋብቻ ከዚህ ቀደም ላገቡት ለብዙዎቹ ሰዎች የተለመደ ነገር ነው። ባል የማግባትና ቤተሰብ የመመሥረት ዕድሉ ካለ በመበለትነት ለብቻ መቀመጥ ምን ይፈይዳል? እርግጥ ነው ይህ ሁሉ «በጌታ ውስጥ» ሊሆን ይገባል (1ኛ ቆሮ. 7፡39)።

ለመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን እግዚአብሔር የሰጠው ትእዛዝ፥ «ብዙ ተባዙ» የሚል ነበር (ዘፍጥረት 1፡28)፤ ስለዚህ የጋብቻ ውጤቱ ቤተሰብ ነው። ዛሬ ከ «ጊዜው ከፋት» የተነሣ ልጆች እንዲኖራቸው የማይፈልጉ ሰዎች፥ በጳውሎስ ዘመን ደግሞ ይብስ አስቸጋሪ እንደነበረ ማረጋገጥ አለባቸው! ክርስቲያኖች ልጆች የማይወልዱና ለእግዚአብሔር እንዲኖሩ የማያሳድጉ ከሆነ፥ ይህንን ተግባር የሚያከናውነው ማን ሊሆን ነው?

«ቤታቸውን የሚያስተዳድሩ» (1ኛ ጢሞ. 5፡14)፡- ሚስት የቤት ውስጥ ጉዳዮችን ማስተዳደር አለባት፥ እንዲሁም ባልዋ ይህንን እንድታደርግ ሊተማመንባት ይገባል። (ምሳሌ 31፡10-31) በርግጥ ጋብቻ የጓደኝነት ሕይወት ነው፤ ነገር ግን እያንዳንዱ የተለየ ኃላፊነት አለበት። ጥቂት ወንዶች ሴቶች በቤት ውስጥ የሚሠሩትን መሥራት ይችላሉ። ባለቤቴ በታመመች ጊዜ ሁሉ፥ ወይም ለሕፃናት ልጆቻችን እንክብካቤ በምታደርግበት ወቅት፥ እኔም በበኩሌ አንዳንድ የቤት ውስጥ ጉዳዮች መፈጸም ነበረብኝ። ዳሩ ግን ኃላፊነቴን ለመወጣት እንዳልቻልሁ ወዲያውኑ ተረድቻለሁ።

የዚህ ሁሉ ውጤት ከሳሾችን ዝም የሚያሰኝ መልካም ምስክርነት ነው። ሰይጣን (ከሳሻችን) የክርስቲያንን ቤት የሚያጠቃበትንና የሚያፈርስበትን ዕድል ለማግኘት ሁልጊዜ ነቅቶ ይጠብቃል። «ሁኔታ» የሚለው ቃል «የእንቅስቃሴዎች መሠረት» የሚል ትርጉም ያለው ወታደራዊ ቃል ነው። በቤት ሥራዋን የማትሠራ ክርስቲያን ሚስት

ለሰይጣን ሥራዎች ምሽግ ትቆፍራለች፤ የዚህም፥ ውጤት አሳዛኝ ነው። ክርስቲያን ሚስትና እናት ከቤት ውጪ መሥራት የሚኖርባት ጊዜያት ቢኖሩም፥ ተገቢው አሠራር ግን በቤት ውስጥ ማገልገሏ ነው። ምኞት ለማግኘት ብቻ የምትሠራው ሚስት አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮች እንዳጣች ከጊዜ በኋላ ትረዳለች። ገንዘብ ሊገዛው የማይችለውን እስካላጣህ ድረስ ገንዘብ ሊገዛው የሚችለውን ማግኘት ጥሩ ነው።

ክርስቲያን ሚስቶችና እናቶች ቤታቸውን የሚያስተዳድሩበት ሁኔታ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ላሉ ሰዎች ምስክርነት ሊሆን ይችላል። መጋቢው በውጭ ባሉት ዘንድ መልካም ስም ማግኘት እንዳለበት (3፡7)፥ እንዲሁም አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ስም ማሰደብ እንደሌለባቸው (6፡1)፥ ሚስቶችም መልካም ምስክርነት ሊኖራቸው ይገባል። ሴቶች የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች መሆን አይችሉም ይሆናል፤ ነገር ግን ጌታን በገዛ ቤታቸው ሊያገለግሉ ይችላሉ። (ለዚህ ከፍተኛ አገልግሎት ተጨማሪ አሳብ ለማግኘት (ቲቶ 2፡4-5 ተመልከት)።

ከዚያ በኋላ ጳውሎስ እያዳንዱን የቤተሰብ አባል፥ ለአባላቱ ፍላጎት እንዴት እንከብካቤ እንደሚያደርግ መመሪያ ይሰጣል (1ኛ ጢሞ. 5፡16)። ጳውሎስ እነዚህ መበለቶች እንዴት ከችግራቸው ነጻ እንደሚወጡ አልነገራቸውም፥ ቋሚ የሆነ ገንዘብ፥ ወደ ቤት መውሰድ፥ ሥራ መስጠት፥ ወዘተ.። እያንዳንዱ አጥቢያ ጉባኤ እንደየግለሰቦቹ ችግር መወሰን ይኖረበታል።

ይህ መመሪያ ለአሁኑ ጊዜ ክርስቲያኖች እንዴት ይጠቅማል? ወላጆቻችንንና አያቶቻችንን ማክበርና ችግር ካለባቸውም መርዳት አለብን። ሁሉም ክርስቲያናዊ ቤተሰብ ተጨማሪ ሰው የማስተዳደር አቅም ያለው አይሆንም፤ እንዲሁም ሁሉም መበለቶች ከልጆቻቸው ጋር ለመኖር የሚፈልጉ አይደሉም። በሽታ ወይም አካለ ስንኩልነት ካለ የሙያ እርዳታ አስፈላጊ ነው፤ ይህም ምናልባት በቤት ውስጥ ሊሰጥ አይችልም ይሆናል። እያንዳንዱ ቤተሰብ በዚህ ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ መወሰን አለበት። የውሳኔ ቀላል የለውም። ዋናው ነገር አማኞች ፍቅርንና ለሌላው የማሰብ ዝንባሌ በማሳየት፥ በሚችሉት ነገር ሁሉ እርስ በርሳቸው መረዳዳት አለባቸው።

4. የቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች (1ኛ ጢሞ. 5፡17-25)

በዚህ ቦታ ያለው መመሪያ የሚያተኩረው በሽማግሌዎች ላይ ነው፤ ነገር ግን መመሪያዎቹ መጋቢው በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ካለው

ከማንኛውም ኃላፊ ጋራ ለሚያደርገው ግንኙነትም ይጠቅማሉ። ሽማግሌዎችና ዲያቆናት እንዲሁም (ሌሎች ኃላፊዎች) በመስማማትና በፍቅር ሲሠሩ ማየት በጣም የሚያስደስት ነገር ነው። አንድ መጋቢ መንፈሳዊ አምባገነን ለመሆን ሲሞክር (1ኛ ጴጥሮስ 5፡3)፥ ወይም አንድ ኃላፊ ቁንጮ ለመሆን ሲጣጣር ማየት አሳዛኝ ነው (3ኛ ዮሐ. 9-10)።

በግልጽ እንደተቀመጠው፥ ጢሞቴዎስ ከኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋራ አንዳንድ ችግሮች ነበሩት። ወጣትም ነበርና ገና ብዙ መማር ነበረበት። ኤፌሶንም ለማገልገል ቀላል ቦታ አልነበረችም። በተጨማሪም ጢሞቴዎስ ጳውሎስን የቤተ ክርስቲያኗ የበላይ ተቆጣጣሪ አድርጎ ይከተለው ነበር። ጳውሎስ ደግሞ ለሚከተለው ሰው ቀላል አልነበረም። ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ያደረገው የመሰነባበቻ ንግግር (ሐዋ. 20)፥ ምን ያህል በትጋት እንደሠራ፥ ምን ያህል ታማኝ እንደነበረና እንዲሁም ምን ያህል ሽማግሌዎቹ ይወዱት እንደነበረ ያሳያል (20፡36-38)። ጳውሎስ በግሉ ጢሞቴዎስን ወደ ኤፌሶን ቢልከውም፥ ወጣቱ ጢሞቴዎስ ከባድ ችግር ነበረበት።

ጳውሎስ ስለ ወይን ጠጅ መመሪያ የሰጠው ምናልባት በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም (1ኛ ጢሞ. 5፡23)። ጢሞቴዎስ የሆድ ሕመም ነበረበትን? የታመመው ከበርካታ ኃላፊነቶች ችግሮች የተነሣ ይሆን? ወይስ የሚመገበው ምግብ ጤናውን ከማሻል ይልቅ እያባሰበት መሆኑን እስከተረዳበት ጊዜ ድረስ፥ በምግብ ራስን መጨቆን እንደሚገባ የሚያስተምሩትን ሰዎች አሳብ (4፡1-5) ለመከተል በመሞከሩ ይሆን? የነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች መልስ አናውቅም። ይሁንና የጢሞቴዎስን ታሪክ ስናጠና ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት እንችላለን። ጳውሎስ በዚህ ቦታ ስለ ወይን የጠቀሰው የአልኮል ኢንዱስትሪዎችን በማበረታታት እንዳልሆነ መረዳት ጠቃሚ ነው። ወይን ጠጅን ለመድኃኒትነት መጠቀም ሕብረተሰቡ በመጠጥ ላይ እንዲያተኩር ማበረታታት አይደለም። እንደተመለከትነው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ጠቅላላ መለየትን ባይጠይቅም፥ ጠጪነትን (ስካርን) ይከለክላል።

ጢሞቴዎስ ከሽማግሌዎች ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት በተመለከተ፥ ጳውሎስ ሦስት አሳቦችን በማቅረብ ይመክረዋል፡-

ሀ. ለሽማግሌዎቹ መክፈል (1ኛ ጢሞ. 5፡17-18)፡- በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንድ መጋቢ ፈንታ ብዙ ሽማግሌዎች ሕዝቡን ያገለግሉ ነበር። እነዚህ ሰዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ለጌታ ሥራ

ስለሚሠዉ፥ አንድ ዓይነት ክፍያ ይገባቸዋል። ዛሬ በብዙ ማኅበረ ምእመናን፥ ሽማግሌዎቹ ሌላ ሥራ ያላቸውና ነገር ግን ቤተ ክርስቲያንን በሥራ የሚረዱ ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ጊዜ ሙሉ ጊዜውን የሚሰጠው የመጋቢዎች ቡድን ብቻ ነው። በእርግጥ ጸሐፊዎች፥ ንብረት ጠባቂዎች፥ ወዘተ. አሉ። ነገር ግን ጳውሎስ የሚጽፈው ስለ እነርሱ አልነበረም።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለት ዓይነት ሽማግሌዎች ነበሩ፡- የማኅበሩን ሥራ የሚቆጣጠሩ አስተዳዳሪ ሽማግሌዎችና የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩ አስተማሪ ሽማግሌዎች ናቸው። እነዚህ ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ጥሪ፥ በመንፈስ ቅዱስ ብቃት፥ እንዲሁም በሰዎቹ በራሳቸው ሥራና ምስክርነት መሠረት ከማኅበሩ ይመረጣሉ። ከተመረጡ በኋላ ይሾሙና ለዚህ አገልግሎት ይለያሉ (የሐዋ. 14፡23፤ 20፡17፥ 28፤ ቲቶ 1፡5)።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርም አስተማሪም ያስፈልገዋል። መንፈስ ቅዱስ «የዕርዳታንና» «የአገዛዝን» ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን ይሰጣል (1ኛ ቆሮ 12፡28)። ቤተ ክርስቲያን ካልተደራጁች የጥረት፥ የገንዘብና እንዲሁም የሥራ ዕድሎች ይባክናሉ። መንፈሳዊ አእምሮ ያላቸው መሪዎች የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን የተለያዩ አገልግሎቶች ካልተቆጣጠሩ፥ በሥርዓት ፋንታ ሥርዓተ አልበኝነት ይሰፍናል። ሆኖም ይህ ቁጥጥር አምባገነናዊ መሆን የለበትም። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ሥራ ልክ ግሮሰሪን ወይም የማምረቻ ድርጅትን እንደምታስተዳድር አታስተዳድርም። ቤተ ክርስቲያን መልካም የንግድ ሥራ መመሪያዎችን መከተል ቢኖርባትም፥ የንግድ ማዕከል አይደለችም። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሚያስተዳድሩበት ጊዜ ሰዎችን በማስገደድ ከሆነ ለወንጌል ዕንቅፋት ነው።

ነገር ግን ማስተዳደር ያለ ትምህርት የሚሰጠው ውጤት በጣም ትንሽ ነው። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል አገልግሎት ታድጋለች (ኤፌሶን 4፡11-13))። በሕፃናት ላይ አስተዳዳሪ መሆን አይቻልም፥ አማኞች ካልተመገቡ፥ ካልነጹና እንዲሁም በቃሉ ካልጠነከሩ ደካማና የማይጠቅሙ በመሆን፥ ችግሮችን ብቻ ይፈጥራሉ።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ መሪዎች በሥራቸው መጠን፥ እንደየአገልግሎታቸው ክፍያ ማግኘታቸውን እንዲያረጋግጥ ነግሮታል። ይህንን አሳቡን ለማስረገጥ ከብሉይ ኪዳን ጠቅሷል (ዘዳግም 25፡4)። (በዚህ አሳብ ላይ በጣም ጥሩ ማብራሪያ የሚሆነው 1ኛ ቆሮ. 9፡7-14

ነው። ከዚያም ጳውሎስ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ቃል አክሏል፡- «ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል» (ሉቃ. 10፡7)። ይህ በዚያን ጊዜ የተለመደ አባባል ነበረ፤ ነገር ግን ጳውሎስ የኢየሱስን ቃል ከብሉይ ኪዳን ቃል ጋራ አዛመደው።

መጋቢዎች ሕዝቡን በመመገብና በመምራት ታማኞች ከሆኑ፥ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ለእነርሱ በትክክል ለመክፈል ታማኝ መሆን አለባት። «እጥፍ ክብር» (1ኛ ጢሞ. 5፡17) «ለጋስ ክፍያ» ተብሎ ሊተረጎም ይቻላል። የአገልጋዮች ለኑሮአቸው የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ነገሮች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት እንዲሟላ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው፤ እንዲሁም እርሱ ለአገልጋዮቹ ታማኞች የሆኑትን አብያተ ክርስቲያናት ይባርካል። ቤተ ክርስቲያን ታማኝ ካልሆነችና የመጋቢዋ ለኑሮው የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ነገሮች ካልተሟሉ መጥፎ ምስክርነት ነው፤ እግዚአብሔርም ይህን ሁኔታ የሚያስተካክልበት ሌላ መንገድ ማዘጋጀት ይቻላል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ያንን በረከት ታጣለች፥ ወይም እርሱ አገልጋዩን ወደ ሌላ ስፍራ ይወስደዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ አንድ መጋቢ ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ብሎ ማገልገል የለበትም (3፡3 ተመልከቱ)። ከቤተ ክርስቲያኑ ጋራ «መደራደር» ወይም ከፍተኛ ደሞዝ በመፈለግ በየስፍራው መዞር የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ከገንዘብ ኮሚቴ ዕርዳታ ለማግኘት በመሻት የራሱን የገንዘብ እጦት በስብከቱ ላይ ማቅረብም ትክክል አይደለም።

ለ. ሽማግሌዎችን መቅጣት (1ኛ ጢሞ. 5፡19-21)፡- ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ቅጣት ከሁለቱ ወደ አንደኛው አቅጣጫ ያዘነብላል። ወይ ቅጣት የሚባል ነገር ሳይኖር ይቀርና ቤተ ክርስቲያኒቱ በአለመታዘዝና በኃጢአት ምክንያት ደካማ ትሆናለች። ወይም ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአባሎቻቸው ላይ ሁልጊዜ ጥፋት ፈላጊ ሆነው ፈራጆች በመሆን ብዙ መንፈሳዊ መመሪያዎችን ያፋልሳሉ።

የቤተ ክርስቲያን አባላትን መቅጣት በማቴዎስ 18፡15-18፤ በ2ኛ ተሰሎንቄ 3፡6-16፥ 2ኛ ጢሞ. 2፡23-26፤ ሮሜ 16፡17-18፤ 2ኛ ዮሐ. 9-11፤ ገላትያ 6፡1-3፤ ቲቶ 3፡10 1ኛ ቆሮ. 5 እና 2ኛ ቆሮ. 2፡6-11 ተብራርቷል።

በዚህ ምንባብ ውስጥ ጳውሎስ (1ኛ ጢሞ. 5፡19-21)፥ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ስለመቅጣት ገልጿል። የቤተ ክርስቲያን አባል ቅጣት የሚያስፈልገውን በደል ፈጽሞ መገኘቱ የሚያሳዝን ነገር ነው፤

ነገር ግን መንፈሳዊ መሪ የሆነ ሰው ሲወድቅና መቀጣት ሲኖርበት ደግሞ የበለጠ ያሳዝናል፤ ምክንያቱም መሪዎች በሚወድቁበት ጊዜ በሌሎች ሰዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያስከትሉበት መንገድ ስለሚኖር ነው።

የቅጣት ዓላማው ማቃናት እንጂ በቀል አይደለም። ዓላማችን ጉዳት ያደረሰውን ለማዳን ነው እንጂ ለማባረር አይደለም። አመለካከታችን ከፍቅርና ከገርነት የመነጨ መሆን አለበት (ገላትያ 6፡1-3)። በገላትያ 6፡1 ላይ ጳውሎስ የጠቀሰው «ማቅናት» የሚለው ግሥ ትርጉሙ «የተሰበረውን አጥንት መጠገን» ማለት ነው። በድርጊቱ ውስጥ የሚያስፈልገውን ትዕግሥትና ርኅራኄ አስቡ።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠው የመጀመሪያ አስጠንቃቂ ማሳሰቢያ ስለ ጭብጦቹ እርግጠኛ እንዲሆንና ያንንም ለማድረግ መንገዱ ምስክሮችን ማግኘት እንደሆነ ነው (1ኛ ጢሞ. 5፡19)። ይህ መመሪያ በዘዳግም 19፡15፥ ማቴ. 18፡16፥ እና በ2ኛ ቆሮ. 13፡1 ላይ ተገልጿል። የመመሪያው ሁለት ገጽታ በዚህ ስፍራ የተሰጠ ይመስለኛል። በመጀመሪያ በመጋቢው ላይ ክስ የሚያቀርቡ ሰዎች በምስክሮች ማስደገፍ አለባቸው። ያልተጣራ ወሬና ጥርጣሬ ለቅጣት ትክክለኛ መሠረቶች አይደሉም። ሁለተኛ፥ ክስ በሚመሠረትበት ጊዜ ምስክሮቹ አብረው መቅረብ አለባቸው። በሌላ አነጋገር ተከሳሹ በምስክሮች ፊት ለፊት ከሳሹን ለመጋፈጥ መብት አለው።

አንድ ምሽት በአንድ የቤተ ክርስቲያን የራት ግብዣ ላይ አንዲት የቤተ ክርስቲያን አባል ወደኔ መጥታ ቤተ ክርስቲያኑን አበላሽተሃል ብላ ልትከሰኝ ጀመረች። እርሷም ውሸት ያለባቸው፥ የወቀሳ ዓይነቶችን አቀረበች። እርሷም እየተቆጣች ስትለፈልፍ፥ በአጠገባችን የነበሩትን ሁለት ኃላፊዎች ለምትናገረው ወቀሳ ምስክሮች እንዲሆኑ ጠየቅኋቸው። በዚህም ጊዜ ወዲያው ንግግሯን አቁማ በንቀት ፈጥና ወጣች።

ቤተ ክርስቲያን ለቃሉ መታዘዝ አቁማ፥ ያልተረጋገጡ ወሬዎችን፥ ውሸቶችን፥ እና ሐሜትን ስትሰማ መመልከት የሚያሳዝን ነው። ብዙ እግዚአብሔርን የሚመስሉ መጋቢዎች በሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው በዚህ መንገድ ተሸንፈዋል፥ እንዲሁም አንዳንዶች ከአገልግሎታቸው በፈቃዳቸው ለቀዋል። «ጭስ ባለበት እሳት አለ» የሚለው በዝግጅት ላይ ለሆነ የእሳት አደጋ ክፍል ሠራተኛ ጥሩ መፈክር ሊሆን ይችላል፤ ዳሩ ግን ይህ ለቤተ ክርስቲያን አይሠራም። «ጭስ ባለበት እሳት አለ» የሚለው የአንድ ሰው ምላስ «የገሃነምን እሳት ያቀጣጥላል» ማለት ይሆናል (ያዕቆብ 3፡6)።

ሁለተኛው የጳውሎስ ማስጠንቀቂያ፥ ጢሞቴዎስ ሁሉንም ነገር በግልጽና በአግባብ እንዲያደርግ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ጉዳዮችን በስውር መሥራት ቦታ የለውም። ጌታ ኢየሱስ «በስውር ምንም አልተናገርሁም» አለ (ዮሐንስ 18፡20)። አንድ ኃላፊ ጥፋተኛ ከሆነ፥ በሌሎች መሪዎች ፊት መገሰጽ አለበት (1ኛ ጢሞ. 5፡20)። ንስሐ እንዲገባ ዕድል ሊሰጠው ያስፈልጋል፥ ንስሐ ከገባም ይቅርታ ሊደረግለት ይገባል (2ኛ ቆሮ. 2፡6-11)። አንድ ጊዜ ይቅር ከተባለ፥ ነገሩ ተስተካክሏል፤ እንደገናም መነሳት የለበትም።

ሦስተኛው የጳውሎስ ማስጠንቀቂያ (1ኛ ጢሞ. 5፡21) ጢሞቴዎስ ምንም ዓይነት ስሜት ቢሰማው ለቃሉ መታዘዝ እንዳለበት ነው። ለተከሰሰው የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሳያደላ ወይም አስከፊ ዝንባሌ ሳያድርበት እርምጃ መውሰድ አለበት። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም ዓይነት የበላይነት የለም፤ እያንዳንዱ አባል በእግዚአብሔርና በቃሉ ፊት አንድ ዓይነት መብት አለው። ፍትሕ በጎደለው ሁኔታ መፍረድ ወይም ልዩነትን ማሳየት ሁኔታውን ማባባስ ነው።

ሐ. ሽማግሌዎችን መምረጥና መሾም (1ኛ ጢሞ. 5፡22-25)፡-
የሁሉንም ሰው ልብ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው (የሐዋ. 1፡24)። ቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎችን ለመምረጥ መንፈሳዊ ጥበብና ምሪት ያስፈልጋታል። በስሜት ተነሣስቶ አንድ አዲስ ክርስቲያንን ወይም አዲስ የቤተ ክርስቲያን አባልን በመንፈሳዊ ኃላፊነት ላይ ማስቀመጥ አደገኛ ነው። የአንዳንድ ሰዎች ኃጢአት በግልጽ ይታያል፤ ሌሎች ደግሞ ኃጢአታቸውን መሸፈን ይችላሉ፤ ኃጢአታቸው ግን ይከተላቸዋል (1ኛ ጢሞ. 5፡24)። ምንም እንኳን ሌሎች እንዲያዩዋቸው ባያገለግሉም፥ ራሳቸውን የሰጡ አማኞች መልካም ሥራ በግልጥ የሚታይ መሆን ይኖርበታል (5፡25)።

በሌላ አነጋገር ከፍተኛ ስሕተት እንዳይገኝባቸው ቤተ ክርስቲያን ለመሪነት የሚታሰቡትን ሰዎች ሕይወት በጥንቃቄ መመርመር አለባት። በኃጢአት ውስጥ የሚመላለሱትን ሽማግሌዎች መሾም ከኃጢአታቸው ጋራ መተባበር ማለት ነው። ዓመፀኛውን ሰው «ደህና ሁን» (እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን) ማለት የክፉ ሥራው ተባባሪዎች የሚያደርገን ከሆነ (2ኛ ዮሐንስ 10-11)፥ እንግዲያውስ ሕይወታቸው

ከእግዚአብሔር ጋር ያልተስተካከለላቸውን ሰዎች ስንሾም ምን ያህል ጥፋተኞች እንሆናለን?

ፍጹም የሆነ መጋቢም ሆነ የቤተ ክርስቲያን አባል የለም፤ ነገር ግን ያ ፍጹም ለመሆን ከመጣር አያግደንም። የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚቆመው ወይም የሚወድቀው ከመሪዎችዋ የተነሣ ነው። ፈሪሃ-እግዚአብሔር የሚታይበት መሪነት ማለት የእግዚአብሔር በረከት ማለት ነው፤ እኛም የምንሻው የዚህ ዓይነቱን አመራር ነው።

ከበላይ አካላት የሚተላለፉ ትእዛዛት

1ኛ ጢሞቴዎስ 6

ይህ ምዕራፍ ጢሞቴዎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ዓይነት አማኞች በሚያገለግልበት ሁኔታ ላይ ጳውሎስ የሰጠው ምክር ተከታይ ነው። ጳውሎስ የወታደር ቤት ቃላት ስለሚጠቀም፥ ዓውዱ ወታደራዊ ነው። «መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል» (6፡12)። «እኔ አዝዝሃለሁ» (6፡13፥ ከ1፡3 ጋራ አንድ ዓይነት ወታደራዊ ቃል ነው)። «ሃብታሞች የሆኑትን እዘዛቸው» (6፡17)። «ጢሞቴዎስ ሆይ፥ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ» (6፡20)። በሌላ አነጋገር፥ ጳውሎስን ከጠቅላይ አዛዡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ትእዛዛትን ለጢሞቴዎስ የሚያስተላልፍ ጀኔራል አድርገን መመልከት እንችላለን።

ዲ. ኤል. ሙዲ፥ ዘማሪው አይራ ሳንኬይን «የክርስቲያን አርበኞች ለጦር ስትሄዱ» የሚለውን መዝሙር በወንጌል ዘመቻቸው እንዲጠቀም አይፈልጉም ነበረ። ሙዲ የተመለከቱዋት ቤተ ክርስቲያን ሠራዊት መስላ አልታየቻቸውም ነበር፤ ምክንያቱም የዛሬው የቤተ ክርስቲያን አባሎች በመታዘዝ ወደ አገልግሎት መስክ ስለማይወጡ እንደ ጥሩ የክርስቶስ ወታደሮች ለመሆን አልበቁም። ወታደሮች በጦርነት ጊዜ እንደዛሬው የማይታዘዙ አባሎች ቢመስሉ ኖሮ በምናቸውም ጦርነት ድልን ባልተቀዳጁ ነበር።

ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አራት ተጨማሪ ቡድኖችን እንዴት እንደሚያገለግልና እንዲሁም የራሱን ሕይወት እንዴት በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እንደሚጠብቅ መክሮታል።

1. ክርስቲያን ባሮች (1ኛ ጢሞ. 6፡1-2)፡- አንዳንድ የታሪክ አዋቂዎች ከሮማ መንግሥት ሕዝብ ግማሽ ያህሉ ባሮች ነበሩ ብለው ገምተዋል። ከነዚህ ውስጥ ብዙዎቹ የተማሩ፥ ጥሩ ባህል ያላቸው ነበሩ፤ ነገር ግን በሕግ ፊት እንደ ሰው አይቆጠሩም ነበር። የወንጌሉ የደኅንነት መልእክትና በክርስቶስ ያለው ነጻነት ለነዚህ ባሮች ተስማማቸውና ብዙዎቹ አማኞች ሆኑ። ባሮች ከጌቶቻቸው ሥራ ጊዜ ከአካባቢው ጉባኤ ጋራ ጎብረት ያደርጉ ነበር። ሆኖም ባሪያ መሆናቸው ለመሰብሰብ እንቅፋት አይሆንባቸውም (ገላትያ 3፡28)።

ነገር ግን አንድ ችግር ነበር፡- አንዳንድ ባሪያዎች በክርስቶስ ያገኙትን አዲስ ነጻነት ምክንያት፥ በማድረግ ላለመታዘዝ፥ ከዚያም ደግሞ በጌቶቻቸው ላይ ለማመፅ ተጠቀሙበት። ምንም እንኳን ወደ ቤተ ክርስቲያን ጎብረት በጸጋ ቢቀላቀሉም፥ በክርስቶስ ያለው መንፈሳዊ ነጻነታቸው በጎብረተሰብ ውስጥ ያላቸውን ስፍራ እንደማይለውጠው መማር ያስፈልጋቸው ነበር።

ሀ. ከማያምኑ ጌቶች ጋራ የሚኖሩ ባሪያዎች (1ኛ ጢሞ. 6፡1)፡- ማንም ክርስቲያን ጌታ ባሮቹን «ከቀንበር በታች» እንደሚኖሩ አድርጎ አይመለከትም፤ ነገር ግን በፍቅርና በአክብሮት ያስተናግዳቸዋል (ቆላ. 4፡1 ፊሊሞና 16)። ባልዳነ ጌታ ላይ የአንድ ባሪያ ማመፅ በወንጌል ላይ ስድብን ያመጣል። «የእግዚአብሔር ስምና» ትምህርቱ ይሰደባል (ሮሜ 2፡24)። ጳውሎስና የጥንት ወንጌላዊያን በኃጢአት የተሞላውን የባርነት ሥርዓት በመቃወም እየዞሩ ያልሰበኩበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው። እንደዚህ ዓይነቱ ልምምድ ቤተ ክርስቲያንን ማህበራዊ ሥርዓትን ለመቃወም እንደምትፈልግ ወታደራዊ አካል አድርጎ ያስቆጥራት ነበር። ይህም የወንጌሉን የመስፋፋት ብቃት በከፍተኛ ደረጃ ያደናቅፈው ነበር።

ለ. ከሚያምኑ ጌቶች ጋር የሚኖሩ ባሪያዎች (1ኛ ጢሞ. 6፡2)፡- እዚህ ላይ ችግር የሚፈጠረው፥ ሁለቱም የዳኑ በመሆናቸው፥ ክርስቲያኑ ባሪያ ለጌታው በአግባቡ ያልታዘዘ እንደሆነ ነው። አንድ ባሪያ «ጌታዬ ወንድሜ ነው» ብሎ ሊከራከር ይችላል። «ሁለታችንም እኩል እስከሆንን ድረስ እኔ የማደርገውን እርሱ ሊነግረኝ አይችልም» እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት በቤትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ችግሮች ሊፈጥር ይችላል።

ጳውሎስ አማኝ ባሪያዎች ለአማኝ ጌቶቻቸው አክብሮት ማሳየት ለምን እንዳለባቸውና በነጻነታቸው ያለ አግባብ መጠቀም እንደሌለባቸው ሦስት ምክንያቶች ይሰጣል። በጣም ግልጽ የሆነው ምክንያት ጌቶቻቸው ክርስቲያኖች ናቸው (የሚያምኑ)። እንዴት አንድ አማኝ ለሌላው አማኝ መጎዳት ምክንያት መሆን ይችላል? ሁለተኛ ጌቶቻቸው የተወደዱ ናቸው። ፍቅር አያምፅም ወይም ከኃላፊነት የሚያመልጥበትን መንገድ አይፈልግም። በመጨረሻም፥ ሁለቱም ጌቶችና ባሮች ከመታዘዝ ይጠቀማሉ። (የጥቅሙ ተካፋዮች የሚለው ለሁለቱም ሊሆን ይችላል)። ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሆነው አንዱ ሌላውን ሲያገለግል ሁለ ገብ የሆነ በረከት ይኖራል።

አንዲት ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥራ ለቅቃ ወደ ክርስቲያን ድርጅት ውስጥ ልትሠራ የሄደች ወጣት ሴት አስታውሳለሁ። እዚያ አንድ ወር ያህል ከቆየች በኋላ ሁኔታው እርሷ ከጠበቀችው ውጪ ነበር።

«በምድር ላይ ገነት እንደመኖር ይሆናል ብዬ አስቤ ነበር» ስትል አማረረች፤ ዳሩ ግን ከችግሮች በስተቀረ ምንም ነገር የለም።

«ለቀድሞው አለቃሽ በርትተሽ የምትሠሪውን ያህል ለክርስቲያኑ አለቃሽም ትሠሪያለሽን?» ብዬ ጠየቅሁዋት። የፊትዋ ሁኔታ መልሱን ሰጠኝ። «የበለጠ ለመሥራት ሞክሪ። እንዲሁም የበለጠ አክብሮት አሳዪው። በቢሮ ውስጥ ያላችሁት ሁሉ የዳናችሁ ስለሆናችሁ ብቻ ተግቶ ከመሥራት ይልቅ ያነሰ መሥራት ትችላላችሁ ማለት አይደለም።» ብዬ መከርኋት። ምክሬን ከተቀበለች በኋላ ችግሮችዋ ተወገዱ።

2. ሐሰተኛ አስተማሪዎች (1ኛ ጢሞ. 6፡3-10)

ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ ስለ ሐሰት አስተማሪዎች ማስጠንቀቂያ በመስጠት ይከፍታል (1፡3-7)፤ እንዲያውም አንዳንድ አደገኛ ትምህርቶቻቸውን በመቃወም አስተምሯል (4፡1-5)። ሐሰተኛ ትምህርቶች በቀላሉ ሰርገው መግባት ስለሚችሉ (የሐዋ. 20፡28-32)፥ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ መንፈሳዊ መሪዎች ሳያቋርጡ ምን ትምህርት እንደሚሰጥ መከታተል አለባቸው። አንድ የማውቀው መጋቢ፥ አንድ የሰንበት ትምህርት አስተማሪ የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ፈንታ የራሱን «ራዕይ» ሲያስተምር አግኝቶታል።

ሀ. የእነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ምልክቶች (1ኛ ጢሞ. 6፡3-5)፡-

የመጀመሪያው ምልክት «ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ጤናማ ቃልና እግዚአብሔርን ለመምሰል በሚስማማ ትምህርት» (6፡3) ለመኖር አይፈልጉም። ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ስለሆነ፥ እግዚአብሔርን ወደመምሰል ያሳድጋል። ኢሳያያስ ለማንኛውም አስተማሪ የሚያቀርበው ፈተና «ወደ ሕግና ወደ ምስክር ሂዱ! እንዲህ ያለውን ቃል ባይናገሩ ንጋት አይበራላቸውም» (ኢሳ. 8፡20)። በቤተ ክርስቲያን «ንጹሕ (ጤናማ) የሆነውን ቃል አጥብቆ መያዝ» (2ኛ ጢሞ. 1፡13) በጣም አስፈላጊ ነው።

ሁለተኛው ምልክት የአስተማሪው የራሱ አመለካከት ነው። ሐሰተኛ አስተማሪ ትሑት በመሆን ፈንታ ይታበያል፤ ነገር ግን ምንም ነገር ስለማያውቅ የሚታበይበት ነገር የለውም (1ኛ ጢሞ. 6፡4 እንዲሁም 1፡7)። ቃሉን የሚያስተውል አማኝ የሚቃጠል ልብ እንጂ

ኩራተኛ ልብ አይኖረውም (ሉቃስ 24፡32 እና ትን. ዳንኤል 9፡1-20 ተመልከቱ)። ይህ «የትዕቢት አመለካከት» አስተማሪውን ስለ ጥቃቅን «ቃላት» እንዲከራከር ያደርገዋል (1ኛ ጢሞ. 6፡3)። «የክርስቶስን ... ጤናማ ቃል» ከመመገብ ይልቅ የጥያቄዎች በሽታ ይዞታል ለማለት ይቻላል። በ (6፡4) «እንደ በሽተኛ ይናፍቃል» የሚለው ቃል «በክፉ መሻቶች የተሞላ» ማለት ነው። የእንደዚህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ያልሆነ ትምህርት ውጤቱ «ቅንዓት፥ ጠብ፥ ስድብ፥ መጥፎ ጥርጣሬ፥ እና የማያቋርጥ ክርክር» ነው (6፡4-5)።

ይህ ሁሉ የሚያሳዝነው ሕዝቡ እውነትን ያገኙ እየመሰላቸው «እውነትን መቀማታቸው» ነው (6፡5)። አለማወቃቸውን የሚለዋወጡባቸው ሳምንታዊ የክርክር ስብሰባዎቻቸው በጸጋ የሚያድጉባቸው መንገዶች እንደሆኑ ያስባሉ። ይሁን እንጂ ውጤቱ መሻሻል ሳይሆን የባሕርይ መበላሸት ነው።

ለ. የትምህርታቸው ዓላማ (1ኛ ጢሞ. 6፡5-10)፡- እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች «እግዚአብሔርን መምሰል ገንዘብ የማግኛ መንገድ ነው» ብለው ይገምቱ ነበር (ቀጥተኛ ትርጉም)። «እግዚአብሔርን መምሰል» በዚህ ቦታ (6፡5) «የክርስትና እምነት መግለጫ» ነው እንጂ፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሆነ እውነተኛ ቅዱስ ኑሮ አይደለም። ሃይማኖታዊ መግለጫቸውን እንደ ገንዘብ ማግኛ ዘዴ ተጠቅመውበታል። እነርሱ ያደረጉት ሃይማኖታዊ ንግድ እንጂ፥ እውነተኛ አገልግሎት አልነበረም።

ጳውሎስ ጥሪውንና አገልግሎቱን ለገንዘብ ማግኛ እንዳይጠቀምበት ሁል ጊዜ ይጠነቀቅ ነበር። እንዲያውም አንድ ጊዜ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተላከለትን ዕርዳታ ማንም ሰው በገንዘብ ወዳድነት እንዳይወቅሰው አልቀበልም ብሏል (1ኛ ቆሮ. 9፡15-19)። ስብከቱን እንደ «የሰው ንብረት መቀሚያ ካባ» አድርጎ በፍጹም አለተጠቀመም (1ኛ ተሰ. 2፡5)። በአሁኑ ዘመን ሞኞችን ሰዎች እየሰበኩ የእርዳታ ተስፋ እየሰጡ ገንዘባቸውን የሚወስዱባቸውን ሃይማኖታዊ ቀማኞችን ማየት አሳዛኝ ነገር ነው።

ጢሞቴዎስንና እኛንም ለማስጠንቀቅ ጳውሎስ ስለ ክፉ ምኞት አደገኝነት አራት ጭብጦችን አካፍሏል፡-

1. ሀብት እርካታን አያመጣም (1ኛ ጢሞ. 6፡6)፡- እርካታ የሚለው ቃል «ውጪ ያለው ሁኔታ ሳይረብሸን በውስጣችን በሰላም የምንጠበቅበት ውስጣዊ ብቃት» ነው። ጳውሎስ ይህንኑ ቃል ወደ

በኋላ ተጠቅሞበታል። «የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለትን ተምሬያለሁና» (ፊሊጵስዩስ 4፡11)። እውነተኛ እርካታ የሚገኘው ፈሪሃ-እግዚአብሔር ካለበት ልብ እንጂ፥ በእጅ ከሞላ ሀብት አይደለም። ለሰላምና ለዋስትና በቁሳቁስ ነገሮች የሚታመን ሰው በፍጹም አይረካም። ቁሳቁስ ነገሮች የመሳብ ኃይላቸው የሚሟሽሽበት መንገድ አለ። ወደ ሥነ-አእምሮ ሐኪሞች የሚሄዱና ራሳቸውን ለመግደል ብዙ ጊዜ የሚሞክሩት ድሆች ሳይሆኑ፥ ሀብታሞች ናቸው።

2. ሀብት ዘለዓለማዊ አይደለም (1ኛ ጢሞ. 6፡7)፡- ይህንን ቁጥር ለመተርጎም እፈልጋለሁ። «ወደዚህ ዓለም ምንም ይዘን ስላልመጣን፥ ምንም ይዘን ለመሄድ አንችልም» (ኢዮብ 1፡21 ተመልከቱ)። በሞት ጊዜ የአንድ ሰው መንፈስ አካሉን ለቅቆ ሲሄድ፥ ምንም ይዞ መሄድ አይችልም፤ ምክንያቱም ያ ሰው ወደ ምድር ሲመጣ (በሚወለድበት ጊዜ) ምንም ይዞ አልመጣም። ማንኛውም የምናከማቸው ሀብት ለመንግሥት፥ ለወራሾቻችን፥ እና ምናልባት ለእርዳታ ድርጅቶችና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይውላል። «ምን ያህል ነገር ትቶ ሄደ?» ለሚለው ጥያቄ ሁልጊዜም መልሱን እናውቀዋለን። «ሁሉንም ነገር!»

3. መሠረታዊ ፍላጎቶቻችን በቀላሉ ይሟላሉ (1ኛ ጢሞ. 6፡8)፡- ምግብና መከለያ (ልብስና መጠለያ) መሠረታዊ ፍላጎቶች ናቸው። እነርሱን ካጣን ሌሎች ነገሮችን የመንከባከብ አቅም እናጣለን። ገንዘብ የማጠራቀም ሱስ የተጠናወተው ሰው፥ ገንዘቡን ደብቆ በረሃብ ጠኔ ሊሞት ያጣጥራል። አንድ ቀላል ኑሮ የሚኖር የክርስትና ቡድን አባል «ክዌከር» አዲስ ጎረቤቱ ሙሉ የቤት ዕቃውንና «የተሳካላቸው ሰዎች» የሚሰበስቧቸውን ውድ መጫወቻዎች ይዞ ሲገባ ተመለከተ። ከዚያም ወደ አዲስ ጎረቤቱ በመሄድ እንዲህ አለው፡- «ወንድም አንድ ነገር ከፈለግህ እኔጋ ና፥ እኔም እንዴት ያለዚያ ልትኖር እንደምትችል እነርግሃልሁ» አለው። ሄነሪ ዴቪድ ሶሮው የተባሉት ታላቁ የ1800 ዓ.ም. ጸሐፊ፥ ሰው ሀብታም ሊባል የሚችለው ያለው ጥቂት ነገር ቢሆንም እንኳ ባለው ነገር በሙሉ ደስተኛ ከሆነ ብቻ ነው።

ዓለም የምትጋፈጣቸው የምጣኔ ሀብትና የኃይል ችግሮች፥ ምናልባት እግዚአብሔር ሰዎች ኑሮአቸውን በቀላሉ እንዲመሩ ለማበረታታት የሚጠቀምበት ይሆናል። ብዙዎቻችን «ሁሉም ነገር ምን ያህል

ዋጋ እንደሚያወጣ እናውቃለን፤ ሆኖም የአንዱንም ነገር ጥቅም አናውቅም»። በምኞት ዕቃዎች ስለተጥለቀለቅን፥ መሠረታዊ በሆኑ ፍላጎቶቻችን መደሰትን ረስተናል።

4. ሀብትን መመኘት ወደ ኃጢአት ይመራል (1ኛ ጢሞ. 6፡9-10)፡- «ሀብታሞች ለመሆን የሚፈልጉ ...» የሚለው ትክክለኛው ትርጉም ነው። ደስተኛና የተሳካለት ሰው ለመሆን በርካታ ቁሳዊ ሀብት እንዲኖረው የሚሻውን ሰው ይገልጻል። ባለጠግነት ግን ወጥመድ ነው፤ ወደ እስራት እንጂ፥ ወደ ነጻነት አይመራም። እርካታን በመስጠት ፈንታ ባለጠግነት አዲስ ምኞቶችን (ፍላጎቶችን) ይጨምራል። እነዚህም ደግሞ መርካት አለባቸው። እርዳታንና ጤንነትን በመስጠት ፈንታ ከልክ በላይ የሆነ ቁሳቁስ ይጎዳል፤ ያቆስላልም። ጳውሎስ በግልጽ ያስረዳው ውጤት «ሰዎችን በሚያበላሽና በሚያጠፋ ከንቱና አደገኛ በሆነ በብዙ ምኞት ወጥመድም ይወድቃሉ» (6፡9፥ አዲሱ ትርጉም)። ይህም እየሰጠመ የሚሄደውን የሰው ሁኔታ ይገልጻል። ሀብቱን ተማምኖ «ብቻውን ቀዘፈ»፥ ነገር ግን ማዕበሉ መጣ፥ እርሱም ሰጠመ።

ሃይማኖትን ሀብት ለማከማቻ መሸፈኛ አድርጎ መጠቀም አደገኛ ነገር ነው። የእግዚአብሔር ሠራተኛ በእርግጥ ደመወዙ ይገባዋል (5፡17-18)፤ ነገር ግን የሚደክምበት ምክንያት ገንዘብ ለማግኘት መሆን የለበትም። ያ እርሱን «ሙያተኛ» እንጂ፥ እውነተኛ እረኛ አያደርገውም (ዮሐንስ 10፡11-14)። «ምን ያህል አገኛለሁ» ከማለት፥ ይልቅ «ምን ያህል መስጠት እችላለሁ?» ብለን መጠየቅ አለብን።

3. መጋቢው ራሱ (1ኛ ጢሞ. 6፡11-16፥ 20-21)

ለሕዝቡ ፍላጎቶች በሚጠነቀቅበት ጊዜ፥ ጢሞቴዎስ ለራሱም መጠንቀቅ ያስፈልገው ነበር። «ለራስህ ተጠንቀቅ» (4፡16) የሚለው ከጳውሎስ ምክሮች አንዱ ነበር። «አንተ ግን» (6፡11) የሚለው ቃል በጢሞቴዎስና በሐሰት አስተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል። እነርሱ የዓለም ሰዎች ሲሆኑ፥ እርሱ ግን «የእግዚአብሔር ሰው» ነው። ይህ የተለየ «መጠሪያ» ለሙሴ (ዘዳግም 33፡1)፥ ለሳሙኤል (1ኛ ሳሙኤል 9፡6)፥ ለኤልያስ (1ኛ ነገስት 17፡18)፥ እና ለዳዊትም (ነህምያ 12፡24) ተሰጥቶአቸው ነበር፤ ስለዚህ ጢሞቴዎስ ከመልካም ጓደኞች ጋር ነበር።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ አራት ምክሮችን ይሰጣል። እነዚህም ከታዘዛቸው፥ በአገልግሎቱ መሳካትንና እንደ እግዚአብሔር ሰው የማያቋርጥ ምስክርነት የሚያስገኙ ነበር።

ሀ. ሽሽ (1ኛ ጢሞ. 6፡11)፡- መሸሽ የፍርሃት ምልክት ሆኖ የሚታይባቸው ጊዜያት አሉ። ነህምያ «እንደኔ ያለ ሰው መሸሽ ይገባዋልን?» በማለት ጠየቀ (ነህ. 6፡11)። ነገር ግን መሸሽ የጥበብ ምልክትና የድል መንገድ የሚሆንባቸው ሌሎች ጊዜያት አሉ። ዮሴፍ በጌታው ሚስት በተፈተነ ጊዜ ሸሸ (ዘፍጥረት 39፡12)። እንዲሁም ዳዊት ንጉስ ሳዖል ሊገድለው በሞከረ ጊዜ ሸሸ (1ኛ ሳሙ. 19፡10)። ጳውሎስ በዚህ ቦታ የተጠቀመበት «ሽሽ» የሚለው ቃል ሩጫ ከሚለው ጋራ በቀጥታ አይገናኝም፤ ነገር ግን ጢሞቴዎስ ራሱን ከኃጢአትና ከሐሰት አስተማሪዎች እንዲለይ የሚጠቁም ነው። ይህ በ6፡5 ላይ ያለውን ምክር ያስተጋባል፡- «ከእነዚህ ራስህን ለይ»።

ሁሉም ጎብረት መልካም አይደለም፤ ሁሉም መለየት ደግሞ መጥፎ አይደለም። የእግዚአብሔር አገልጋይ በሐሰተኛ ትምህርቶችና ፈሪሃ-እግዚአብሔር በሌለባቸው ልምምዶች ላይ አቋም የሚወስድባቸውና ራሱን ከእነርሱ የሚለይባቸው ጊዜያት አሉ። ሆኖም በግላዊ ጥላቻ ወይም በሥጋዊ የወገናዊነት መንፈስ ሳይሆን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ጽኑ እምነት ላይ በመመሥረት መሥራቱን ማረጋገጥ አለበት።

ለ. ተከተል (1ኛ ጢሞ. 6፡11)፡- መለየት ያለ አዎንታዊ ዕድገት ብቸኝነት ነው። እነዚህን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሕይወታችን ውስጥ ማሳደግ አለብን፤ አለዚያ በምናቀርበው መልካም አሳብ ሳይሆን፥ በተቃውሞ አሳብ ብቻ እንታወቃለን። «ጽድቅ» ማለት «የግል ፍጹምነት» ማለት ነው።

«እግዚአብሔርን መምሰል» ማለት «ተግባራዊ ቅድስና» ማለት ነው። የመጀመሪያው የሚሄደው ከባሕርይ ጋር ሲሆን፥ ሁለተኛው ከጠባይ ጋር ነው።

«እምነት» የሚለው ቃል «ታማኝነት» ተብሎ ቢተረጎምም የተሻለ ይሆናል። ታላቁ ችሎታ እምነት የሚጣልበት ሆኖ መገኘት እንደሆነ በሚገባ ተገልጿል።

«ፍቅር» ራሱን ስለሌላ ሰው መሥዋዕት የሚያደርገው «አጋፔ» ፍቅር ነው። ለመስጠት እንጂ ለመቀበል አይፈልግም።

«ትዕግሥት» ወደ ፊት መቀጠል በሚያዳግትበት ጊዜ በዚያው በመቆየት የ «መጽናት»ን አሳብ ይይዛል። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ጸንቶ የሚቆየው የግል ርካታ ሳይሆን፥ የመንፈስ ጥንካሬ ነው።

«ትሕትና» ደካማነት ሳይሆን፥ ነገር ግን «በቁጥጥር ሥር ያለ ኃይል» ነው። የጸና ደፋርነት ያለ ትሕትና ሰውን ጨካኝ ሊያደርግ ይችላል። ምናልባት «የውሃት» የሚለው ትርጉም በደንብ ይገልጸዋል።

ሐ. ተዋጋ (1ኛ ጢሞ. 6፡12-16)፡ - ግሱ ሲተረጎም «ሳታቋርጥ ተዋጋ» ማለት ነው። «ሥቃይ» የሚለውን ቃል ያሳስበናል። ይህም ለሯጮችና ለወታደሮች የሚያገለግል ቃል ነው። ጦርነትን ለማሸነፍ ወይም በውድድር ለማሸነፍ በብርቱ የሚደክመውንና ያለውን ሁሉ የሚሰጠውን ሰው ይገልጻል። ጳውሎስ የሕይወቱ መጨረሻ ሲቃረብ መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ (2ኛ ጢሞ. 4፡7) ብሎ ጻፈ።

ዳሩ ግን «ውጊያው» ከአማኞች ጋር አይደለም። በእግዚአብሔር ሰውና በዙሪያው ባለው ጠላት መካከል የሚደረግ ነው። የሚዋጋው እምነትን ለመከላከል ነው። ይህም ቤተ ክርስቲያን የያዘችው እውነት ነው (6፡20 ተመልከት)። እንደ ጥንቱ ነህምያ፥ የዛሬዎቹ ክርስቲያኖች በአንድ እጃቸው ለግንባታ የሚረዳ የሲሚንቶ መለሰኛ ማንካ፥ በሌላኛው ደግሞ የውጊያ ሰይፍ መያዝ ያስፈልጋቸዋል (ነህምያ 4፡17)። አንዳንድ ክርስቲያኖች ጠላትን በመዋጋት በጣም ብዙ ጊዜ ሲያጠፉና የራሳቸውን ሥራ ለመሥራትና ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት ጊዜ ሲያጡ መመልከት በጣም ያሳዝናል። በሌላ በኩል ጠላትን ጠንክረን ካልተቃወምነው፥ የገነባነው ከኛ ሊወሰድብን ይችላል።

በውጊያው ውስጥ የሚያበረታታን ነገር ምንድን ነው? «የዘለዓለም ሕይወት» አለን፥ እናም እርሱን በመያዝ በልምምዳችንም ውስጥ እንዲሠራ መፍቀድ ያስፈልገናል። በእግዚአብሔር መጠራታችን የድልን ዋስትና ይሰጠናል። በክርስቶስ የማመናችንን ምስክርነት በአደባባይ ሰጥተናል፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ከኛ ጋር ይቆማሉ።

ሌላው በውጊያ ጊዜ የሚያበረታታን የአዳኛችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት ነው። እርሱ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ፊት «መልካም ምስክርነት መስክሯል» (6፡13)፤ በመሆኑም በጠላቱ ፊት አልወላወለም። እግዚአብሔር አብ ከእርሱ ጋራ እንደነበረ፥ ለእርሱ እየተጠነቀቀለት እንደሆነና ከሙታን እንደሚነሣ ያውቅ ነበር። «ነገሮች ሁሉ ሕይወት እንዲኖራቸው የሚያደርገው» (ቀጥታ ትርጉም) እና ለኛ

የሚጠነቀቀው እግዚአብሔር ስለሆነ፥ መፍራት አያስፈልገንም። የጢሞቴዎስ ተፈጥሮአዊ ዓይነ-አፋርነትና ፍርሃት ከውጊያው እንዲያፈገፍግ ሊያደርገው ይችላል፤ ነገር ግን ማድረግ ያለበት ኢየሱስ ክርስቶስንና ደፋር ምስክርነቱን ማስታወስ ነበር። ይህም የሚያበረታታው ነበር።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ወታደራዊ ትእዛዛት ይሰጣል፦ «እኔ አዝሃለሁ» (ቁ. 13 እንዲሁም 1፡3)። ትእዛዛቱን መጠበቅና መታዘዝ ነበረበት። ለምን? ምክንያቱም አንድ ቀን አዛዡ ይገለጽና እርሱም የሥራውን ዘገባ ያቀርባል። ዝግጁ የሚሆንበት ብቸኛው መንገድ «ያለ እድፍ እና ያለነቀፋ» ትእዛዛቱን መፈጸም ነበር (6፡14)።

«መገለጥ» (6፡14) የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ «የክብር መገለጥ» የሚል ትርጉም ይሰጣል። በጳውሎስ ጊዜ ይህን ቃል በአፈ ታሪክ ውስጥ የአማልክትን መገለጥ ለመግለጽ ይጠቀሙበት ነበር። ይህም በተለይ አንድን ሰው ከችግር ለማዳን መገለጻቸውን ያሳይ ነበር። ጳውሎስ ይህንን ቃል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአትና (2ኛ ጢሞ. 1፡10) ስለ መመለሱ ለመግለጽ (2ኛ ጢሞ. 4፡1፥ 8) ተጠቅሞበታል። ክርስቶስ ዳግም የሚመጣበትን ጊዜ አናውቅም፤ ነገር ግን ይህ «በራሱ ሰዓት» (1ኛ ጢሞ. 6፡15) ይሆናል፤ እርሱም ሰዓቱን ያውቀዋል። የኛ ድርሻ በየዕለቱ ታማኞች መሆንና በእርሱ ውስጥ መኖር ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡28)።

የ 1ኛ ጢሞ. 6፡16 ዋና አሳብ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት የሆነው እግዚአብሔር አብ ነው። ሌሎች መጠሪያውን ሊወስዱ ቢችሉም፥ የሚገዛ እርሱ ብቻ ነው። «ብቻውን የሆነ ገዢ» (6፡15) «ኃይል» ከሚል ቃል የመጣ ነው። የምድር ነገሥታትና ገዢዎች ኃይልና ሥልጣን ያላቸው ይመስላቸው ይሆናል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የሁሉ ጌታና ልዑል ነው (መዝሙር 2 ተመልከቱ)።

«የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ» (1ኛ ጢሞ. 6፡15) ኢየሱስ ክርስቶስን እንድናስብ ያደርገናል (ራዕይ 17፡14፤ 19፡16)፤ ነገር ግን በዚህ ስፍራ መጠሪያውን የተጠቀመው ለእግዚአብሔር አብ ነው። በእርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ አብን ለእኛ ይገልጥልናል፤ ስለዚህም በትክክል ይህንን መጠሪያ ሊጠቀምበት ይችላል።

«የማይሞት» (1ኛ ጢሞ. 6፡16) ማለት «ለሞት ያልተገዛ» ማለት ነው። ሰው ለሞት የተገዛ ሲሆን፥ እግዚአብሔር ግን አይደለም። የማይሞት እግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህም ዋና አብሮት የነበረ ማንነቱ

ነው። እርሱ «የማይሞት፥ የማይታይ እና ብቻውን ጠቢብ አምላክ» ነው (1፡17) እግዚአብሔር ለሞት ባለመገዛቱ እርሱ ሕይወትና ሕይወት ሰጪ ነው። እርሱ የማይበላሽና ለመበስበስ ወይም ለመለወጥ ያልተገዛ ነው። በዚህ ሕይወት አማኞች በሚሞት አካል ውስጥ ናቸው፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ የእርሱን የማይሞት ባሕርይ እንካፈላለን (1ኛ ቆሮ. 15፡50-58)።

ጳውሎስ እነዚህን ሁሉ እውነቶች ስለ እግዚአብሔር ያስረዳው ጢሞቴዎስ «የእምነትን መልካም ገድል እንዲጋደል» እና ተስፋ እንዳይቆርጥ እንደሆነ ልብ በል። እግዚአብሔር የሁሉ ገዢ ስለሆነ ሕይወትን መፍራት የለብንም፤ እንዲሁም እርሱ አለመሞትን ስለሚያካፍለን ሞትን መፍራት አያስፈልገንም።

ጢሞቴዎስ ፈሪሃ-እግዚአብሔርን በማታውቅ የኤፌሶን ከተማ ውስጥ ይኖር ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በክቡር ብርሃን ይኖራል። «የእግዚአብሔር ክብር መታየት እንደሚያቃጥል እሳት ነበረ» (ዘጸአት 24፡17)። «ብርሃንን እንደልብስ ለብሰህ» [መዝሙር (104)፡2]። ዮሐንስ ስለ መንግስተ ሰማይ የሰጠው መግለጫ ለከተማይቱ ብርሃን በሚሰጠው በእግዚአብሔር ክብር ላይ ያተኩራል (ራእይ 21፡11፥ 23-24፤ 22፡5)። እርግጥ ብርሃን የቅድስና ምልክት ነው (1ኛ ዮሐ. 1፡5-7)። እግዚአብሔር ከኃጢአት ተለይቶ ይኖራል፤ እንዲሁም እግዚአብሔር በቅድስናው የተከበረ ነው።

ለኃጢአተኛው የሰው ልጅ ወደ ቅዱስ እግዚአብሔር መቅረብ የማይቻል ነው። ወደ እርሱ መቅረብ የምንችለውና እርሱም ሊቀበለን የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ ነው። ያዕቆብ እግዚአብሔርን በብሉይ ኪዳን ዘመን በምድር ላይ ከሚገለጽባቸው መንገዶች በአንደኛው መልክ ተመለከተው (ዘፍጥረት 32፡30)፤ እንዲሁም እግዚአብሔር ለሙሴ ከክብሩ የተወሰነ ክፍል እንዲመለከት ፈቀደለት (ዘጸአት 33፡18-23)። «እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም» (ዮሐንስ 1፡18)። ይህ እግዚአብሔርን በማንነቱ፥ በመንፈሳዊ ባሕርዩ ማየትን ያመለክታል። እኛ ለማየት የምንችለው የማንነቱን ነፀብራቅ ብቻ ሲሆን፥ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ስብዕና ውስጥ እግዚአብሔርን እንደ ማየት ነው።

ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ስብዕና ይህን ያህል የጻፈው ለምንድን ነው? ምናልባት በሮማ ግዛት ውስጥ የነበረውን «የሐሰት ንጉሥ» በተመለከተ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ይሆናል። በየጊዜው «ቄሳር ጌታ

ነው» እያሉ ማንቆለጳጰስ የተለመደ ነበረ። በእርግጥ ክርስቲያኖች «ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው» ይሉ ነበር። «ዘለዓለማዊ ኃይልና ክብር ያለው» እግዚአብሔር ብቻ ነው (1ኛ ጢሞ. 6፡16)። ጢሞቴዎስ መልካሙን የእምነት ገድል የሚጋደል ከሆነ፥ አምልኮና ሙሉ መሰጠት የሚገባው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ መወሰን ነበረበት።

መ. ታማኝ ሁን (1ኛ ጢሞ. 6፡20-21)፡- እግዚአብሔር እውነቱን ለጳውሎስ ሰጥቷል (1፡11)፤ እንዲሁም ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሰጥቶታል። አደራውን መጠበቅና በተራቸው ለማስተላለፍ ለሚችሉ ለሌሎች ሰዎች መስጠት የጢሞቴዎስ ኃላፊነት ነበር (2ኛ ጢሞ. 2፡2)። ይህ እግዚአብሔር እውነትን የሚጠብቅበትና በዓለም ዙሪያ የሚያሠራጭበት መንገድ ነው። እኛ የእምነት ትምህርት ወኪሎች ነን፤ በመሆኑም የእርሱን የምስራች ቃል በማካፈል ታማኞች እንድንሆን እግዚአብሔር ይጠብቅብናል።

«በውሸት እውቀት ከተባለ» (1ኛ ጢሞ. 6፡20)፤ ስለዚህ ቃል ጳውሎስ በዚህ ቦታ የሚያመለክተው «የተለየ መንፈሳዊ እውቀት» እንዳላቸው ስለሚናገሩት የሐሰት መምህራን ቡድን «ኖስቲኮች» ነው። (ለእውቀት የግሪኩ ቃል ኖሲስ ተብሎ ይነበባል። «አግኖስቲክ» ማለት ግን ስለ ሃይማኖት ጉዳይ ምንም የማያውቅ ማለት ነው። ኖስቲክ ስለ ሃይማኖት ጉዳይ በጣም ብዙ አውቃለሁ የሚል ነው)።

በዚህ ቦታ ወደ ኖስቲክስ ሐሰተኛ ትምህርቶች ዝርዝር ውስጥ መግባት አያስፈልግም። ጳውሎስ ወደ ቆላስይስ ደብዳቤ የጻፈው እነርሱን ለመቃወም ነበር። እነርሱ ከራእይና ከሌሎች ልምምዶች «የተለየ መንፈሳዊ እውቀት» አለን ይሉ ነበር። እንዲሁም ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ «የተደበቁ እውነቶች» በተለይም «የትውልድ ዝርዝሮችን» እንዳገኙ ይናገሩ ነበር፥ ቁስ አካልን ክፉ ነው ብለው ይቆጥሩ ነበር፥ እንዲሁም እነዚህ ሰዎች ተከታታይነት ያላቸው «ነፀብራቆች» እግዚአብሔርን ከሰው ጋር እንደሚያገናኙ ያስተምሩ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ከእነዚህ «ነፀብራቆች» ታላቁ ብቻ እንደሆነ ይናገራሉ።

ኖስቲኮች እንግዳ የሆነ ትምህርት ነበራቸው። ይኸውም ከክርስትና፥ ከምሥራቃውያን የጸሎትና የተመስጦ ልምምድ «አሪየንታል ሚስቲሲዝም»፥ ከግሪክ ፍልስፍና እና ከአይሁድ ሕግ-አጥባቂነት የተቀየጠ ነበር። ዛሬ እንደምናያቸው ብዙዎቹ የምሥራቅ ኑፋቄዎች፥ ይህኛውም «አንድ ነገርን ለሁሉም ሰው»

ትቷል፤ ነገር ግን ጳውሎስ ትምህርታቸውን በአንድ አስደንጋጭ ዓረፍተ ነገር አጠቃልሎታል፡- «ለዓለም የሚመች ከንቱ ልፍለፋ»። ፊሊፕስ «የተቃራኒ አሳቦች አምላክ የለሽ ቅየጣ» በማለት ይተረጉመዋል።

ጢሞቴዎስ እነዚህን ትምህርቶች ማስወገድ የሚያሻው ለምንድን ነው? ምክንያቱም የነዚህ ትምህርቶች ተሳታፊ የሆኑት አንዳንድ ሰዎች «ከእምነት ስተዋልና» (6፡21) ነው። አንድን ሰው ከእምነት እንዲስት የሚያደርጉት (6፡10) ትክክል ያልሆኑ ዓላማዎች (የገንዘብ መውደድ) ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን ትክክል ያልሆኑ ትምህርቶችም ጭምር ናቸው። እነዚህ ውሸቶች ቀስ በቀስ ወደ አንድ ሰው አሳብና ልብ መንገዳቸውን ያቀናሉ፤ እናም ከመንቃቱ በፊት ከእውነት መንፈስ ይርቃል።

4. ሀብታሞች (1ኛ ጢሞ. 6፡17-19)

ጳውሎስ ገንዘብን ስለ መውደድ አደገኝነት መጀመሪያውኑ ጽፏል። ነገር ግን ለሀብታሞች እንዲያስተላልፍ የተለየ «ትእዛዝ» ለጢሞቴዎስ ያክልለታል። ምናልባት ይህ ትእዛዝ እኛን እንደማይመለከት እናስብ ይሆናል፤ ነገር ግን ይመለከተናል። ዛሬ የምንኖርበት የኑሮ ደረጃ በጢሞቴዎስ ማኅበረ ምእመናን ዓይን ያለ ጥርጥር ሀብታሞች ያደርገናል።

ሀ. ትሑት ሁን (1ኛ ጢሞ. 6፡17)፡- ሀብት አንድን ሰው የሚያስታብየው ከሆነ፥ ራሱንም ሆነ ሀብቱን አያስተውልም። «ሀብት ለማከማቸት እርሱ ጉልበት ሰጥቶሃልና አምላክህን እግዚአብሔርን አስብ» (ዘዳግም 8፡18)። እኛ ባለቤቶች ሳንሆን፥ ባለአደራዎች ነን። ሀብት ቢኖረን፥ ከእግዚአብሔር ቸርነት የተነሣ ነው እንጂ እኛ ባለን የተለየ ችሎታ ምክንያት አይደለም። የቁሳቁስ ሀብት አንድን ሰው ትሑት ሊያደርገውና ራሱን ሳይሆን፥ እግዚአብሔርን እንዲያከብር ምክንያት ሊሆነው ይገባል።

«በአሁኑ ዓለም ባለጠጋ» መሆንና በሚቀጥለው ድሃ መሆን ይቻላል (1ኛ ጢሞ. 6፡17)። እንዲሁም በዚህ ምድር ውስጥ ድሃ መሆንና በሚቀጥለው ደግሞ ሀብታም መሆን ይቻላል። ኢየሱስ ስለ ሁለቱም ተናግሯል (ሉቃስ 16፡19-31)፤ ነገር ግን አንድ አማኝ ያለውን እግዚአብሔርን ለማክበር ከተጠቀመበት፥ በዚህ ምድር እና በሚመጣውም ሀብታም ሊሆን ይችላል (ማቴ. 6፡19-34)። በእርግጥ በዚህ ምድር ድሀ የሆነ ሰው ያለውን የተወሰነ ነገር እግዚአብሔርን ለማክበር ሊጠቀምበትና በሚቀጥለው ዓለም ትልቅ ሽልማት ሊያገኝ ይችላል።

ለ. በገንዘብ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ታመን (1ኛ ጢሞ. 6፡17)፡- በጌታችን ምሳሌ ውስጥ ያለው ሀብታሙ ገበሬ (ሉቃስ 12፡13-21) ሀብቱ መመኪያው እንደሆነ አሰበ፤ ነገር ግን ሀብቱ መመኪያው ሊሆን እንደማይችል የሚያስረዳ ፍንጭ ነበር። ለጥቃት የሚያመለክት ነበር። በትክክል በእግዚአብሔር አይታመንም ነበር። ሀብት በጠቀሜታው (ባለማቋረጥ በመለዋወጡ) ብቻ ሳይሆን፥ በዘለቄታውም የሚተማመኑበት አይደለም። ሌቦች ሀብትን ሊሰርቁት ይችላሉ፤ መዋዕለ ነዋይ ዋጋው ሊቀንስ ይችላል፤ እንዲሁም ከጊዜ ብዛት ቤትና መኪና ያረጃሉ። እግዚአብሔር ሀብትን ከሰጠን፥ ልንታመንበት የሚገባው በሰጪው እንጂ፥ በስጦታው ላይ አይደለም።

ሐ. እግዚአብሔር በሰጠህ ነገር ተደሰት (1ኛ ጢሞ. 6፡17)፡- አዎን ደስታ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል። በርግጥ የመክብብ ተደጋጋሚ ዋና አሳብ፥ «የሕይወትን በረከት ዛሬ ተደሰት ምክንያቱም ሕይወት አንድ ቀን ያበቃል» የሚል ነው (2፡24፤ 3፡12-15፥ 22፤ 5፡18-20፤ 9፡7-10፤ 11፡9-10)። ይህ ለምኞት ብቻ የሚኖሩበት የኃጢአት ሕይወት አይደለም፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር የሰጠን ነገር ሁሉ ለክብሩ መደሰት ነው።

መ. እግዚአብሔር በሚሰጥህ ነገር ተጠቀምበት (1ኛ ጢሞ. 6፡18-19)፡- ሀብታችንን ለሌሎች መልካም ለማድረግ ልንጠቀምበት ያስፈልጋል፤ ማካፈልና ገንዘባችንን ሥራ ላይ ማዋል አለብን። ይህን በምናደርግበት ጊዜ፥ ራሳችንን በመንፈሳዊ መንገድ እንገነባለን፤ እንዲሁም ለወደፊቱ መዋዕለ ንዋይ እናተርፋለን (ሉቃስ 16፡1-13 ተመልከት)። «እውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ» (1ኛ ጢሞ. 6፡19) የሚለው እነዚህ ሰዎች እንዳልዳኑ አያመለክትም። ባለ ጠግነት አንድን ሰው ጥራዝ-ነጠቅ ምኞት ወዳለበት የይምሰል ዓለም ሊስበው ይችላል፤ ነገር ግን ባለጠግነት ላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሲጨመር አንድን ሰው ወደ እውነተኛ ሕይወትና ወደ ጽኑ አገልግሎት ይመራዋል።

የጳውሎስ የመጨረሻ ዓረፍተ ነገር ለጢሞቴዎስ ብቻ አልነበረም። ምክንያቱም ተውላጠ ስሙ ብዙ ቁጥር ስለሆነ ነው፡- «ጸጋ ከሁላችሁ ጋራ ይሁን»። ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ በሚጽፍበት ጊዜ ጢሞቴዎስን ብቻ ሳይሆን፥ ጠቅላላው ቤተ ክርስቲያንና ሽማግሌዎቹን እያሰበ ነበር። እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪ ጢሞቴዎስ የሐዋርያውን ቃል መጠበቅ

ያስፈልገው ነበር፤ ነገር ግን ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላትም የመስማትና የመታዘዝ ኃላፊነት ነበረባቸው። እንዲሁ ዛሬ እኛም ኃላፊነት አለብን።

የቲቶ መልእክት አስተዋጽኦ

ዋና አሳብ፡- ክርስቲያኖች መልካምን ሥራ በማድረግ መቀጠል አለባቸው (3፡8)።

1. የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ምዕራፍ 1
    1.1. የእግዚአብሔርን ቃል ስበክ (1፡1-4)
    1.2. ችሎታ ያላቸውን መሪዎች ሹም (1፡5-9)
    1.3. ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ዝም አሰኝ (1፡10-16)
2. የክርስቲያን ግዴታ ምዕራፍ 2-3
    2.1. በዕድሜ የገፉ ቅዱሳን (2፡1-4)
    2.2. ወጣት ቅዱሳን (2፡4-8)
    2.3. ክርስቲያን ባሮች (2፡9-15)
    2.4. ክርስቲያኖች እንደ ዜጎች (3፡1-8)
    2.5. ችግር የሚፈጥሩ ሰዎች (3፡9-11)
    2.6. ማጠቃለያ (3፡12-15)

የእኛ ሰው በቀርጤስ

ቲቶ 1

ጢሞቴዎስ በኤፌሶን ከተማ በሚሠራበት ጊዜ ቲቶ በቀርጤስ ደሴት ላይ በሥራ ተወጥሮ ነበር። ቲቶ በቆሮንቶስ ውስጥ ባለች ቤተ ክርስቲያን ልዩ ሥራ ተሰጥቶት ጳውሎስን በሚገባ ያገለገለ ግሪካዊ አማኝ ነበር (ገላትያ 2፡3፤ 2ኛ ቆሮ. 7፡13-14፤ 8፡6፥ 16፥23፤ 12፡18)። እንደ ጢሞቴዎስ ሁሉ (1ኛ ጢሞ. 1፡2)፥ ቲቶም ወደ ክርስቶስ የተማረከው በጳውሎስ የግል አገልግሎት ውስጥ ይመስላል (ቲቶ 1፡4)። ጳውሎስ ሲጽፍ «ስለ ቲቶ ማወቅ ቢያስፈልግ፥ እናንተን ለመርዳት አብሮኝ የሚሠራ ባልንጀራዬ ነው» ብሏል (2ኛ ቆሮ. 8፡23)።

ነገር ግን በቀርጤስ ደሴት የሚኖሩት ሰዎች አብሮ ለመሥራት የተመቹ አልነበሩም፤ ስለዚህም ቲቶ ተስፋ የመቁረጥ አዝማሚያ ይታይበት ጀመር። ልክ እንደ ጢሞቴዎስ፥ እርሱም ወጣት ሳይሆን አይቀርም፤ ነገር ግን ከጢሞቴዎስ በተቃራኒ፥ ለዓይናፋርነትና ለአካላዊ ሕመም የተጋለጠ አልነበረም። ጳውሎስ ከቲቶ ጋራ በቀርጤስ ነበር። በመሆኑም ያልተስተካከሉትን ነገሮች እንዲያርም ቲቶን በዚያ ተወው። በጴንጠቆስጤ ቀን ከቀርጤስ የመጡ አይሁዶች ስለነበሩ (የሐዋ. 2፡11)፥ ወንጌልን ወደ ትውልድ አገራቸው ያደረሱት እነርሱ ሊሆኑ ይችላሉ።

ቲቶ የሚጋፈጣቸው ብዙ ችግሮች ነበሩት። ቤተ ክርስቲያናቱ ብቁ የሆኑ መሪዎች ያስፈልጓቸው ነበር፤ እንዲሁም በየቤተ ክርስቲያናቱ ያሉት የተለያዩ ቡድኖች እረኛ ያስፈልጋቸው ነበር። አንዱ የስሕተት አስተማሪዎች ቡድን የአይሁድን ሕግ ከጸጋ ወንጌል ጋራ ለማደባለቅ ይሞክር ነበረ (ቲቶ 1፡10፥ 14)፤ አንዳንድ የአሕዛብ ወገን አማኞች ደግሞ የጸጋን መልእክት በማበላሸት ወደ ልቅነት በመምራት ለውጠውት ነበር (2፡11-15)። በተፈጥሮአቸው የቀርጤስ ሰዎች አብሯቸው ለሚሠራ ሰው የሚመቹ አልነበሩም (1፡12-13)፤ በመሆኑም ቲቶ ከመጠን ያለፈ ትዕግስትና ፍቅር ያስፈልገው ነበር። ቲቶ «ወደ ሌላ ቦታ ሂድ የሚል የእግዚአብሔርን ጥሪ ቢሰማ» ይሻለው ነበር፤ ነገር ግን ተጋፈጠውና ሥራውን አጠናቀቀ።

ይህንን ደብዳቤ በምታነቡበትና በምታጠኑበት ጊዜ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የጻፈው የመጀመሪያው ደብዳቤ በአጭሩ ማጠቃለያ ፍሬ አሳብ እንደሆነ ትረዳላችሁ። በዚህ በመጀመሪያው ምዕራፍ፥ ጳውሎስ ቲቶ ሊያሟላቸው ስለሚያስፈልጉ ሦስት ኃላፊነቶች ያሳስበዋል።

1) የእግዚአብሔርን ቃል ስበክ (ቲቶ 1፡1-4)

በዚህ ረጅም ሰላምታ፥ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ቃል አስፈላጊነት ላይ ያተኩራል። «ካታ» የሚለውን የግሪክ ቋንቋ መስተዋድድ አራት ጊዜ ተጠቅሟል። የቃሉም ትርጉም «በታች» የሚል ነው፤ ነገር ግን በዚህ ዓውደ-ምንባብ (ካታ) በአገልግሎትና በእግዚአብሔር ቃል መካከል ያለውን ግንኙነት እንድናይ ይረዳናል። አራቱን ሐረጎች ተመልከቱ፡-

ሀ. «በእግዚአብሔር ለተመረጡት እምነት እንዲሆንላቸው» (ቲቶ 1፡1)፡- የጳውሎስ አገልግሎት በእግዚአብሔር ቃል የተገዛ ነበር። እርሱ «የእግዚአብሔር ባርያ» ነበረ (ጳውሎስ ይህንን ሐረግ የተጠቀመው በዚህ ቦታ ብቻ ነው)፥ እንዲሁም ከኢየሱስ ክርስቶስ «ለተለየ ተልእኮ የተላከ መልእክተኛ» ነበር፤ ነገር ግን የአገልግሎቱ ዓላማ እምነቱን ማካፈል ነው። የዚህም እውነት አካል በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ይገኛል። «በእግዚአብሔር የተመረጡት» ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው የታመኑበት ናቸው (1ኛ ጴጥ. 1፡1-5፤ ኤፌ. 1፡4)።

ለ. «እንደ አምልኮት ያለው እውነት» (ቲቶ 1፡13)፡- ቃሉ ራሱ በቀጥታ የተጠቀሰው አንድ ጊዜ ብቻ ቢሆንም፥ ልክ በ1ኛ ጢሞቴዎስ ውስጥ እንደነበረው፥ «እግዚአብሔርን መምሰል» በዚህም ደብዳቤ ውስጥ «መልካም ሥራ» የሚለው ቃል በጣም አስፈላጊ ጽንሰ-አሳብ ነው። መደጋገሙ ነጥቡን ያጎለዋል (ቲቶ 1፡16፤ 2፡7፥ 14፤ 3፡1፥ 5፥ 8፥ 14)። የወንጌሉ እውነት ሕይወትን እግዚአብሔርን ካለመምሰል (2፡12) ወደ ተቀደሰ አኗኗር ይለውጣል። የሚያሳዝነው ግን፥ ዛሬ እንደሚታዩ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባላት በቀርጤስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መዳናቸውን በአፋቸው የሚያውጁና፥ ዳሩ ግን የተግባራቸው ፍሬ የከንፈራቸውን ፍሬ የሚያፈርስባቸው ሰዎች ነበሩ (1፡12)።

ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የምንታመንበት እምነት፥ ዛሬ የሚያድነንና ሕይወታችን እግዚአብሔርን እንዲመስል የሚያደርግ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ለወደፊቱም ደግሞ ተስፋን ይሰጠናል (1፡2)።

እግዚአብሔር የተስፋ ቃል ስለሰጠንና ሊዋሽ ስለማይችል፥ ለወደፊቱ ዋስትና አለን (ዘኍልቁ 23፡19 ተመልከቱ)። ሕያው በሆነው በክርስቶስ ስለታመንን፥ ዳግመኛ «ሕያው ወደሆነው ተስፋ» (1ኛ ጴጥሮስ 1፡3) ተወልደናል። አሁን እኛ አማኞች የዘለዓለም ሕይወት አለን (1ኛ ዮሐንስ 5፡11-12፤ ዮሐንስ 3፡16)፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ፥ ከዚህ በሚልቅ ሁኔታ በዘለዓለሙ ሕይወት ሐሴት እናደርጋለን።

ሐ. «መድኃኒታችን እግዚአብሔር እንዳዘዘ» (ቲቶ 1፡3)፡- እግዚአብሔር መልእክቱን በስብከት ውስጥ ይገልጣል። ይህ ቃሉን የማወጅን ድርጊት ማለት ሳይሆን፥ የመልእክቱን ይዘት ማለት ነው። «በስብከት ሞኝነት (የመሰቀሉን ቃል) የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና» (1ኛ ቆሮ. 1፡21)። ይህ የወንጌሉ ቃል ለጳውሎስ አደራ ተሰጥቶት ነበረ (1ኛ ጢሞ. 1፡11 ተመልከቱ)፥ እርሱም ለቲቶ አደራ ሰጠው። ይህ አገልግሎት እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ እንጂ፥ በሰው የተሰጠ አልነበረም (ገላ. 1፡10-12)።

እንደ አንደኛ ጢሞቴዎስ «አዳኝ» የሚለው መጠሪያ በቲቶ ብዙ ጊዜ ተደጋግሟል (1፡3-4፤ 2፡10፥ 13፤ 3፡4፥ 6)። በእግዚአብሔር ስጦታ የተጻፈው ቃል አዳኙን ይገልጣል፤ ምክንያቱም ኃጢአተኞች የሚፈልጉት አዳኝን ነው። የእግዚአብሔር ጸጋ ደኅንነትን እንጂ፥ ኩነኔን አያመጣም (2፡11)። ኢየሱስ ወደ ምድር እንደ ፈራጅ ሆኖ ሊመጣ ይችል ነበር፤ ነገር ግን እንደ አዳኝ ሆኖ መምጣቱን መረጠ (ሉቃስ 2፡10-11)።

መ. በሃይማኖት ኅብረት (ቲቶ 1፡4)፡- ኅብረት የሚለው ቃል የጋራ ማለት ነው። ይህ እምነት የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ የጋራ ንብረት እንጂ፥ ጥቂት የተመረጡ ወገኖች ብቻ የሚታደሉት አይደለም። በተለያዩ የእምነት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖች የተለያዩ መለያዎች ይኖራቸው ይሆናል፤ ነገር ግን አንዱን የሚያድነውን እምነት የያዙት ሁሉ «የጋራ ደኅንነትን» (ይሁዳ 3) ይካፈላሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተቀመጠ የተወሰነ የእውነት አካል አለ፡- «ለቅዱሳን ሁሉ አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠው እምነት» (ይሁዳ 3) ከዚህ «የጋራ እምነት» የወጣ ማንኛውም ትምህርት፥ የሰሕተት ትምህርት ነው። በመሆኑም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በትዕግሥት አይታለፍም።

እነዚህን አራት ዐረፍተ ነገሮች እንደገና በምትመለከቱበት ጊዜ ጳውሎስ በአገልግሎቱ ውስጥ ያለውን ነገር በሙሉ ከእግዚአብሔር ቃል ጋራ እንዳዛመደው መመልከት ትችላላችሁ። የርሱ ጥሪና ስብከት በክርስቶስ ባለ እምነት ላይ የተደገፈ ነበር። ቲቶ ይህንን እውነት እንዲጨብጥና የእግዚአብሔርን ቃል የአገልግሎቱ መጀመሪያ እንዲያደርግ ይፈልግ ነበር። በሦስቱም የመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ላይ ትኩረት ተሰጥቷል። የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የእግዚአብሔር ቃል በዘዴና በተግባር የሚሰጥባቸው «የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች» መሆን ይኖርባቸዋል።

2. ብቁ የሆኑ መሪዎችን መሾም (ቲቶ 1፡5-9)

ጳውሎስ ቲቶን በቀርጤስ ደሴት ላይ የተወበት አንዱ ምክንያት፥ አጥቢያ ጉባኤዎችን እንዲያደራጅና የሚጎድላቸውን ነገር «እንዲያስተካክል» ነበር። ይህ ሐረግ የሕክምና አነጋገር ነው፤ የተጣመመ እጅ ስለማስተካከል የሚያገለግል ነበር። ቲቶ የደሴቲቱ መንፈሳዊ አምባገነን አልነበረም፤ ነገር ግን እርሱ ለመሥራት ሥልጣን የነበረው የጳውሎስ ሕጋዊ፥ ሐዋርያዊ ወኪል ነበር። በመሠረታቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሽማግሌዎችን መሾም የጳውሎስ መመሪያ ነበር (የሐዋ. 14፡23)፤ ነገር ግን ይህንን ተግባር ለመፈጸም በቀርጤስ ብዙ ሊቆይ አልቻለም ነበር።

እዚህም የተዘረዘሩትን ብዙዎቹን መመዘኛዎች (ቲቶ 1፡6-8) ማለትም «የማይነቀፍ፥ የአንዲት ሚስት ባል የሚሆን፥ ... የማይሰክር፥ የማይጨቃጨቅ፥ ነውረኛ ረብ የማይወድ ... እንግዳ ተቀባይ ... ጠንቃቃ» በ1ኛ ጢሞ. 3፡2-3 ጥናታችን ላይ ተነጋግረንባቸዋል። እነዚህ መለኪያዎች በቀርጤስ ደሴት ላሉ ክርስቲያኖችና በኤፌሶንም ከተማ ላሉት የመቅረባቸው እውነት የሚያረጋግጥልን፥ እግዚአብሔር ለመሪዎች የሚሰጠው መለኪያ የማይለዋወጥ መሆኑን ነው። የታላቅ ከተማ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ የትንሽ ከተማ ቤተ ክርስቲያን ሁለቱም በመሪነት ቦታዎች ውስጥ እግዚአብሔርን የሚመስሉ ሰዎች ይፈልጋሉ።

አሁን፥ ዘጠኝ ተጨማሪ መመዘኛዎችን እንመልከት፡-

ሀ. «የሚያምኑ ልጆች ያሉት» (ቲቶ 1፡6)፡- «የሚያምን» ማለት «ታማኝ» ማለት ነው። የኤጲስ ቆጶስ (የጳጳሳት) ልጆች ክርስቲያኖች መሆን አለባቸው። ለነገሩ፥ የእግዚአብሔር አገልጋይ የራሱን ልጆች ወደ ክርስቶስ ማምጣት ካልቻለ፥ በውጪ ካሉት ምን መሳካት

ሊጠብቅ ይችላል? ይህ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስም በአትኩሮት የገለጸለት ይህንኑ መመሪያ ነው (1ኛ ጢሞ. 3፡5)፡- ክርስቲያናዊ አኗኗርና ክርስቲያናዊ አገልግሎት በቤት መጀመር አለባቸው። በቤተ ክርስቲያን በሽማግሌ ቤት ውስጥ የሚገኙ ልጆች መዳን ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን የመታዘዝና ሕይወትን የመስጠት መልካም ምሳሌዎች መሆን አለባቸው። የእነርሱ በ «ሁከት» (ከቁጥጥር ውጪ መኖር) ወይም ባለመታዘዝ («የማይገዛ» መገዛት የማይችል) መከሰስ፥ አባታቸው ለመሪነት ብቁ እንዳይሆን ያደርገዋል። እርግጥ ይህ የሚመለከተው ገና በአባታቸው ቁጥጥር ሥር ያሉትን ልጆች ነው።

ብዙ ጊዜ አዳዲስ ክርስቲያኖች የአገልግሎት ጥሪ ይሰማቸውና፥ የቤተሰባቸውን መንፈሳዊ ሕይወት ከማስተካከላቸው በፊት፥ ለመሾም ይፈልጋሉ። ልጆቹ ትንንሾች ከሆኑ ችግሩ እምብዛም አይከብድም፤ ነገር ግን ያደጉ ልጆች በድንገት ቤተሰባቸው «ሃይማኖተኛ» በሚሆንበት ጊዜ በከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ይወድቃሉ! ጥበበኛ አባት ቤተሰቡን በማስገደድ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከመውሰዱ በፊት፥ በመጀመሪያ ልጆቹን ወደ ክርስቶስ ይማርክና እንዲያድጉ ጊዜ ይሰጣቸዋል። ብዙውን ጊዜ እነዚህን መመሪያዎች ተከትለን ቢሆን ኖሮ በአገልግሎት ውስጥ ብዙ የተጎዱ የቤተሰብ መሪዎች አይኖሩንም ነበር።

ለ. «እንደ እግዚአብሔር ባለ አደራ» (ቲቶ 1፡7)፡- ባለ አደራ የራሱ የሆነ ነገር የለውም፤ ነገር ግን ጌታው በእጁ ያደረገለትን ሁሉ ያስተዳድራል። ምናልባት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታዋቂው ባለ አደራ በጲጥፋራ ቤት ሥራ ሁሉ ሥልጣን የነበረው ዮሴፍ ነው (ዘፍጥረት 39፡1-9)። ለአንድ ባለ አደራ እጅግ አስፈላጊው ባሕርይ ታማኝነት ነው (1ኛ ቆሮ. 4፡1-2፤ ማቴ. 25፡21)። ጌታው የሚሰጠውን ነገር ሁሉ ለራሱ የግል ፍላጎት ከማዋል ይልቅ፥ ለጌታው በጎነትና ክብር መጠቀም አለበት (ሉቃስ 16፡1-13 ተመልከት)።

ሽማግሌው «ይህ የኔ ነው!» በፍጹም ማለት የለበትም። እርሱ ያለው ነገር ሁሉ የመጣው ከእግዚአብሔር ስለሆነ (ዮሐንስ 3፡27)፥ ለእግዚአብሔር ጥቅም መዋል አለበት። ጊዜው፥ ንብረቱ፥ ፍላጎቱ፥ እና ችሎታው ሁሉም ከጌታ የተሰጡት ስለሆኑ፥ እግዚአብሔርን ለማክበርና ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት በታማኝነት ሊጠቅመባቸው ይገባል።

በመሠረቱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብቻ ሳይሆን፥ ክርስቲያኖች ሁሉ ታማኝ ባለ አደርዎች ሊሆኑ ይገባል።

ሐ. የግይኮራ (ቲቶ 1፡7)፡- ሽማግሌ የራሱን መንገድ ለማበጀት የሚጋፋ «አምባገነን» መሆን የለበትም። የቤተ ክርስቲያን አባላት የሽማግሌዎቹን መሪነት ማክበርና መከተል ሲኖርባቸው፥ መሪነት እንጂ አምባገነንነት እንዳልሆነ ማረጋገጥ አለባቸው። የራሱን ፈቃድ የሚከተል መጋቢ፥ የሕዝቦቹን ገንቢ አሳቦችና ሂሶችን የማይቀበልና ሁልጊዜም የራሱን መንገድ የሚያዘጋጅ እብሪተኛ ነው።

መ. የማይቆጣ (ቲቶ 1፡7)፡- ቶሎ ኩፍ የሚል ዓመል ሊኖረው አይገባም። በጋጢአት ላይ የሚሰነዘር የጽድቅ ቁጣ አለ (ኤፌሶን 4፡26)፤ ነገር ግን አብዛኛው ቁጣችን ከጽድቅ የራቀና ሰዎችን ለማጥቃት የሚሰነዘር ነው። ቁጣ በራሱ መልካም ነገር ነው። ጻድቅ ሰው ስሕተት በሚሠራበት ጊዜ መቆጣት ይኖርበታል። አንድ ሰው እንዲህ ብሏል «ቁጣ በጣም ድንቅ ነገር ከመሆኑ የተነሳ እርሱን ማጣት ያሳፍራል»። ይህ በእርግጥም የጠቢብ ምክር ነው።

ሠ. በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ (ቲቶ 1፡8)፡- «መልካም የሆነውን የሚወድ ሰው» የሚለው አማራጭ ትርጉም ነው፤ ይህም መልካም ሰዎችን ይጨምራል፤ ነገር ግን መልካም መጻሕፍትን፥ መልካም ሙዚቃን፥ መልካም ምክንያቶችን እንዲሁም ሌሎች ብዙ መልካም ነገሮችንም ይጨምራል። አንድ ሰው መልካም የሚሆነው መልካም ልብ ስላለውና ራሱን በመልካም ነገሮች ስለሚከብ ነው። ራሱን የሰጠ የእግዚአብሔር አገልጋይ እያወቀ ለራሱና ለቤተሰቡ መጥፎ ከሆኑ ነገሮች ጋራ ራሱን ያዛምዳል ማለት ለማመን የሚያዳግት ነው።

ረ. ጻድቅ (ቲቶ 1፡8)፡- «ትክክለኛ» የሚለው ጥሩ ትርጉም ነው። በቃሉ የሚጸናና የሚሰብከውን የሚኖር ታማኝ ሰው መሆን አለበት። የእርሱ ጠባይ ትክክለኛና ጻድቅ ሆኖ መመላለስ ነው።

ሰ. «ቅዱስ» (ቲቶ 1፡8)፡- «የማይነቀፍ» የሚለው ቃል አሳቡን ይሰጠናል «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ» (1ኛ ጴጥሮስ 1፡16)። «የቅዱስ» መሠረታዊ ትርጉሙ «የተለየ» ነው። ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት አዲስ ፍጥረታት ስለሆኑ፥ ከጠፉት ጋጢአተኞች የተለዩ ናቸው (2ኛ ቆሮ. 5፡17)።

ሸ. ራሱን የሚገዛ (ቲቶ 1፡8)፡- ትርጉሙ «ራሱን የሚቆጣጠር» የሚል ሲሆን፥ የሰውን ምኞት ድርጊትን ይመለከታል። «ሥርዓት ያለው»

የሚለው ለዚህ ቃል ተመሳሳዩ ነው። አንድ መጋቢ ሥራውን እንዲሠራ ሰዓቱን በሥርዓት መጠቀም አለበት። በተለይ ልበ ቅን አባላት ቡናና ኬክ በሚያንበሸብሹለት ወቅት ፍላጎቶቹን መግዛት አለበት፤ አሳቡንና ሥጋውን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ማስገዛት አለበት (ገላ 5፡23)።

ቀ. በታመነ ቃል የሚጸና (ቲቶ 1፡9)፡- ታማኝ የሚለው ቃል ለጳውሎስ ተወዳጅ ቃል ነበረ (1ኛ ጢሞ. 1፡15፤ 4፡9፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡11፤ ቲቶ 3፡8)። እግዚአብሔር ሊዋሽ ስለማይችል፥ የእግዚአብሔር ቃል ልንታመንበት የሚገባ ነው (ቲቶ 1፡2)። ቃሉ ታማኝ ስለሆነ፥ ቃሉን የሚያስተምሩትና የሚሰብኩት ሰዎች ታማኝ መሆን ይኖርባቸዋል። እንደገና ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ (1፡10) ውስጥ ባገኘነው ደኅና ትምህርት በሚለው ቃል ይጠቀማል። ይህ መንፈሳዊ ዕድገትን የሚያፋጥን ጤናማ ትምህርት ማለት ነው።

ስለዚህ ሽማግሌዎቹ ጣምራ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል አገልግሎት አላቸው፡- 1) ቤተ ክርስቲያንን በ «ጤናማ» ትምህርት መገንባት፥ እና 2) ጤናማ ያልሆነ ትምህርት የሚያስፋፉትን የሐሰት አስተማሪዎች በመቃወም ማስተማር ነው። «ትምህርት እኛ አንፈልግም፤ ለጥሞና የሚረዱን አሳቦችን ብቻ ስጡን» የሚለው ተላላ አባል ምን እንደሚል የማያውቅ ነው። ከእውነት (ማለትም ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት) ውጪ መንፈሳዊ ዕርዳታም ሆነ ጤና ሊኖር አይችልም።

እውነተኛውን ትምህርት የሚቃወሙትን መጥቀሱ፥ ጳውሎስን ቲቶ ማሟላት ስለነበረበት ሦስተኛ ኃላፊነት እንዲናገር ገፋፋው፡-

3. ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ጸጥ ማሰኘት (ቲቶ 1፡10-16)

በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሐሰት አስተማሪዎች ለመነሣት ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም ነበር። እግዚአብሔር እውነትን በሚዘራበት ቦታ ሁሉ፥ ሰይጣን ውሸትን ለመዝራት ብቅ ይላል። ቲቶ በ1ኛ ጢሞቴዎስ ከተብራራው ጋር የሚመሳሰል ጠላት ገጥሞት ነበር። ይኸውም የአይሁድ ሕግ-አጥባቂነት፥ ሰው ሰራሽ ልማዶች እና አፈ ታሪኮች ድብልቅ የሆነ ነበር። ጳውሎስ ስለ እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ሦስት ጭብጦችን ሰጥቷል።

ሀ. በግል ሕይወታቸው ምን ይመስሉ እንደ ነበር። ጳውሎስ ስለ እነርሱ የሚለው መልካም ነገር አልነበረም! እነርሱ የማይገዙ በመሆናቸው፥ ለእግዚአብሔር ቃልም ሆነ ለእግዚአብሔር አገልጋይ ሥልጣን የማይታዘዙ ነበሩ። «ዓመፀኛ» የሚለው ማንነታቸውን በጥሩ ሁኔታ

ይገልጻዋል። ራሳቸውን በሥልጣን ሥር ከማይጥሉ አገልጋዮች ተጠንቀቁ።

ከንቱ ለፍላፊዎች ነበሩ። የተናገሩት ነገር ለጊዜው አድማጮቻቸውን ቢማርካቸውም፥ ይዘት ወይም ተጨባጭ ነገር አልነበረውም። ንግግራቸው ሁሉ ከንቱና ፍሬ የሌለው ነበር። በሥራ ሳይሆን በንግግር የሚቀድማቸው የለም። ለሌሎች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው መንገር ይችላሉ። ራሳቸው ግን አያደርጉትም። በተለይ ቲቶ 1፡16ን አስተውል።

በጣም የሚያሳዝነው፥ በስሕተት ትምህርታቸው ሰዎችን ማሳታቸው ነበር። እውነትን እንዲያስተምሩ ይናገራሉ፤ ነገር ግን የስህተት ሸቃጮች ነበሩ። እነርሱ ራሳቸው በሰይጣን ተታልለው፥ «የማይገባውን እያስተማሩ» (1፡11) ሌሎችን ሰዎች አሳቱ።

እነርሱ ሥጋዊና ዓለማዊ ሰዎች ነበሩ፤ «ውሸተኞች፥ ክፉዎች አራዊት፥ በልተው የማይጠግቡና፥ ሥራ ፈቶች» (1፡12)። እንዴት ያለ ክስ ነው! ለመንፈሳዊ ሕይወት ውብ ነገሮች በመኖር ፈንታ፥ ለራሳቸው ፍላጎቶች ይኖሩ ነበር። የጳውሎስ ቅጽሎች የሚያስገርሙ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች «አውሬዎች» ብቻ ሳይሆኑ፥ ነገር ግን «ክፉ አውሬዎች»፥ በላተኞች ብቻ ሳይሆኑ፥ ነገር ግን «ሥራ ፈት በላተኞች» ነበሩ። እነርሱ ባለዝናዎች እንጂ፥ አገልጋዮች አልነበሩም። በተከታዮቻቸው ወጪ የደስታ ኑሮ ይኖራሉ። (ለሰው አመለካከት ትክክል ስለሚመስል ተከታዮቻቸው ያከብሩዋቸዋል።)

ጳውሎስ በቁጥር 16 ላይ ባሕርያቸውን አጠቃልሎታል። እነርሱ «የሚያስጸይፉ» ነበሩ። ይህም ማለት «ለዛ የሌላቸው፥ የሚያስጠሉ» ማለት ነው። መልካም መንፈሳዊ ባሕርይ ያላቸው ክርስቲያኖች የነዚህን መምህራን ባሕርይና ጠባይ ሙሉ ለሙሉ ስለሚጠየፉ፥ በፍጹም ሊከተሏቸው አይችሉም ነበር። «የማይታዘዙ» ማለት «እነርሱን ለማሳመን በሚደረገው ጥረት ለማመን ፍላጎቱም ዝግጅቱም የሌላቸው» ማለት ነው። አእምሮአቸው ቀድሞውኑ የተሞላ ስለሆነ፥ እውነትን አይጋፈጡም። «ለበጎ ሥራ የማይበቁ» ማለት በቀጥታ ሲተረጎም «ፈተናውን ማለፍ ያልቻለ» ማለት ነው። የማይበቁ መሆናቸው ስለተረጋገጠ፥ እግዚአብሔር አይጠቀምባቸውም። ይኸው ራሱ የግሪክ ቃል በ1ኛ ቆሮንቶስ 9፡27 ላይ «የተጣለ» ተብሎ ተተርጉሟል። በዚያ ስፍራ በሯጭ ጽንሰ አሳብ «ከጨዋታ ውጪ» ማለት ነው።

ጳውሎስ እነዚህ መምህራን ማን እንደሆኑ ካስረዳ በኋላ፥ ሁለተኛውን አሳብ ያካፍላል።

ለ. ምን አድርገው እንደነበረ። ሁኔታው ግልጽ ነበር፡- እነዚህ ሐሰተኞች መምህራን ከቤት ወደቤት እየተዘዋወሩ ውሸት በመናገር፥ የሰዎቹን እምነት ይገለብጡ ነበር። ሁሉም ቤተሰቦች ጤናማ ባልሆነ ትምህርታቸው ተበክለው ነበር። አንዱ ነገር፥ ጳውሎስ ያልተቀበልውን የአይሁድን ሕግ-አጥባቂነት («ከተገረዙት ወገን የሚሆኑ» ቲቶ 1፡10 እና 3፡9) ያስተምሩ ነበር። እንዲሁም እነርሱ ከእውነት የራቀ ትርጉም የሚሰጧቸውን (1፡4) የብሉይ ኪዳንን የትውልዶች ታሪክ «የአይሁድን ተረት» (1፡14) ያስተምሩ ነበር።

አንዳንድ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚያወጧቸው ነገሮች ሁልጊዜም ያስደንቁኛል። አንድ ቀን በቺካጎ ሬድዮ ጣቢያ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢትን በስልክ ንግግር ሳብራራ ነበር። አንድ ሰው ደወለና ስለ ዳንኤል ትንቢቶች የራሱን እንግዳ ትርጉም በመስጠት፥ ፕሮግራሙን ለመሻማት ሞከረ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰጠውን ግልጽ ማብራሪያ ወደ ጎን በመተው የልቡን አሳብ ይናገር ጀመር። እኔም ከእውነት የራቀውን ይህን አሳብ በተቃወምሁ ጊዜ፥ በጣም ተቀየመኝ።

ዶክተር ዴቪድ ኩፐር እንዲህ ይሉ ነበር፡- «የቅዱሳት መጻሕፍት አሳብ መልካም መዓዛ የሚሰጥ ከሆነ፥ ሌላ ጣዕም አትፈልግ»። ግልጽ ለሆኑት ለእግዚአብሔር ቃል ትምህርቶች ሌላ «ጥልቅ ትርጉም» መፈለግ አስፈላጊ አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ አቀራረብ አጥኚው የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር እንዲያገኝ ያስችለዋል።

የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ብዙውን ጊዜ በግል ቤቶች ስለሚሰበሰቡ «ቤቶች በሙሉ» (ቲቶ 1፡11) እንዴት በሐሰተኛ አስተማሪዎች እንደታወኩ ለማስተዋል ቀላል ነው። ዛሬ በቤታቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚያካሄዱ ሰዎች እንግዶች እንግዳ ትምህርቶች ይዘው እንዳይመጡ መጠንቀቅ አለባቸው። እነዚህን ክፍለ ጊዜዎች የሚከታተሉ የሐሰት ትምህርቶችና ቡድኖች አሉ። ስለሆነም የተለወጡትን ለመሳብ ወኪሎቻቸውን ስለሚልኩ መጠንቀቅ አለብን።

ሐ. ለምን እንዳደረጉት፡- ዋናው ዓላማቸው «ለነውረኛ ረብ» (1፡11) ገንዘብ መሰብሰብ ነው። እነርሱ ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ አልነበሩም፤ ነገር ግን ሃይማኖትን የራሳቸውን ኪስ ለመሙላት ይጠቀሙበት ነበር። ይህ ጳውሎስ «ነውረኛ ረብ የማይወድ» የሚለው አንድን ሽማግሌ ለመመረጥ ከሚያበቁ ነጥቦች እንደ አንዱ

አድርጎ ያቀረበበትን ምክንያት ያስረዳል። እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ ለግል ጥቅሙ አያገለግልም፤ እርሱ ሌሎች በእምነት እንዲያድጉ ለመርዳት ያገለግላል።

ነገር ግን ከዚህ ምኞት ጀርባ ሌላ ችግር ነበር፡- የእነርሱ አእምሮና ሕሊና ረክሶ ነበር (1፡15)። ይህ አንድ ሰው ሁለት ዓይነት ኑሮ ሲኖር የሚሆነው ነው። በውጪ አክብሮትን ይሻል፤ በውስጡ ግን እየተበላሸ ይሄዳል። ማንም ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል አይችልም። እነዚህ አላዋቂ ገንዘብን መውደዳቸው፥ የስሕተት ትምህርት እንዲያስተምሩና የሐሰት ኑሮ እንዲኖሩ አደረጋቸው። ውጤቱም ስለ ኃጢአታቸው የማይወቅሳቸውን የረከሰ ሕሊና መያዝ ነበር። ይህ ጳውሎስ ወደ ጻፈው «የደነዘዘ ኅሊና» አንድ ርምጃ መጠጋት ነው (1ኛ ጢሞ. 4፡2)።

ቲቶ 1፡15 አንዳንድ ያስተማሩ ሰዎች ክፉ ሥራቸውን ለመደገፍ ከሚጠቀሙባቸው ጥቅሶች አንዱ ነው። «ለንጹሐት ሁሉ ንጹሕ ነው» የሚለው፥ ለኃጢአት ሁሉ የሚሰጥ ማመካኛ ነው። ለምሳሌ አንድን ታዳጊ ወጣት አስታውሳለሁ። ስለሚያነበው መጥፎ የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት ሳስጠነቅቀው፥ የእርሱ መከላከያ «ውበት በተመልካቹ ዓይን ውስጥ ነው። እኔ በማነብበው ውስጥ ኃጢአትን ብታይ የአንተ ልብ ራሱ የቆሸሸ መሆን አለበት፥ ለነገሩ፥ ለንጹሐት፥ ሁሉ ንጹሕ ነው» የሚል ነበር።

በመጀመሪያ ደረጃ፥ ጳውሎስ እነዚህ ሕግ-አጥባቂዎች ምግቦችን በተመለከተ ያላቸውን የተሳሳተ ትምህርት እየተቃወመ ነበር። የአይሁድ የአመጋገብ ሕግጋት ለክርስቲያን አማኞችም ይሠራሉ ብለው ያስተምሩ ነበር (1ኛ ጢሞ. 4፡3-5 ተመልከቱ)። የተከለከለ ምግብ ከበላህ ራስህን ታረክሳለህ፤ ዳሩ ግን ያንን እምቢ ካልህ የበለጠ ቅዱስ ትሆናለህ።

ጳውሎስ «እውነቱ የዚህ ተገላቢጦሽ ነው» በማለት ይሟገታል። እነዚህ አስተማሪዎች የረከሰ አእምሮና ሕሊና አላቸው። ስለዚህ መልካም ምግብ በሚያዩበት ጊዜ፥ ኃጢአት እይታቸውን ስላረከሰባቸው፥ ኃጢአትን ያያሉ፤ ነገር ግን ንጹሕ አእምሮና ኅሊና ያለን እኛ ሁሉም ምግቦች ንጹሐን እንደሆኑ እናውቃለን። አስተማሪዎቹን የሚያረክሷቸው ምግቦቹ አይደሉም፤ ይልቁንም አስተማሪዎቹ ምግቦቹን ያረክሳሉ!»

ነገር ግን ይህ መመሪያ ክፉ መሆናቸውን ለምናውቃቸው ነገሮች ማገልገል የለበትም። ለምሳሌ በታወቁ በታላላቅ ሠዓሊዎች የተሳሉ ሥዕሎችና በወሲብ ሥዕሎች መካከል ያለው ልዩነት «በተመልካቹ ዓይን ውስጥ» ነው ከማለት የራቀ ነው። ታላቅ ሠዓሊ የሰውን አካል ለመሠረታዊ ጥቅሙ አይበዘብዝም። ለአንድ ክርስቲያን የወሲብ ስሜት

ለሚቀሰቅሱ የኃጢአት ልምምዶች ራስን ማጋለጥና፥ «ልቤ ንጹሕ ስለሆነ ንጹሕ ነበርሁ» ማለት፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለኃጢአት ማመካኛ አድርጎ መጠቀም ነው። ጳውሎስ እዚህ ላይ ያመለከተው ለምግብ ስለሆነ፥ እኛም በዚህ መልኩ መጠቀም አለብን።

እነዚህን ሦስት ነጥቦች ስለ እነዚህ የስሕተት አስተማሪዎች ካካፈለ በኋላ፥ ጳውሎስ አንድ ተጨማሪ ጉዳይ ይናገራል።

መ. ቲቶ ምን ማድረግ እንደነበረበት፡- በአጠገባቸው ጸጥ ብሎ በመቆም፥ ድል እስኪያደርጉ ድረስ መጠበቅ የለበትም። መጀመሪያ፥ «ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት» መምከርና ማሳመን ነበረበት (ቲቶ 1፡9)። የሰይጣንን ውሸቶች ለመቃወም ብቸኛው መሣሪያ የእግዚአብሔር እውነት ነው። «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» የሚለው የሁሉም ክርክር መዝጊያ ነው።

ቲቶ አፋቸውን በመዝጋት (1፡11)፥ ከማስተማርና የስሕተት ትምህርታቸውን ከማስፋፋት ማገድ ነበረበት። «በብርቱ ሊወቅሳቸው» (1፡13) ይገባ ነበር። ጳውሎስ ይህንኑ ተመሳሳይ ምክር ለጢሞቴዎስም በመጨረሻው ደብዳቤ ላይ ሰጥቶታል፡- «ፈጽመህ እየታገስህና እያስተማርህ፥ ዝለፍና ገስጽ ምከርም» (2ኛ ጢሞ. 4፡2)።

በመሠረቱ የጳውሎስ ዓላማ እነዚህን አስተማሪዎች ማሳመንና በእምነት ጤናማዎች እንዲሆኑ መርዳት ነበር (ቲቶ 1፡13)፤ ነገር ግን ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ፥ ቤተ ክርስቲያንን ከእነርሱ የስሕተት ትምህርት መጠበቅ አለበት። የሐሰት ትምህርት እንደ እርሾ ነው፡- በምሥጢር ይገባል፡ በፍጥነት ያድጋል፤ ሙሉ በሙሉ ይስፋፋል (ገላትያ 5፡9)። የሐሰት ትምህርትን ለመዋጋት ጥሩው ጊዜ የመስፋፋት ዕድል ከማግኘቱ በፊት ከመጀመሪያው ነው።

የአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን አባላት አመለካከት፡- «አንድ ነገር እስካመንህ ድረስ፥ የምታምነው ነገር ምንነት ልዩነት አያመጣም» የሚል ነው። ጳውሎስ ከእንደዚህ ዓይነቱ ጅል አመለካከት ጋር አይስማማም። የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ወይም ውሸት ማመን በሞትና በሕይወት መካከል ያለውን ልዩነት ያመጣል። ማመን የሚፈልጉትን መምረጥ ይቻላል፤ ነገር ግን በዚያ ምክንያት የሚመጡትን ውጤቶች መለወጥ አይቻልም።

ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል፡- «እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል» (ዮሐንስ 8፡32)።

ጤናማ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊኖረን ይችላል?

ቲቶ 2-3

ከሐሰተኛ አስተማሪዎች በተለየ ሁኔታ፥ ቲቶ «ሕይወት ለሚገኝበት ትምህርት የሚገባውን መናገር» ነበረበት (2፡1 ቀጥተኛ ትርጉም)። ተሐዋስያን ሥጋዊ አካል እንደሚጎዱ፥ የሐሰት ትምህርትም ለመንፈሳዊው አካል ማለትም ለቤተ ክርስቲያን ጠንቅ ነው። ይህንን ክፍል በሚያካትቱ ቁጥሮች ውስጥ፥ በጤናማ ትምህርትና በተግባራዊ ምክሮች መካከል ያለውን ትስስር እንመለከታለን። ይህም ሁለቱ ጎን ለጎን መሄድ ስላለባቸው ነው። ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላሉ ብዙ የተለያዩ የአገልግሎት መስኮች አብራርቷል፡-

1. በዕድሜ የገፉ ቅዱሳን (ቲቶ 2፡1-4)

እንደ ቲቶ ላለው ወጣት ሰው፥ በማኅበረ ምእመናኑ ውስጥ ካለው በዕድሜ ከገፉ አባል ጋር ላለመግባባት ብሎም ጭራሹን ለመዘንጋት በጣም ቀላል ነበር።

አንድ ጊዜ አንድ መጋቢ ራሱም ከዕለታት አንድ ቀን ሽማግሌ እንደሚሆን ዘንግቶት እንዲህ አለኝ፥ «ወጣቶች የሚሰበሰቡበትን ቤተ ክርስቲያን እፈልጋለሁ»። ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌውንም ወጣቱንም ትፈልጋለች። እነርሱም እርስ በርሳቸው ሊገላገሉ ይገባቸዋል። የእግዚአብሔር ጸጋ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የትውልድ ልዩነት ለማገናኘት ያስችለናል። ይህንን ለማድረግ አንደኛው መንገድ፥ ሁሉም አባላት፥ ወጣትና ሽማግሌ፥ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ባዘጋጃቸው መመዘኛዎች መኖር ነው።

ሽማግሌዎች ልከኞች መሆን ነበረባቸው። ይህም ማለት «የወይን ጠጅ በመጠቀም በኩል ልከኞች» መሆን ማለት ነው። ሽማግሌች ጊዜ ስላላቸው፥ በአንድ ብርሌ መጠጥ ብዙ መቆየት ይችሉ ነበር።

ጭምት ማለት «ክብሩን ጠባቂ» ማለት ነው፤ ነገር ግን ፈጽሞ የማይስቅ፥ ጸጥ ያለ ክቡር ሰው ማለት አይደለም። የሽምግልና ዕድሜ አክብሮትን የሚያስገኝ የክብር ምንጭ ነው። ይህም ክብር በዕድሜ ለገፋው ቅዱስ ሰው ሥልጣን ይሰጠዋል። በራሴ የመጋቢነት አገልግሎት ውስጥ ስለረዱኝ የተከበሩ ሰዎች እግዚአብሔርን በጣም አመሰግናለሁ!

ለመናገር በሚቆሙበት ጊዜ፥ መላው ቤተ ክርስቲያን ያዳምጣቸዋል። እንዲሁም በጥንቃቄ ያስተውላል።

«ራሳቸውን የሚገዙ» በሕይወት ወደ ጥንቃቄ እና ራስን ወደ መቆጣጠር የሚመራውን የአእምሮ ዝንባሌ ይገልጻል። በአለማወቅ ላይ የሚመሠረቱት የሞኝነትና የግድ የለሽነት ተቃራኒ ነው። የሕይወትና የዓላማ ጽናት በክርስትና ሕይወት ውስጥ አስፈላጊዎች ናቸው። በተለይም ጊዜያቸው አጭር ለሆነና ጊዜያቸውን ለማጥፋት ለማይችሉ ሽማግሌዎች እነዚህ ነገሮች አስፈላጊዎች ናቸው።

በእምነትና በፍቅር፥ በመጽናትም ጤናሞች፡- እነዚህ ሁሉ አንድ ላይ ይሄዳሉ። ሽማግሌዎቹ የሚያምኑት ምን እንደሆነ ማወቅ አለባቸው፤ እንዲሁም መሠረታዊ እምነታቸው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የተስተካከለ መሆን አለበት። ምክንያቱም የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረታዊ ትምህርት ማወቅ፥ የወንድማማች ፍቅርና በሕይወት ውስጥ በሚያጋጥሙ መከራዎች መታገሥን ለመሳሰሉ አስፈላጊ ምግባሮች ምትክ ስለማይሆን ነው። በእርግጥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያለ ትክክለኛ እምነት አማኙን በፍቅርና በመጽናት ሊያበረታታው ይገባል።

በቁጥር 3 ላይ የሚገኘው «እንዲሁም» የሚለው ቃል፥ አሮጊቶች ሴቶች ከሽማግሌዎቹ ጋራ አንድ ዓይነት መመዘኛዎችና በተጨማሪ የተዘረዙት መስፈርቶች ሊኖራቸው እንደሚገባ ያሳያል። የነዚህ አሮጊቶች ሴቶች ጠባይ (ባሕርይ) ሁልጊዜም ቅድስናን ማንጸባረቅ አለበት። ሐሜትን የሚያስፋፉ (ይህን ቃል የሚተካው የግሪኩ ቃል «ዲያብሎሶች» የሚል ሲሆን፥ ትርጉሙም «ሐሜተኞች» ማለት ነው)። ወሬኞች (በውሸት የሚከሰሱ) መሆን የለባቸውም። በወይን ጠጅ አጠቃቀማቸውም ልከኞች መሆን አለባቸው።

ስለ አሮጊቶች ሴቶች በሚናገርበት ጊዜ የጳውሎስ ትኩረት በማስተማር ላይ ነው፡- «የመልካም ነገሮች አስተማሪዎች»። ልምድ ያላቸው እግዚአብሔርን የሚመስሉ ሴቶች ብዙ ጊዜ እጅግ በጣም ጥሩ አስተማሪዎች ናቸው። በ2፡4 ላይ ያለው «አስተምር» የሚለው ቃል በቁጥር 2 ላይ ራሱን የሚገዛ ከሚለው ቃል ጋር ይዛመዳል። በመሆኑም ምናልባት «ራሱን የሚቆጣጠር አእምሮ በማሠልጠን» ተብሎ መተርጎም አለበት። አሮጊቶች ለወጣት ሴቶች ቤታቸውን እንዴት እንደሚንከባከቡ ማሳየት ብቻ ሳይሆን፥ በልባቸውና በአእምሮአቸው ውስጥ ትክክለኛ የሆነ መንፈሳዊና አእምሮአዊ አመለካከት ማስቀመጥ አለባቸው።

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ ለመንፈሳዊ አገልግሎት አንዱ ታላቅ ኃይል በሽማግሌ አማኞች ራስ ላይ ያርፋል። በጡረታ ላይ ያሉት ለአገልግሎት ጊዜ አላቸው። ብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እነዚህን አስፈላጊ ሰዎች ማደራጀታቸውንና ማንቀሳቀሳቸውን ማየት መልካም ነገር ነው። በራሴ አገልግሎት ውስጥ በዕድሜ ከሚበልጡኝ እንዴት እንደሚጸለይ ከሚያውቁ፥ ቃሉን ከሚያስተምሩ፥ ከሚጎበኙ፥ ችግር ከሚፈቱ፥ የቤተ ክርስቲያንን ግንባታ ከሚረዱ ቅዱሳን ሰዎች በጣም ታግኝለሁ።

2. ወጣት የሆኑ ቅዱሳን (ቲቶ 2፡4-8)

እግዚአብሔርን የሚመስሉ አሮጊቶች ወጣት ሴቶችን እንዴት መልካም ሚስቶች፥ እናቶችና የቤት አስተዳዳሪዎች እንደሚሆኑ የማስተማር ኃላፊነት አለባቸው፤ እንዲሁም ወጣቶቹ ሴቶች የመስማትና የመታዘዝ ኃላፊነት አለባቸው። የክርስቲያን ቤት ከጣዖት አምልኮ ደኅንነት አግኝተው ለተመለሱ ወጣት ሴቶች ሙሉ ለሙሉ አዲስ ልምምድ ስለነበረ፥ ከእነዚህ ፍጹም አዲስ ከሆኑት የሕይወት ተቀዳሚ ሁኔታዎችና መብቶች ጋር መላመድ ነበረባቸው። የማያምኑ ባሎች ያሏቸው ሴቶች የተለየ ማበረታቻ ያስፈልጋቸው ነበር።

በቤት ውስጥ ከሁሉም የሚበልጠው ቀዳሚ ነገር ፍቅር መሆን አለበት። ሚስት ባሏንና ልጆችዋን ከወደደች፥ ጋብቻውንና ቤቷን የተሳካ ለማድረግ በመጣር ላይ ነች ማለት ነው። በምዕራባውያን ማኅበረሰብ ወንድና ሴት በፍቅር ይያያዛሉ። ከዚያም ይጋባሉ፤ ነገር ግን በምሥራቁ ዓለም ጋብቻዎች ከፍቅር ጋር ያላቸው ቁርኝት እምብዛም ነው። ብዙውን ጊዜ ሁለቱ ይጋቡና ከዚያ በኋላ እርስ በርስ መዋደድን መማር ነበረባቸው። (ኤፌሶን 5፡18-33 በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ በእውነት ለመዋደድ ለሚፈልጉ ባልና ሚስት ምናልባት በጣም ጥሩው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው።)

እርግጥ ነው እናት ልጆችዋን ትወዳለች። በመሠረቱ ይህ ከተፈጥሮ የሚመጣ ነው። ዳሩ ግን ይህ በተፈጥሮ የሚገኝ ነገር ቁጥጥር ያስፈልገዋል። አንድ ጊዜ አንዲት «ዘመናዊት እናት» «ልጄን ለመምታት እስከሚሳነኝ ድረስ ከመጠን በላይ እወድዳታለሁ» ስትል ሰማኋት፤ እውነታው ግን እርሷ ለራሷ ሰገብጋባ ፍቅር ብቻ ያላት እንጂ፥ በእውነት ልጇን የምትወድ አልነበረችም። «በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው ልጁን ይጠላል፤ ልጁን የሚወድድ ግን ተግቶ ይገስጸዋል» (ምሳሌ 13፡24)። በምሥራቃውያን ቤተሰብ ብዙውን ጊዜ

ልጆችን የሚቀጣው አባትየው ቢሆንም፥ እናትየው የቅጣቱ ተግባር አካል ከመሆን ማምለጥ አትችልም ነበር፤ ይህም ካልሆነ ልጁ ለከለላ ወደ እናቱ ጉያ ሊሮጥ ይችላል።

«ራሳቸውን የሚገዙ» (ቲቶ 2፡5)፡- ራሱን የሚቆጣጠር አእምሮ የሚለው የተለመደ ቃል ነው። (በቁጥር ሁለት ላይ «ራሳቸውን የሚገዙ» ተብሏል)። አመለካከት የሥራ ውጤትን ይወስናል። በመሆኑም አንድ ሰው በትክክል ከላሰበ፥ በሚገባ ለመሥራት አይችልም። አንዲት ሴት በቤት ውስጥ ለምታከናውነው የቤት አገልግሎት ትክክለኛና የታረመ አመለካከት ያስፈልጋታል። «ራስን መቆጣጠር» የሚለው አሳብ በዚህ ቃል ውስጥ ተጠቃሏል። ወላጆች ራሳቸውን ካላረሙ፥ በፍጹም ልጆቻቸውን ለማረም አይችሉም።

«ንጹሐች» ማለት «ንጹሕ አእምሮና ልብ ያላቸው» ማለት ነው። ክርስቲያን ሚስት ለባልዋ በአእምሮዋ፥ በልብዋ፥ እንዲሁም በሥራዋ ታማኝ ናት።

«በቤት የሚሠሩ»፡- ይህ ቃል ቤትዋ እርሷ ልትጠበቅበት የሚገባ እሥር ቤት እንደሆነ የሚያመለክት አይደለም! አሳቡ «ቤቷን የምትንከባከብ» ማለት ነው። ጳውሎስ ሲጽፍ «ቤቶቻቸውንም ሊያስተዳድሩ» (1ኛ ጢሞ. 5፡14) ብሏል። አስተዋይ የሆነው ባል የቤተሰቡን ጉዳዮች ሚስቱ እንድታስተዳድር ይፈቅዳል፤ ምክንያቱም ይህ የእርሷ አገልግሎት ነው።

በጎዎች (ቲቶ 2፡5)፡- «ደግ» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ቤተሰብዋን በጭካኔ አያያዝ አትመራም፤ ነገር ግን «የርኅራኄ ሕግ» (ምሳሌ 31፡26) ትለማመዳለች።

ሚስት «በቤት ውስጥ በምትሠራበት» ጊዜ፥ በቤት ውስጥ መሪ የሚሆነው ባልየው ነው፤ ስለዚህም ሚስት ታዛዥ መሆን አለባት። ነገር ግን ፍቅር ባለበት ስፍራ (ቲቶ 2፡4)፥ ብዙም የታዛዥነት ችግር የለም። እንዲሁም እግዚአብሔርን የማክበር ፍላጎት ባለበት በዚያ፥ ሊፈታ የማይችል ችግር የለም።

«የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ» የሚለው ቃል በቤት ውስጥ ለመረዳዳትና ለመታዘዝ ጥሩ አነሣሽ ምክንያት ነው። በክርስቲያኖች መካከል የሚፈጸሙ የቤተሰብ ችግሮችና የጋብቻ መፍረስን የመሳሰሉ ነገሮች፥ ያልዳኑ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዲሳለቁ መንገድ የሚከፍትበትን ሁኔታ መመልከት በእጅጉ የሚያሳዝን ክስተት ነው።

ቲቶ ራሱን ከአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለመጠበቅ፥ አሮጊቶች ሴቶች ወጣት ሴቶችን እንዲያገለግሉ መፍቀድ ነበረበት፤ ነገር ግን እርሱም አብሮ ለሚፈረድባቸው ወጣት ወንዶች ምሳሌ መሆን ነበረበት። ምክርና ምሳሌነት እነርሱን በእምነት ለመገንባት የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች መሆን ነበረባቸው (2፡6-7)። ብዙ የኃጢአት ፈተናዎች ስለ ነበሩ፥ ራሳቸውን እንዲቆጣጠሩ መምከር ነበረበት።

ነገር ግን ጳውሎስ ስለ መካሪው ቲቶ ከመጻፍ ይልቅ ስለ አርአያው ቲቶ ብዙ ጽፏል! አንድ መጋቢ በሕይወቱ የበለጠ ይሰብካል። በሁሉም ነገር ሳያቋርጥ መልካም ምሳሌ መሆን አለበት። መጋቢው ቤተ ክርስቲያኑ እንድትሆን የሚፈልገውን ነገር ሁሉ እርሱ ራሱ በመጀመሪያ መሆን አለበት። «እየተናገሩ አያደርጉትምና» (ማቴ. 23፡3) የሚለው ጌታችን ፈሪሳውያንን የከሰሰበት ቃል ነበር። ይህ ግብዝነት ነው።

«ቱፓስ» የሚለው የግሪኩ ቃል «ምሳሌ» የሚለውን ቃል ይሰጠናል (ቲቶ 2፡7)። በመሠረቱ ቃሉ «ማተሚያ መሰል መሣሪያ የሚያወጣው ቅርጽ» ማለት ነው። ቲቶ ሕይወቱ ሌሎችን ለመማረክ እንዲችል፥ «መንፈሳዊ ቀርጽ» ሆኖ መመላለስ ነበረበት። ይህም መልካም ሥራን፥ ጤናማ ትምህርትን፥ ጠንካራ አመለካከትንና ማንም ሰው ጠላትም እንኳን ለመንቀፍ እስከማይችል ድረስ ጤናማ ንግግር ማስተላለፍን የሚያጠቃልል ነበር። ብንወድም ብንጠላም፥ ሁልጊዜ ተቃራኒዎችና ጸብን የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። የአንድ መጋቢ ስብከት ከወቀሳ ውጪ ሆኖ የሚያቆመው ዓይነት መሆን አለበት።

በቤተ ክርስቲያን መጋቢ መሆን ቀላል አይደለም። የሰዓት ፊርማ አትፈርሙም፤ ዳሩ ግን ሁልጊዜ በሥራ ላይ ናችሁ። የምትሰብኩትን ለመለማመድ መጠንቀቅ አለባችሁ፤ ከመድረክ ላይና ከመድረክ ስትወርዱ አንድ ዓይነት ሰው መሆን አለባችሁ። በንግግር ወይም በባሕርይ ግብዝ መሆን የአንድን ሰው አገልግሎት ያበላሸዋል። ማንም የቤተ ክርስቲያን አባል ፍጹም እንዳልሆነ፥ ማንም መጋቢ ፍጹም አይደለም፤ ነገር ግን በጣም ጥሩ ምሳሌ ለመሆን መጣጣር አለበት። ቤተ ክርስቲያን ከመሪዋ በላይ ከፍ ልትል በፍጹም አትችልም።

3. ክርስቲያን ባሮች (ቲቶ 2፡9-15)

ብዙ ጊዜ ጳውሎስ ባሮችን በተመለከተ የሚናገረው ነገር ነበረው (ኤፌሶን 6፡5-9፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡1-2 ተመልከቱ)። ምክንያቱም ጳውሎስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ደኅንነት ከተጻፉት ትላልቅ ዐረፍተ ነገሮች በአንዱ ስላስደገፈው፥ ለቲቶ ስለተጻፈው ስለዚሁ ቃል በጣም

ደስተኞች ነን። ጳውሎስ ሁልጊዜ ትምህርትንና የሥራ ኃላፊነትን ያያይዝ ነበር።

ጳውሎስ እነዚህ ክርስቲያን ባሪያዎች ማስወገድ ስላለባቸው ሦስት የተለመዱ ኃጢአቶች አስጠንቅቋቸዋል (ቲቶ 2:9-10)። በመጀመሪያ፥ ስለ አለመታዘዝ ምክር ሰጥቷል። ክርስቲያን ባሪያዎች ለጌቶቻቸው መታዘዝና እነርሱን ለማስደሰት መሻት ነበረባቸው፤ ይህም ማለት ተጨማሪ ነገር ማድረግ አለባቸው ማለት ነው። «ከልብ» ያልመነጨ ታዛዥነት ማሳየት ይቻል ነበር። (ኤፌሶን 6:6)። ሥራውንም ቢሆን ያለምንም ፈቃደኝነት እያንጎራጎሩ መሥራት ይቻላል። አንዳንድ ያልዳኑ ጌቶች የማያስቡ ይሆኑና ባሪያዎቻቸውን ከልክ በላይ ያሠሯቸው ይሆናል።

ሁለተኛው፥ በኃጢአት ምክንያት ሲገሠጽ ተገቢ ያልሆነ መልስ እንዳይሰጡና «ክፉ ቃል እንዳይመልሱላቸው» (ቲቶ 2:9፥ አዲሱ ትርጉም) ነው። አንድ ባሪያ የተሰጠውን ኃላፊነት እንደተጠበቀው ሳይወጣ ሲቀር ጌታው በጭካኔ ሊቀጣው ስለሚችል መከራከር የለበትም። ምናልባት ጌታው ስለሥራው የሚኖረው ግንዛቤ ከባሪያው ያነሰ ሊሆን ስለሚችል፥ ከጌታው ጋር ለመከራከር ወይንም ስለሌሎች «ብሶት ሊያሰማ» ይችል ይሆናል፤ ሆኖም ግን ይህ ለክርስቲያን ባሪያ ደካማ ምስክርነት ነው።

እንዲሁም ክርስቲያን ባሪያዎች የሰርቆት ኃጢአትንም ማስወገድ ነበረባቸው። ይህ ምናልባት አናሲሞስ በፊሊሞና ላይ የሠራው ኃጢአት ነበር (ፊሊሞና 18 ተመልከት)። ትንንሽ ነገሮችን (ዕቃዎችን) ሰርቆ መሸጥና ከዚያም ተሰብረዋል ወይም ጠፍተዋል ብሎ ለጌታው መናገር ለባሪያ ቀላል ይሆን ይሆናል።

በአሁኑ ጊዜ በጎብረተሰባችን ውስጥ ባሪያዎች የሉም፤ ነገር ግን ተቀጣሪ ሠራተኞች አሉ። ክርስቲያን ሠራተኞች የተቃውሞ ድምፅ ሳያስተጋቡ መታዘዝ አለባቸው። ከአሠሪዎቻቸው መስረቅ የለባቸውም። ከመረቀት ማያያዣ እና እርሳስ ጀምሮ እስከ ቢሮ የጽሕፈት መኪናዎችና ተሽከርካሪዎች ድረስ፥ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር ሠራተኞቻቸው ስለሚሰርቋቸው አሠሪዎች በየዓመቱ ይከስራሉ። «እኔ ነኝ ለዚህ ያደረስኳቸው» የሚለው፥ ወይንም «የኔም ሀብት ጭምር መሆን አለበት» ማለት ምክንያት አይሆንም።

ክርስቲያን ሠራተኞች ለምን መታመን እንደሚገባቸው ጳውሎስ ጥሩ ምክንያት ሰጥቷል (በጎ ታማኝነትን ሁሉ እንዲያሳዩ)፡- ይህ

የእግዚአብሔርን ቃል «በክብር ያስጌጠዋል»። በታማኝነት በምናገለግልበት ጊዜ፥ «መጽሐፍ ቅዱስን እናስውበዋለን»፤ እንዲሁም የክርስትናን መልእክት ለማያምኑ ሰዎች ማራኪ እናደርገዋለን። ጳውሎስ በጢሞቴዎስ ቤተ ክርስቲያን ለሚገኙት ባሪያዎች በጻፈ ጊዜ (1ኛ ጢሞ. 6፡1) «የእግዚአብሔር ስምና ትምህርቱ እንዳይሰደብ» የሚል አሉታዊ አሳብን ነበር የተጠቀመው፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን መልእክት ማራኪ ለማድረግ የሚጠቅመው አዎንታዊ አነሳሽ ምክንያትና የእግዚአብሔርን ትምህርት ከመሰደብ የሚታደገው አሉታዊ አነሳሽ ምክንያት፥ ሕይወታችንን ሊቆጣጠረው ይገባል።

በዚህ ስፍራ (ቲቶ 2፡11) ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ባለን በዚህ ደኅንነት ውስጥ ምን ነገር እንዳለበት በማብራራት (ቁ. 10)፥ «የአዳኝ»ን ትርጉም ገልጾታል። ትኩረቱ ጸጋ ላይ ነው። ይህም ባልተገባቸው ኃጢአተኞች ላይ የተገለጸው የእግዚአብሔር ያልተመጠነ ስጦታ ነው። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ጸጋ፥ ሦስት ድንቅ አገልግሎቶች ጠቅሷል (2፡11-14)፡-

ሀ. ጸጋው ያድናል (ቲቶ 2፡11፥ 14)፡- ሰዎች ራሳቸውን ሊያድኑ አልቻሉም። ለጠፋው የሰው ዘር የእግዚአብሔር ጸጋ ደኅንነትን ማምጣት ነበረበት። ደኅንነቱ በኃጢአተኞች ፍለጋ አልተገኘም፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፥ ሞትና ትንሣኤ በኩል ተገለጠላቸው። በኃጢአት እሥራት ውስጥ ያሉትን ለመቤዠት እግዚአብሔር በጸጋው ልጁን ላከ። ይህ መዳን ለሚቀበሉት ሰዎች ሁሉ ነው (1ኛ ጢሞ. 2፡4-6)። ዓለም-አቀፋዊ ችግር ስለነበረ፥ እግዚአብሔር ለሚያምኑ ሁሉ ዓለም-አቀፋዊ መፍትሔ ሰጠ።

ጳውሎስ ይህንን ደኅንነት በይበልጥ አብራርቷል (ቲቶ 2፡14)። ክርስቶስ «ራሱን ለእኛ ሰጠ»፥ ይህም እርሱ የኛ ምትክ ሆነ ማለት ነው። «እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ» (1ኛ ጴጥ. 2፡24)። መቤዠት የሚለው ቃል «ዋጋ ከፍሎ ነጻ ማውጣት» ማለት ነው። እኛ ሁላችንም የኃጢአት ባሪያዎች ስለ ነበርን (ቲቶ 3፡3)፥ ራሳችንን ነጻ ለማውጣት አንችልም ነበር፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ስለ እኛ ኃጢአት ቤዛ አድርጎ ሰጠ። በእርሱ ሞት የእግዚአብሔርን ቅዱስ ሕግ ጥያቄ አሟላ፤ ስለዚህም በክርስቶስ የሚያምኑትን እግዚአብሔር በጸጋው ይቅር ሊላቸውና ነጻ ሊያደርጋቸው ይችላል።

እኛ ከበደል ሁሉ ነጻ ወጥተናል። ይህም ኃጢአት ሕይወታችንን ሁለተኛ አይገዛም ማለት ነው። (የዚህ ክፍል ዓውደ ምንባብ ጳውሎስ ለባሪያዎች የሰጠው ምክር እንደሆነ አስታውሱ። የ«መቤዠት»ን ትርጉም ያውቁ ነበር)። «ዓመፃ» ማለት «ሕግ-ተላላፊነት» ማለት ነው። ሳንድን በፊት በነበረው ሁኔታችን፥ በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ያመፅን ሰዎች ነበርን፤ ነገር ግን አሁን ያ ሁሉም ተለውጧል። ይህ ጳውሎስን ወደ ሁለተኛው የጸጋ አገልግሎት መራው፡-

ለ) ጸጋው ያድሰናል (ቲቶ 2፡12፥ 14)፡- ደኅንነት ቦታን መለወጥ (ከኃጢአት ባርነት ነጻ መውጣት) ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን የአመለካከት፥ የፍላጎት የስሜት እና የድርጊት ለውጥም ነው። የተቤዠን ያው ጸጋ፥ ሕይወታችንን በማደስ፥ እግዚአብሔርን የምንመስል ሰዎች ያደርገናል። «ማስተማር» ሥርዓት የማስያዝ አሳብ አለው። እርሱን የሚያስከብሩ ሰዎች እንድንሆን፥ በእግዚአብሔር ጸጋ እንሠለጥናለን፤ ሥርዓት እንይዛለን።

እግዚአብሔርን የሚመስል ሕይወት አሉታዊውንና አዎንታዊውንም ያካትታል። «እግዚአብሔርን አለመምሰልና (እግዚአብሔርን የማይመስል ሁሉ) ዓለማዊ ምኞትን» እንክዳለን (1ኛ ዮሐንስ 2፡15-17 ተመልከቱ)። ግሱ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንተወዋለን ማለት ነው። ያለቀ ጉዳይ ነው። ከዚያም በአዎንታዊው ላይ እንቀጥላለን፡- «ራሱን የሚቆጣጠር» ራሱን የሚገዛ፥ -ልከኛ» ለሚሉት ጭምት፥ የተለመደ ቃል ነው (ቲቶ 2፡2 ተመልከት)። ይህአማኝ ከራሱ ጋራ ስላለው ግንኙነት ትኩረት ይሰጣል፤ በ«ጽድቅ» የሚለው ቃል ደግሞ ከሌሎች ሰዎች ጋራ የሚያደርገውን ግንኙነት የሚመለከት ነው። ምንም እንኳ እነዚህ ባሕርያት መለያየት ባይኖርባቸውም፥ «እግዚአብሔርን መምሰል» የሚለው ክርስቲያን ከጌታ ጋራ ስለሚያደርገው ግንኙነት ይናገራል።

ክርስቲያኖች በአሁኑ ዘመን ውስጥ ይኖራሉ፤ ነገር ግን እንደ ዘመኑ አይኖሩም ወይም ለእርሱ አይኖሩም። ክርስቶስ ከዚህ ክፉ ዘመን ተቤዥቶናል (ገላትያ 1፡4)፤ በመሆኑም እኛ ይህንን ዘመን ልንመስል አይገባንም (ሮሜ 12፡1-2)። እንደ መለኪያዎቹም ልንመላለስ አይገባንም (ኤፌሶን 2፡2)። «ሊመጣ ያለውን የዓለም» ኃይል (ዕብራውያን 6፡5) ስለቀመስን፥ የአሁኑን ዓለም ከከንቱነቱና ከአምላክ የለሽነቱ ጋራ ለመንከባከብ መጣር የለብንም።

እግዚአብሔር ስለሚያጠራንና የራሱ ልዩ ንብረቶች ስለሚያደርገን (ቲቶ 2፡14)፥ ጸጋ ያድሰናል። ይህ የማንጻት መንገድ «መቀደስ» ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፥ ግቡም አማኙ የበለጠ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲመስል ማድረግ ነው (ሮሜ 8፡29)። ቅድስና ከኃጢአት መለየት ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን ለእግዚአብሔር መሰጠትም ነው (2ኛ ቆሮ. 6፡14-7፡1)። «የተለየ» የሚለው «ለእግዚአብሔር ርስት የተለዩ ሕዝብ» ማለት ነው (ዘዳግም 14፡2፤ 26፡18)።

ሐ. ጸጋ ይሸልመናል (ቲቶ 2፡13)፡- እኛ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመለስ እየተጠባበቅን ነው፤ ብቸኛው ተስፋችንና ክብራችንም ይኸው ነው። በግሪክ ቋንቋ አንድ የመስተዋድድ ተሳቢ ብቻ ስለሚገኝ፥ ይህ ቁጥር ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደሆነ ያረጋግጣል፡- «የታላቁን የአምላካችንንና የመድሐኒታችንን» ይላል። ጳውሎስ በክርስቶስ መመለስ ዙሪያ የሚከሰቱትን ሁኔታዎች ለመዘርዘር አልፈለገም። አማኞች ሁልጊዜ የእርሱን መመለስ መጠባበቅና እርሱን ፊት ለፊት እንደሚያዩት ሆነው መኖር አለባቸው።

4. ክርስቲያኖች እንደ ዜጋ (ቲቶ 3፡1-8)

ክርስቲያኖች ጠባያቸው ከሌሎች የተለየ በመሆኑና ለአምልኮ የግል ስብሰባዎችን ስለሚያደርጉ፥ ብዙ ጊዜ በሮም አገዛዝ በጥርጣሬ ይታዩ ነበር (1ኛ ጴጥ. 2፡11-25 እና 3፡13-4፡5)። እምነታቸውን ሳይተዉ ጥሩ ዜጎች ሆነው መኖራቸው አስፈላጊ ነበር። ጣዖት አምላኪ የሆኑ ጎረቤቶቻቸው ለሕግ ላይታዘዙ ይችላሉ፤ ነገር ግን ክርስቲያኖች ለመንግሥት ሥልጣን መገዛት አለባቸው (ሮሜ 13 ተመልከት)። «ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ» (ቲቶ 3፡1) ማለት «ጎብረተሰቡን በሙሉ በሚያካትቱ ሁኔታዎች ሁሉ መተባበር» ማለት ነው። ሰማያዊ ዜግነታችን (ፊሊ. 3፡20)፥ በምድር ካለን የዜግነት ኃላፊነት ነጻ አያደርገንም።

አማኙ በመንግሥት ላይ ክፉ አመለካከት ሊኖረውና ይህንኑ በስድብ ነቀፋዎችና በጠብ ድርጊቶች ይፋ ማውጣት የለበትም። «ገር» የሚለው (ቲቶ 3፡2) ቃል፥ «ልከኛ አመለካከት፥ ጣፋጭ ማሳመኛ» ማለት ነው። እንደዚህ ዓይነት ባሕርይ ያላቸው ክርስቲያኖች በሕጉ ቃል ላይ ብዙ አያተኩሩም፤ ነገር ግን ሥነ-ምግባራዊ ጉዳይ ካልሆነ በቀር ለመተው የሚፈቅዱ ናቸው።

እንደገና ጳውሎስ ተግባርን ከትምህርት ጋራ ያያይዘዋል፡- «በጣዖት አምላኪ ጎረቤቶቻችሁ ላይ በጣም ነቃፊ አትሁኑባቸው»

በማለት ይጽፋል። እግዚአብሔር ሳይታደጋችሁ በፊት ግን እንደነበራችሁ አስታውሱ፡- ቁጥር 3 ተጨማሪ ማብራሪያ ይፈልጋል፥ ምን ማለት እንደሆነ ከራሳችን ልምምድ እናውቃለን።

«የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር» (3፡4) ምንኛ ትልቅ ልዩነት ፈጥሯል! «የእግዚአብሔርን ቸርነት» ግሩም መግለጫ ከፈለጋችሁ፥ 2ኛ ሳሙኤልን በግንበብ፥ ሽባ የነበረውን ልዑል ሚምፊቦስቴን ዳዊት እንዴት እንዳስተናገደው አስተውሉ። ሚምፊቦስቴ የሳዖል ቤተሰብ አባል ስለነበረ፥ እንደሚገደል ይጠባበቅ ነበር፤ ነገር ግን ዳዊት በቸርነቱ፥ ማረው። ከልጆቹ እንደ አንዱም አድርጎ በቤተ መንግሥት ጠረጴዛ ላይ አስተናገደው።

ደኅንነት የሚመጣው በእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን በምህረቱም ጭምር ነው (ቲቶ 3፡5)። «እርሱ አዳነን» እንጂ፥ እኛ ራሳችንን አላዳንም። እርሱ እንዴት ሠራው? በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፥ በአዲስ ልደት ተአምር ሠራው። በአዲስ ኪዳን ጊዜ ሰዎች የሚጠመቁት ለመዳን ብለው ሳይሆን፥ ከዳኑ በኋላ ስለ ነበር፥ በዚህ ቦታ «መታጠብ» የሚለው ቃል ጥምቀትን የሚያመለክት አይመስለኝም (የሐዋ. ሥራ 10፡43-48 ተመልከት)። በዚህ ስፍራ «መታጠብ» ማለት «ሙሉ ለሙሉ መነከር» ማለት ነው። አንድ ኃጢአተኛ ክርስቶስን በሚታመንበት ጊዜ፥ ከኃጢአቱ ሁሉ ይነጻል፤ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ስለሚያድር አዲስ ፍጥረት ይሆናል።

ጳውሎስ ይህንኑ የመንጻት ልምምድ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያዛምደዋል (ኤፌሶን 5፡26)። ደኅንነት ወደ አንድ ኃጢአተኛ ሰው ሕይወት የሚመጣው እርሱ ክርስቶስን ሲያምንና፥ የእግዚአብሔር መንፈስ አዲስ ልደትን ለማምጣት፥ የእግዚአብሔርን ቃል ሲጠቀም ነው። እኛ ከመንፈስና (ዮሐንስ 3፡5-6፥ «ውኃው» ኒቆዲሞስ ቀደም ብሎ በቁ. 4 የጠቀሰውን የሥጋን መወለድ ያመለክታል፥) ከቃሉ ተወልደናል (1ኛ ጴጥ. 1፡23-25)። በቲቶ 3፡6 «ያን» የሚለው ቃል በተለወጥን ጊዜ ወደ ተሰጠን መንፈስ ቅዱስ የሚያመለክት ቃል ነው (የሐዋ. 2፡38፤ ሮሜ 8፡9፤ 5፡5)።

ክርስቲያኖች የሆንን እኛ መታጠብና በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆን ብቻ ሳይሆን፥ ጸድቀናልም (ቲቶ 3፡7)። ይህ ድንቅ ትምህርት ከሮሜ 3፡21-8፡39 ድረስ በዝርዝር ተብራርቷል። ጽድቅ በመስቀል ላይ ከተፈጸመው ከክርስቶስ ሥራ የተነሣ እግዚአብሔር የሚያምነውን

ኃጢአተኛ ሰው ጻድቅ ብሎ የሚያውጅበት፥ የእግዚአብሔር ቸርነት ሥራ ነው። እግዚአብሔር የልጁን ጽድቅ በእኛ መዝገብ ላይ ስለሚያደርግ፥ እኛ ከኩነኔ እንተርፋለን። እርሱ ኃጢአታችንን መርሳት ብቻ ሳይሆን፥ ነገር ግን ኃጢአተኞች እንደነበርን እንኳን ይረሳል።

የዚህ ቸርነት፥ ፍቅር፥ ምህረት እና ጸጋ ውጤቱ ምንድን ነው? ተስፋ! እኛ የእግዚአብሔር ወራሾች ነን! ይህም ማለት ዛሬ ወደርሱ ባለጠግነት መቅረብ እንችላለን፥ በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ የእርሱን ሀብት እና መንግሥቱን ለዘለዓለም እንካፈላለን። ይህ ተስፋ ከቲቶ 2፡13 ጋራ ይዛመዳል፡- «የተባረከውን ተስፋችንን እየጠበቅን»፤ ነገር ግን በዚህ ውስጥ ሌላ ተጨማሪ ነገር እናያለን፡- እግዚአብሔርን የሚመስል፥ ኑሮ መኖር እና «በመልካም ሥራ በጥንቃቄ መጽናት» (3፡8) አለብን። ያልዳነው ዓለም እኛ የእግዚአብሔር ስለመሆናችን የሚያረጋግጥበት ብቸኛው መንገድ መንፈሳዊ ሕይወታችን ነው።

«መልካም ሥራ» ሃይማኖታዊ ሥራ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሥራ ማለት ላይሆን ይችላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሥራት፥ በመዘምራን ቡድን መዘመር፥ የአገልግሎት ቦታ መያዝ መልካም ነው፤ ነገር ግን ያልዳኑትን ጎረቤቶቻችንን ማገልገል፥ በጎብረተሰቡ ውስጥ ረዳት መሆን፥ ብሎም በችግር ውስጥ ያሉትን በመርዳት መልካም ስም ማትረፍም መልካም ነው። ለሕፃን ልጅ ትኩረት ሰጥታ ለምትጠብቀው እናት ይህ ሥራዋ የወንጌል ሥርጭትን ያህል መንፈሳዊ ሥራ ነው። ለጠፉት ለመመስከር ቤተ ክርስቲያን ልትጠቀምበት የምትችለው በጣም ጥሩው መንገድ፥ የአባሎችዋን የመሥዋዕትነት አገልግሎት ነው።

5. ችግር የሚፈጥሩ ሰዎች (ቲቶ 3፡9-11)

በየአብያተ ክርሲያኖቻችን «ችግር ፈጣሪ ሰዎች» ባይኖሩ ኖሮ ጥሩ ነበር፤ ነገር ግን ሰዎች ባሉበት ቦታ ሁሉ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። በዚህ ጉዳይ፥ ጳውሎስ ቲቶን በእምነት ውስጥ አላስፈላጊ በሆኑ ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ መከራከር ከሚፈልጉት ሰዎች ራሱን እንዲያገል አስጠነቀቀው። አንድ ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በኋላ፥ አንድ ወጣት ወደኔ ቀረበና ስለ እምነት ክፍሎች (መለኮተ ትምህርት) የተለያዩ መላ-ምታዊ ጥያቄዎች መነጋገር ጀመርን። ወጣቱ ለማለት የሚችለው፡- «አሁን ... ይህኛው ትክክል ከነበረ ... ያኛው ትክክል ከነበረ ...» በማለት መከራከር ብቻ ነበር። በዚያን ጊዜ በልምድ የበሰልኩ አልነበርኩኝም፥ ቢሆንም ግን በጥሩ ሁኔታ መሸነት ነበረብኝ። በዚህም ምክንያት፥ የግል ችግር ከነበራቸው እና እርዳታ ከሚፈልጉ ከብዙ ቅን ሰዎች ጋራ

የመነጋገር ዕድል አመለጠኝ። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መከራከር የሚወዱ ክርስቲያን ነን ባዮች ብዙውን ጊዜ በሕይወታቸው ውስጥ አንዳንድ ኃጢአት እየደበቁ እንደሆኑ ተምሬያለሁ። እነዚህ ሰዎች ያልተረጋጉና ብዙ ጊዜ በሥራ ቦታ ወይም በቤት ውስጥ የደስታ ምልክት የማይታይባቸው ናቸው።

ነገ ግን ሌላም ዓይነት ችግር ፈጣሪ ሰው አለ። ለዚህም ደግሞ መፍትሔ ልናገኝለት ይገባናል፦ «በቃሉ እውነት የማይጸና»። ይህም ማለት «የሚያማርጥ፥ መከፋፈልን የሚፈጥር ሰው» ማለት ነው። ይህ ሰው የራሱን ፈቃድ ብቻ የሚያስቀድምና ትክክል የሆነ የሚመስለው ነው። ሰዎች ምርጫ እንዲያደርጉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሰዎች ወደ ሰዎች እየሄደ የሚያስገድድ ነው። «አንተ የምትወግነው ከእኔ ነው ወይስ ከመጋቢው?» ይህ የሥጋ ሥራ ነው (ገላትያ 5፡20 ተመልከት)። የዚህ ዓይነቱ ሰው ቢያንስ ሁለት ጊዜ መመከር አለበት። ከዚያም የማይታረም ከሆነ ማስወገድ ያስፈልጋል።

ይህንን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዴት በሥራ ላይ እናውለዋለን? እስቲ አንድ መንገድ ልጠቁም። አንድ የቤተ ክርስቲያን አባል ጥረቱ ተከታይ ለማግኘት ከሆነና ተናድዶ ከቤተ ክርስቲያን ከወጣ፥ ይሂድ። ከተመለሰና (ምናልባት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁ አልፈለጉት ይሆናል) ንስሐ የመግባት ዝንባሌ ካሳየ እንደገና ተቀበሉት። ይህንን ጠባዩን ከደገመና ነገር ግን ንሥሐ ከገባ፥ ሁለተኛ ጊዜ እንደገና ተቀበሉት፤ ነገር ግን ሦስተኛ ጊዜ ከደገመ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ጎብረት እንደገና አትቀበሉት (ቲቶ 3፡10)። ለምን አንቀበለውም? «እንዲህ ያለው ሰው የተበላሸና ኃጢአትን በመሥራት በራሱ ላይ የፈረደ መሆኑን እወቅ» (3፡11 ከአዲሱ ትርጉም)። አብያተ ክርስቲያናት ይህንን መመሪያ ቢከተሉ ኖሮ፥ በብዙ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ችግር የሚያመጡ «የቤተ ክርስቲያን ዘዋሪዎች» አይኖሩም ነበር።

6. ማጠቃለያ (ቲቶ 3፡12-15)

በመዝጊያዎቹ ቁጥሮች ጳውሎስ አንዳንድ የግል መረጃዎችን ለቲቶ ከማስተላለፉም ሌላ፥ የመልእክቱን ዋና አሳብ ያሳስበዋል፦ የእግዚአብሔር ሰዎች «ከወገኖች ያሉት ደግሞ ፍሬቢሶች ሆነው እንዳይቀሩ የግድ ስለሚያስፈልገው ነገር በመልካም ሥራ እንዲጸኑ ይማሩ» (3፡14)።

ስለ አርጢሞን ምንም አናውቅም፤ ቲኪቆስን በሐዋርያት ስራ 20:4 እናገኘዋለን። ጳውሎስ መጀመሪያ በሮም በታሠረ ጊዜ አብሮት ነበረ። በመሆኑም ጳውሎስ ለኤፌሶን (ኤፌ. 6:21) ለቆላስይስ (ቆላ. 4:7-8)፥ እና ለፊሊሞና (ቆላስይስ 4:7-9 ከፊሊሞና 10 ጋር አመሳክር) የጻፋቸውን ደብዳቤዎች አድርሷል። አርጢሞን ወይም ቲኪቆስ ቲቶን በቀርጤስ ይተኩትና ቲቶ ጳውሎስን በኒቆጵልዩን ይገናኘዋል።

ዜግስና አጵሎስ ይህን ደብዳቤ ለቲቶ አድርሰው ሊሆን ይችላል (ቲቶ 3:13፤ የሐዋ. ሥራ 18:24-28 ተመልከት)። ጳውሎስ ለአገልግሎት ልኮአቸው ስለ ነበር፥ ቲቶ በተቻለው አቅም ሊረዳቸው ይገባው ነበር።

ጳውሎስ ለቲቶ የጻፈውን ደብዳቤ ከተለመደ ቡራኬው በአንዱ ይፈጽመዋል፡- (2ኛ ተሰሎንቄ 3:17-18) «ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን»

ጸጋ ... እና መልካም ሥራ! አብረው ይሄዳሉ።

የሁለተኛ ጢሞቴዎስ አስተዋጽኦ

ዋና አሳብ፡- ለመጨረሻዎቹ ቀናት አገልግሎት መዘጋጀት

ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለማበረታታት አራት ጥሪዎችን ያቀርባል፡-

1. የመጋቢነት ጥሪ - ምዕራፍ 1
    1. ብርቱ መሻት (1፡1-7)
    2. የማያሳፍር ሥቃይ (1፡8-12)
    3. መንፈሳዊ ታማኝነት (1፡13-18)
2. ተግባራዊ ጥሪ - ምዕራፍ 2
    1. መጋቢ (2፡1-2)
    2. ወታደር (2፡3-4፥ 8-13)
    3. ሯጭ (2፡5) (ስፖርተኛ)
    4. ገበሬ (2፡6-7)
    5. ሠራተኛ (2፡14-18)
    6. ዕቃ (2፡19-22)
    7. ባሪያ (2፡23-26)
3. ትንቢታዊ ጥሪ - ምዕራፍ 3
    1. ከሐሰት ሽሽ (3፡1-9)
    2. እውነት የሆኑትን ተከተል (3፡10-12)
    3. በእግዚአብሔር ቃል ጸንተህ ኑር (3፡13-17)
4. ግላዊ ጥሪ - ምዕራፍ 4
    1. ቃሉን ስበክ (4፡1-4)
    2. አገልግሎትህን ፈጽም (4፡5-8)
    3. ትጉና ታማኝ ሁን (4፡9-22)

የበረቱ ክርስቲያኖች

2ኛ ጢሞቴዎስ 1

ጳውሎስ ሁለተኛ ጢሞቴዎስን በሚጽፍበት ጊዜ፥ የእርሱ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ተለውጦ ነበር። በሮም ወኅኒ ቤት ተጠብቆ፥ የተወሰነበትን ሞት ይጠባበቅ ነበር (2ኛ ጢሞ. 4፡6)። በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት የጳውሎስ የአገልግሎት ተባባሪዎች ሁሉ ተለይተውት፥ ሉቃስ ብቻ ይረዳው ዘንድ ከሐዋርያው ጎን ቆሞ ነበር (4፡11)። በእርግጥ ጨለማ የነገሠበት ጊዜ ነበር።

ነገር ግን ጳውሎስ አብዝቶ የሚያስበው ለራሱ ሳይሆን፥ ለጢሞቴዎስና ለወንጌሉ አገልግሎት መሳካት ነበር። በመጀመሪያው ደብዳቤው እንደጻፈው፥ ጳውሎስ ውድ የሥራ ጓደኛውን ታማኝ እንዲሆን ያበረታታዋል። እንደተመለከትነው ጢሞቴዎስ ዓይን አፋርና በሥጋ ካለበት ሕመም የተነሣ ሌሎች ሰዎች የርሱን ስፍራ እንዲወስዱና የመጋቢነት ሥልጣኑን ለመልቀቅ ተፈትኖ ነበር።

ጳውሎስ፥ ቲኪቆስ ጤሞቴዎስን ይተካ ዘንድ ወደ ኤፌሶን ላከው፤ ይህንም ያደረገው ጤሞቴዎስን ከእርሱ ጋር በሮም እንዲሆን ፈልጎት ነው (4፡9፥ 12)። እግዚአብሔር በቅርብ ጊዜ ጳውሎስን ከትዕይንቱ ውጪ ስለሚያደርገው፥ ጢሞቴዎስ የእርሱን ቦታ በመሸፈን ለአብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ አመራር እንዲሰጥ ነበር። ቀላል ሥራ ባይሆንም፥ ነገር ግን ጢሞቴዎስ በእግዚአብሔር እርዳታ ሊወጣው ይችል ነበር። ጳውሎስ በመጀመሪያው ምዕራፍ፥ ለጢሞቴዎስ ስኬታማነት አስፈላጊ የሆኑትን ሦስት ነገሮች ይጠቅሳል።

1. ብርቱ መሻት (2ኛ ጢሞ. 1፡1-7)

የወንጌል አገልግሎት ብርታት ለጎደላት ለፈሪ ነፍስ ቦታ የለውም። በእርግጥ ብርቱ መሻት ለማንኛውም ዓይነት ሥራ ስኬታማነት አስፈላጊ ነው። ጳውሎስ ይህንን አመለካከት እሳትን ከማቀጣጠል ጋራ ያወዳድረዋል (1፡6)። ጢሞቴዎስ ወደ ኋላ እንደ ተመለሰ ወይም መንፈሳዊ ግለት እንዳጣ አድርገን ማጠቃለል የለብንም። ይልቁንም ጳውሎስ ረዳቱ ጢሞቴዎስን በሕይወቱ ውስጥ በመንፈሳዊ ኃይል እንዲበረታ፥ እሳቱ ደምቆ እያበራ መንደዱን እንዲቀጥል እያበረታታው ነበር። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ አራት ማበረታቻዎችን ሰጥቶት ነበር፡-

ሀ. የጳውሎስ ፍቅር (2ኛ ጢሞ. 1፡1-2)፡- «ለተወደደው ልጄ ጢሞቴዎስ» የሚለው «በእምነት እውነተኛ ልጄ ለሆነ ለጢሞቴዎስ» ከሚለው አገላለጽ እጅግ የበረታ ነው (1ኛ ጢሞ. 1፡2)። ይህም የመጀመሪያ መልእክቱን በጻፈ ጊዜ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ባነሰ ሁኔታ ይወደው ነበረ ማለት ሳይሆን፥ ነገር ግን ያንኑ ፍቅር አሁን በበለጠ ገለጸው ማለት ነው። የጳውሎስ የሕይወቱ ማብቂያ እየተቃረበ ሲሄድ፥ ጢሞቴዎስ ምን ያህል ለእርሱ ውድ እንደነበረ ተረዳ።

የጳውሎስ የራሱ ሁኔታዎች አስቸጋሪ ነበሩ፤ ዳሩ ግን በጣም ይበረታ ነበር። አንዱ ነገር እርሱ የክርስቶስ አምባሳደር «ሐዋርያ» ነበርና እናም ጌታው ለርሱ እንደሚጠነቀቅለት ያውቅ ነበር። የሚደርስበት ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ስለ ነበር፥ የሚያስፈራው ነገር አልነበረም። በተጨማሪም፥ ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ «የሕይወት ተስፋ» ነበረው፤ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጓል (1፡10)። ጳውሎስ ወደ ጢሞቴዎስ ጸጋ፥ ምህረትን፥ ሰላምን ለማስተላለፍ መቻሉ አስገራሚ አይደለም (ጳውሎስ ለመጋቢዎች በሚጽፍበት ጊዜ በሰላምታው ላይ «ምህረት» መጨመሩን ማጤን አስፈላጊ ነው። 1ኛ ጢሞ. 1፡2፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡2፤ ቲቶ 1፡4። ጳውሎስ መጋቢዎች ምህረት እንደሚያስፈልጋቸው ያውቅ ነበር)።

ለ. የጳውሎስ ጸሎት (2ኛ ጢሞ. 1፡3-4)፡- ታላቁ ሐዋርያ ለእርሱ እንደሚጸልይለት ማወቅ ምን ያህል ማበረታቻ ነው! የጢሞቴዎስን ድካምና ችግሮቹን የሚያውቀው ጳውሎስ በግልጽና እውነተኛ በሆነ የልብ ሸክም ይጸልይለት ነበር። ጸሎቱ ከርኅራኄ ከአሳቢነት የመነጨ እንጂ፥ የተለመደ አልነበረም። ጳውሎስ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደሚሞት ስለሚያውቅ፥ ጢሞቴዎስ በእነዚያ መጨረሻዎቹ የኅብረትና የአገልግሎት ጊዜያት ወደ ሮም መጥቶ እንዲገናኘው ጓግቶ ነበር። ይህ ወደ ጳውሎስ ልብ ደስታን የሚያመጣ ነበር።

ጳውሎስ ከመለወጡ በፊት ያደረጋቸውን ክፉ ነገሮች «በንጹህ ሀሊና» እንዳደረገ በመናገር ለመከላከል እንደሞከረ አድርገን ማሰብ የለብንም። መቼም በክርስቲያኖች ላይ ፍርሃትን በማምጣቱ፥ ክርስቶስን በመካድ ሰዎች እንዲሳደቡ በማድረጉና፥ እስጢፋኖስን ለመግደል በመስማማቱ በደለኛ ነበር! ጳውሎስ እግዚአብሔርን የሚያገለግል እየመሰለው (ዮሐንስ 16፡2 ተመልከቱ)፥ በመንፈሳዊ ድንቁርና ውስጥ

ይመላለስ ነበር (1ኛ ጢሞ. 1፡13)፤ ነገር ግን እነዚህ ጭብጦች ለንጹሕ ሕሊና ዋስትና አይሰጡም።

ጳውሎስ ከመጀመሪያዎቹ ዓመታት ጀምሮ «ከዕብራውያን ዕብራዊ» (ፊሊ. 3፡5) ስለነበረ፥ እግዚአብሔርን ያውቅ ነበር። ቅድመ-አያቶቹ ግትር የሆነውን የአይሁድ እምነትን ሰጥተውት ነበር፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን በተገናኘ ጊዜ፥ የእርሱ ይሁዲ እምነት ክርስቶስ በክርስትና ለሰጠው ነገር የማስፈጸሚያው ዝግጅት መዘጋጃ እንደነበር ተረዳ። እርሱ እግዚአብሔርን በንጹሕ ሕሊና ስለማገልገል «ከአባቶቹ» አልተማረም፤ ነገር ግን ስለ እውነተኛው አምላክ ከአባቶቹ ሰምቶ ነበር፤ እናም አሁን ያንን እግዚአብሔር በንጹሕ ሕሊና ያገለግል ነበር። ንጹህ ሕሊና የነበረው መሆኑ ለጸሎቱ ኃይል ሰጥቶታል።

ሐ. ጳውሎስ በጢሞቴዎስ ላይ የነበረው እርግጠኝነት (2ኛ ጢሞ. 1፡5)፡- ጳውሎስ የጢሞቴዎስ እንባ የውድቀትና ያለመታመን ምልክቶች ናቸው ብሎ አላሰበም። ጳውሎስ የጢሞቴዎስ እምነት ጽኑ እንደነበርና ከሚጋፈጣቸው መከራዎች ባሻገር ይህ እምነት እንደሚያቆመው እርግጠኛ ነበር። በግልጽ እንደተቀመጠው፥ ከቤተሰቡ በመጀመሪያ ወደ ክርስቶስ የተግረከችው የጢሞቴዎስ አያት ሎይድ ነበረች፤ ከዚያም እናቱ አውንቄ ተለወጠች። የጢሞቴዎስ አባት ግሪካዊ ስለ ነበር (የሐዋ 16፡1)፥ አውንቄ የአይሁድን ግትር እምነት አልተለማመደችም ነበር። ሆኖም የጢሞቴዎስ እናትና ሴት አያት ጥቅሙን ያውቁት ስለ ነበር፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ተምሮ ነበር (2ኛ ጢሞ. 3፡15)። ይህም ወንጌሉን ለመስማት ትልቅ ዝግጅት ሆነለት። ጳውሎስ በመጀመሪያው የወንጌል ጉዞው ወደ ልስጥራን በመጣ ጊዜ፥ ያ ሁኔታ ነበር። ምናልባት ለጢሞቴዎስ መለወጥ መልካም አጋጣሚ የሆነው። ጳውሎስ በሁለተኛ ጉዞው በተመለሰ ጊዜ፥ ጢሞቴዎስን በክርስትና የአገልግሎት መስክ ውስጥ አስገባው።

ጳውሎስ የጢሞቴዎስን ሕይወትና አገልግሎት አብረው በነበሩበት በነዚያ ዓመታት ውስጥ ተከታትሎ ነበር። የጢሞቴዎስ እምነት እውነተኛ ስለመሆኑ እርግጠኛ ነበር። በእርግጥ የጢሞቴዎስ ውርስ ከፍተኛ ነበር፤ እግዚአብሔርን በሚፈሩ ሰዎች ቤት ውስጥ በማደጉ፥ በድንቅ ሐዋርያ በመሠልጠኑና ጌታን ለማገልገል አስደናቂ ዕድሎች በማግኘቱ፥ ውርሱ ታላቅ ነበር።

መ. እግዚአብሔር ለጢሞቴዎስ የሰጠው ስጦታ (2ኛ ጢሞ. 1፡6-7)፡- ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እግዚአብሔር ለአገልግሎት የጠራበትንና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም የሾመችውን ጊዜ ያስታውሰዋል። ጳውሎስ በጢሞቴዎስ ላይ እጁን ጭኖ ነበር (1ኛ ጢሞ. 4፡14)። በጳውሎስ በኩል፥ ለጢሞቴዎስ በአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ ስጦታ እግዚአብሔር ሰጠው። በሐዋርያት ዘመን እጅ መጫን የተለመደ ልምምድ ነበር (ሐዋ. 6፡6፤ 13፡3)፤ ነገር ግን ዛሬ ማንም አማኝ ሐዋርያት እንዳደረጉት ዓይነት ሥልጣንና መብት የለውም። ዛሬ በሰዎች ላይ ለአገልግሎት እጃችንን በምንጭንበት ጊዜ፥ ምሳሌያዊ ድርጊት እንጂ፥ የግድ ልዩ የሆነ መንፈሳዊ ስጦታ እያስተላለፍን አይደለም።

እግዚአብሔርን እንድናገለግል የሚያስችለን መንፈስ ቅዱስ ነው፤ በእርሱ አማካኝነት ፍርሃትንና ድካምን ለማሸነፍ እንችላለን። በ2ኛ ጢሞ. 1፡7 ላይ ፍርሃት የሚለው ቃል፥ «ዓይናፋርነት፥ ፈሪነት» ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ለምስክርነትና ለአገልግሎት ኃይል ይሰጠናል (ሐዋ. 1፡8)። እግዚአብሔርን ካለመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለማገልገል መሞከር ከንቱ ነው። ችሎታ፥ ሥልጠና እና ልምድ የመንፈስ ቅዱስ ኃይልን ቦታ ሊወስዱ አይችሉም።

እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ፍቅርን ይሰጠናል። ለጠፉት ነፍሳትና ለእግዚአብሔር ሕዝብ ፍቅር ካለን፥ በመከራ ለመጽናትና የእግዚአብሔርን ሥራ ለመፈጸም እንችላለን። ራስ ወዳድነት ወደ ፍርሃት ይመራል። ምክንያቱም ራስ ወዳዶች ከሆንን፥ እግዚአብሔርን በማገልገላችን ስለምናገኘው ትርፍ ብቻ ከማሰላት ባሻገር፥ ክብር፥ ኃይል ወይም ገንዘብ እንዳናጣ እንሰጋለን። በመንፈስ የተነቃቃ እውነተኛ የክርስቲያን ፍቅር (ሮሜ 5፡5)፥ ለሌሎች መስዋዕት እንድንሆንና እንዳንፈራ ያስችለናል። መንፈስ ፍቅር ይሰጣል (ገላ. 5፡22)።

ራስን መቆጣጠር (መግዛትም) የሚሰጠው እርሱው ነው። ይህ ቃል በመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ ብዙ ጊዜ ከምናገኛቸው እንደጭምትና ልከኛ ከመሳሰሉ ቃላት ጋር ይያያዛል (ቲቶ 1፡8፤ 2፡2፥ 4፥ 6፥ 12፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡9፥ 15)። የግል ሥነ-ሥርዓት የሚለው «ራስ የመግዛትን መንፈስ» ለሚለው ጥሩ ትርጉም ነው (2ኛ ጢሞ. 1፡7)። አስተዋይና ሚዛናዊ አእምሮ ኖሮት፥ ሕይወቱን በመቆጣጠር የሚመላለሰውን ሰው ይገልጻል። «አምፕሊፋይድ» የተባለው የእንግሊዝኛ የመጽሐፍ ቅዱስ

ትርጉም «ረጋ ያለና ማመዛዘን የሚችል አእምሮ፥ ሥነ-ሥርዓትና ራስን መቆጣጠር» በማለት ያስነብባል።

ጢሞቴዎስ በሕይወቱ ውስጥ አዳዲስ መንፈሳዊ ማጣፈጫዎች አያስፈልጉትም ነበር። ማድረግ ያለበት ነገር ቢኖር፥ የነበረውን «ማነሣሣት» ነበር። ጳውሎስ በመጀመሪያ መልእክቱ፡- «በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል» (1ኛ ጢሞ. 4፡14) በማለት ጽፎለት ነበር። አሁን ደግሞ «አነሣሣ - እሳት እንደሚያቀጣጥል፡- የእግዚአብሔርን ስጦታ አነሣሣ» ይለዋል። በምንወድቅበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ አይተወንም (ዮሐ. 14፡16)፤ ነገር ግን መንፈሳዊ ሕይወታችንን ችላ ካልን ሊሞላን፥ ኃይል ሊሰጠን፥ እና ሊጠቀምብን አይችልም። መንፈስን ማሳዘን (ኤፌ. 4፡30) እና ማዳፈን (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡19) ይቻላል።

ጢሞቴዎስ ለመበረታታትና በአገልግሎቱ መንፈሳዊ ድፍረት ለማግኘት ምክንያቶች ነበሩት። ጳውሎስ ይወደውና ይጸልይለት ነበር። በሕይወቱ ውስጥ ያለፈባቸው ልምምዶቹ ለአገልግሎቱ መዘጋጂያ ሆነውለት ነበር፤ ጳውሎስም በጢሞቴዎስ እምነት እውነተኛነት ይተማመን ነበር። በውስጡ ያለው መንፈስ ለአገልግሎት የሚያስፈልገውን ኃይል በሙሉ ይሰጠው ነበር። ከዚህ በላይ ምን ሊፈልግ ይችል ኖሯል።

2. የማያሳፍር ሥቃይ (2ኛ ጢሞ. 1፡8-12)

«የማያፍር» የሚለው የዚህ ምዕራፍ ቁልፍ አሳብ ነው፤ ጳውሎስ አላፈረም ነበር (ቁ. 12)፥ ጢሞቴዎስን እንዳያፍር መክሮታል፥ (ቁ. 8)። ሄኔሲፎሩ በጳውሎስ ሠንሠለት እንዳላፈረ መስክሯል (ቁ. 16)።

ሀ. በጌታ ምስክርነት አትፈር (2ኛ ጢሞ. 1፡8-10)፡- ለጢሞቴዎስ ተፈጥሮአዊ ዓይናፋርነቱ በሚመሰክርበት ጊዜ የሚደርሱበትን ሥቃይ ያለባቸውን ሁኔታዎች ለመቋቋም የሚያስችለው ይመስለው ነበር። ስለዚህ አንድ ጊዜ እንደገና ጳውሎስ ለረዳቱ የሚያስፈልገውን ማበረታቻ ይሰጠዋል።

1. እግዚአብሔር ኃይልን ይሰጠናል (2ኛ ጢሞ. 1፡8)፡- በተፈጥሮአችን ማንኛችንም ብንሆን ሥቃይ አያስደስተንም። ጌታችንም እንኳን እንዲህ ብሎ ጸልዮአል፡- «አባት ሆይ፥ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ» (ሉቃስ 22፡42)፤ ጳውሎስም የሚያሳምመውን መውጊያ ከሥጋው እንዲያነሣለት ሦስት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጸልዮአል (2ኛ ቆሮ. 12፡7-8)፤ ነገር ግን ሥቃይ የታማኝ

ክርስቲያን ሕይወት አካል ሊሆን ይችላል። ክርስቲያኖች ስህተት በመሥራታቸው መሠቃየት የለባቸውም (1ኛ ጴጥ. 2፡20፤ 3፡17)፤ ይልቁንም አንዳንድ ጊዜ ትክክል ስለሠሩና እግዚአብሔርን ስላገለገሉ ይሰቃያሉ። መልካም ስለሠራን በምንሠቃይበት ጊዜ፥ የክርስቶስን ሥቃይ እየተካፈልን ነው (ፊሊ. 3፡10)፤ እንዲሁም በመላው ቤተ ክርስቲያን ምትክ እንሠቃያለን (ቆላስይስ 1፡24)።

ከዓመታት በፊት በእምነቱ ምክንያት በእሥር ቤት ውስጥ ስልነበረ አንድ ክርስቲያን አንብቤ ነበር። በእግሩ ተቃጥሎ እንዲሞት ተፈርዶበት ነበር፤ እርሱም ሥቃዩን ለማለፍ በፍጹም እንደማይችል እርግጠኛ ነበር። አንድ ምሽት፥ ትንሽ ጣቱን በሻማ ነበልባል ላይ በማስቀመጥ ሙከራ አደረገ። ያም አቃጠለውና ወዲያው ጣቱን መለሰው። «አምላኬን ሳላሰድበው አልቀርም» በማለት ለራሱ ተናገረ። «እኔ ሕመሙን ልሸከም አልችልም»፤ ነገር ግን የሚሞትበት ሰዓት በቀረበ ጊዜ፥ እግዚአብሔርን አመሰገነና ለኢየሱስ ክርስቶስ ወርቃማ ምስክርነት ሰጠ። እግዚአብሔር ከትክክለኛ ጊዜ በፊት ሳይሆን፥ በሚያስፈልገው ሰዓት ኃይልን ሰጠው።

2. እግዚአብሔር በጸጋው ጠርቶናል (2ኛ ጢሞ. 1፡9)፡- እኛ እግዚአብሔር «ከዘላለም ዘመናት በፊት» የወሰነው የታላቁ ዘላለማዊ ዕቅድ ተካፋዮች ነን። እግዚአብሔር የመጨረሻውን ከመጀመሪያው ጀምሮ ያውቃል። እርሱ ለሕዝቡ ለክብሩ የሚወጥናቸው ዓላማዎች አሉት። ሥቃይ ከዕቅዶቹ መካከል አንድኛው አካል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሆኖም በዚህ ምክር ላይ ተሰቃይቷል፤ እንዲሁም እርሱን የሚያምኑት ሁሉ ይሰቃያሉ።

በዚህ ቁጥር ውስጥ ትኩረት የተደረገው በጸጋ ላይ ነው። እግዚአብሔር አዳንነ እንጂ፥ ራሳችንን አላዳንንም (ኤፌ. 2፡8-9፤ ቲቶ 3፡5)። እርሱ የጠራን፥ በመልካም ሥራችን ላይ በመመሥረት ሳይሆን፥ ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ በጸጋው ነው።

እኛ ሥራ ላይ የምናውላቸው የእርሱ ዓላማዎች ናቸው፤ እኛም እነዚህ ዓላማዎች መሠቃየትን የሚያካትቱ ከሆነ፥ በእምነት ልንቀበላቸው እንችላለን። በዚህም ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ መልካም እንደሆነ እናውቃለን። ይህ በእግዚአብሔር አስቀድሞ የተወሰነ ክስተት አይደለም በመሆኑም በቸሩ ሰማያዊ አባታችን ጥበበኛ ዕቅድ መተማመን

እንጂ፥ ሁሉም ክስተቶች በሆነ ኃይል አስቀድመው የተወሰኑ ስለሆነ የሚሆነውን ሁሉ በአይቀሬነቱ መቀበል ያሻል የሚል እምነት አይደለም።

ይህ ሁሉ ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ተሰጥቶናል። በጥረታችን ልናገኘው አንችልም ነበር፤ የሚገባን አልነበርንምና። ይህ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው!

3. ክርስቶስ ሞትን አሸንፏል (2ኛ ጢሞ. 1፡10)፡- ዓይነ አፋርነታችን ከፍርሃት የሚመነጭ ነው። ምን እንፈራለን? መሠቃየትና ሊመጣ የሚችል ሞት? ጳውሎስ ራሱ ይህንን መልእክት በሚያጽፍበት ጊዜ ከሞት ጋር ተፋጦ ነበር፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻውን ጠላታችንን ሞትን አሸንፎታል! በራሱ ሞትና ትንሣኤ፥ ክርስቶስ «ሞትን ደመሰሰ» (የማይሠራ አደረገው፤ መውጊያውን አውጥቶ ወሰደ) «ሞት ሆይ መውጊያህ የታለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሣትህ የታለ?» (1ኛ ቆሮ. 15፡55)።

ክርስቶስ ሞትን ደምሳሽ ብቻ ሳይሆን (ዕብራውያን 2፡14 ተመልከት)፥ ነገር ግን እርሱ የሕይወትና የሕያውነት ገላጭ ነበር። በብሉይ ኪዳን የዘላለም ሕይወት፥ ሞት፥ ትንሣኤ እና ዘላለማዊነት በጥላ ውስጥ ነበሩ። እዚህና እዚያ ደብዛዛ ብርሃን ታገኛላችሁ፤ ነገር ግን ብዙው ቦታ የጽልመት ጥላ ያረፈበት ነበር። በኋላ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞትና በሲኦል ላይ የራሱን ብርሃን አበራ። በወንጌሉ በኩል የዘለዓለም ሕይወት፥ የትንሣኤ እና የመንግሥተ ሰማይ ተስፋ ዋስትና ሰጠን።

«የነፍስ ማንቀላፋት» እና ሌላ እንግዳ ትምህርቶች የሚያስተምሩ የሃይማኖት ቡድኖች አሳባቸውን የሚያገኙት ብዙውን ጊዜ ከመዝሙረ ዳዊትና ከመጽሐፈ መክብብ ነው። ግልጽ የሆነው የአዲስ ኪዳን ብርሃን በብሉይ ኪዳን ላይ እንዲያበራ ከማድረግ ይልቅ፥ እነርሱ አዲሱን በብሉይ ኪዳን ጥላ ይመለከታሉ። ለወንጌሉ ብርሃን ጀርባህን ከሰጠህ፥ ሌላ ተጨማሪ ጥላ ትፈጥርና የበለጠ ታጨልመዋለህ።

«አለመጥፋት» (2ኛ ጢሞ. 1፡10) ማለት «አለመበላሸት» ማለት ሲሆን፥ ወደ ትንሣኤ አካል ያመለክታል። የአሁኑ ሰውነት የሚበላሽ ነው፤ ይሞታል፤ ደግሞም ይበሰብሳል፤ ነገር ግን ክርስቶስን ስናይ የሚኖረን የከበረ ሥጋ ለመበስበስ ወይም ለሞት የተሰጠ አይሆንም (1ኛ ቆሮ. 15፡49-58፤ ፊሊ. 3፡21)። በእርግጥ የምንካፈለው ሰማያዊ ውርስ «የማይጠፋ፥ እድፈት የሌለበት፥ የማያልፍ» ይሆናል (1ኛ ጴጥ. 1፡4)።

ለ. በጌታ እሥረኛ አትፈር (2ኛ ጢሞ. 1፡11-12)፡- እስረኛ ቢሆንም፥ ጳውሎስ አሁንም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ምስክርነት ይሰጥ ነበር። የሚያሳዝነው፥ በኤፌሶን የነበሩት ሰዎች በሚያስፈልገው ጊዜ ጳውሎስን ሸሽተውታል (ቁ. 15)። አብዛኛዎቻቸው በጳውሎስ ፈንታ ሮም መጥተው ሊመሰክሩ ይችሉ ነበር፤ ነገር ግን አላደረጉትም። ከሐዋርያው ጋራ አብሮ መቆጠር እንኳን አሳፍሯቸው ነበር! ጢሞቴዎስም ከሕዝቡ ጎን ቢሰለፍ ኖሮ፥ ሁኔታው በኤፌሶን (እና በዙሪያ ባሉት ከተሞች 4፡13 ተመልከቱ) የሚያካሂደውን አገልግሎት በበለጠ ያቀልለት ነበር፤ ነገር ግን ጳውሎስ እውነተኛ ሆኖ እንዲጸና መከረው። ጢሞቴዎስ ከእስረኛው ጳውሎስ ጋራ ስላለው ግንኙነት ማፈር እንደሌለበት አራት ምክንያቶች ሰጥቶታል፡-

1. ጳውሎስ በእግዚአብሔር የተጠራ ነበር (2ኛ ጢሞ. 1፡11)፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ጳውሎስን በደማስቆ መንገድ ተገናኝቶት ነበር (የሐዋ. ሥራ 9)፤ በዚህም ጊዜ በግሉ ወደ አገልግሎት ጠርቶታል። ጳውሎስ የወንጌሉ «አዋጅ ነጋሪ» (ሰባኪ) ነበር። በጥንት ጊዜ «አዋጅ ነጋሪ» የንጉሱ ወይም የንጉስ ነገስቱ የታወቀ መልእክተኛ ነበር። በመሆኑም የእርሱ መልእክት ታላቅ አክብሮት ይሰጠው ነበር። በእስያ የነበሩ አማኞች ጳውሎስን አለመቀበላቸው ጥሪውን ወይም መልእክቱን አልለወጠውም።

2. ጳውሎስ አዋጅ ነጋሪ ብቻ ሳይሆን፥ «ለአንድ ተልእኮ የተላከ ነበር»፡- አንድ ሰው የተወሰኑ መመዘኛዎችን ማሟላትና በጌታ በግል ወይም በእርሱ መንፈስ መመረጥ ስለነበረበት፥ ሁሉም ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ አልነበረም (ሐዋ. 1፡15-26፤ 1ኛ ቆሮ. 9፡1፤ 2ኛ ቆሮ. 12፡12)። አንድ ሐዋርያ ኢየሱስ ክርስቶስን ወክሎ ስለሚናገር፥ ሐዋርያን አለመቀበል ማለት ጌታን አለመቀበል ነው።

3. ጳውሎስ የአሕዛብ አስተማሪ ነበር፡- ይህ ማለት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን በእረኝነት ያገልግል ነበር ማለት ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ በሮማ እንዲታሰር ያደረገው ይህ አሕዛብ የሚለው ቃል ነው (የሐዋ. 22፡21-24)። በእስያ የሚገኙት አሕዛብ አማኞች አድናቆታቸውን ከእርሱ ጎን በመቆም መግለጽ ነበረባቸው፤ እንዲያውም የመዳንን መልካም ዜና ያመጣላቸው ጳውሎስ ነበር። ነገር ግን በእሥራቱ አፈሩና ገሸሽ ለማለት ሞከሩ።

4. ጳውሎስ በክርስቶስ ይተማመን ነበር (2ኛ ጢሞ. 1፡12)፡- ጳውሎስ አላፈረም ነበር! ለምን? ምክንያቱም ክርስቶስ ታማኝ እንደሆነና እንደሚጠብቀው ያውቅ ነበር። በክርስቶስ ስብዕና ላይ የሚያደርገውን ትኩረት ተመልከት፡- «ያመንኩትን አውቃለሁና» ምንም እንኳ ትምህርቶች አስፈላጊ ቢሆኑም፥ ደኅንነት የተወሰኑ ትምህርቶችን የማመን ውጤት አይደለም። አንድ ኃጢአተኛ የሚድነው አዳኝ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚያምን ነው። ጳውሎስ ነፍሱን ለአዳኙ እንክብካቤና ጥንቃቄ አደራ ሰጥቷል። እንዲሁም ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ ያንን አደራ በታማኝነት እንደሚጠብቅ እርግጠኛ ነበር። በአንድ የተወሰነ ቀን የሚሆነው ነገር ለጳውሎስ ምን ልዩነት ያመጣል? ዋናው ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮቹን በሚሸልምበት «በዚያን ቀን» የሚሆነው ነው (1፡18 እና 4፡8 ተመልከት)።

በነዚህ አስቸጋሪ ቀናት፥ ለክርስቶስ እውነተኞች ሆነን በመቆም፥ ለእርሱ ለመሰቃየት ፈቃደኞች መሆንና በርሱም አለማፈር አስፈላጊ ነው። እንደ ጳውሎስ ወደ እስር ቤት አንጣል ይሆናል፤ ነገር ግን በሌሎች መንገዶች እንሰቃያለን፡- ጓደኞችን በማጣት፥ በሥራችን ዕድገትን በመከልከል፥ ደንበኞችን በማጣት፥ በመሰደብ፥ እንዲሁም በመሳሰሉት፥ ደግሞም ስለ ጽድቅ ብለው ከሚሰቃዩት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ጎን መቆማችንም አስፈላጊ ነው።

3. መንፈሳዊ ታማኝነት (2ኛ ጢሞ. 1፡13-18)

በዘመናት መካከል የእግዚአብሔር ሥራ በፈተናቸው ሰዓት በጽንአት በቆሙ ወንዶችና ሴቶች ሲከናወን ኖሯል። ቢያወላውሉ ለእነርሱ አመቺ ሊሆንላቸው ይችል ነበር፤ ነገር ግን በጽንአት ቆሙ። ጳውሎስ እንዲህ ዓይነት ሰው ስለ ነበር፥ ጢሞቴዎስ ምሳሌውን እንዲከተል አበረታታው።

ሀ. ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ ሁን (2ኛ ጢሞ. 1፡13-14)፡- እግዚአብሔር ለጳውሎስ የመንፈሳዊ እውነትን አደራ ሰጥቶት ነበር (1ኛ ጢሞ. 1፡11)፤ እርሱም ለጢሞቴዎስ አስተላለፈው (6፡20)። አሁን ውድ የሆነውን የመንፈሳዊ እውነት አደራ «አጥብቆ መያዝና» (2ኛ ጢሞ. 1፡13) «መጠበቅ» (1፡14) ብሎም ለሌሎች ማስተላለፍ የጢሞቴዎስ ብቸኛ ኃላፊነት ነበር።

በቁጥር 13 ላይ ምሳሌ ማለት «ቅርጽ፥ የሕንፃ ንድፍ» ማለት ነው። በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች የሚመዘኑበት የተወሰነ

መለኪያ ነበረ። ጢሞቴዎስ ይህንን ጽሑፍ ከለወጠው ወይም ከተወው ሌሎች አስተማሪዎችንና ሰባኪዎችን የሚመዝንበት ምንም ነገር አይኖረውም ነበር። እኛም ዛሬ በዚሁ ምክንያት ጳውሎስ ያስተማረውን አጥብቀን መያዝ ያስፈልገናል።

ሆኖም፥ የጢሞቴዎስ ትምህርት በ«እምነትና በፍቅር» የለዘበ መሆን እንዳለበት እናስተውል። «እውነትን በፍቅር እየያዝን» (ኤፌሶን 4፡15) የሚለው መለኮታዊ ምሳሌ ነው። እምነትን ለመከላከል ካለን ጽኑ ፍላጎት የተነሣ፥ ጠበኛና ችግሮችን የሚፈጥር አሳዳጅ ሰው መሆን ምንኛ ቀላል ነው!

እውነትን ለጢሞቴዎስ የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ፥ እንዲጠብቀው እርሱ ይረዳዋል። ከመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ውጪ፥ የእግዚአብሔርን ቃል መረዳት፥ በጨለማ ውስጥ የወደቀ መርፌ በዳበሳ የመፈለግን ያህል አዳጋች ነው። እኛን ማስተማር ያለበት (ዮሐንስ 16፡13) እውነቱን እንድንጠብቅና ለሌሎች እንድናካፍል የሚያስችለን እርሱ ነው።

የሰው ልጅ ታሪክ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ፥ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል ተቃውሟል። ለሰው ልጅ የቀረበው የመጀመሪያው ቃል «በውኑ እግዚአብሔር ... አዝዞአልን?» የሚለው ነበር (ዘፍጥረት 3፡1)። አሁንም ያንኑ ጥያቄ መጠየቅ ይቀጥላል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በሙሉ፥ የእግዚአብሔር ቃል ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ ሰዎች ጥቃት ደርሶበታል። ሆኖም ግን እስከ ዛሬ ድረስ ቆሞአል። ለምን? ምክንያቱም ራሳቸውን የሰጡ ወንዶችና ሴቶች (እንደ ጳውሎስና ጢሞቴዎስ) አደራውን ስለጠበቁትና ለሌሎች አዲስ ትውልድ ክርስቲያኖች ስለ አስተላለፉት ነው። አንድ ቤተ ክርስቲያን ወይም የክርስቲያን ድርጅት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ እውነት ግድ የለሽ ሲሆን፥ ብዙ ጊዜ መሪዎች ስለ እግዚአብሔር ቃል ያላቸው አቋም መዳከም ይጀምራል።

ለ. ለእግዚአብሔር አገልጋይ ታማኝ ሁን (2ኛ ጢሞ. 1፡15-18)፡- በዚያን ጊዜ የእስያ ክፍለ ሃገር የሮማ አውራጃዎች የሆኑትን ሊጽያን፥ ሚስያ፥ እና ፍርግያን ያጠቃልል ነበር። ጳውሎስ በሁለተኛው የወንጌል ጉዞው (የሐዋ.16፡6) በዚያ አካባቢ እንዳያገለግል ተከልክሎ ነበር፤ ነገር ግን በሦስተኛ ጉዞው የእስያ ዋና ከተማ በሆነች በኤፌሶን ለሦስት ዓመታት ያህል በመቆየት፥ ጠቅላላ አካባቢውን በወንጌል አዳረሰ (የሐዋ.19፤ 20፡31። በእስያ የነበሩት

ሰባት አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ በዚህ አካባቢ ነበሩ (ዮሐ. ራእይ 1:4፥ 11)።

ፊሎንሰና ሄርዋጌኔስ እነማን እንደ ነበሩ አናውቅም (2ኛ ጢሞ. 1:15) ጳውሎስን የተቃወሙና ወደ ሮም ስለእርሱ ለመሚገት ያልመጡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። እስያውያን አማኞች ከጳውሎስ ጎን መቆም እንደነበረባቸው ታስቡ ይሆናል፤ ነገር ግን፥ ይህን ከማድረግ ይልቅ፥ በእርሱ አፍረው ነበር፤ (ቢያስተውሉም ባያስተውሉም) በዚያኑ ጊዜ በክርስቶስም አፍረው ነበር (4:16 ተመልከት)።

ይህ በርግጥ ለጳውሎስ የጽልመት ጉም ያንጣበበት ሰዓት ነበር። ዴማስ ጥሎት ሄዷል (4:10)፤ ሌሎች ተባባሪዎች ወደ ሩቅ የአገልግሎት ቦታዎች ተልከዋል፤ የሐሰት ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተስፋፉ ነበር (2:17-18)። ጳውሎስ በነጻነት ቃሉን ለመስበክና እምነቱን ለመከላከል ምን ያህል ይወድ ነበር! ነገር ግን እርሱ በሮማ እስር ቤት ነበር። ሥራውን መፈጸም የጢሞቴዎስ ግዴታ ነበር።

ነገር ግን ኤፌሶንን ለመተው የደፈረና ጳውሎስን ለመርዳት ወደ ሮም የመጣ አንድ ሄኒሲፍሩ የተባለ ሰው ነበር። የስሙ ትርጉም «ትርፍ የሚያመጣ» የሚል ሲሆን፥ በእርግጥም ለጳውሎስ ትርፋማ ጓደኛ ነበር። በኤፌሶን ውስጥ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን የነበረ ሊሆን ይችላልል (በ1:18 «አገለገለኝ» የሚለው ዲያቆን የሚለውን ቃል ከሰጠን ቃል የመጣ ነው)። ጳውሎስ በኤፌሶን ውስጥ ባገለገለበት ጊዜ፥ ሄኒሲፍሩ ከቤተሰቡ ጋራ ታማኝ አገልጋይ ነበር። ጢሞቴዎስ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ስለነበር፥ ይህንን የተመረጠ ቅዱስ ሰው ሳያውቅ አይቀርም።

እዚህ ላይ እያንዳንዱ መጋቢ በጌታ ሥራ ውስጥ ለሚረዱት ታማኝ አባሎች የሚሰጠው ምስጋና እንዳለው ለመጥቀስ እፈላጋለሁ። እኔና ባለቤቴ ባገለገልንባቸው በሦስቱም አብያተ ክርሲያናት ውስጥ የተመረጡ ቅዱሳንን አግኝተናል፡- ቤታቸው ለኛ የተከፈተ ነበር (በዚያ መኖራችንን ለቤተ ክርስቲያን በሙሉ አልተናገሩም ነበር)። የእነዚህ ሰዎች ልብ የኛን ሸክምና መሻት የሚረዳ ነበር። ጸሎታቸውም በአስቸጋሪ ጊዜያት ውስጥ አጽንቶናል። እነዚህ አማኞች ከመድረኩ በስተጀርባ ያገለግልላሉ፤ ነገር ግን «በዚያን ቀን» (1:19) ጌታ በግልጥ ይሸልማቸዋል።

ሄኒሲፎሩ ከኤፌሶን ወደ ሮም ተጉዞ የእሥረኛውን ፍላጎት ለማገልገል ጳውሎስን በትጋት ጠበቀው። የቀድሞ መጋቢውን ማግኘት አስቸጋሪ መሰለው (1፡17)። ምናልባት አንዳንድ የሮም ክርስቲያኖች በመጀመሪያ እሥረኝነቱ ጊዜ እንደነበረ ጳውሎስን እስከ አሁን ይቃወሙት ይሆናል (ፊሊጵስዩስ 1፡12-17 ተመልከቱ)። ምናልባት የሮም ባለሥልጣናት የማይተባበሩና ምርጥ እሥረኛቸው ምንም ዓይነት እርዳታ እንዲቀበል አልፈለጉም ይሆናል። በመጀመሪያ እሥራቱ፥ ጳውሎስ በቤቱ ውስጥ ይኖር ነበር (ሐዋ. 28፡30)፤ ነገር ግን አሁን በሮማ እሥር ቤት ውስጥ በጽኑ ጥበቃ ውስጥ ነበር።

ነገር ግን ሄኒሲፎሩ በአሳቡ ጸና። ጳውሎስን አግኝቶ ከአጠገቡ ለመቆምና ለመርዳት የራሱን ሕይወት በአደጋ ውስጥ አስገባ። አንዳንድ ተመራማሪዎች ሄኒሲፎሩም ደግሞ እንደታሰረና ምናልባትም ሳይገደል እንዳልቀረ ያምናሉ። ይህን አሳባቸውንም፥ ጳውሎስ በ4፡19 ላይ «ለሄኒሲፎሩ ቤተሰዎች» ሰላምታ ሲያቀርብ፥ እርሱን ለይቶ ባለመጥቀሱ እውነታ ላይ ይመሠርታሉ። እንዲሁም ጳውሎስ ለቤተሰቡ በአሁኑ ጊዜ ምሕረት እንዲደረግላቸው ሲጠይቅ፥ ለሄኒሲፎሩ ግን የወደፊት ምሕረትን ጠይቋል (1፡16፥ 18)።

ነገር ግን ችግሩ ይህ ነው፡- ሄኒሲፎሩ ሞቶ ከሆነ፥ ጳውሎስ ለሞተ ሰው ጸሎት አድርጓል ማለት ነው (1፡18)፤ ዳሩ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሞተ ሰው ለመጸለይ ምንም ዓይነት ፈቃድ የለንም።

ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ በሚጽፍበት ጊዜ፥ ሄኒሲፎሩ ስለመሞቱ ምንም ማረጋገጫ የለንም። ጳውሎስ የእርሱን ስም ሳይጠቅስ፥ እግዚአብሔር ቤተሰቦቹን እንዲባርክ የጠየቀበት ምክንያት በቀላሉ በጊዜው ሄኒሲፎሩ ከቤተሰቡ ጋራ አልነበርም ማለት ነው። «በሮሜ ባደረ ጊዜ» (ቁ. 17) የሚለው፥ ይህ ጽሑፍ በሚጻፍበት ጊዜ ሄኒሲፎሩ በሮም እንዳልነበረ ያመለክታል፤ ስለዚህ በሮማና በኤፌሶን መካከል አንድ ቦታ ነበር፤ በመሆኑም ጳውሎስ ለርሱና ለቤተሰቡ ይጸልያል። በቅርቡ ጳውሎስ ከእርሱ ጋራ ብዙ ጊዜ ስላሳለፈ፥ ለሄኒሲፎሩ ሰላምታ መስጠት አስፈላጊ አልነበረም። ስለዚህም ጳውሎስ ለቤተሰቡ ብቻ ሰላምታ ይልካል።

ሄኒሲፎሩ በጳውሎስ ሠንሠለት አላፈረም ነበር። ሐዋርያው በቀን ለሃያ አራት ሰዓታት በሙሉ ከአንድ የሮማ ወታደር ጋራ በሰንሰለት እጁ ይታሠር ነበር። ሄኒሲፎሩ በኤፌሶን ለመቆየት ብዙ ምክንያቶችን ለመፍጠር ይችል ነበር፤ ነገር ግን አደገኛ የሆነ ጉዞ ወደ ሮም በማድረግ

ጳውሎስን አገለገለ። ጳውሎስ ስለዚህ ሰው አገልግሎት የሰጠው መግለጫ «ብዙ ጊዜ አሳርፎኛል» የሚል ነበር። የግሪኩ ቃል «እንደገና ማብረድ» ማለት ነው። አምፕሊፋይድ የተባለው የእንግሊዘኛ ትርጉም ደግሞ «እንደ ንጹህ አየር አወደኝ» ብሎ ተርጉሞታል። በፈተናችን ሰዓት «እንደ ንጹህ አየር» ስለሆኑ ክርስቲያኖች ጌታን እንዴት አድርገን እናመሰግናለን!

በጳውሎስ ደብዳቤ ባይሆን ኖሮ ሄኒሲፎሩ ጳውሎስንና ቤተ ክርስቲያንን እንዳገለገለ በፍጹም አናውቅም ነበር፤ ነገር ግን ጌታ ያውቅ ነበር፤ እናም ጌታ «በዚያን ቀን» ይሸልመዋል።

ለተሳካ አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች አልተለወጡም፡- እነርሱም ብርቱ ፍላጎት፥ የማያሣፍር ሥቃይ፥ እና መንፈሳዊ ታማኝነት ናቸው።

ሁኔታውን ማወቅ

2ኛ ጢሞቴዎስ 2

አንድን ትልቅ ስብሰባ ስካፈል አንድ ሰው በደረቱ ላይ ሁለት ስሞች መለጠፉን አስተዋልኩ። ለምን እንዲህ እንዳደረገ ስጠይቀው፡- «አ ማንነቴን የመለየት ችግር አለብኝ» ብሎ መለሰልኝ።

ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ማንነትን የመለየት ችግር እንዲያጋጥመው አልፈለገም። ስለዚህ መጋቢ ማን እንደሆነና ምን እንደሚያደርግ በጥንቃቄ ገለጸለት። (በእርግጥ እነዚሁ መመሪያዎች ለሁሉም ክርስቲያኖች ይሆናሉ።) ጳውሎስ የክርስቲያን አገልጋይን ሰባት መግለጫዎች አቅርቧል።

1. ባለ አደራ (2ኛ ጢሞ. 2፡1-2)

አገልግሎት ለራሳችን የምናገኘውና የምናስቀረው ነገር አይደለም። እኛ እግዚአብሔር ለሰጠን መንፈሳዊ ሀብት ባለአደራዎች ነን። አደራውን መጠበቅና በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ በሥራ ላይ ማዋል የኛ ኃላፊነት ነው። እነርሱም በተራቸው ለሚቀጥለው የአማኞች ትውልድ ቃሉን ማካፈል አለባቸው።

ዋናውን አሳባችንን ከሰዎች አስተሳሰቦችና ፍልስፍናዎች ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ቃል ማግኘታችን አስፈላጊ ነው። የዘመኑን አስተማሪዎች በታዋቂነታቸው፥ በትምህርታቸው ወይም በችሎታቸው አንመዝናቸውም። በእግዚአብሔር ቃል፥ በተለይም በጳውሎስ በተሰጡት የጸጋ ትምህርቶች እንፈትናቸዋለን። ጳውሎስን ትክክል ስለመሆኑ የምንፈትነው እኛ ሳንሆን፥ እኛን የሚፈትነን ጳውሎስ ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ጉልበት ይጠይቃል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተደበቁትን የበለጸጉ ማዕድናት «ወርቅ፥ ብር፥ የከበረ ድንጋይ» (1ኛ ቆሮ. 3፡10-23፤ ምሳሌ 2፡1-10፤ 3፡13-15፤ 8፡10-21 ተመልከት) ቆፍረን ማውጣት አለብን። ይህ ጉልበት ሊመጣ የሚችለው ከእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው። የጳውሎስ ታላቅ አገልግሎት ምሥጢሩ የእግዚአብሔር ጸጋ ነበር (1ኛ ቆሮ. 15፡10)።

የእግዚአብሔርን ቃል የማጥናት፥ የመረዳትና የማስተማር ችሎታ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ነው። «ለማስተማር የሚበቃ» የሚለው ከአንድ መጋቢ እግዚአብሔር ከሚፈልጋቸው መመዘኛዎች አንዱ ነው (1ኛ ጢሞ. 3፡2፥ 2ኛ ጢሞ. 2፡24)። «ለማስተማር የሚበቃ» የሚለው ለመማር የሚበቃ የሚለውን አሳብ ይዞአል፤ ስለዚህ አንድ ባለ አደራ ትጉህ የእግዚአብሔር ቃል ተማሪም መሆን አለበት።

2. ወታደር (2ኛ ጢሞ. 2፡3-4፥ 8-13)

ጳውሎስ ብዙ ጊዜ በመልእክቶቹ ውስጥ ወታደራዊ ገለጻዎችን ተጠቅሟል። በወታደራዊ ግዛት በመኖሩና ብዙ ጊዜ ራሱ በእሥር ቤት ውስጥ ስለነበር፥ ይህ አስደናቂ አይደለም። በእነዚህ ቁጥሮች የአንድን «የኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር» ባሕርያት ገልጿል። ሀ. መከራን ይቀበላል። (2ኛ ጢሞ. 2፡3)፡- ብዙ ሰዎች የመጋቢነት አገልግሎት ቀላል ሥራ እንደሆነ ያስባሉ። ሰባኪያን ብዙውን ጊዜ ሰነፎች እንደሆኑና ደሞዛቸውን በመቀበላቸው ሊያፍሩ እንደሚገባቸው ለሚያመለክቱ ቀልዶች ዒላማዎች ናቸው፤ ነገር ግን ራሱን የሰጠ ክርስቲያን አገልጋይ መንፈሳዊ ጽናትን በሚጠይቅ ውጊያ ውስጥ ነው (ኤፌሶን 6፡10-12 ተመልከቱ)። ለ. ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም (2ኛ ጢሞ. 2፡4)። ላስከተተው የጦር አዛዥ ሙሉ ለሙሉ ራሱን የሰጠ ነው። በእኛ ሁኔታ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በእርስ በርስ ጦርነት ወቅት አንድ ሰዓት ሠሪ የነበረ ወታደር የተነገረው ታሪክ ትዝ ይለኛል። አንድ ቀን የማስጠንቀቂያ ጥሩምባ ድምፅ አሰማና ሰዎቹ ካምፕ እንዲለቁ ተነገራቸው። ወታደሩ «አሁን መሄድ አልችልም» ደርዘን የሚሆኑ የሚጠገኑ ሰዓቶች አሉኝ» ብሎ አጉረመረመ። አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናቸው እነርሱን ለመደገፍ ስለማትችል አንድ መጋቢ ወይም የመጋቢ ሚስት ተቀጥሮ ወይም ተቀጥራ መሥራት አስፈላጊ ይሆናል። ይህ በእነርሱ በኩል መሥዋዕትነት ሲሆን፥ በሥራው ላይ ደግሞ ትርፍ ማስገኘት ነው፤ ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ድጋፍ የሚያገኝ መጋቢ ፍላጎቱን በሚከፋፍሉና አገልግሎቱን በሚያዳክሙ ተቀጽላ ነገሮች መያዝ የለበትም። ብዙ ጊዜያቸውን ከቤተ ክርስቲያናቸው ይልቅ በራሳቸው የርስት ጉዳይ ላይ የሚያሰልፉ መጋቢዎች አጋጥመውኛል። ዓላማችን ጌታን ደስ ማሰኘት እንጂ፥ ራሳችንን አይደለም።

ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስን ከፍ ያደርጋል (2ኛ ጢሞ. 2፡8-9)፡- «ኢየሱስ ክርስቶስን አስብ» ተብሎ ነው ይህ ሐረግ ሊተረጎም የሚገባው። ልክ በውጊያ ስልት የታወቀውን የጦር አዝማች ስም እየጠሩ ለምሳሌ

ዘራፍ፥ ዘራፍ፥ አካኪ ዘራፍ፤ ብለው እንደሚያሰሙት የጦርነት የጥሪ ጩኸት ድምፅ ይመስላል። ኢየሱስ የመዳናችን ራስ ነው (ዕብራውያን 2፡10)፤ ስለዚህ የኛ ዓላማ ሞገስንና ክብርን ለርሱ ማምጣት ነው። ለሚሠቃይ ክርስቲያን ወታደር ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ያህል ማበረታቻ ነው! መከራን መቀበል ወደ ክብር እንደሚመራና የተሸነፉ መምሰል ወደ ድል እንደሚመራ በማስመስከር ክርስቶስ ሞቶ እንደገና ተነሣ። ኢየሱስ እንደ ክፉ አድራጊ ተቆጥሮ ስለነበረ፥ የእርሱ ወታደሮችም በተመሳሳይ ሁኔታ ይታያሉ።

ክርስቶስን ከፍ ለማድረግ ጥሩው መንገድ በቃሉ አገልግሎት ውስጥ ነው። ጳውሎስ ታሥሮ ነበር፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ሊታሠር አይችልም። «ቃሉም እጅግ ፈጥኖ ይሮጣል» [መዝ. (147)፡15] «የእግዚአብሔር ቃል ያድግና ይበዛ ነበር» (የሐዋ. 12፡24)።

መ. ስለ ጠቅላላው ሠራዊት ያስባል። (2ኛ ጢሞ. 2፡10)፡- «የተመረጡት» በጸጋው የተለዩና በመንፈሱ የተጠሩት የእግዚአብሔር ሕዝብ ናቸው (2ኛ ተሰ. 2፡13-14)። ጳውሎስ መከራን የተቀበለው ለጌታ ብሎ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያንም ጭምር ነው። ብዙዎችን በወንጌል መድረስ እንዲቻል ለመርዳት ፈለገ። ስለ ራሱ ብቻ የሚያስብ ወታደር ታማኝ ያልሆነና ሊደገፉበት የማይበቃ ነው።

ሠ. የጦር አዛዡን ያምናል (2ኛ ጢሞ. 2፡11-13)፡- ይህ «የታመነ አባባል» ምናልባት በአማኞች ይባል የነበረ የቀድሞ የእምነት መግለጫ ክፍል ሊሆን ይችላል። (በመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች «የእምነት አባባሎች» 1ኛ ጢሞ. 1፡15፤ 4፡9 እና ቲቶ 3፡8ን ተመልከት)። ድልን የሚሰጠን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለን እምነት ነው (1ኛ ዮሐ. 5፡4)። ጠላቶቹን እርሱ ስላሸነፋቸው፥ ልንፈራቸው አይገባም። ከክርስቶስ ጋር በሞቱ፥ በመቀበሩና በትንሣኤው በመተባበራችን፥ ድልን አግኝተናል (ሮሜ 6 ተመልከት)።

ምን ዓይነት የተቃራኒ አሳቦች ግንኙነት ነው! ሞት ወደ ሕይወት ይመራል! መከራ በክብር ወደ መግዛት ይመራል! ምንም የምንፈራው ነገር የለንም! ዋናው ነገር ጌታችንን እንዳንክደው ነው፤ ምክንያቱም እዚህ ከካድነው፥ እርሱ በአባቱ ፊት ይክደናል (ማቴ. 10፡33)። በዚያ

በክብር በሚሆነው ታላቅ «የስም ጥሪ» ላይ ሜዳልያዎቹ ሲሰጡ፥ ስሙን ከካድን ሽልማታችንን እናጣለን።

ነገር ግን ጳውሎስ የእኛ መጠራጠርና አለማመን እንኳን እርሱን እንደማይለውጠው ግልጽ አድርጓል። «የታመነ ሆኖ ይኖራል፤ ራሱን ሊክድ አይችልምና» (2ኛ ጢሞ. 2፡13)። እምነትን በራሳችን እምነት ወይም ስሜቶች ላይ አናደርግም፥ ምክንያቱም እነሱ ስለሚለወጡና ስለሚወድቁ ነው። እምነታችንን በክርስቶስ ላይ እናስቀምጣለን። ታላቁ ወንጌላዊ ጄ ሀድሰን ቴይለር ብዙ ጊዜ እንዲህ ይል ነበር፡- «ድሉን የምንጎናጸፈው ታማኝ ለመሆን በመሞከር ሳይሆን፥ ታማኝ የሆነውን በማየት ነው።»

3. ስፖርተኛ (2ኛ ጢሞ. 2፡5)

ጳውሎስ በጽሑፎቹ አንዳንድ ጊዜ ስፖርታዊ ገለጻዎችን ተጠቅሟል፡- እነርሱም ነጻ ትግል፥ ቦክስ (ቡጢ)፥ ሩጫ፥ እና ልምምድ ናቸው። ግሪኮችና ሮማውያን ለስፖርት ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበራቸው የኦሎምፒክና የስእትሚያን ውድድሮች ለእነርሱ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ነበሩ። ቀደም ሲል ጳውሎስ ጢሞቴዎስን፥ እንደ ሯጭ ልምምድ እንዲያደርግ አሳስቦታል (1ኛ ጢሞ. 4፡7-8)። አሁን ጳውሎስ ሕጎቹን እንዲያከብር ይመክረዋል።

በሩጫ ውድድር ለማሸነፍና አክሊል ለማግኘት የሚጥር ሰው፥ የውድድሩን መመሪያዎች (ሕጎች) ለመጠበቅ መጠንቀቅ አለበት። በግሪክ ጨዋታዎች በተለይ፥ ዳኞቹ ሕግጋቱን በማስጠበቁ ረገድ በጣም ጥንቁቆች ነበሩ። እያንዳንዱ ተወዳዳሪ የሀገሩ ዜጋና መልካም ስም ያለው መሆን ነበረበት። ለውድድሩ ጊዜ በሚዘጋጅበት ወቅት፥ የተወሰኑ መመዘኛዎችን መከተል ነበረበት። አንድ ተወዳዳሪ ሯጭ በማንኛውም ነገር ጎዶሎ ሆኖ ከተገኘ፥ ከውድድር ውጪ ይሆናል። ተወዳድሮ ካሸነፈም በኋላ፥ አንድ ሕግ ጥሶ ቢገኝ አክሊሉን ያጣል። ጂም ቶርፕ የተባለ ታላቅ አሜሪካዊ አትሌት፥ የኦሎምፒክን ሕግ በሚጥስ መንገድ የስፖርት ውድድሮችን ስላደረገ፥ የኦሎምፒክ ሜዳሊያዎቹን አጥቷል።

በሰው አመለካከት፥ ጳውሎስ ተሸናፊ ነበር። «በእስያ ያሉት ሁሉ» ከእርሱ ፈቀቅ ብለው ስለነበረ (1፡15)፥ በመመልከቻ ቦታዎች ላይ ቆሞ እያጨበጨበ የሚያበረታታው አልነበረም። እንደ ክፉ አድራጊ፥ በእሥር ቤት ውስጥ ይሠቃይ ነበር፥ ሆኖም ጳውሎስ አሸናፊ ነበር። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተዘረጉትን ሕግጋት ጠብቆ ስለነበር፥ አንድ ቀን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሽልማቱን ይቀበላል። ጳውሎስ

ለወጣቱ ጢሞቴዎስ፡- «ሰዎች ምንም ነገር ቢናገሩ፥ ዋናው ነገር አንተ የእግዚአብሔርን ቃል መታዘዝህ ነው። ሩጫውን የምትሮጠው ሰዎችን ለማስደሰት ወይም ለራስህ ዝናና ከበሬታ ለማትረፍ ሳይሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ደስ ለማሰኘት ነው» ይል ነበር።

4. ገበሬ (2ኛ ጢሞ. 2፡6-7)

ይህ በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ የሚገኝ ሌላው ምርጥ ሥዕላዊ አገላለጽ ነው። አንድ ጊዜ ጳውሎስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ሁሉም አማኞች በአንድነት ከሚሠሩበት እርሻ ጋር አወዳድሯል (1ኛ ቆሮ. 3፡5-9)። እያንዳንዱ ክርስቲያን የሚፈጽመው የተወሰነ ሥራ አለው። ይህም ማረስ፥ መዝራት፥ ማጠጣት ወይም ማጨድ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን የሚያሳድግ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

በገበሬውና በእርሻው መግለጫ ውስጥ ብዙ ተጨባጭ እውነቶች ይገኛሉ። በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ገበሬ መሥራት አለበት። እርሻን ለራሱ ከተወው፥ በብዛት አረሞችን ያበቅላል። ሰለሞን ስለታካች ሰው እርሻ ሲጽፍ፥ ይህ እውነት በአእምሮው ውስጥ ነበረ። (ምሳ. 24፡30-34)። እውነተኛ አገልግሎት ከባድ ሥራ ነው፤ ስለዚህም መጋቢውና የቤተ ክርስትያን አባላት አንድ ገበሬ በእርሻው ውስጥ በትጋት እንደሚሠራ፥ በመንፈሳዊ እርሻቸው ውስጥ በትጋት መሥራት አለባቸው። መጋቢዎች የሰዓት ፊርማ አይፈርሙም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ፊሽካ እንደነፋላቸው ሁሉ፥ በጠዋት መነሳትና በሥራቸው ላይ መገኘት አለባቸው።

ገበሬ ትዕግሥት ያስፈልገዋል። «እነሆ ገበሬው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሠ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል» (ያዕ. 5፡7)። አንድ መጋቢ የሆነ ጓደኛዬ ብዙ ጊዜ እንዲህ ይለኝ ነበር፡- «መከሩ የሰብሰባው ፍጻሜ አይደለም የዘመኑ ፍጻሜ ነው» ይለኝ ነበር።

ገበሬ ከመከሩ ድርሻውን ሊያገኝ ይገባዋል። «የሚደክመው ገበሬ ፍሬውን ከሚበሉት መጀመሪያ እንዲሆን ይገባዋል» (2ኛ ጢሞ. 2፡6)። ጳውሎስ እዚህ ጋ ታማኝ መጋቢ «በቤተ ክርስቲያን ድጋፍ ማግኘት እንዳለበት እየገለጸ ነው። ተመሳሳይ አሳብ ጳውሎስ ነጥቡን ለማስረዳት ወታደርን፥ ገበሬን፥ እረኛን በተጠቀመበት በ1ኛ ቆሮ. 9፡7 ላይ ይገኛል፤ «ለሠራተኛ ደምወዙ ይገባዋል» (1ኛ ጢሞ. 5፡18)። ጳውሎስ ማንም ሰው ወንጌልን ለግል ጥቅም ማግኛ አደረገው ብሎ እንዳይከስሰው ገንዘብ የማግኘት መብቱን ሆነ ብሎ ተወው (1ኛ ቆሮ.

9፡14-18)፤ ነገር ግን ይህ መመሪያ ለሁሉም የእግዚአብሔር ሰዎች አስፈላጊ አይደለም።

አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስታድግና ስትስፋፋ (ስትበዛ)፥ ሕዝቡ ለመጋቢያቸውና ለሌሎች ሠራተኞች ያላቸውን ድጋፍ በታማኝነት ማሳደግ አለባቸው። «እኛ መንፈሳዊን ነገር የዘራንላችሁ ከሆንን የእናንተን የሥጋዊን ነገር እኛ ብናጭድ ትልቅ ነገር ነውን?» (1ኛ ቆሮ. 9፡11)። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ገንዘባቸውን የሚያጠፉበትንና ለራሳቸው ሠራተኞች ጥንቃቄ ከማድረግ የሚታቀቡበትን ማየት የሚያሳዝን ነው። እግዚአብሔር ታማኝ ባሪያዎቹን የምታከብረውን ቤተ ክርስቲያን ያከብራል።

ስለዚህ ስለ ገበሬ ምሳሌ ሌላ እውነት አለ፡- ለሕዝቡ ቃሉን የሚያካፍሉ መንፈሳውያን መሪዎች በረከቶቹን ለማግኘት የመጀመሪያዎቹ ናቸው። ሰባኪውና አስተማሪው ሁልጊዜ ከሰሚዎቹ ይልቅ ከስብከቱ ወይም ከትምህርቱ ብዙ ነገር ያገኛሉ፤ ምክንያቱም በዝግጅት ወቅት ብዙ ነገር ከውስጣቸው ስለሚያስቀሩ ነው። የተዘሩ ዘሮች በሌሎች ሕይወት ውስጥ ፍሬ ሲያፈሩ በማየትም ትልቅ ደስታ ያገኛሉ። ግብርና ከባድ ሥራ በመሆኑ፥ ብዙ ተስፋ የሚያስቆርጡ ነገሮች ሊኖሩት ይችላሉ፤ ነገር ግን ውጤቶቹ ይህን ሁሉ የሚክሱ ናቸው።

5. ሠራተኛ (2ኛ ጢሞ. 2፡14-18)

በዚህ አንቀፅ ውስጥ ትኩረት የተሰጠበት ነገር ሠራተኛው ሥራው ሲፈተን እንዳያፍር፥ በሥራው ትጉህ መሆን እንዳለበት ነው። «በትክክል መከፋፈል» ማለት «በቀጥታ መቁረጥ» ማለት ሲሆን፥ ለብዙ የተለያዩ ሥራዎች ሊያገለግል ይችላል፡- ለምሳሌ በቀጥታ መስመር ማረስ፥ ቀጥተኛ እንጨት መቁረጥ፥ ጠርዞችን በቀጥታ መስፋት ነው።

መጋቢው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሠራተኛ ነው። ቃሉ ባለአደራው ሊጠብቀውና ሊሠራበት የሚገባው የከበረ ሀብት ነው። የወታደሩ ሰይፍና የገበሬው ዘር ነው። እንዲሁም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመገንባት፥ ለመለካትና ለመጠገን የሚሆን የሠራተኛው መሣሪያም ነው። ቃሉን በትክክል የሚጠቀሙ ሰባኪና አስተማሪ ቤተ ክርስቲያናቸውን እግዚአብሔር እንዲገነባ በሚፈልገው ዓይነት መንገድ ይገነባሉ፤ ነገር ግን ጠማማ ሠራተኛ ለራሱ ለማድረግ የሚፈልገውን እንዲል የእግዚአብሔርን ቃል በማታለል የሚጠቀም ነው (2ኛ ቆሮ. 4፡2)። የሚያሳዝነው ግን፥ በቤተ ክርሲትያኖቹ ውስጥ ያሉንን

አገልግሎቶች እግዚአብሔር በሚፈትንበት ጊዜ፥ አንዳንዶቹ አመድ ይሆናሉ (1ኛ ቆሮ. 3፡10-15)።

ተፈትኖ የወጣ ሠራተኛ ቃሉን በትጋት በማጥናት፥ ከራሱ ሕይወት ጋር ለማዛመድ ይፈልጋል። የሚያሳፍር ሠራተኛ በሌሎች «ሃይማኖታዊ ጉዳዮች» ጊዜውን ስለሚያባክን፥ ለክፍሉ ወይም ለጉባኤው የሚሰጠው ብዙ ጥቅም የለም። ተፈትኖ የወጣ ሠራተኛ «በማይረባ ቃል» በመጣላት ጊዜውን አያጠፋም (2ኛ ጢሞ. 2፡14)፤ ምክንያቱም የዚህ ዓይነቱ ክርክር የእግዚአብሔርን ሥራ እንደሚያዳክም ስለሚያውቅ ነው (1ኛ ጢሞ. 6፡14 እና ቲቶ 3፡9ን ተመልከት)።

ተፈትኖ የወጣ ሠራተኛ ከ«ከንቱ መለፍለፍ» ይርቃል (2ኛ ጢሞ. 2፡16 እና 1ኛ ጢሞ. 6፡20 ተመልከት)፥ ምክንያቱም ይህ በበለጠ ከእግዚአብሔር እንደሚያርቅ ስለሚያውቅ ነው። በአንዳንድ «የጎብረት ጊዜዎች» ደህና የተባሉ ሰዎች መንፈሳዊ አላዋቂነታቸውን ሲለዋወጡ ከጥቅም ይልቅ ጉዳቱ እንዳያመዝን እፈራለሁ።

ተፈትኖ የወጣ ሠራተኛ ሐሰተኛ ትምህርት አደገኛ መሆኑን ስለሚያውቅ፥ ይቃወመዋል። ጳውሎስ ከጭንቁር ጋር አመሳስሎታል (2ኛ ጢሞ. 2፡17)። ጭንቁር ወደ ሌላው የሰውነት ክፍል እንደሚስፋፋ፥ እንደሚበክልና እንደሚገድል ሁሉ፥ ሐሰተኛ ትምህርትም ተስፋፍቶ የአማኞችን አካል ማለትም ቤተ ክርስቲያንን ይበክላል። ይህ ብክለት መገለጥና መወገድ አለበት። ቤተ ክርስቲያንን ጤናማ እድገት ሊኖራት የሚችለው የእግዚአብሔርን ቃል «ስታስተምር» ብቻ ነው።

ጳውሎስ ሐሰተኛ አስተማሪዎች የነበሩበትን ሁለት ሰዎች ጠቅሷል። ደግሞም ስሕተታቸውን ለይቶ አሳይቷል። እዚህ ላይ ሔሜኔዎስ ተብሎ የተጠራው (2ኛ ጢሞ. 2፡17)፥ በ1ኛ ጢሞ. 1፡20 ላይ የተጠቀሰው ሰው ሳይሆን አይቀርም። ስለ ግብረአበሩ ስለ ፊሊጦስ የምናውቀው ነገር የለም። ሁለቱም ትንሣኤ ሙታን ከአሁን ቀደም ሆኗል ብለው በማስተማር «ስለ እውነት ስተዋል»። ምናልባትም ደኅንነት በመንፈሳዊ መልኩ የሆነ ትንሣኤ ነው፤ ስለዚህ አንድ አማኝ የሥጋን ትንሣኤ መጠበቅ የለበትም ብለው አስተምረው ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን አካላዊ ትንሣኤን መካድ አደገኛ ነገር ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡12-19 ተመልከት)፥ ምክንያቱም ይህ የክርስቶስን ትንሣኤና የእግዚአብሔርን ሕዝብ የማዳን ዕቅድ ፍጻሜ የሚያካትት ስለሆነ ነው። እነዚህ ሐሰተኛ አስተማሪዎች «የአንዳንዶችን እምነት መገልበጥ» መቻላቸው አስደናቂ

አይደለም (2ኛ ጢሞ. 2፡18)። ትንሣኤ ሙታን የወንጌል መሠረታዊ እውነት ነው።

እንደ እግዚአብሔር ሠራተኛ ከእኛ እያንዳንዱ ሰው ተቀባይነት ያገኘል አሊያም ሐፍረትን ይከናነባል። ተቀባይነት ማግኘት የሚለው ቃል «ተፈትኖ ያለፈ» ማለት ነው። ቃሉ ብረታ ብረትን ለመፈተንና ለማሳለፍ የሚያገለግል ነው። የምናልፍበት እያንዳንዱ ፈተና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማግኘት ቃሉን እንድናጠና ያስገድደናል። ቃሉን በትክክል ስንጠቀምበት፥ ፈተናዎቻችንን ለማሸነፍ እንችላለን። ደግሞም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እናገኛለን። ማርቲን ሉተር አንድ ጊዜ ጸሎት፥ ጥናትና መከራ አንድን መጋቢ ይሠሩታል ብሏል፤ ይህም እውነት ነው። ካልተፈተንን ተቀባይነትን ልናገኝ አንችልም።

«ማፈር» ማለት ምን ማለት ነው? በእርግጠኝነት ይህ ማለት የሠራተኛው ሥራ ከመመዘኛ በታች በመሆኑ፥ ተቀባይነት ሳያገኝ ሲቀር ማለት ነው። ይህ ማለት ዋጋን (ደመወዝን) ማጣት ማለት ነው። እንዲያውም በጳውሎስ ጊዜ አንድ ግምበኛ ዝርዝሮቹን ተከትሎ ካልሠራ በገንዘብ ይቀጣ ነበር። ጌታ የእኛን ሥራዎች ሲገመግም እንደ ሠራተኞች የእግዚአብሔርን ቃል በቅንነትና በጥንቃቄ ይዘን እንደሆነ ይገለጣል። አሁን ፈተኞች የሆኑ አንዳንዶች ኋለኞች ይሆናሉ!

6. ዕቃ (2ኛ ጢሞ. 2፡19-22)

በዚህ ማብራሪያ ጳውሎስ አንድን «ትልቅ ቤት» ማለትም የክርስትናን ስም የያዘ ቤተ ክርስቲያን መሆኑን ገልጿል። የቤቱ መሠረት የእግዚአብሔር ማኅተም ስላለበት፥ የተጠበቀና የተደላደለ ነው፤ (በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማኅተም የባለቤትነትና የዋስትና ምልክት ነው። የሮማውያንን ማኅተም ለመስበር ማንም አይደፍርም ነበር።) ጳውሎስ ከሙሴ መጽሐፍ ጠቅሷል፡- «ጌታ የእርሱ የሆኑትን ያውቃል» (ዘኁ. 16፡5)። ይህ በእግዚአብሔር በኩል የሚሆነውን የክርስቲያን ሕይወትን ያሳያል፡- እግዚአብሔር የምናምነውን እኛን እንደ እርሱ ምርጦች አድርጎናል። (2ኛ ጢሞ. 2፡10ን ተመልከት)።

ነገር ግን በሰው በኩል መፈጸም ያለበት የክርስትና ሕይወት ሁኔታም አለ፡- «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዓመፅ ይራቅ» (2፡19)። ይህ እግዚአብሔር በዘኁ 16፡26 ሕዝቡን ከቆሬና ከዓመፀኞች ድንኳን እንዲርቁ ያስጠንቀቀበትን ክፍል ወደ ኋላ ተመልሶ ይጠቅሳል። በሌላ አነጋገር፥ የእግዚአብሔር ምርጦች የሆኑ ሰዎች መመረጣቸውን፥

እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት በመኖር ያስመሰክራሉ። «ቅዱሳንና ነውር የሌለን እንሆን ዘንድ» በክርስቶስ ተመርጠናል (ኤፌ. 1፡4)።

ይህ ትልቅ ቤት የታተመ ጠንካራ መሠረት ያለው ብቻ ሳይሆን፥ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያገለግሉ ዕቃዎችም (የተለያዩ ዓይነት ቁሳቁሶች) አሉት። ጳውሎስ ቁሳቁሶቹን በሁለት ክፍሎች ይከፍላቸዋል፡- የከብር የሆኑ (ወርቅና ብር) እና የውርደት የሆኑ (እንጨትና ሸክላ)። ይህም የክርስቲያን ዓይነቶችን መለየቱ ሳይሆን፥ ነገር ግን በቃሉ እውነተኛ አስተማሪዎችና በገለጻቸው ሐሰተኛ አስተማሪዎች (2ኛ ጢሞ. 2፡16-18) መካከል ያለውን ልዩነት እያሳየ ነው። ታማኝ መጋቢ ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብርን የሚያመጣ እንደ ወርቅ ወይም እንደ ብር ዕቃ ነው። የአንድ ቤት ባለቤት ዋጋ ያላቸውንና የተዋቡ ቁሳቁሶችን ፊት ለፊት በማስቀመጥ ለራሱ ክብርን ያገኛል። በለንደን ከፍተኛ ግምብ ውስጥ የሚገኙትን የኢንግላንድን የዙፋን ጌጦች በዋጋ ከማይተመኑ የጠረጴዛ ዕቃዎችና ቁሳቁሶች ጋር ያየሁበትን የመጀመሪያ ጊዜ አስታውሳለሁ። በግርማቸውና በውበታቸው ተመስጬ ነበር። እግዚአብሔር ቃሉን በታማኝነት ለሚያገለግሉ ሠራተኞቹ የሚሰጠው ውበት የዚያን ዓይነት ነው።

ሐሰተኛ አስተማሪዎች እርባና የሌላቸው ናቸው፤ እንደ እንጨትና ሸክላ ናቸው። ምንም ያህል ዛሬ ተወዳጅ ቢሆኑም ለውርደት የተሠሩ ቁሳቁሶች ናቸው። እንጨትና ሸክላ የእሳትን ፈተና አይቋቋሙም። ጢሞቴዎስ የሚለው ስም በአንድነት «እግዚአብሔርን የሚያስከብር» የሚል ትርጉም ከሚሰጡ ከሁለት የግሪክ ቃላት እንደመጣ ማስተዋል ጠቃሚ ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንደሰሙ እንዲኖር እያበረታታው ነበር!

ዋናው ነገር የከበሩት ዕቃዎች በተዋረዱት እንዳይቆሽሹ ነው። «ከእነዚህ» የሚለው ቃል የሚጠቅሰው የውርደት ዕቃዎችን ነው (2፡21)። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ራሱን ከሐሰተኛ አስተማሪዎች እንዲለይ አጥብቆ ይመክረዋል። ይህንን ካደረገ እግዚአብሔር ያከብረዋል፤ ይለየዋል፤ እንዲሁም ለአገልግሎት ያስታጥቀዋል። «ለጌታውም የሚጠቅም» (2፡21) ያ እንዴት ያለ ታላቅ ክብር ነው! ጠቃሚ የክብር ዕቃ የሆነ ሰው በዓለም ተወዳጅ ለመሆን በሃይማኖት ሰዎች መካከል እንኳ የማይገባ ክብርን አይፈልግም። ቅዱስ ሆኖ መኖር አለበት፥ ይህ ማለት ደግሞ ከሚያረክሰው ከማንኛውም ነገር መለየት አለበት ማለት ነው።

ይህ የሥጋ ኃጢአቶችንም ያካትታል (2፡22)። ጳውሎስ ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያዎችን በ1ኛ ጢሞ. 6፡11-12 ተጠቅሟል «ሽሽ ... ተከተል ... ተጋደል»። እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለየት ሚዛናዊ ነው፡- ኃጢአትን እንሸሻለን፤ ነገር ግን ጽድቅን እንከተላለን። ሚዛናዊ ካልሆንን፡- ከመለየት ይልቅ ገለልተኞች እንሆናለን። በእርግጥ የእግዚአብሔር ሰው ጳውሎስ «በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር» ኅብረት እንድናደርግ ያዘናል (2ኛ ጢሞ. 2፡22)። እንዲያውም የቃሉ አገልግሎት ዓላማ ይህ ነው (1ኛ ጢሞ. 1፡15)። እውነተኛ አማኞች ከተሳሳተ የመለየት አመለካከት የተነሣ ገለልተኞች መሆናቸው የሚያሳዝን ነው።

እግዚአብሔር እንደ ዕቃ ሊጠቀምብን እንዲችል፥ ባዶ፥ ንጹሕና የተዘጋጀን መሆን አለብን። እርሱ ይወስደንና ይሞላናል፤ ከዚያም ለክብሩ ይጠቀምብናል፤ ዳሩ ግን በኃጢአት ከተሞላን ወይም በአለመታዘዝ የረከሰን ከሆንን፥ በመጀመሪያ ያነጻናል፥ ይቀጣናል፤ ያ ደግሞ የሚያስደስት ልምምድ ላይሆን ይችላል። በ«ትልቁ ቤት» ውስጥ ወይም የክርስትናን ስም በሚሸከሙ ሕዝብ መካከል እውነተኛና ሐሰተኛ አማኞች አሉ። መንፈሳዊ ግምገማ ማካሄድና ለክብር የተቀደሰን ዕቃዎች እንድንሆን መጠንቀቅ አለብን።

7. ባሪያ (2ኛ ጢሞ. 2፡23-36)

«ባሪያ» (2፡24) በግሪክ ዱሉስ ሲሆን፥ ትርጉሙም በትክክል «ባሪያ» ማለት ነው፤ ስለዚህ ጳውሎስ ራሱን «የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ» ብሎ ጠርቷል (ሮሜ 1፡1፤ ፊሊ. 1፡1)። ባሪያ ሙሉ በሙሉ በጌታው ትእዛዝ ሥር የሚተዳደር እንጂ፥ የራሱ ፈቃድ የለውም። አንድ ጊዜ እኛ ክርስቲያኖች የኃጢአት ባሪያዎች ነበርን አሁን ግን የእግዚአብሔር ባሪያዎች ነን (ሮሜ. 6፡16-19)። በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደ ነበረ ባሪያ «ጌታዬን እወዳለሁ ... ነጻ አልወጣም» (ዘጸ. 21፡5) እንላለን።

ለእግዚአብሔር ባሪያ ቃሉን ማስተማር ቀላል አይደለም። ሰይጣን ይቃወመዋል፤ ሰሚዎቹንም ሊያጠምድ ይሞክራል (2ኛ ጢሞ. 2፡26)። ደግሞም አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሮአቸው (ትምህርት ለመቀበል) የሚያስቸግሩ ናቸው። «የሰነፎችንና ያልተማሩትን ምርመራ» ይወዳሉ (2፡23)፤ የሚያሳድገውንም የእግዚአብሔርን ቃል ለመብላት ፍላጎት የላቸውም። በውስጡ ካላለፉ በስተቀር፥ ለአንዳንድ

ሰዎች መንፈሳዊ እውነትን ማካፈል ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ መረዳት አይቻልም።

እነዚህን አስቸጋሪ ሰዎች ችላ ማለት ምንኛ በቀለለ ነበር፤ ግን ያኔውኑ ሰይጣን ያገኛቸዋል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ጥልን የሚፈጥሩ ክርክሮችን እንዲያርቅ እንጂ፥ ሰዎችን እንዳያርቅ አስጠንቅቆታል። መከራከር ወይም መጣላት የለበትም። የእግዚአብሔርን ቃል በቅንነት የሚያስተምር ታጋሽና ትሁት አገልጋይ መሆን አለበት። ስሕተትን መግለጥና ስሕተት እንደሆነ ማስረገጥ ብቻ በቂ አይደለም። በተጨማሪም ጠቃሚ እውነቶችን ማስተማርና ቅዱሳንን በእምነት መመሥረት አለብን።

የእግዚአብሔር ባሪያ የሚቃወሙትን ማስተማር አለበት። ምክንያቱም ይህ እነርሱን ከሰይጣን እሥራት ሊታደጋቸው የሚችልበት ብቸኛ መንገድ ስለሆነ ነው። ሰይጣን ሐሰተኛ (ውሸታም) ነው (ዮሐ. 8፡44)። በሔዋን እንዳደረገው ሰዎችን በሐሰተኛ ተስፋዎቹ ያጠምዳል (ዘፍ. 3ና 2ኛ ቆሮ. 11፡3ን ተመልከት)። የባሪያ ዓላማ ክርክሮችን ማሸነፍ ሳይሆን ነፍሳትን መማረክ ነው። የተታለሉ ሰዎች በንስሐ ሲመለሱና «ተሳስቼ ነበር - አሳቤን ቀይሬአለሁ» ብለው እውነትን ሲቀበሉ ለማየት ይሻል።

«ይመለሳሉ» (2ኛ ጢሞ. 2፡26) የሚለው ቃል ከስካር መንፈስ የተላቀቀውን ሰው ይገልጻል። ሰይጣን በራሱ ውሸቶች ሰዎችን ያሰክራል፥ የባሪያው ሥራ ደግሞ ራሳቸውን እንዲያውቁ ማድረግና እነሱን መታደግ ነው። በቁጥር 26 ላይ ያለው የመጨረሻ ሐረግ በ3 መንገድ ሊተረጎም ይችላል፡- (1) ፈቃዱን እንዲያደርጉ ባሪያ አድርጎ ከወሰዳቸው ከዲያቢሎስ ወጥመድ ነጻ ወጥተዋል (2) የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ በእግዚአብሔር ባሪያ በኩል ተማርከዋል፤ (3) ባሪያ አድርጎ ወስዷቸው ከነበረው ከዲያብሎስ ወጥመድ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ነጻ ወጥተዋል። እኔ ሦስተኛውን ትርጉም እመርጣለሁ።

እነዚህን ሰባት የአገልግሎት ሥራ ክፍሎች ስትመረምር፥ ሥራው ምን ያህል አድካሚ እንደሆነ ማየት ትችላለህ። አገልግሎቱ ሥነ-ሥርዓትንና ሥራን ስለሚጠይቅ፥ ጊዜውን እንዲሁ ለሚያቃጥል ሰነፍ ስፍራ የለውም። የሚዋጋቸው ጠላቶችና ሊጠናቀቁ የሚገባቸው ሥራዎች ስላሉ፥ ለታካች ሰው ቦታ የለውም።

የቤተ ክርስቲያን አባላት ለመጋቢዎቻቸው መጸለይና በጌታ ሥራ ውስጥ ማበረታታት ይገባቸዋል። የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት መጋቢዎች ራሳቸውን ለራሳቸው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፥ ሥራቸውን በታማኝነት መሥራት አለባቸው (የሐዋ. 6:1-7ን ተመልከት)። አብያተ ክርስቲያናት አገልጋዮቻቸው ሙሉ በሙሉ ለአገልግሎት ሥራ ራሳቸውን መስጠት እንዲችሉ፥ በቂ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው።

በሌላ አነጋገር፥ አገልጋዮችና ምእመናን በጌታ ሥራ ውስጥ አብረው መድከም አለባቸው።

ከማለቁ በፊት ምን ማድረግ እንደሚገባ

2ኛ ጢሞቴዎስ 3

የዚህ ምዕራፍ አትኩሮት በእውቀትና በኃላፊነት ላይ ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ስለ መጨረሻው ዘመን ባሕርይ ካስታወቀው በኋላ፥ እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለበት መመሪያ ይሰጠዋል። ተግባር በእውቀት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። ብዙ ክርስቲያኖች ወዴት እንደሚሄዱ የማያውቀውን የአሮጥላን ነጂ ይመስላሉ። እርሱ ለተሳፋሪዎቹ «መንገዱ ጠፍቶብኛል ነገር ግን ፍጥነታችን አስደሳች ነው» ይላቸዋል።

«እነዚህ የመጨረሻ ቀናት» የኢየሱስ ክርስቶስን አገልግሎት ጀምረዋል (ዕብ. 1፡1-2)፥ እስከሚመለስም ድረስ ይቀጥላሉ። «የመጨረሻ ቀናት» የተባሉትም፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያሉትን ዓላማዎች እየፈጸመባቸው ስለሆነ ነው። ጌታችን መመለሱን ስላዘገየ፥ አንዳንዶች በመምጣቱ ተስፋ ያፈዛሉ (2ኛ ጴጥ. 3፡3-7)፤ ነገር ግን እርሱ እንደ ተስፋ ቃሉ ይመጣል።

በዚህ «በመጨረሻ ቀናት» ክፍለ ጊዜ ውስጥ የተለያዩ ዓይነት «ጊዜያት» (ወቅቶች) ይኖራሉ፤ ነገር ግን «ጊዜያቱ» ወደ ማለቂያቸው መዝጊያ ሲቃረቡ፥ የሚያስጨንቁ ይሆናሉ። ይህም ቃል «አደገኛ፥ ለመቋቋም የሚያዳግት፥ ጭካኔ የተሞላበት» የሚል ትርጉም ይይዛል። ይኸው ተመሳሳይ የግሪክ ቃል አጋንንት ያደሩባቸውን ሁለቱን የጌርጌሴኖን ሰዎች ምን ያህል አስቸጋሪዎች እንደነበሩ ለመግለጽ ያገለገለ ቃል ነው (ማቴ. 8፡28)። ይህ የመጨረሻው ዘመን ዓመፅ በአጋንንት የሚነሣሣ እንደሚሆን ያሳያል (1ኛ ጢሞ. 4፡1)።

እነዚህ ባሕሪያት በጳውሎስ ጊዜ መታየት እንደ ጀመሩ ጥርጥር የለውም፤ አሁንም በመጠን ጨምረዋል። በዓለም ላይ ብዙ ሰዎች ስለሚኖሩ ወይም የተሻለ የዜና ስርጭት ስላለን ብቻ አይደለም። ክፉት በጥልቀትና በስፋት እያደገና በኅብረተሰቡም ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ ተቀባይነት እያገኘና እያደገ እንደሆነ በግልጽ ይታያል። እዚህና እዚያ ትንንሽ የዓመፅ ጥርቅሞች በእርግጥ መታየታቸው ብቻ አይደለም። ኅብረተሰቡ ሁሉ በሁከት እና በዓመፅ ውስጥ የሚመላለስ ይመስላል። «በሚያስጨንቅ ዘመን» ውስጥ ነው ያለነው (2ኛ ጢሞ. 3፡1)።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በአስጨናቂ ዘመን ውስጥ አገልግሎቱ ውጤታማ እንዲሆን ሊታዘዛቸው የሚገባቸውን ሦስት መመሪያዎች ሰጥቶታል።

1. ከሐሰተኞች ራቅ (2ኛ ጢሞ. 3፡1-9)፡-

«ከእነዚህ ደግሞ ራቅ» (3፡5)። የታመነ አማኝ፥ ጳውሎስ በዚህ ክፍል ከጠቀሳቸው ሰዎች ጋር ምንም ጉዳይ ሊኖረው አይገባም። እነዚህ ሰዎች የሚንቀሳቀሱት በሃይማኖት ስም መሆኑን ማስተዋል ጠቃሚ ነው፥ «የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል» (3፡5)። «ሃይማኖተኞች» ናቸው፤ ነገር ግን ዓመፀኞች ናቸው! ስለ እነዚህ ሰዎች ጳውሎስ ሦስት እውነታዎችን አብራርቷል፡-

ሀ. ባሕሪዎቻቸው (2ኛ ጢሞ. 3፡2-5)፡- ቢያንስ አሥራ ስምንት የተለያዩ ባሕሪያት እዚህ ተዘርዝረዋል። ምናልባትም ጳውሎስ የበለጠ ሊዘረዝር ይችል ነበር። «በፍቅር» ላይ ትኩረት ተደርጓል፡- «ራሳቸውን የሚወዱ»፥ ገንዘብን የሚወዱ (የሚመኙ) «ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ!» የሁሉም ችግር መሠረት በልብ ውስጥ ያለው ችግር ነው። እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ (በፍጹም ልባችን) እንድንወደው እንዲሁም ባልንጀራችንን እንደራሳችን እንድንወድ አዞናል (ማቴ. 22፡34-40)፤ ነገር ግን ራሳችንን ከሁሉም በላይ ከወደድን፥ እግዚአብሔርን ወይም ባልንጀራችንን አንወድም።

በዚህ ዓለም ውስጥ እግዚአብሔር፥ ሰዎች እና የዚህ ዓለም ንብረቶች አሉ። እግዚአብሔርን ማምለክ፥ ሰዎችን መውደድና፥ የዚህን ዓለም ንብረት መጠቀም አለብን። ዳሩ ግን ራሳችንን ማምለክ ከጀመርን፥ እግዚአብሔርን ረስተን የዚህን ዓለም ንብረት መውደድና ሰዎችን ለራሳችን ጥቅም ብቻ መጠቀም እንጀምራለን። ይህ የምስኪን ሰው ሕይወት ዓይነተኛ ባሕርይ ነው። ሆኖም ይህ ዛሬ የብዙ ሰዎችን ሕይወት ያንጸባርቃል። በዓለም ዙሪያ ለነገሮች ያለው ናፍቆት የሰዎች ልብ ከእግዚአብሔር እንደተመለሰ የሚያሳይ አንዱ ማስረጃ ነው።

በእርግጥ አንድ ሰው ራሱን ከወደደና ካመለከ ውጤቱ ትዕቢት (ኩራት) ይሆናል። ሰይጣን ለሔዋን ያቀረበላት አሳብ «እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ» የሚል ነበር (ዘፍ. 3፡5)። ውጤቱ ደግሞ ሰዎች «የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው» (ሮሜ 1፡25)። ሰው የራሱ አምላክ ሆነ! አሁን ፍጥረት ፈጣሪ ነው! «ትምክህተኞች፥

ትእቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች (ለፈዝና ለመራራ ቃላት የተሰጡ)» (2ኛ ጢሞ. 3፡2)።

«ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ» የሚለው ይህ ኑፋቄ ወደ ቤተሰቡ ውስጥ እንደ ደረሰ ያሳያል። ልጆች «የማያመሰግኑ» እና ወላጆቻቸው ለእነርሱ ያደረጉላቸውን ነገር ከምንም የማይቆጥሩ ናቸው። ወደ ወላጆቻቸው ባላቸው ዝንባሌ «ቅድስና የሌላቸው» ናቸው። «አባትህንና እናትህን አክብር» የሚለውን ትምህርት አይቀበሉትም፤ አያከብሩትምም።

«ፍቅር የሌላቸው» የሚለው ሐረግ «የቤተሰብ ፍቅር» የሚለውን ከሚገልጽ አንድ ቃል የተተረጎመ ነው። በዚህ ዘመን ቤተሰብ በጥቃት ውስጥ ይገኛል፥ እንደዚሁ የቤተሰብ ሕይወት ከተበላሸ ሕዝብና አገርም ይጎዳል።

እግዚአብሔር በወንዶችና በሴቶች፥ እንዲሁም በቤተሰብ ውስጥ ባስቀመጠው ተፈጥሮአዊ ፍቅር ምትክ፥ ዛሬ እግዚአብሔር የሚኮንነው ተፈጥሮአዊ ያልሆነ ፍቅር ተስፋፍቶ ይታያል (ሮሜ 1፡18-27፤ 1ኛ ቆሮ. 6፡9-10 ን ተመልከት)። ይህ አላግባብ ያለውን ተፈጥሮአዊ ልምምድ ስለሚቃረን እግዚአብሔር ይፈርድበታል (ሮሜ 1፡28-32)።

በቤቶች ውስጥ ብቻ ሳይሆን፥ በውጪም በጎብረተሰቡና በንግዱ ዓለም የእነዚህ አስጨናቂ ጊዜያት ባሕሪያት ሊታዩ ይችላሉ። «እርቅን የማይሰሙ» (2ኛ ጢሞ. 3፡3) የሚለው ለመስማማት የማይሞክሩትን ሰዎች ይገልጻል። የማይሸነፉና የማይታረቁ በመሆናቸው የራሳቸውን መንገድ ይዘው ለመጓዝ ይፈልጋሉ።

አቋማቸውን ለመከላከል «ሐሜተኞች» («በውሸት የሚከሱ») ይሆናሉ። በዚህም የሌሎችን ስም ለማጥፋት ይሞክራሉ። የሚያሳዝነው፥ በተመሰከረላቸው ክርስቲያኖች አካባቢ እንኳን ከዚህ ዓይነቱ ተግባር የተወሰነው ክፍል ይስተዋላል። «ክርስቲያን መሪዎች» በእትሞቻቸው ገጾች ውስጥ እርስ በርሳቸው ይወቃቀሳሉ።

ዛሬ የሕብረተሰባችን መፈክር «የምትፈልገውን ነገር አድርግና ተደሰትበት!» የሚል ነው። የሚያሳዝነው ከእነዚህ ሰዎች የተወለዱ አንዳንድ ልጆች በአደንዛዥ ዕፆች፥ በአልኮል ወይም በአባላዘር በሽታዎች ምክንያት የተሸመደመዱ ወይም አካለ ጎደሎ ስለሆኑ ሁልጊዜ አይደሰቱበትም።

ይህ ራስን ያለመግዛት ጦስ በተለያዩ መንገዶች ራሱን ይገልጻል። «ጨካኝ» ማለት «ያልተገራ፥ ጠበኛ» ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን ምኞት መፈጸም፥ ካልቻሉ እንደ ጨካኝ አውሬዎች ይሆናሉ። መልካም የሆነውን ከማክበር ይልቅ፥ መልካም የሆነውን ንቀው ክፉ የሆነውን ያከብራሉ። ዛሬ በሕብረተሰብ ውስጥ የትክክልና የስሕተት መመዘኛዎች ጨርሶ ባይጠፉም ስፍራ ተቀያይረው እንመለከታለን። ነቢዩ ኢሳይያስ፡- «ክፉውን መልካም መልካሙንም ክፉ ለሚሉ ወዮላቸው» ሲል አስጠንቅቋል (ኢሳ. 5፡20)።

«ከዳተኞች» (2ኛ ጢሞ. 3፡4) የሚለው ሌሎችን አሳልፈው የሚሰጡና መታመን የማይችሉትን ሰዎች ይገልጻል። ጓደኝነትም ሆነ ሽርክና ለእነርሱ ምንም ለውጥ አያመጣም፤ የራሳቸውን ምኞት ለመፈጸም የሚረዳቸው ከሆነ፥ ይዋሻሉ፤ ቃላቸውንም ያጥፋሉ።

«ችኩል» ማለት «ግዴለሽ፥ ፈጣን፥ የሚሠራውን ነገር በጥንቃቄ ሳያስብ የሚያከናውን» ማለት ነው። ጳውሎስ የሞኝነት ጥረትን እንጂ፥ ቅን ድፍረትን አልኮነነም።

«በትዕቢት የተነፉ» የሚለው ቃል ከፍተኛ አሳብ ያለውን ሰው አይገልጽም። ይልቁንም የራሱን ጠቃሚነት በማሰብ በትዕቢት «የተወጠረ» ሰው ማለት ነው። «በራስ ብቃት ወይም ባገኙት ውጤት መታበይ» የሚለው ምናልባት ተመሳሳዩ ሊሆን ይችላል።

«ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ» የሚለው በተድላና በእግዚአብሔር መካከል መምረጥ እንዳለብን አያመለክትም። ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ስንኖር፥ እጅግ በጣም ትልቅ ተድላን ስለምናገኝ ነው [መዝ. (16)፡11]። ምርጫው ተድላን በመውደድ ወይም እግዚአብሔርን በመውደድ መካከል ነው። እግዚአብሔርን ከወደድን የሕይወትን ሙላት በዚህ ምድርና በሚመጣውም ዓለም ለዘላለምም እናገኛለን፤ ነገር ግን የኃጢአት ተድላ መቆየት የሚችለው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው (ዕብ. 11፡25)። በተድላ በሰከረ ዓለም ውስጥ እንደምንኖር ማንም ሊክደው አይችልም፤ ነገር ግን እነዚህ ተድላዎች ብዙውን ጊዜ ባዶ መዝናኛና ማምለጫዎች ብቻ ናቸው፤ አርኪና እውነተኛ ደስታ አይሰተዋልባቸውም።

ጳውሎስ አሁን የጠቀሳቸው ሰዎች ራሳቸውን ሃይማኖተኛ አድርገው እንደሚቆጥሩ ገልጿል «የአምልኮት መልክ አላቸው» (2ኛ ጢሞ. 3፡5) የሚለው እውነተኛ የክርስቲያን እምነት ሳይሆን፥ በውጪ የሚታይ ሃይማኖትን ያሳያል፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ኃይል

በሕይወታቸው ውስጥ በፍጹም ተለማምደው ስለማያውቁ ነው። በእነርሱ ሕይወት ውስጥ የሚታየው ኃይል የሌለው መምሰልና እውነት የሌለበት ሃይማኖት ነበር።

ለ. የለወጧቸው ሰዎች (2ኛ ጢሞ. 3፡6-7)፡- ጳውሎስ «ሞኞች ሴቶች» ብሎ መግለጹ ሁሉም ሴቶች እንዲህ ናቸው ወይም ወንዶች ለሐሰተኛ አስተማሪዎች ማታለል የተጋለጡ አይደሉም ማለት አይደለም። በጳውሎስ ዘመን ሴቶች በጎብረተሰቡ ዘንድ ዝቅተኛ ደረጃ ስለነበራቸው፥ ለዚህ ዓይነት ልምምድ በተለይ የተጋለጡ ነበሩ። ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ለዚህ ሐሰተኛ ሃይማኖት ሥርዓት የተሸነፉ ሰዎች ተመሳሳይ ባሕሪያት አሏቸው።

በአእምሮ ወቀሳ የተዋከቡና ከእስራትና ከፍርሀት የሚያመልጡበትን መንገድ የሚፈልጉ ናቸው። የተለያዩ ምኞቶቻቸውን ለመቆጣጠር ይሳናቸዋል። እዚህ ላይ ያለው አትኩሮት በወሲባዊ ችግሮች ላይ ሊሆን ይችላል። በመጨረሻም ይህንንና ያንን መንገድ በመሞከር ሁልጊዜ እውነትን ይፈልጋሉ፤ ሆኖም ለመርካት በፍጹም አይችሉም። ይህ ዓይነት ሰው ለሐሰት አስተማሪዎችና ለሃይማኖታዊ ሽቃጮች ወጥመድ ደህና ቀለብ ነው።

እነዚህ ሐሰተኞች የሃይማኖት መሪዎች ሰዎች ያሉባቸውን ችግሮች እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም፥ ፈጣንና ቀላል መፍትሔዎችን እንደሚሰጡ ቃል ይገባሉ። ወደ ሰዎች ሕይወት ሰርስረው በመግባት የሰዎችን ሕይወት ወዲያው ይቆጣጠራሉ። እነዚህ መሪዎች ብዙም ሳይቆይ የተከታዮቻቸውን ታማኝነት፥ ገንዘብና አገልግሎት ከእጃቸው ያስገባሉ። የለወጧቸው ሰዎችም ቀድሞ ከነበሩበት በባሰ ውድቀት ውስጥ ይገባሉ። ችግሮቻቸው አሁንም አሉ፤ ነገር ግን ሁሉ ነገር እንደ ተስተካከለ አድርገው እንዲያስቡ የሐሰት ትምህርት መሪዎች አታልለዋቸዋል።

እንግዲህ አስታወሱ፥ ይህ ሁሉ ድብቅ ሥራ የሚሠራው በሃይማኖት ስም ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን «ከእነዚህ ደግሞ ራቅ» ማለቱ አያስደንቅም።

ሐ. የሃይማኖት መሪዎቻቸው (2ኛ ጢሞ. 3፡8-9)፡- በሙሴና በግብፅ አስማተኞች መካከል ስለተደረገው ውድድር ዘጸ. 7-9 አንብብ። በአፈ-ታሪክ አስማተኞቹ በጳውሎስ የተጠቀሱት ሁሉት ሰዎች ኢያኔስና አያንብሪስ ናቸው ይባላል (2ኛ ጢሞ. 3፡8)። እነዚህ ሰዎች ሙሴ ያደረገውን አስመስለው በመሥራት ተቃወሙት።

የአሮን በትር ወደ እባብነት ስትለወጥ፥ አስማተኞቹም በትሮቻቸውን በመጣል ወደ እባብነት ለወጡ። ሙሴ ውኃውን ወደ ደም ለወጠ። አስማተኞቹም ተመሳሳይ ተአምር ሠሩ። ሙሴ እንቁራሪቶቹን በሙሉ ሲያወጣ አስማተኞቹም ተአምሩን ደገሙት፤ ነገር ግን ወደ ቅማል ተአምር ሲደርሱ፥ አስማተኞቹ ሊያደርጉት አልቻሉም (ዘጸ 8፡16-19)።

ሰይጣን አስመስሎ የሚያደርግ ነው፤ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ሰይጣን አስመስሎ ይሠራል። በመጨረሻው ዘመን የሚኖሩ የሃይማኖት መሪዎች የማስመሰል እምነት ይኖራቸዋል። ዓላማቸውም ውሸትን ማስፋፋትና የእግዚአብሔርን ቃል እውነትነት መቃወም ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን በመካድ፥ የሰውን ጥበብና ፍልስፍናን ይተካሉ። «ዘመናዊ» ለመሆን ሲሞክሩ፥ የኃጢአትን እውነታና ደኅንነት ለሰዎች ማስፈለጉን ይክዳሉ። ጳውሎስ እነዚህ ሰዎች «አእምሮአቸው የጠፋባቸው» በሚል ቃል ይገልጻቸዋል። ይህም «ተፈትኖ ውሸት ሆኖ የተገኘ» ማለት ነው።

በመጨረሻ ኢያኔስና ኢያንብሬስ ተጋልጠው፥ በእግዚአብሔር ፍርድ መሳለቂያዎች ሆነዋል። በሐሰተኛ የሃይማኖት መሪዎች ላይም ይህ ይሆናል። የእግዚአብሔር ፍርድ ሲወርድ፥ የእነዚህ አስመሳዮች እውነተኛ ባሕርይ ለሁሉ ይገለጣል።

2. እውነተኛ የሆኑትን ሰዎች ተከተል (2ኛ ጢሞ. 3፡10-12)

ጳውሎስ የታመነ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደነበረ ለጢሞቴዎስ ሊያስታውሰው ስለ ፈለገ፥ ስለ ሐሰተኛ መሪዎች ከመናገር ይመለሳል። በእነዚህ አስቸጋሪ ጊዜያት ትክክለኛ መንፈሳዊ መሪዎችን መከተላችን አስፈላጊ ነው። ባሕሪያቶቻቸው ምንድናቸው?

ሀ. ለተመልካች ሁሉ ሕይወታቸው የተገለጸ ነው (2ኛ ጢሞ. 3፡10)፡- ጳውሎስ የሚደብቀው ምንም ነገር አልነበረውም። እንደ ጌታው «በስውር ምንም አልተናገርኩም» (ዮሐ. 18፡20) ለማለት ይችል ነበር። «ከታናሽነቴ ጀምሬ የኖርሁትን ኑሮዬን አይሁድ ሁሉ ያውቃሉ» (የሐዋ. 26፡4) በማለት ጳውሎስ ለአግሪጳ ተናግሯል። ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር ስለኖረና ስለሠራ በደንብ ያውቀው ነበረ። ጳውሎስ ከእውነት የራቁ ሐተታዎችን ወይም ሃይማኖታዊ ቅስቀሳ ከኋላው አልደበቀም።

ለ. እውነተኛ ትምህርት ያስተምራሉ (2ኛ ጢሞ. 3፡10)፡- «ትምህርቴን» የሚለው በጳውሎስ አባባል፥ እውነተኛ እምነት

የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ማለት ነው። አንድ ሰባኪ ምንም ያህል ማራኪ ቢሆን፥ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ካልሰበከ ድጋፍ አይገባውም። ዛሬ በሬድዮና በቴሌቭዥን ሃይማኖታዊ ለማስመሰል ትንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተጨመረበትን የሳይኮሎጂ፥ የስኬት ማነሳሻና ራስ አወዳሽ ትምህርቶች ድብልቅ የሆነውን «የሐሰት ክርስትና» በብዛት እንሰማለን። ተጠንቀቁ!

ሐ. የሰበኩትን ይኖሩበታል (2ኛ ጢሞ. 3፡10)፡- የጳውሎስ «የሕይወት ዘይቤ» «አኗኗር» መልእክቶቹን የሚደግፍ ነበር። መስዋዕትነትን እየሰበከ በድሎት አልኖረም። ለሌሎች ከሚቀበለው እጅግ የበለጠ ይሰጣቸው ነበር። ወዳጆቹን ማጣት፥ በመጨረሻም የራሱን ሕይወት ማጣት ቢያስከትልበትም እንኳን፥ ለእውነት የቆመ ነበር። ጳውሎስ ባሪያ እንጂ፥ ታዋቂ ሰው አልነበረም።

መ. ዓላማቸው እግዚአብሔርን ማስከበር ነው (2ኛ ጢሞ. 3፡10)፡- በአገልግሎት ውስጥ ስለ ጳውሎስ «ዓላማ» ምንም ዓይነት ጥያቄ አልነበረም፡- የሚፈልገው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግና እግዚአብሔር እንዲሠራ የሰጠውን ሥራ መፈጸም ነበር (የሐዋ. 20፡24፥ ፊሊ. 1፡21)። ሐዋርያው ጳውሎስ የሚፈልገውን እንደሚሞላለት በእግዚአብሔር የታመነ የ «እምነት» ሰው ነበር። የሰዎችን ተቃውሞ የተቋቋመ የ «ትዕግሥት» ሰው ነበር። ሌሎችን ለማገልገል ራሱን በፈቃዱ የሰጠ የ «ፍቅር» ሰው ነበር።

በ2ኛ ጢሞ. 3፡10 መጨረሻ ላይ ያለው ትዕግሥት የሚለው ቃል «መጽናት፥ ወደፊት መግፋት፥ አዳጋች ሲሆን ባሉበት ስፍራ ጸንቶ የመቆየት ችሎታ» ማለት ነው።

ሠ. መከራ ለመቀበል ፈቃደኞች ናቸው (2ኛ ጢሞ. 3፡11-12)፡- ጳውሎስ ለሌሎች መከራ ተቀበለ እንጂ፥ ሌሎች ለርሱ መከራ እንዲቀበሉለት አልጠየቀም። ከከተማ ከተማ መሰደዱ እግዚአብሔርን በመምሰል ይኖር እንደነበር የሚገልጽ ማስረጃ ነው። ዛሬ አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን መምሰል ማለት ከስደት መሸሽ እንደሆነ ያስባሉ፤ ዳሩ ግን እውነቱ የዚህ ተገላቢጦሽ ነው።

ጳውሎስ ስለ ክርስቲያን መሪ ያለው አስተሳሰብ ዛሬ ካለው አስተሳሰብ ጋር ሲወዳደር የቱን ያህል የተራራቀ እንደነበረ ሳስበው ይደንቀኛል። ምናልባትም የእርሱ አስተሳሰብ ውድቅ በሆነም ነበር። በዛሬ ዘመን በሚገኝ በአንዱ መንፈሳዊ ድርጅት ውስጥ ለአገልግሎት ቢያመለክት ተቀባይነት ያገኝ ይሆን? የአሥር ቤት ታሪክ ነበረው፤

በሥጋዊ ሕይወቱ የጎሰቆለ ነው፤ በተገኘበት ቦታ ሁሉ ችግሮችን ፈጥሮአል። ድሀ ነበር፥ ለሀብታሞች ግብጥ አላቀረበም ነበር። ሆኖም እግዚአብሔር ተጠቀመበት። እንዲሁም ጳውሎስ ታማኝ ስለነበረ፥ ዛሬ እኛም እየተባረክን ነን።

3. በእግዚአብሔር ቃል ጽና (2ኛ ጢሞ. 3፡13-17)፡-

የሰይጣንን ውሸቶች ለማሸነፍ፥ ብቸኛው መንገድ የእግዚአብሔር እውነት ነው። «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል!» የሚለው ለማንኛውም ጥያቄ የመጨረሻ መልስ ነው። ክፉዎችና አታላዮች እየባሱ ይሄዳሉ። ገናም የበለጠ እያታለሉ ይሄዳሉ። ለምን? ምክንያቱም በሰይጣን እየተታለሉ ስላሉ ነው! በዚህ በመጨረሻ ዘመን ብዙ ማታለልና ግስመሰል ይኖራል፤ በመሆኑም አንድ አማኝ እውነትን ከሐሰት ለመለየት የሚችልበት ብቸኛ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል በማወቅ ነው።

ጢሞቴዎስ ከሕፃንነቱ ጀምሮ የእግዚአብሔርን ቃል ተምሮ ነበር። አንዳንድ ሰዎች «ልጅ እያለሁ መጽሐፍ ቅዱስ ያስፈልገኝ ነበር፥ አሁን ግን ትልቅ ሰው ስለሆንኩ ካለ እርሱ መኖር እችላለሁ» ለማለት ይከጅላሉ። እንዴት የተሳሳቱ ናቸው! አዋቂዎች ከልጆች ይልቅ የእግዚአብሔር ቃል ምሪት በጣም ያስፈልጋቸዋል፤ ምክንያቱም አዋቂዎች ብዙ ፈተናዎች ያጋጥሙአቸዋል፤ እንዲሁም ብዙ ውሳኔዎችን ይወስናሉ። የጢሞቴዎስ አያትና እናት በታማኝነት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን አስተምረውታል። (በቁ. 14 ከማን የሚለው ቃል እነዚህን ሴቶች የሚያመለክት ነው፤ 1፡5ን ተመልከት)። ጢሞቴዎስ በተማረው መጽናት ነበረበት። የእግዚአብሔርን ቃል አውቀን ልንጨርስ አንችልም።

ይህ ክርስቲያን ወላጆች ለልጆቻቸው መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያስተምሩ ለመምከር ጥሩ ጊዜ ነው። በቤታችን ባለቤቴና እኔ፥ ለሕፃናት የተዘጋጁ ሥዕላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች የሚለውን የኬኔዝ ቴይለር ዝግጅት ለልጆቻችን እናስጠና ነበር። እንዲያውም ሁለት እንደነዚህ ዓይነት መጻሕፍትን ጨርሰናል! ማንበብ የቻሉት ታላላቅ ልጆች ለትንንሾቹ ታሪኮችን ሲያካፍሉና ጥያቄዎችን ለመመለስ ሲያግዟቸው ማየት ምን ያህል ደስ ያሰኝ ነበር። ቀስ በቀስ ልጆቹ ከፍ ወዳሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ መጻፍሕፍት፥ ከዚያም ወደ ራሳቸው መጽሐፍ ቅዱስ ተሸጋገሩ። የሰንበት ትምህርት ቤታችን መጽሐፍ ቅዱስን በቃል የማጥናት ፕሮግራም በማካተቱ ዕድለኞች ነበርን። ልጅህ

እንደተወለደ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ከበበው። ካደገ በኋላ ይህ ዕድል አይኖርህም።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ጳውሎስ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት አንዳንድ አስፈላጊ ዓረፍተ ነገሮችን አስቀምጧል፡-

ሀ. ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው (2ኛ ጢሞ. 3፡15)፡- በቀጥታ ሲተረጎም «የተቀደሱት ደብዳቤዎች» የሚል ይሆናል። ይህ ወጣቱ ጢሞቴዎስ የዕብራይስጥ ፊደልን የተማረው በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ፊደልን በመቁጠር እንደሆነ የሚያሳይ ነው። «ቅዱስ» የሚለው ቃል «ለተቀደሰ አገልግሎት የተለየ» ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ለተለዩ ቅዱስ አገልግሎቶች የተለየ ነው፥ እንዲሁም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉትን መጻሕፍት ጨምሮ፥ ከማንኛውም ሌላ መጽሐፍ የተለየ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ የሆነ መጽሐፍ አድርገን ማየት አለብን።

መጽሐፍ ቅዱስን የምንይዝበት ሁኔታ ምን ያህል እንደምናከብረው ለሌሎች ያሳያል። በዚህ ጉዳይ ላይ የተለየ አሳብ ለማቅረብ ባልፈልግም፥ መጽሐፍ ቅዱስን በወለል ላይ ተጥሎ ማየት እንደምጠላ መገለጽ አለብኝ። መጽሐፍ ቅዱስንና ሌሎች መጻሕፍትን ስንይዝ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከላይ መሆን አለበት። መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና በጥንቃቄ ምልክት በማድረግና በግድ የለሽነት በማበላሸት መካከል ልዩነት አለ። ቡና በስኒ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚያስቀምጡ ሰዎች አይቻለሁ! ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ቃል ትክክለኛውን አመለካከት ይሰጠናል (1ኛ ተሰ. 2፡13)።

ለ. ቅዱሳን መጻሕፍት ወደ ደኅንነት ይመሩናል (2ኛ ጢሞ. 3፡15)፡- እኛ የዳነው መጽሐፍ ቅዱስን በማመን ሳይሆን (ዮሐ. 5፡39 ን ተመልከት)፥ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸውን ክርስቶስን በማመን ነው። ሰይጣን መጽሐፍ ቅዱስን ያውቃል፤ ነገር ግን አልዳነም። ጢሞቴዎስ እግዚአብሔርን በሚፈራ ቤተሰብ ውስጥ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማጥናት ያደገ ነበር። ሆኖም ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ እስከመራው ድረስ አልዳነም ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ ከደኅንነት ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ደኅንነት እንደሚያስፈልገን ይገልጻል። በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ምን ያህል የረከሰን መሆናችንን የሚያሳይ መስተዋት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱ የጠፋ ኃጢአተኛ አሁን እንደተፈረደበትና (ዮሐ. 3፡18-21) አሁን አዳኝ እንደሚያስፈልገው

ያስረዳል። የጠፋ ኃጢአተኛ ራሱን ማዳን እንደማይችልም ግልጽ ያደርጋል።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለደኅንነት ያዘጋጀውን አስደናቂ እቅድም ይገልጻል፤ ይኸውም ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን መሞቱ ነው! ብናምነው ያድነናል (ዮሐ. 3፡16-18)። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ለደኅንነታችን ማረጋገጫ በመስጠት ይረዳናል (1ኛ ዮሐ. 5፡9-13 ተመልከት)፤ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በጸጋ እንድናድግና ክርስቶስን እንድናገለግል የሚያደርገን መንፈሳዊ ምግባችን ይሆናል። ሰይጣንን የምንዋጋበትና ፈተናን የምናሸንፍበት ሰይፋችን ነው።

ሐ. ቅዱሳት መጻሕፍት እውነትና አስተማማኝ ናቸው (2ኛ ጢሞ. 3፡16)፡- «ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የተጻፉ ናቸው» ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ተመርቶ መጻፍ የሚሰጠው ትምህርት በጣም አስፈላጊ ነው፤ ሰይጣንም ከመጀመሪያው የተቃወመው ይህንኑ ትምህርት ነው («በውኑ እግዚአብሔር አዝዟልን?» ዘፍ. 3፡1)። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊታመኑበት የማይችሉትን መጽሐፍ ይሰጣል ተብሎ አይታሰብም። እርሱ የእውነት አምላክ ነው (ዘዳ. 32፡4)። ኢየሱስ «እውነት» ነው (ዮሐ. 14፡6)። እንዲሁም «መንፈስ ቅዱስ እውነት» ነው (1ኛ ዮሐ. 5፡6)። ኢየሱስ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት «ቃልህ እውነት ነው» ብሏል (ዮሐ. 17፡17)።

የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል ለመጻፍ፥ የእግዚአብሔርን ሰዎች ተጠቅሟል (2ኛ ጴጥ. 1፡20-21)። መንፈስ ቅዱስ የጸሐፊዎችን ተፈጥሮአዊ ባሕሪያት አላጠፋም። በእርግጥ፥ እግዚአብሔር በቸርነቱ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመጻፍ ተግባር፥ ጸሐፊዎቹን አዘጋጅቶ ነበር። እያንዳንዱ ጸሐፊ የራሱ የሆነ የተለየ መንገድ እና የቃላት አጠቃቀም አለው። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ከተለየ የሁኔታዎች ስብስብ የወጣ ነው። ሰዎችን በማዘጋጀቱ፥ ታሪክን በመምራቱና በመንፈሱ አማካኝነት በመሥራቱ፥ እግዚአብሔር የቅዱሳት መጻሕፍት መገኛ ተአምር ሠራ።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ «የመንፈስ ቅዱስ መሪነት»፥ መንፈስ ቅዱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ላይ ያለውን መለኮታዊ ተጽዕኖ ማለታችን ነው። ይህም የጻፉት ትክክለኛና የሚታመን ስለመሆኑ ዋስትና የሚሰጥ ነው። መገለጥ ማለት እውነትን ከእግዚአብሔር ወደ ሰው ማስተላለፍ

ሲሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ይህንን ግንኙነት አስተማማኝ በሆነ መንገድ መመዝገብ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ራሱ፥ ስለ ሰው፥ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሕይወት፥ ስለ ሞት፥ ስለ ታሪክ፥ ስለ ሳይንስና ስለ እያንዳንዱ ሌላ ጉዳይ የሚናገረው ማንኛውም ነገር እውነት ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ የሰዎችንና የሰይጣንን ውሸቶች ስለሚያካትት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር እውነት ነው ማለት አይደለም። ዘገባው ግን እውነት ነው።

መ. ቅዱሳት መጻሕፍት የሚጠቅሙ ናቸው (2ኛ ጢሞ. 3፡16)፡- ለትምህርት (ትክክል ለሆነው)፥ ለተግሣጽ (ትክክል ላልሆነው)፥ ለማቅናት (እንዴት ለመስተካከል እንደሚቻል)፥ በጽድቅም ላለው ምክር (እንዴት ትክክል ሆኖ መቆየት እንደሚቻል) የሚጠቅሙ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠናና በተግረው የሚኖር ክርስቲያን በቅድስና ያድጋል። ከዚህ ዓለም ብዙ ወጥመዶችም ለማምለጥ ይችላል።

ሠ. ቅዱሳት መጻሕፍት ለአገልግሎት ያስታጥቁናል (2ኛ ጢሞ. 3፡17)፡- ቀደም ሲል ጳውሎስ ጢሞቴዎስን «የእግዚአብሔር ሰው» ብሎ ጠርቶት ነበር (1ኛ ጢሞ. 6፡11)፤ በዚህ ስፍራ ግን ጳውሎስ ማንኛውም ክርስቲያን «የእግዚአብሔር» ሰው መሆን እንደሚችል ይገልጻል። እንዴት? የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት፥ በመታዘዝ እና ይህም ቃል ሕይወቱን እንዲቆጣጠር በመፍቀድ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ሁሉም «የእግዚአብሔር ሰዎች» ሙሴ፥ ሳሙኤል፥ ኤልያስ፥ ኤልሳዕ፥ ዳዊትና ጢሞቴዎስ ለእግዚአብሔር ቃል ራሳቸውን የሰጡ ሰዎች እንደነበሩ ማስተዋል ይጠቅማል።

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሁለት ቃላት በተለይ አስፈላጊዎች ናቸው፡- «ፍጹም» እና «የተዘጋጀ»። «ፍጹም» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ሙሉ፥ ብቁ፥ በሚገጥም ሁኔታ» ማለት ነው። ኃጢአት የሌለበትን ፍጹምነት አያመለክትም። ይልቁንም ለመጠቀሚያነት ብቁ መሆንን ያሳያል።

«የተዘጋጀ» ተመሳሳይ ትርጉም አለው «ለአገልግሎት መታጠቅ»። በሌላ አነጋገር የእግዚአብሔር ቃል አማኝ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት እንዲኖርና እግዚአብሔር የሚፈልገውን ሥራ

እንዲያደርግ ያዘጋጀዋል። ቃሉን በበለጠ ስናውቅ፥ በበለጠ ለእግዚአብሔር ለመኖርና ለመሥራት እንችላለን።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዓላማ ጠቃሚ ነገሮች ቢሆኑም መንፈሳዊ ትምህርቶችን ለመረዳት ወይም እምነትን ለመከላከል ብቻ አይደለም። ዘላቂ ዓላማው የሚያነቡትን ምእመናን ለማስታጠቅ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝቦች የእግዚአብሔርን ሥራ እንዲሠሩ የሚያስታጥቃቸው የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ጊዜው እየተሻሻለ በመምጣት ላይ አይደለም፤ ዳሩ ግን እኛ ክርስቲያኖች በክፉ ጊዜያት እንኳ የተሻልን ሰዎች መሆን እንችላለን። ራሳችንን ሐሰት ከሆነው መለየት፥ እውነት ወደ ሆነው ማስጠጋትና በእግዚአብሔር ቃል ጥናታችን መቀጠል አለብን። ከዚያ በእነዚህ አስቸጋሪ ጊዜያት እግዚአብሔር ለአገልግሎት ሊያስታጥቀን ይችላል። በኋላም ሌሎች እውነትን ወደ ማወቅ ሲመጡ በማየት ደስታን እናገኛለን።

የመሰነባበቻ ቃላት

2ኛ ጢሞቴዎስ 4

የአንድ ታላቅ ሰው የመጨረሻ ቃላት አቢይ ጉዳዮች ናቸው። ወደ ልቡ ውስጥ ዘልቆ ለማየት የሚረዳን መስኮት፥ ወይም ሕይወቱን ለመገምገም የሚረዳን መለኪያ ናቸው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስና ለቤተ ክርስቲያን የተናገራቸውን የመጨረሻ ቃላት እናገኛለን።

ጳውሎስ ወደ መጨረሻው ሲመጣ ምንም ጸጸት አለማሰማቱ የሚገርም ነው። ችግር የፈጠሩበትን ሰዎች እንኳን ይቅር ብሏል (4፡16)። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከአሥራ ሰባት ሰዎች በላይ ተጠቅሰዋል። ይህም ጳውሎስ ነፍስ ማራኪ ከመሆኑ በላይ፥ ጓደኛ የሚያፈራ መሆኑን ያሳያል። የሚሞትባቸው ቀናት የተቆጠሩ ቢሆኑም፥ ጳውሎስ ስለ ሌሎች ያስብ ነበር።

ሐዋርያው ለጢሞቴዎስ ሦስት የማጠቃለያ ምክሮችን ሰጥቶ ነበር። እያንዳንዳቸውንም በምክንያት አስደግፏል።

1. ቃሉን ስበክ! (2ኛ ጢሞ. 4፡1-4)

«እመክርሀለሁ» የሚለው «በጥብቅ እመሰክርብሃለሁ» ተብሎ መነበብ ነበረበት። ይህ ወሳኝ ጊዜ ነበር፤ በመሆኑም ጳውሎስ ጢሞቴዎስ አስፈላጊነቱ ምን ያህል እንደሆነ እንዲሰማው ፈልጓል። ወሳኝ የነበረው፥ ጳውሎስ ሞትን ፊት ለፊት የተጋፈጠበት ጊዜ ስለ ነበር ብቻ አይደለም፤ ዳሩ ግን በበለጠ ሁለቱም ጳውሎስና ጢሞቴዎስ አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለፍርድ ስለሚቀርቡ ነው። አንዳንድ ጊዜ አንድ ቀን እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እንደምናየውና በሥራችን እንደሚፈርድ ማሰብ ለእኛ ጥሩ ነው።

በአንድ በኩል፥ ይህ ማስተዋል፥ ሥራችንን በጥንቃቄና በታማኝነት እንድንሠራ ያበረታታናል። ሰዎችን ከመፍራትም ያድነናል፤ ምክንያቱም የመጨረሻ ፈራጃችን እግዚአብሔር ስለሆነ ነው። በመጨረሻም፥ እግዚአብሔር አንድ ቀን በሥራችን እንደሚፈርድ ማስተዋል ችግሮች ሲያጋጥሙን እንኳን ጉዞአችንን እንድንቀጥል ያበረታታናል። የምናገለግለው እርሱን እንጂ ራሳችንን አይደለም።

በዚህ ክፍል ጳውሎስ ያካፈለው ዋና ኃላፊነት «ቃሉን ስበክ!» የሚለው ነው። ሌላው ጳውሎስ የተናገረው ነገር ሁሉ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው። «ስበክ» የሚለው ቃል «እንደ አዋጅ ነጋሪ መናገር» ማለት ነው። በጳውሎስ ዘመን፥ አንድ መሪ ለሕዝቡ ማስታወቂያዎችን የሚናገር ልዩ አዋጅ ነጋሪ ነበረው። በጉልህና በጠራ ድምፅ ሁሉም እንደሚሰማው አድርጎ ማስታወቂያዎቹን እንዲናገር፥ በመሪው የተላከ ነበር። ይህ ሰው የመደራደር መብት ያለው አምባሳደር አልነበረም፤ መስማትና ማስተዋል የሚያስፈልገውን አዋጅ የያዘ መልእክተኛ ነበር። የመሪውን መልእክተኛ አለማስተዋል አደገኛ ነበር፤ መልእክተኛውን ማዋረድ ደግሞ የባሰ ክፉ ነገር ነበር።

ጤሞቴዎስ ሰማያዊ ሥልጣንን ከኋላው ደጀን አድርጎ የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ ነበረበት። የእግዚአብሔር ቃል ለኃጢአተኞችም ሆነ ለቅዱሳን የሚያስፈልግ ነው። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በራሳቸው አስተያየት መልካም የሚመስሉትን፥ ዳሩ ግን መጥፎ የሚሆኑትን ሌሎች ነገሮች መተካታቸው አሳዛኝ ነው። በራሴ የመጋቢነት አገልግሎት፥ የቃሉ ስብከት በአብያተ ክርስቲያናትና በግለሰቦች ሕይወት ውስጥ ሊያደርግ የሚችለውን ነገር አይቻለሁ፤ ስለዚህ ምንም ነገር የእርሱን ቦታ ሊወስድ እንደማይችል አረጋግጣለሁ።

ጢሞቴዎስ ሲያመችም ሳያመችም፥ ቃሉን ለመስበክ እያንዳንዱን አጋጣሚ ለመጠቀም ትጉህና ንቁ መሆን አለበት። የመሥራት አጋጣሚዎችን መፍጠር ሲገባን ላለመሥራት ምክንያቶችን መፍጠር ይቀለናል። ጳውሎስ ራሱ ሁልጊዜ በምኩራብ ቢሆን፥ በተናወጠ ባህር ላይ ወይም በእሥር ቤት ውስጥ እንኳ፥ ቃሉን ለማካፈል አጋጣሚ ያገኝ ነበር። «ነፍስን የሚጠባበቅ አይዘራም፥ ደመናትንም የሚመለከት አያጭድም» (መክ. 11፡4)። ላለመሥራት ሰበቦችን መፍጠር አቁምና ሥራህን ጀምር!

ስብከት በሦስት መሠረታዊ ነገሮች መገለጽ አለበት። እነዚህም፡- ወቀሳ፥ ማስጠንቀቂያ እና ልመና (ዘለፋ፥ ግሣፄ፥ ምክር) ናቸው። የሰባኪያንን ጥናታዊ ጥንታዊ መመሪያ ለመጥቀስ «ተደላድሎ የተቀመጠውን ማመሰቃቀልና ተደላድሎ ማመቻቸት አለበት» የሚል ነበር። ወቀሳ ቢኖርና ማስወገጃው ከሌለ በሰዎች ሽክም ላይ እንጨምራለን። መገሠፅ የሚገባቸውን ደግሞ ካበረታታን ኃጢአትን እንዲሠሩ እየረዳናቸው ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት ሚዛናዊ መሆን አለበት።

የእግዚአብሔር አገልጋይ ቃሉን ሲሰብክ ትዕግስተኛ መሆን አለበት። ሁልጊዜ ቅጽበታዊ ውጤቶችን አያይም። ስብከቱን የሚቃወሙትን መታገስ አለበት። ከሁሉም በላይ ትምህርቱን መስበክ አለበት። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ብቻ መናገር፥ የሚሰቡ ምሳሌዎችን ማቅረብ ወይም ጥቅስ ማንበብና መልሶ መርሳት የለበትም። እውነተኛ ስብከት የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ማብራራትና መተግበር ነው። ማንኛውም ሌላ ነገር ሃይማኖታዊ ለፈፋ ብቻ ነው።

ጳውሎስ «ቃሉን ስበክ» (4፡2) የሚል ኃላፊነት ሲሰጥ፥ ምክንያቱንም ደግሞ አስከትሏል (4፡3-4)። ብዙ ሰዎች «ጤናማ ትምህርት» የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል የማይፈልጉበት ጊዜ ይመጣል (እናም እዚህ ለብዙ ጊዜ ነበረ!)። ለሃይማኖታዊ አዳዲስ ልምምዶች ሥጋዊ ፍላጎቶች ይኖራቸዋል። «ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ» ስለሆነ ከእግዚአብሔር እውነት ጋር ለማይስማሙ ነገሮች ያሏቸውን ፍላጎቶች የሚያረኩ አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። አንድ ሰባኪ በሚያገለግልበት ስፍራ የብዙ ሰዎች መከማቸት ሁልጊዜም እውነትን እየሰበከ እንደሆነ የሚያሳይ ምልክት አይደለም። እንዲያውም፥ ምናልባት የሰዎችን «የሚያሳክክ ጆሮ» እየኮረኮሩ መስማት ከሚያስፈልጋቸው ይልቅ መስማት የሚፈልጉትን እየሰጣቸው እንደሆነ የሚያስረዳ ሊሆን ይችላል።

«የሚያሳክክ ጆሮ» ያለውን ሰው ከእውነት ለማራቅ ያለው እርምጃ በጣም ቀላል ነው። ሰዎች አንድ ጊዜ እውነትን ከጣሉ ወደ ተረቶችና አፈታሪኮች ይመለሳሉ። ሰው-ሠራሽ ተረቶች ስለ ኃጢአት ይወቅሱአቸውና ንስሐ እንዲገቡ ያደርጉአቸዋል ለማለት አይቻልም! ውጤቱም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነትና ትምህርት የሌለበትን ሃይማኖታዊ ለፈፋ የሚያዳምጡ የውሸት ክርስቲያኖችን ጉባዔ ማፍራት ነው። የእነዚህ ሰዎች ሕይወት በእግዚአብሔር ላይ ስላልተመሠረተ ለሌላው ለማንኛውም ሐሰተኛ ትምህርት የተጋለጡ ይሆናሉ። ብዙዎቹ አሳቾች አስቀድመው የአብያተ ክርስቲያናት አባላት የነበሩ መሆናቸው የታወቀ ነገር ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን አትኩሮት አስተውል፡- «ቃሉን ስበክ ... ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሱበት ዘመን ይመጣል ... እውነትን ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ» (4፡24)። ይህ በጤናማ ትምህርት ላይ የተደረገ ትኩረት በሦስቱም የጳውሎስ የመጋቢነት መልእክቶች ውስጥ ይገኛል። ይህ ትኩረት ዛሬም በእርግጥ ያስፈልጋል።

2. አገልግሎትህን ፈጽም (2ኛ ጢሞ. 4፡5-8)

«አገልግሎትህን ፈጽም» ማለት «እግዚአብሔር እንድታደርግ የሚፈልግብህን ማናቸውንም ነገር ፈጽም» ማለት ነው። የጢሞቴዎስ አገልግሎት ልክ እንደ ጳውሎስ አይሆንም፤ ለክርስቶስ ግን አስፈላጊ (ጠቃሚ) ይሆናል። ማንኛውም የእግዚአብሔር ምሪት ያለበት አገልግሎት ትንሽ ወይም የማያስፈልግ አይደለም። በዚህ በመጨረሻ ምዕራፍ፥ ጳውሎስ ስለ እነርሱ ምንም የማናውቃቸውን ጥቂት አብረውት የሠሩ ሠራተኞች ስም ጠቅሷል፤ ዳሩ ግን እነርሱም የሚፈጽሙት አገልግሎት ነበራቸው።

አንድ ጊዜ አንድ ወጣት ሰባኪ ለታወቁት የ1800 ዓ.ም. እንግሊዛዊ ሰባኪ ቻርለስ ስፐርጅን፥ ለእርሱ የሚገባውን ያህል ትልቅ ቤተ ክርስቲያን እንደሌለው በቅሬታ ተናግሮ ነበር።

ስፐርጅን «ለስንት ሰዎች ትሰብካለህ?» ብለው ጠየቁት። ሰውየውም «አ! ለ100 ያህል» ብሎ መለሰ። ወዲያውም ስፐርጅን «በፍርድ ቀን መልስ ለመስጠት ያ በቂ ይሆናል» ብለው መለሱለት።

የአገልግሎትን አፈጻጸም በአሐዛዊ መረጃ (በስታትስቲክስ) ወይም ሰዎች በሚያዩት ነገር ብቻ አንለካም። ታማኝነት አስፈላጊ መሆኑንና እግዚአብሔር ደግሞ ልብን እንደሚያይ እናውቃለን። ለዚህ ነበር ጢሞቴዎስ «ነገርን ሁሉ በልክ ማድረግ» (4፡5)፥ እንዲሁም አገልግሎቱን በጸና ዓላማ መፈጸም የነበረበት። (በእነዚህ መልእክቶች ውስጥ ይህን «ልክ» የሚለውን ቃል ብዙ ጊዜ አግኝተናል)።

ጢሞቴዎስ ሰባኪ ብቻ አልነበርም፤ «መከራን መቀበል» (4፡5) የነበረበት ወታደርም ጭምር (2፡3-4) ነበር። ጳውሎስ በመከራ ውስጥ ሲያልፍ ከአንዴም ብዙ ጊዜ አይቷል (3፡10-12፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡1-10)። ብዙዎቹ የጢሞቴዎስ መከራዎች የሚመጡት እውነትን መስማት ከማይፈልጉ «ሃይማኖታዊ ቡድኖች» ሕዝቦች ነበር። ክርስቶስን የሰቀሉት፥ እንዲሁም ጳውሎስን ያሳደዱትና ያሳሠሩት «ሃይማኖታዊ ቡድኖች» ነበሩ።

«የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ» (2ኛ ጢሞ. 4፡5) የሚለው መመሪያ፥ ማናቸውም የጢሞቴዎስ አገልግሎት በውስጡ ነፍሳትን መማረክን ማካተት እንዳለበት ያሳስበዋል። ይህም እያንዳንዱ ስብከት «ስለገህነም በመስበክ ሰዎችን በማስፈራራት የሚጠራ» መልእክት ይሆናል ማለት አይደለም። ምክንያቱም ቅዱሳን መመገብም

ስለሚያስፈልጋቸው ነው፤ ነገር ግን ሰባኪ የሚሰብከው ምንም ዓይነት ነገር ይሁን በአሳቡ የጠፉትን ነፍሳት መያዝ አለበት ማለት ነው። ይህ ለጠፉት ያለው ሸክም የአንድን መጋቢ የግል አገልግሎትም ማንጸባረቅ አለበት። (ስለሚዛናዊ አገልግሎት ገለጻ የሐዋ. 20፡17-28 ተመልከት)።

እግዚአብሔር የተለዩ ሰዎችን እንደ ወንጌላውያን ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል (የሐዋ. 21፡8፥ ኤፌ. 4፡11)። ሆኖም ይህ መጋቢን ከነፍስ ማዳን ኃላፊነቱ አያወርደውም። ሁሉም ሰባኪ ተመሳሳይ ስጦታዎች የሉትም፤ ዳሩ ግን እያንዳንዱ ሰባኪ ተመሳሳይ ሸክም ሊካፈልና ተመሳሳይ የሚያድን መልእክት ሊያውጅ ይችላል። አንድ ወዳጄ አንድ ታላቅ ሰባኪ ሲሰብክ ለመስማት ሄደና መልእክቱ እንዴት እንደነበር ጠየቅሁት። እርሱም «አንዲት ቁንጫ ለማዳን የሚበቃ ወንጌል አልነበረበትም» ብሎ መለሰልኝ።

ጳውሎስ ከኃላፊነቱ በስተኋላ ያለውን ምክንያት ሰጥቷል (2ኛ ጢሞ. 4፡6-8)፡- እርሱ ከእይታ ሊሰወር ስለተቃረበና፥ ጢሞቴዎስ የእርሱን ቦታ መሸፈን ስለ ነበረበት ነው። በዚህ የግል ምስክርነትን በያዘ ውብ አንቀጽ ውስጥ፥ ጳውሎስን በሦስት የተለያዩ አቅጣጫዎች ሲመለከት ታገኙታላችሁ።

ዙሪያውን ቃኘ (4፡6) ጊዜው አጭር እንደሆነ ተገነዘበ። በሮም ውስጥ በችሎት ላይ ቀርቦ የመጀመሪያውን ዙር ጥያቄ ጨርሷል! (4፡17)፤ ነገር ግን ጳውሎስ መጨረሻው እንደቀረበ አውቆ ነበር። ሆኖም በሞት አሳብ አልተርበደበደም ነበር! «መሠዋት» እና «መሄድ» የሚሉ ሁለት ቃላት (4፡6)፥ ስለ እምነቱና ስለ ጽናቱ ይነግሩናል። «መሠዋት» ማለት «በመሠዊያ ላይ እንደመጠጥ ቁርባን መፍሰስ» ማለት ነው። በፊሊጵስዩስ 2፡7-8 ተመሳሳይ ገለጻ ተጠቅሟል። ጳውሎስ «ቁሳር እኔን አይገድለኝም። ሕይወቴን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መሥዋዕት አድርጌ እሰጣለሁ። ከዳንኩበት ቀን ጀምሮ ሕያው መሥዋዕት ሆኜ እያገለገልኩት ነበርኩኝ። አሁን ሕይወቴን ለእርሱ በመተው ያንን መሥዋዕት ሙሉ አደርጋለሁ» እያለ ነበር።

መሄድ (2ኛ ጢሞ. 4፡6) የሚለው ቃል ብዙ ትርጉሞች ያሉት ውብ ቃል ነው። «መልህቅ መንቀልና ጉዞ መቀጠል» ማለት ነው። ጳውሎስ ሞትን ከዓለም እስር ተላቆ ወደ ዘለዓለሙ መንግሥት ጉዞ እንደመቀጠል አድርጎ ይመለከተዋል። እንዲሁም ቃሉ «ድንኳን መንቀል» ማለት ነው። ይህ በ2ኛ ቆሮ. 15፡1-8 ጳውሎስ አማኞች የማይሞተውን የክብር ሰውነት ለመቀበል የሚሞቱትን ሞት ድንኳንን

ከመንቀል ጋር ካወዳደረበት ጋር ተመሳሳይ ነው። («በእጁ ያልተሰራ ቤት» - የከበረ ሰውነት እንጂ በሰማያት ያለ «ታላቅ አዳራሽ» አይደለም)።

መሄድ «እስረኛን መፍታት» የሚል ትርጉም አለው። ጳውሎስ እየተጋፈጠ የነበረው ከመገደል ጋር ሳይሆን ከመለቀቅ ጋር ነበር! «የበረን ቀንበር ማላቀቅ ወይም ማንሣት» ሌላው የዚህ ቃል ትርጉም ነው። ጳውሎስ ለብዙ ዓመታት በከባድ አገልግሎት ውስጥ ነበር። አሁን ጌታው ከቀንበር አላቆት ከፍ ወዳለ ሥራ ያሳድገዋል።

ጳውሎስ ወደ ኋላ ተመልከቶ (2ኛ ጢሞ. 4:7) ሕይወቱንና አገልግሎቱን ይገመግማል። እነዚህ ሁለቱ ምስሎች ስፖርታዊ ናቸው:- ነጻ ትግል እንደሚታገል ወይም እንደ ቦክሰኛ መልካሙን ገድል ተጋድሏል፤ ደግሞም እንደ ሯጭ የዕድሜ ልክ እሩጫውን በድል ፈጽሞአል። ደምቡን በመጠበቅ ለሽልማት ተዘጋጅቷል (ፊሊ. 3:13-14፤ የሐዋ. 20:24 ን ተመልከት)። ሦስተኛው ምስል የአለቃውን ንብረት በታማኝነት የጠበቀውን አገልጋይ የሚያመለክት ነው፥ «ሃይማኖትን ጠብቄያለሁ» (2ኛ ጢሞ. 4:7)። ጳውሎስ በመጋቢነት መልእክቶቹ ይህንን ምስል ብዙ ጊዜ ተጠቅሞአል።

ወደ ኋላ ተመልከቶ ምንም የሚጸጸቱበት ነገር አለማግኘት የሚያጽናና ነው። ጳውሎስ ሁልጊዜ ተወዳጅ፥ እንዲሁም ብዙ ጊዜ የተመቸው ሰው አልነበረም፤ ሆኖም በታማኝነቱ ጸንቷል፤ ያ ነው ዋጋ የነበረው።

በመጨረሻ ጳውሎስ ወደፊት ተመለከተ (4:8):- አሸናፊ የሆነ የግሪክ ወይም የሮም ስፖርተኛ በሕዝቡ ይሸለማል። እንዲሁም ብዙ ጊዜ የቅጠል አክሊል ወይም የዛፍ አበባ ጌጥ ያገኝ ነበር። «አክሊል» የሚለው ቃል የመጣው እስጢፋኖስ ከሚለው ሲሆን፥ የአሸናፊው አክሊል ነው፤ እስጢፋኖስ የሚለውም ስም ከዚህ ቃል የተገኘ ነው። (የነገሥታት አክሊል ዲያዴማ በመባል ይታወቃል)፤ ይሁን እንጂ ጳውሎስ የሚጠወልግ የቅጠሎች አክሊል አያገኝም፤ የእርሱ በፍጹም የማይጠወልግ (የማይጠፋ) የጽድቅ አክሊል ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሁልጊዜ በትክክል የሚፈርድ «ጻድቅ ፈራጅ» ነው። በሮም የነበሩ የጳውሎስ ፈራጆች ጻድቅ አልነበሩም። ቢሆኑ ኖሮ፥ ይፈቱት ነበር። ጳውሎስ ከአንዱ ፍርድ ቤት ወደ ሌላው ፍርድ ቤት ብዙ ጊዜ ቢቀርብም፥ አሁን የመጨረሻ ፈራጁ ጌታው እና አዳኙ በሆነው

በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ቀርቧአል። ጌታ ፊት ለመቅረብ የተዘጋጀህ ስትሆን፥ የሰዎችን ፍርድ መፍራት አይገባህም።

የጽድቅ አክሊል ለታማኝ እና ለጻድቅ ሕይወት የእግዚአብሔር ሽልማት ነው፤ ለታማኝነትና ለቅድስና ያለን ማበረታቻ የጌታ መገለጥ ተስፋ ቃል ነው። ጳውሎስ መገለጡን በመውደዱና በመናፈቁ እየተመላለሰ፥ በታማኝነት አገለገለ። ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ባሉት ምክሮቹ የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ እንደ መሠረት አድርጎ የተጠቀመው ለዚህ ነው (4፡1ን ተመልከት)።

ሐዋርያት እንድንሆን አልተጠራንም፤ ሆኖም ጳውሎስ ያገኘውን ዓይነት አክሊል ልንደፋ እንችላለን። የክርስቶስን መገለጥ ከወደድን፥ ስለ ፈቃዱ በመገዛት ከኖርንና እንድናደርገው የጠራንን ሥራ ከፈጸምን አክሊል እንደፋለን።

3. ትጉህና ታማኝ ሁን (2ኛ ጢሞ. 4፡9-22)፡-

ለጢሞቴዎስ የተሰጠው ምክር «ፈጥነህ እዚህ ና» የሚል ነው (4፡9)። ቲኪቆስ በኤፌሶን የጢሞቴዎስን ቦታ ይሸፍናል (4፡12)። ጢሞቴዎስ ወደ ሮም ሲፈጥን ሳለ፥ ጢሮአዳ ደርሶ በርኖሱን፥ መጻሕፍቱንና ብራናዎቹን መውሰድ ይችላል (4፡13)። ጳውሎስ ምናልባት እዚያ የተዋቸው ለመሄድ በመቸኮሉ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ጳውሎስ ከምድር ላይ የሚሰናበትበት ጊዜ ሲደርስ «በእምነት ውድ ልጁ የሆነውን» አጠገቡ እንዲገኝ መፈለጉን ማየት ልብን የሚነካ ነገር ነው። ደግሞም ጳውሎስ ነገሮቹን በተግባር የሚፈጽም ሰው ነበር፡- በርኖሱን ለመቀት፥ መጻሕፍቱን ደግሞ ለጥናት ይፈልጋቸዋል። «መጻሕፍቱ» የፓፒረስ ጥቅልሎች፥ ምናልባትም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ይሆናሉ፤ «ብራናዎቹ» ደግሞ ከእንስሳ ቆዳ የተሰሩ መጻሕፍት ይሆናሉ። እነዚህ «ብራናዎች» ምን እንደሆኑ አናውቅም፤ ዳሩ ግን እንደ ጳውሎስ ያለ ምሑር ለጥናትና ለጽሑፍ የሚሆኑ ነገሮችን መፈለጉ አያስገርመንም።

ደብዳቤውን ከማብቃቱ በፊት ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ «ከክረምት በፊት እንዲመጣ» አሳስቦታል (4፡21)። ለምን? ለመጓዝ አደገኛ ስለሚሆን በክረምት መርከቦች ሁሉ ወደብ ላይ ይቆማሉ። ጢሞቴዎስ ረዥም ጊዜ ከጠበቀ፥ ወደ ጳውሎስ ለመጓዝ ያለውን እድል ያጣል፤ ከዚያ በኋላ ላያገኘው ይችላል።

ጢሞቴዎስ ትጉህና ታማኝ መሆን ያለበት ለምንድነው? የመልሱን ክፍል የሚሰጠውን ቁ. 10 ተመልከት፡- በጳውሎስ አካባቢ የነበሩ

አንዳንዶች ታማኞች ባለመሆናቸው፥ ጳውሎስ ሊደገፍባቸው አይችልም ነበር። ዴማስ በአዲስ ኪዳን ሦስት ጊዜ ብቻ ተጠቅሶአል፤ ሆኖም እነዚህ ሦስት ገለጻዎች አሳዛኝ የመውደቅ ታሪክ ይናገራሉ። ጳውሎስ ዴማስን ከማርቆስ እና ከሉቃስ ጋር አብረውት ከሚሠሩት እንደ አንዱ አድርጎ ጠቅሶታል (ፊሊ. 24)። ከዚያም «ዴማስ» ብቻ ተብሎ ነበር የተጠራው (ቆላ. 4፡14)። በዚህ በ(2ኛ ጢሞ. 4፡10) ውስጥ ደግሞ «ዴማስ ትቶኛል» የሚል ነው።

ጳውሎስ ምክንያቱን ሰጥቷል፡- ዴማስ «የአሁኑን ዓለም ወዷል»። እንደ አማኝ «ሊመጣ ያለውን ዓለም ኃይል የቀመሰ» ነበር (ዕብ. 6፡5)፤ ነገር ግን «የአሁኑን ክፉ ዓለም» (ገላ. 1፡4) መረጠ። ጆን ቡንያን በመናኝ ጉዞ መጽሐፉ ዴማስን በአንድ ተራራ ላይ ያለ የብር ማዕድን ጠባቂ አድርጎ አስቀምጦታል። ምን አልባት ዴማስን ወደ ዓለም እንዲመለስ ያነሣሣው የገንዘብ ፍቅር ሊሆን ይችላል። የዴማስ እንዲያ ባለ አሳፋሪ ሁኔታ መውደቅ የጳውሎስን ልብ ሳይሰብር አይቀርም፤ ሆኖም ይህ በማንም አማኝ ላይ ሊደርስ ይችላል። ጳውሎስ በመጋቢነት መልእክቶቹ ስለ ሀብት ብዙ ሊናገር ለምን እንዳስፈለገው ምናልባት ይህ ያስረዳ ይሆናል።

ሌላው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በሮም የፈለገበት ምክንያት የሚቀጥለው ፍርድ ቤት የሚቀርብበት ጊዜ ስለ ደረሰና ከእርሱ ጋር ያለው ሉቃስ ብቻ ስለሆነ ነው። ከጳውሎስ ጋር መቆም ይችሉ የነበሩ በሮምና በኤፌሶን የነበሩ ምእመናን ትተውታል (2ኛ ጢሞ. 4፡16)፤ ነገር ግን ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እንደማይተወው ያውቅ ነበር። በእርግጥ ጌታም ጳውሎስን አልተወውም ነበር! (4፡17)። ጌታ ከጳውሎስ ጋር እንደሚሆን ቃል ገብቶ ነበር። ቃሉንም ጠብቋል።

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ውስጥ ተስፋ በቆረጠ ጊዜ፥ ጌታ ወደ እርሱ መጥቶ አበረታታው (ሐዋ. 18፡9-11)። በኢየሩሳሌም ከታሠረ በኋላም ጳውሎስ እንደገና በጌታ ተጎብኝቶ ተበረታታ (ሐዋ. 23፡11)። በዚያ አስፈሪ ማዕበል ጊዜ ጳውሎስ በመርከብ ላይ ሳለ ጌታ እንደገና ጉልበትና ብርታት ሰጠው (ሐዋ. 27፡22-26)። አሁን በዚያ አስጨናቂ የሮሜ እሥር ቤት ውስጥ «አልለቅህም ከቶም አልተውህም» (ዕብ. 13፡5) ብሎ ቃል የገባውን ጌታ አበረታች ጉብኝት እንደገና አገኘ።

ነገር ግን የጳውሎስ አሳብ ለራሱ ከአደጋ ለማምለጥ ወይም ምቾት እንዳልነበር አስተውል። ግድ የሚለው ለአሕዛብ ደኅንነት ቃሉን የመስበክ ጉዳይ ነው። አሕዛብን ማገልገል የጳውሎስ የተለየ ጥሪ ነበር

(ኤፌ. 3 ተመልከት)፤ እሱም ደግሞ በታላቋ የሮም ከተማ ውስጥ እንኳን በወንጌል አያፍርም ነበር (ሮሜ 1፡16)።

እንዴት ያለ ሰው ነው! ወዳጆቹ ተዉት፤ እርሱ ደግሞ እግዚአብሔር ይቅር እንዲላቸው ይጸልያል። ጠላቶቹ በሁሉም አቅጣጫ ያሳድዱታል፤ እርሱ ደግሞ እንዴት እንደሚድኑ ሊነግራቸው ቀዳዳዎችን ይፈልጋል! መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችሁን ሲቆጣጠር፥ እንዴት ያለ ለውጥ ያመጣል።

«ከአንበሳ አፍም ዳንሁ» (2ኛ ጢሞ. 4፡17)። ይህ «አንበሳ» ማን ወይም ምንድን ነው? እውነተኛውን አንበሳ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ጳውሎስ የሮማ ዜጋ ስለነበረ፥ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ወደ አንበሶች ሊጣል አይችልም። በምትኩ ራሱ ተቆርጦ ይገደላል። «አንበሳው» ንጉሥ ኔሮ ነበር? ላይሆን ይችላል፤ ከኔሮ ቢያመልጥ ኖሮ፥ በነጻ ይለቀቅ ነበር ማለት ነው፤ ሆኖም ፍርድ ፊት ሲቀርብ ያ የመጀመሪያው ጊዜ ነበር። አንበሳው የሰይጣን ምሳሌ ነው (1ኛ ጴጥ. 5፡8)። ምናልባት ጳውሎስ የሚጠቅሰው እራሱን ለማሸነፍና የወንጌልን ሥራ ለማደናቀፍ የተወጠነውን የሰይጣን ዕቅድ ሊሆን ይችላል። «ከአንበሳ አፍ መዳን» ማለት «ከትልቅ አደጋ ማምለጥ»ን የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነበር [መዝ. (22)፡21]።

ነገር ግን ለክርስቲያን ከመከራ እና ከሞት በላይ አደገኛ የሆኑ ነገሮች እንኳን አሉ። ለምሳሌ ኃጢአት። ጳውሎስ ያሰበው ይህንን ነበር (2ኛ ጢሞ. 4፡18)። ጌታ «ከክፉ ነገር ሁሉ» እንደሚያድነውና ለሰማያዊውም መንግሥት እንደሚያበቃው እርግጠኛ ነበር። የጳውሎስ ትልቅ ፍራቻ ሞት ላይሆን፥ ጌታውን እንዳይክድ ወይም የእግዚአብሔርን ስም የሚያሰድብ ነገር እንዳያደርግ ነበር። ጳውሎስ ለዘለዓለሙ የሚለይበት ጊዜ እንደደረሰ እርግጠኛ ነበር (4፡6)። የሕይወት ሩጫውን በመልካም ሁኔታ መፈጸምና ከማንኛውም አለመታዘዝ ነጻ ለመሆን ፈልጓል።

በዚህ ጳውሎስ በጻፈው የመጨረሻ መልእክት መዝጊያ ውስጥ፥ ምን ያህል መጋቢዎች እንደተገለጹ ማየት ልብን የሚያጽናና ነው። በሐዋርያት ሥራና በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ በዙሪያው እንዳሉ ወዳጆችና አብረውት እንደሚሠሩት ሆነው ቢያንስ 100 የተለያዩ ወንዶች እና ሴቶች እንደተጠቀሱ አምናለሁ። ጳውሎስ ሥራውን በራሱ ሊሠራ አይችልም ነበር። ሥራው እንዲሠራ የሚረዱትን ሌሎች ሰዎች

የሚያሳትፍና በሥራው ትልቅነት ውስጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የሚያደርግ ሰው ታላቅ ሰው ነው።

ሉቃስ (4፡11) ከጳውሎስ ጋር የተጓዘ (ቆላ. 4፡14) «ተወዳጅ ሐኪም» ነው። የሉቃስ ወንጌልና የሐዋርያት ሥራ መጻሕፍት ጸሐፊ ነው (በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የዶክተር ሉቃስን የዓይን ምስክርነት ዘገባ የሚገልጹትን «እኛ» የሚሉትን ክፍሎች አስተውል)። ምናልባት ይህንን መልእክት (2ኛ ጢሞ.) ሉቃስ የጻፈለት ጳውሎስ በቃሉ ነግሮት ሊሆን ይችላል። ዶክተር እንደመሆኑ፥ ሉቃስ የጳውሎስን የ «ጭንቁር» ገለጻ ሳያደንቅ አይቀርም (2፡17)።

ቁርቂስ (4፡10) ወደ ገላቲያ በጳውሎስ የተላከ ነበር። ስለ እርሱ ምንም የምናውቀው ነገር የለም፤ ማወቅም አያስፈልገንም። ይህም በጣም በሚያስፈልገው ሰዓት ጳውሎስን የረዳ ሌላው ታማኝ አገልጋይ ነበር።

ቲቶ (4፡10) የጳውሎስ የቅርብ ረዳት ሲሆን፥ ከጢሞቴዎስ ጋር የታመነ «ችግር አቃላይ» ነበር። ጳውሎስ በቀርጤስ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የነበሩትን ችግሮች እንዲያቃና ቲቶን በዚያ ተወው (ቲቶ 1፡5)። ለቲቶ የጻፈውን የጳውሎስ መልእክት ስናጠና፥ ከዚህ ከተመረጠ የእግዚአብሔር አገልጋይ ጋር በተሻለ ሁኔታ ተዋውቀናል። ቲቶ ጳውሎስን በታሰረባቸው ጊዜያት መካከል በኒቆጵልዮን አግኝቶት ነበር (ቲቶ 3፡12)። አሁን ጳውሎስ ወደ ሮም ጠራውና ወደ ድልማንያ (ዘመናዊዋ ዩጎዝላቪያ) ላከው።

ግርቆስ (2ኛ ጢሞ. 4፡11) የመጀመሪያው የጳውሎስ የተልእኮ አገልግሎት ጓደኛ የነበረው የበርናባስ የአክስት ልጅ ነበር (ሐዋ. 13፡1-3)። እናቱ በኢየሩሳሌም የታወቁ ክርስቲያን ነበሩ (ሐዋ. 12፡5፥ 12)። የሚያሳዝነው፥ ዮሐንስ የተባለው ግርቆስ በዚያ በመጀመሪያው የተልእኮ ጉዞ ተለየው (ሐዋ. 13፡5፥ 13)። በሁለተኛው ጉዞ ጳውሎስ ግርቆስን ለመውሰድ እምቢ አለ። ይህ ደግሞ በጳውሎስና በበርናባስ መካከል መለያየትን አመጣ (የሐዋ. 15፡36-41)። ሆኖም ጳውሎስ አሁን ግርቆስ ጠቃሚ ሠራተኛ መሆኑን አምኗል፤ ስለዚህ በሮም ግርቆስ አብሮት እንዲሆን ፈለገ። በክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ አንድ ውድቀት የዚያን ሰው ሕይወት በሙሉ ዋጋ ቢስ እንደማያደርግ ማወቅ እንዴት መልካም ነው።

ቲኪቆስ (2ኛ ጢሞ. 4፡12) ጳውሎስን በፈቃደኝነት የተከተለና ምናልባትም ለሐዋርያው የግል አገልጋይ በመሆን ያገለገለ ከእስያ አገር የመጣ አማኝ ነበር (ሐዋ. 20፡4)። በጳውሎስ የመጀመሪያ እሥራት ጊዜ

አብሮት ነበር (ቆላ. 4:7-8፥ ኤፌ. 6:21-22)። ጳውሎስ ቲቶን ለመተካት ሲል ቲኪቆስን ወደ ቀርጤስ ላከው [ቲቶ 3:12]። አሁን ቲኪቆስ ቲቶን እንዲያግዝ ወደ ኤፌሶን ላከው። አሁንም ጢሞቴዎስን እንዲተካ ወደ ኤፌሶን እየላከው ነበር። ሌሎችን መተካት የሚችሉትን ሰዎች ማግኘት ምን ዓይነት በረከት ነው! በእግር ኳስ ጨዋታ ወቅት፥ ኳሱን ለአግቢው የሚያቀብል ሰው ክብሩን ሁሉ ላይወስድ ቢችልም፥ ቡድኑ እንዲያሸንፍ በማድረጉ ግን ትልቅ አስተዋጽኦ ማድረጉ የሚካድ አይደለም።

አክርጳ (2ኛ ጢሞ. 4:13) በጢሮአዳ የኖረና ለጳውሎስ መስተንግዶ ያደረገለት ሰው ነበረ። ጳውሎስ በችኮላ ሳይሆን አይቀርም የወጣው (ለእስር በመፈለጉ ይሆን?)፤ ምክንያቱም በርኖሱንና መጻሕፍቱን ትቶ ስለነበረ ነው። ሆኖም አክርጳ የታመነ ወንድም ስለ ነበረ፥ ወደ ጳውሎስ ለማድረስ አንድ ሰው እስከሚወስዳቸው ድረስ ይጠብቃቸው ነበር። እንደዚህ ዓይነት ዝቅተኛ ግምት የሚሰጣቸው ሥራዎች እንኳን ለጌታ የሚሆኑ አገልግሎቶች ናቸው።

«የናስ አንጥረኛው እስክንድሮስ» (4:14) በ1ኛ ጢሞ. 1:20 ላይ ከተጠቀሰው እስክንድሮስ ጋር አንድ ነው? ማንም አያውቅም። ደግሞም በአጠራጣሪ ጉዳይ ላይ አስተማማኝ ያልሆነ አሳብ በማቅረብ የሚገኝ ጠቀሜታም አይታየኝም። ስሙ የተለመደ ነበር፤ ነገር ግን ይህ ሐሰተኛ ሰው በጳውሎስ ላይ ነገሮችን ለማባባስ ወደ ሮም ሄዶ ሊሆን ይችላል። «ሰይጣንም የራሱ ሠራተኞች አሉት።» በነገራችን ላይ፥ «ጌታ እንደሥራው ይመልስለታል» (2ኛ ጢሞ. 4:14) የሚለው የጳውሎስ አነጋገር፥ የፍርድ ጸሎት አይደለም፤ ምክንያቱም ይህ ከኢየሱስ ትምህርት ጋር የሚቃረን ስለሚሆን ነው (ማቴ. 5:43-48)። «ጌታ ብድራቱን ይከፍልለታል» የሚለው የተሻለ አተረጓጎም ነው።

ጵርስቅላ እና አቂላ (2ኛ ጢሞ. 4:19) ጳውሎስን በብዙ መንገዶች የረዱ ባልና ሚስት ነበሩ (የሐዋ. 18:1-3፥ 24-28፤ ሮሜ 16:3-4፤ 1ኛ ቆሮ. 16:19 ን ተመልከት)። አሁን በኤፌሶን ሆነው ጢሞቴዎስን በአገልግሎቱ ይረዱት ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ማንም መሪያቸው ቢሆን ሥራቸውን አክብረው ሲሠሩ መመልከት የሚያስደስት ነገር ነው።

ሄኔሲፎሩ (2ኛ ጢሞ. 4:19) እና ቤተሰቡን በምዕራፍ 1 አይተናቸዋል።

ኤርስጦስ (4:20) የቆሮንቶስ ከተማ መጋቢ ሊሆን ይችላል (ሮሜ 16:23)፤ በመቄዶንያ ከጢሞቴዎስ ጋር ያገለገለውም እርሱ ሊሆን ይችላል (ሐዋ. 19:22)።

የኤፌሶን ጥሮፊሞስ (2ኛ ጢሞ 4:20) የቲኪቆስ ወዳጅ ነበር (የሐዋ. 20:4)። ደግሞም ከጳውሎስ ጋር መሆኑ በኢየሩሳሌም ሕዝቡ እንዲነሳባቸው ተጨማሪ ምክንያት ሆኖ ነበር (የሐዋ. 21:28-29) በሚሊጢስ ያገለግል ነበር፤ አሁን ግን ታሞ ነበር። ጳውሎስ ለምን አልፈወሰውም? እንደሚታወቀው የታመመ ሰው ሁሉ በተአምር መዳን የለበትም።

ሌሎቹ የተጠቀሱት ሰዎች (2ኛ ጢሞ. 4:21) እኛ የማናውቃቸው ናቸው። ለጌታ ግን እንዲህ አይደለም።

«ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን» (4:22) የሚለው መልእክቱ የተጭበረበረ አለመሆኑን የሚያሳይ በጳውሎስ መልእክቶች መጨረሻ ላይ እንደ «ንግድ ምልክት» የሚያገለግል የጳውሎስ የግል መሰናበቻ ነበረ።

መጽሐፍ ቅዱስ የጳውሎስን የመጨረሻ ቀናት አይዘግብም። አፈ ታሪክ ግን ወንጀለኛ ሆኖ እንደተገኘና የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት ይነግረናል። ከከተማ ውጪ ተወስዶ አንገቱ ሳይሰየፍ አልቀርም።

ነገር ግን ጢሞቴዎስና ሌሎች ራሳቸውን የሰጡ አማኞች ሥራውን ቀጠሉ! ጆን ዌስሊይ ይል እንደነበረው «እግዚአብሔር ሠራተኞቹን ይቀብራል፤ ዳሩ ግን ሥራው ይቀጥላል»። የሚመጡት ትውልዶች (ጌታ ቶሎ ካልተመለሰ) ወንጌልን እንዲሰሙና ለመዳን ዕድል እንዲያገኙ አንተና እኔ ታማኞች መሆን አለብን።

የፊሊሞና መልእክት አስተዋጽኦ

ዋና አሳብ፡- ባሪያ የሆነው አናሲሞስ በክርስቶስ እንደ ተወደደ ወንድም ሆኖ እንዲያዝ የተደረገ ልመና (ቁ. 15-16)።

I. አድናቆት (1-7) - «አምላኬን አመሰግናለሁ»

1. የጳውሎስ ፍቅር፥ 1-3
2. የጳውሎስ ምስጋና፥ 4-5፥ 7
3. የጳውሎስ ጸሎት፥ 6

II. ልመና (8-16) - «እለምንሃለሁ»

1. የፊሊሞና ባሕሪይ፥ 8-9
2. የአናሲሞስ መለወጥ፥ 10-14
3. የእግዚአብሔር ፈቃድ፥ 15-16

III. ማረጋገጫ (17-25) «እኔ እከፍላለሁ»

1. የጳውሎስ ጓደኝነት፥ 17-19
2. የጳውሎስ መተማመን፥ 20-22
3. የጳውሎስ ሰላምታ፥ 23-25

የሁለት ከተሞች ታሪክ

ፊሊሞና

ጳውሎስ በሮም እሥር ቤት ውስጥ ነበር። ወዳጁ ፊሊሞና በቆላስይስ ነበር፥ በመካከላቸው ሆኖ ያገናኛቸውም አናሲሞስ የተባለ ከባለቤቱ የኮበለለ ባሪያ ነበረ። ዝርዝር ጉዳዩ ግልጽ አይደለም፤ ዳሩ ግን አናሲሞስ ግርግር በበዛበት ታላቅ ከተማ ውስጥ እሰወራለሁ በሚል ተስፋ ጌታውን ዘርፎ ወደ ሮም እንደኮበለለ ይመስላል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነና አናሲሞስ ጳውሎስን ተገናኘ፥ ጌታንም ተቀበለ!

እንግዲህ ምን ይሁን? ለጳውሎስ የሚያስፈልገውን እርዳታ ለማድረግ አናሲሞስ አብሮት መቆየት ይኖርበት ይሆናል፤ ዳሩ ግን በቆላስይስ ለጌታው ያለው የባርነት ኃላፊነቱስ? ሕጉ ዓመፀኛ ባሪያውን ጌታው እንዲገድል ይፈቅድለታል። ፊሊሞን ግን ክርስቲያን ነበር። አናሲሞስን ከማረው ሌሎች ጌቶች (እንዲሁም ባሮች) ምን ያስባሉ? ከቀጣው ደግሞ ምስክርነቱን ምን ያህል ይጎዳል? ለፍርድ የቸገረ ነገር!

ወደ ቆላስይስ ሰዎች ከተጻፈው መልእክት ጋር ይህም ደብዳቤ ምናልባት ወደ ቆላስይስ የተወሰደው በቲኪቆስና በአናሲሞስ ይሆናል (ቆላ. 4፡7-9)። በውስጡ ጳውሎስ ፊሊሞና ችግሮቹን እንዲፈታ ለማገዝ ሲሞክር በሦስት አስፈላጊ ሚናዎች ውስጥ እናየዋለን። በዚያውም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር አብ ለእኛ ምን እንዳደረገልን የሚገልጸውን ውብ ምስል እናያለን። ማርቲን ሉተር «እኛ ሁላችን አናሲሞሶች ነን» ማለቱ ትክክል ነበር።

1. ጳውሎስ፥ የተወደደው ወዳጅ (ፊሊ. 1፡7)

ጳውሎስ በቆላስይስ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን አልመሠረታትም፤ አልጎበኛትምም (ቆላ. 1፡1-8፤ 2፡1)። ቤተ ክርስቲያኒቱ የተጀመረችው በኤፌሶን በነበረው አገልግሎቱ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም (ሐዋ. 19፡10፥ 20፥ 26)። እንዲሁም ኤጳፍራ መሥራች መጋቢ ሳይሆን አይቀርም (ፊሊ. 23)። ቤተ ክርስቲያኒቱ በፊሊሞናና በባለቤቱ በአፍብያ ቤት ትገለገል ነበር። አንዳንድ ሰዎች አርክጳ ልጃቸው እንደሆነ ይገምታሉ። ይህ ግን የተረጋገጠ እውነት አይደለም። ኤጳፍራ ጳውሎስን ለመርዳት ወደ ሮም ስለሄደ፥ የርሱን የአገልግሎት ቦታ የወሰደ ሽማግሌ ሊሆን ይችላል። ይህ እውነት ከሆነ፥

ለቤተ ክርስቲያን ሁሉ በጻፈው ደብዳቤ ለአክርጳ የሰጠውን ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ያብራራል (ቆላ. 4፡17)።

በሰላምታው ጳውሎስ ለክርስቲያን ወዳጆቹ ያለውን ጥልቅ ፍቅር ገለጸ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ እሥር እንደሆነ ያሳሰባቸዋል (9-10፥ 13፥ 23)። ምንም እንኳ የደብዳቤው ሽክም ከጳውሎስ ልብ ወደ ፊልሞና ልብ የሚተላለፍ ቢሆንም፥ ጢሞቴዎስም በሰላምታው ውስጥ ተካትቷል። የጳውሎስ አገልግሎት የ «ቡድን» ሥራ ስለ ነበር፥ ብዙ ጊዜ ደብዳቤዎቹን ሲጽፍ አብረውት የሚሠሩትን ሰዎች ስሞች ያስገባል። «አብሮኝ የሚሠራ» የሚለውን ቃል መጠቀም ይወድ ነበር (ሮሜ 16፡3፥ 9፥ 21፤ ፊልጵ. 2፡25፤ 4፡3፤ ቆላ. 4፡11፤ 1ኛ ቆሮ. 3፡9 ን ተመልከት)።

የአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት በቤት ውስጥ ይሰበሰቡ ነበር (ሮሜ 16፡5፥ 23፤ 1ኛ ቆሮ. 16፡19)። ምናልባትም በፊሊሞና ቤት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን በቆላስይስ ከነበሩት ሁለት ጉባኤዎች አንዷ ልትሆን ትችላለች (ቆላ. 4፡15)። ጳውሎስ ፊሊሞናን በክርስቶስ ወደ ማመን አምጥቶታል (ፊሊሞና 19ን ተመልከት)፥ ፊሊሞናም ለሌሎች ክርስቲያኖች በረከት ሆነ (ቁ. 7)።

ደብዳቤዎቹን እግዚአብሔርን በሚያመሰግኑና በሚያወድሱ ቃላት መክፈት የጳውሎስ ልማድ ነበር (ከገላትያ በስተቀር)። በምስጋናው ውስጥ፥ ጳውሎስ ወዳጁ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ስላለው ፍቅርና እምነት ይጠቅሳል። ፍቅሩ ተግባራዊ ነበር፡- በቃሉና በሥራው ቅዱሳንን አበረታቶአል።

ጳውሎስ ለፊሊሞና እንደሚጸልይለትና ሌሎች ክርስቶስን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር ምስክርነቱን ውጤታማ («የእምነትህ ህብረት») እንዲያደርግለት እንደሚጠይቅ ነግሮታል። እንዲሁም ወዳጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ባለው ነገር ሁሉ ጥልቅ መረዳት እንዲኖረው ጸልዮአል። ክርስቶስን በተሻለ ሁኔታ ባወቅነውና በረከቶቹን በተለማመድን መጠን፥ እነዚህን በረከቶች ለሌሎች ለማካፈል የበለጠ እንፈልጋለን።

2. አማላጁ ጳውሎስ (ፊሊሞና 8-16)

ግምቶች እንደሚያስረዱት በሮማ መንግሥት እንደሚገዙና የሚሸጡ ዕቃዎች የሚቆጠሩ ከ60 ሚሊዮን በላይ ወንድና ሴት ባሪያዎች ነበሩ። የተለመደው ምሳሌ «ብዙ ባሪያዎችን ማሳደር ብዙ ጠላቶች ማፍራት ነው» የሚል ነበር። አንድ ተራ ባሪያ በ500 ዲናር (ለተራ የጉልበት ሠራተኛ 1 ዲናር የቀን ደመወዙ ነበር)፥ የሚገዛ ሲሆን፥

የተማሩና ባለሙያ የሆኑት ባሪያዎች እስከ 50 000 ዲናሮች ያወጡ ነበር። ጌታ ባሪያውን ነጻ ሊያወጣ፥ ወይም ባሪያ ገንዘብ ካጠራቀመ ነጻነቱን ሊገዛ ይችል ነበር (የሐዋ. 22፡28)።

አንድ ባሪያ ከኮበለለ፥ ጌታው ስሙንና ምልክቱን ለባለሥልጣናት ያስመዘገብና ባሪያው «የሚፈለግ» በሚል ዝርዝር ውስጥ ይገባል። የጠፋውን ባሪያ ያገኘ ማንኛውም ነጻ ዜጋ በማረፊያ ቦታ ሊያቆየውና ለባለቤቱ አግላጅ ሊሆን እንኳን ይችል ነበር። ባሪያው ወዲያው ወደ ባለቤቱ አይመለስም፤ ወይም ወዲያው የሞት ፍርድ አይፈረድበትም። አንዳንድ ጌቶች ጨካኞች እንደነበሩ እውነት ቢሆንም (አንድ ሰው ባሪያውን ሰው የሚበሉ ዓሶች ወዳሉበት ገንዳ ወርውሮታል)፥ ብዙዎቹ አስተዋይና ሰብዓዊ ነበሩ። ለነገሩ ባሪያ፥ ውድና ዋጋ ያለው የግል ንብረት ስለ ነበር፥ እሱን ለማስወገድ ጌታውን የሚጎዳው ነበር።

ጳውሎስ ለአናሲሞስ ሲማልድ አምስት ጠንካራ ልመናዎችን አቅርቧል። ለሌሎች በረከትን እንዳመጣ ሰው የፊሊሞናን መልካም ስም በማንሳት ጀመረ። በቁጥር 8 ላይ «ስለዚህ» የሚለው ቃል «በዚህ መሠረት» የሚል ትርጉም አለው። ፊሊሞና «የሰውን ልብ የሚያሳርፍ» አማኝ ስለሆነ፥ የሐዋርያውን ልብ እንዲያሳርፍ ዕድል ሊሰጠው ፈለገ! ፊሊሞና ለብዙ ቅዱሳን በረከት ነበረ። አሁን ደግሞ ገና በቅርብ ለዳነውና ከባሮቹ አንዱ ለሆነው በረከት ሊሆን ይችላል!

ጳውሎስ ሐዋርያዊ ሥልጣኑን ሊጠቀምና ወዳጁን እንዲታዘዝ ሊያስገድደው ይችል ነበር፤ ዳሩ ግን በክርስቲያናዊ ፍቅር ሊለምነው መረጠ (ቁ. 9)። ጳውሎስ እንዴት ባለ ጥበብ ስለ ራሱ የግል ሁኔታ ፊሊሞናን እንዳሳሰበው አስተውል፡- «እኔ ጳውሎስ ሽማግሌው፥ አሁንም ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ እሥር የሆንሁ፥» (ቁ. 9)። እንደ ጳውሎስ መከራ እየተቀበለ ያለውን የቅዱስ ሰው ልመና ማን ወደ ጎን ሊተው ይችላል! ጳውሎስ በዚህ ጊዜ ምናልባት ስድሳ ዓመቱ ይሆናል፤ ግን በዚያን ዘመን ለወንዶች ይህ የዕድሜ ባለጸጋ የሚያሰኘው ዕድሜ ነበር። ከፊሊሞና መልካም ባሕርይና ክርስቲያናዊ ፍቅር ጋር የጳውሎስ ሦስተኛ ልመና የአናሲሞስ መለወጥ ነበር (ቁ. 10)። አናሲሞስ ከአሁን በኋላ «ባሪያ ብቻ» አልነበረም፤ አሁን በእምነት የጳውሎስ ልጅና የፊሊሞና ክርስቲያን ወንድም ነበር! በኢየሱስ ክርስቶስ «ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም» (ገላ. 3፡28)። ይህ የአናሲሞስ መለወጥ የሥራውን ሁኔታ ወይም የባርያነት ደረጃውን ይለውጣል ማለት አይደለም፤ ወይም ለሕጉና በጌታው ያለበትን ዕዳ ይሰርዛል ማለት አይደለም። ሆኖም

አናሲሞስ በእግዚአብሔር ፊትና በእግዚአብሔር ሕዝብ ፊት አዲስ አቋም ነበረው ማለት ነው። ፊሊሞና ደግሞ ይህንን ከግምት ውስጥ ማስገባት ነበረበት።

አራተኛው ልመና አናሲሞስ ጳውሎስ በሮም ለነበረው አገልግሎት ጠቃሚ እንደነበረ በመግለጽ የቀረበ ነበር (ቁ. 11-14)። አናሲሞስ የሚለው ቃል «ትርፋማ» (ትርፍ ያለው) ማለት ነው፤ ስለዚህ በቁጥር 11 ላይ ሥውር የሆነ የቃል ትርጉም አለ። (ፊሊሞና ማለት «የሚወድ» ወይም «ቸር» ማለት ነው። ባሪያው እንደ ስሙ እንዲኖር ከተጠበቀ ጌታውስ?) ጳውሎስ አናሲሞስን ይወድ ስለነበረ፥ አብሮት እንዲሠራ በሮም ያስቀረው ነበር፤ ግን ፊሊሞና ምን ማድረግ እንዳለበት ሊነግረው አልፈለገም ነበር። ጌታ ከልጆቹ የሚፈልገው በፍቅር የተነሣሳ የውዴታ መሥዋዕትና አገልግሎትን ነው።

አምስተኛው ልመና ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ይያያዛል (15-16)። ይህንን የንግግር ነጥብ ሲያቀርብ ጳውሎስ «ምናልባት» ቀኖናዊ (ግትር) አልነበረም። እንደ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በሕይወት ውስጥ የሚገኙትን በጣም አስቸጋሪ ልምምዶች እንኳን እንደሚቆጣጠር ማመን አለብን። እግዚአብሔር ጳውሎስን እዚያ አግኝቶት አማኝ እንዲሆን አናሲሞስን ወደ ሮም እንዲሄድ ፈቀደለት። (ፊሊሞናና ቤተሰቦቹ ለባሪያው እንደ መሰከሩለትና እንደጸለዩለት እርግጥ ነው።) አናሲሞስ ተመልሶ ሊመጣ በሚችልበት ሁኔታ ሄዶ ነበር። እሱና ጌታው ለዘለዓለም አብረው እንዲሆኑ ለአጭር ጊዜ ሄዶ ነበረ። ወደ ሮም ሲሄድ ባሪያ ሆኖ ሄደ። ወደ ቆላስይስ ሲመለስ ግን ወንድም ሆኖ ተመለሰ። በእነዚህ ጉዳዮች ውስጥ የእግዚአብሔር አሠራር እንዴት በቸርነት የተሞላ ነው!

እነዚህን አምስት ልመናዎች ስትመለከት፥ ጳውሎስ ወዳጁ ፊሊሞና ዓመፀኛ ባሪያውን መቀበልና ይቅር ማለት እንዳለበት እንዴት ባለ ትህትና እንዳሳመነው ማየት ትችላለህ፤ ነገር ግን ለፊሊሞና ይህንን ማድረግ ቀላል አይሆንም ነበር። በአናሲሞስ ጉዳይ ላይ ቀላል እርምጃ ቢወስድ፥ ሌሎች ባሪያዎች «ክርስቲያኖች እንዲሆኑ» እና እነርሱ ደግሞ ጌቶቻቸውን እንዲያቃልሉ ሊያደርግ ይችላል፤ ነገር ግን በሰውየው ጉዳይ ላይ ጠንካራ እርምጃ ቢወስድ፥ የፊሊሞናን ምስክርነትና የቆላስይስን አገልግሎት ሊያበላሽበት ይችላል።

እዚህ ላይ ጳውሎስ የተሟላ ምላሽ አቅርቧል። ሐዋርያውን በተመለከተ፥ ዋጋ የሚያስከፍል መፍትሔ ነበር፤ ነገር ግን ዋጋውን ለመክፈል ፈቃደኛ ነበር።

3. ጳውሎስ፥ ሽክም የሚሰማው ጓደኛ (ፊሊሞና 17-25)

«ጓደኛ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል ኮይኖኒያ ማለትም «በጋራ ማከናወን» ማለት ነው። በቁጥር 6 ላይ «ኅብረት» ተብሎ ተተርጉሟል። ጳውሎስ ከፊሊሞና ጋር «የሥራ ተባባሪ» ለመሆንና የአናሲሞስን ችግር እንዲፈታ ለመርዳት ፈቃደኛ ሆነ። ሁለት አሳቦችን አቅርቧል፡- «እንደኔ አድርገህ ተቀበለው» እና «ይህን (ማንኛውንም ከአንተ የሰረቀውን) በእኔ ላይ ቁጠር»።

እንደ ፊሊሞና አዲስ «ጓደኛ» ጳውሎስ ሮሜን ትቶ ወደ ቆላስይስ መሄድ አይችልም ነበር፤ ዳሩ ግን አናሲሞስን እንደ ግል ወኪሉ አድርጎ መላክ ይችል ነበር። ሐዋርያው አናሲሞስን የምትቀበልበት መንገድ እኔን በምትቀበልበት መንገድ ነው፥ እርሱ እንደ ልቤ ነውና ብሎአል (ቁ. 12)።

ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ለአማኞች ያደረገውን የሚያሳይ መግለጫ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በጣም በተያያዘ ሁኔታ የሚታዩ በመሆናቸው፥ እግዚአብሔር ልጁን እንደሚቀበል ይቀበላቸዋል! እኛ «በውድ ልጁ» ተቀባይነት ያገኘንና (ኤፌ. 1፡6) የእግዚአብሔርን ጽድቅ የለበስን (2ኛ ቆሮ. 5፡21) ነን። በራሳችን መልካም ሥራ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ በፍጹም አንችልም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር «በኢየሱስ ክርስቶስ» ወደ እርሱ ስንመጣ ሊቀበለን ይገባል። በቁጥር 17 ላይ «ተቀበለው» የሚለው ቃል «ወደ አንድ ቤተሰብ ክበብ ውስጥ ማስገባት» ማለት ነው። ባሪያ ወደ ጌታው ቤተሰብ ሲደባለቅ አስቡት! ዳሩ ግን አንድ ያጠፋ ኃጢአተኛ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ሲገባ ደግሞ አስቡት!

ጳውሎስ የሚናገረው ፊሊሞና የባሪያውን ወንጀሎች እንዲተውና አናሲሞስ ያለበትን ዕዳ እንዲረሳ አይደለም። ይልቁንም ጳውሎስ ራሱ ለመክፈል ፈቃደኛ ሆነ። «በእኔ ቁጠረው - እኔ እከፍለዋለሁ!» በቁጥር 19 ላይ ያለው አነጋገር በዚያን ዘመን የነበረ ሕጋዊ የተስፋ ቃል ማስታወሻ ይመስላል። ይህ ዕዳው እንደሚከፈል ለወዳጁ የሚገልጽ የጳውሎስ ማረጋገጫ ነበር።

ችግሩን ለመፍታት ከፍቅር የበለጠ ነገር ያስፈልጋል፤ ፍቅር ዋጋ መክፈል አለበት። እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ ቢወድም፥ ዓለም ሁሉ

ስላልዳነ፥ በፍቅሩ አያድነንም። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን በጸጋው ያድናል (ኤፌ. 2፡8-9)፥ ጸጋ ደግሞ ዋጋን የሚከፍል ፍቅር ነው። እግዚአብሔር ለራሱ ሕግ ታማኝ መሆን ስላለበት፥ በቅድስናው እኛ ያለብንን ዕዳ ዝም ብሎ ሊያልፈው አይችልም። ስለዚህ ዕዳችንን ከፈለልን!

የሥነ-መለኮት ሰዎች ይህንን «የማዛወር ትምህርት» ይሉታል። «ማዛወር» ማለት «ሌላውን ተጠያቂ ማድረግ» ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት፥ ኃጢአቴ ወደ እርሱ ተዛወረ፤ እኔ መሆን የሚገባኝን እርሱ ሆነ። እንደ አዳኜ አድርጌ ስታመንበት፥ የእርሱ ጽድቅ ለኔ ተዛወረ፤ በመሆኑም አሁን እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ይቀበለኛል። ኢየሱስ ለአብ «እኔ ዕዳውን በመስቀል ላይ ሙሉ በሙሉ ስለከፈልኩለት ከአሁን በኋላ የአንተ ዕዳ የለበትም። እኔን እንደምትቀበል ተቀበለው። ወደ ቤተሰቡ መሃል እንዲገባ ፍቀድለት» ይለዋል።

ሆኖም በክርስቶስ በኩል ተቀባይነትን በማግኘትና በክርስቶስ ዘንድ ተቀባይነት ያለው በመሆን መካከል ልዩነት እንዳለ መረዳት አለብን። ለደኅንነት ኢየሱስ ክርስቶስን ያመነ ማንም በእርሱ በኩል ተቀባይነትን ያገኘ ነው (ሮሜ 4፡ 1-4)፤ ነገር ግን አማኝ በየዕለት ኑሮው በጌታ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ለመሆን በእግዚአብሔር እርዳታ መጣር አለበት (ሮሜ 12፡2 እና 14፡18፤ ዕብ. 12፡28፤ 2ኛ ቆሮ 5፡9)። አብ በልጁ ያመኑትን ይመለከትና ለልጁ እንደተናገረው «በእናንተ ደስ ይለኛል» ለማለት ይፈልጋል።

ቁጥር 19 ፊሊሞናን በክርስቶስ ወዳለ እምነት የመራው ጳውሎስ እንደነበረ ይናገራል። ጳውሎስ ይህንን ልዩ የሆነ ግንኙነት ወዳጁ አናሲሞስን እንዲቀበለው ለማበረታታት እንደ ተጨማሪ የማሳመኛ አሳብ ተጠቀመበት። ፊሊሞናና አናሲሞስ በጌታ ያሉ መንፈሳውያን ወንድማማቾች ብቻ አልነበሩም፤ ነገር ግን ሁለቱም አንድ «መንፈሳዊ አባት» ነበራቸው - እርሱም ጳውሎስ ነው! (ቁ. 10 እና 1ኛ ቆሮ. 4፡ 15ን ተመልከት)።

በቁጥር 21 ላይ ፊሊሞና የበለጠ እንዲያደርግና አናሲሞስን ነጻ እንዲያደርገው ጳውሎስ እየጠቆመ ይሆን? እንደዚህ ከሆነ ለምን በቀጥታ ባርነትን አይኮንንም ነበር? ያን ለማድረግ ይህ ደብዳቤ ትክክለኛ ቦታ ይሆን ነበር። ብዙ ጊዜ ለባሪያዎችና ለጌቶቻቸው የምክር ቃል ቢኖረውም ኤፌ. 6፡5-9፤ ቆላ. 3፡22-4፡1፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡1-2፤ ቲቶ

2፡9-10)፥ ጳውሎስ በዚህም ሆነ በሌሎች ደብዳቤዎቹ ባርነትን አልኮነነም ነበር። በርግጥ ክርስቲያን ባሪያዎች ከቻሉ ነጻነታቸውን እንዲያገኙ አበረታቷቸዋል (1ኛ ቆሮ. 7፡21-24)።

በአሜሪካ የእርስ በርስ ጦርነት ጊዜ ሁለቱም ወገኖች ባርነትን ለመደገፍ ወይም ለመቃወም የሚያቀርቧቸውን አሳቦች እውነትነት ለግረጋገጥ አንዱን መጽሐፍ ቅዱስን ነበር የተጠቀሙት። ከታወቁት ክርክሮች ውስጥ አንዱ «ባርነት ይህን ያህል የተሳሳተ ነገር ከሆነ፥ ኢየሱስና ሐዋርያት ይህንን በተመለከተ ለምን ምንም ሳይናገሩ አለፉ? ጳውሎስ ባርነትን ሥርዓት ለማስያዝ መመሪያዎችን ሰጠ እንጂ አልኮነነውም» የሚል ነበር።

በጣም ጥሩ ከሆኑት ግብራሪያዎች አንዱ አሌክሳንደር ማክላረን ዘ ኤክስፓዚተርስ ባይብል በሚል ርእስ በቆላስይስ መጽሐፍ ላይ ባዘጋጁት የመጽሐፍ ቅዱስ ግብራሪያ ውስጥ በዘ ኤክስፖዚተርስ ባይብል (*The Expositor's Bible*) ተሰጥቷል።

«በመጀመሪያ፥ የክርስትና መልእክት በቅድምያ ለግለሰቦች ሲሆን፥ ለኅብረተሰቡ የሚሰጠው አትኩሮት በሁለተኛ ደረጃ ብቻ ነው። ተጽዕኖ ያሳደረባቸው ክፍሎች ብዙሀኑን እንዲለውጡ ይተዋቸዋል። ሁለተኛ፥ በመንፈሳዊና ሥነ-ምግባራዊ ስሜቶች ላይ ይሠራል። በተግባራዊ እንቅስቃሴዎችና በተቋሞች ላይ የሚሠራው ከዚያ በኋላና ይህንኑ መሠረት በማድረግ ብቻ ነው። ሦስተኛ፥ ዓመፅን ይጠላል፤ ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ የበራውን ሕሊና ያምናል፤ ስለዚህ ከምንም ፖለቲካዊም ሆነ ማኅበራዊ መዋቅር ጋር ቀጥተኛ ተሳትፎ አያደርግም፤ ነገር ግን እነዚህን በሚገባ የሚለውጡ መመሪያዎችን በማዘጋጀት፥ በሰዎች አእምሮ ውስጥ ሰርፀው እንዲገቡ ይተዋቸዋል።»

የቀድሞ ክርስቲያናች በባርነት ላይ ግልጽ የሆን ዘመቻ ጀምረው ቢሆን ኖሮ፥ በተቃውሞው በደቀቁና የወንጌል መልእክት ከማኅበራዊና ፖለቲካዊ መርሐ ግብር ጋር በተምታታ ነበር። በእንግሊዝና በአሜሪካ ባርነትን ለማሸነፍ ለሰዎች ምን ያህል አስቸጋሪ እንደነበረ አስቡት። እነዚያ ሁለት አገሮች ደግሞ መንገዱን ለማዘጋጀት የሚረዳ ጠቅላላ ትምህርትና የክርስትና ሃይማኖት ነበራቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንኳን በዘመናዊ የሰብዓዊ መብቶች እንቅስቃሴ ውስጥ ስላሉትም ትግሎች አስቡ። በአሥራ ዘጠነኛውና በሃያኛው ክፍል ዘመን ለአርነት የሚደረገው ትግል አስቸጋሪ ከሆነ፥ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመንግ ትግሉ ምን ይመስል ይሆን!

ክርስቲያኖች የምድር ጨውና የዓለም ብርሃን ስለሆኑ (ማቴ. 5፡13-16) መንፈሳዊ ተጽዕኖአቸው ለእግዚአብሔር ክብር በጎበረተ ሰብ መካክል መሰማትና መታወቅ አለበት። እግዚአብሔር ዮሴፍን በግብፅ፥ አስቴርንና ነህምያን በፋርስ፥ እንዲሁም ዳንኤልን በባቢሎን ተጠቅሟል፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ደግሞ ጌታን በታማኝነት ያገለገሉ በፖለቲካ ሥልጣን የነበሩ አማኞች ነበሩ፤ ነገር ግን በሮማ ግዛት የነበሩ ክርስቲያኖች ዛሬ እኛ እንደምንችለው በአካባቢ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ መዋቅሮች ውስጥ መሥራት አይችሉም ነበር፤ ስለዚህ ለውጥ ለማምጣት ምንም የፖለቲካ ሥልጣን አልነበራቸውም። ምንም እንኳ ባርነትን ለማብቃት ዘመናት የወሰደ ቢሆንም ለውጡ ከውስጥ መፍለቅ ነበረበት።

ጳውሎስ በተለመዱት የግል ጥያቄዎቹና ሰላምታዎቹ ደብዳቤውን ይፈጽማል። እንደሚፈታና ፊሊሞናንና አፍብያን በቆላስይስ እንደሚጎበኛቸው ሙሉ በሙሉ ተስፋ አድርጎ ነበር። ሐዋርያውን ፊት ለፊት ሲገናኘው እንዳያፍር ስለሚፈልግ ይህ ጭብጥ እንኳን ፊሊሞና የጳውሎስን መመሪያዎች እንዲከተል ያበረታታዋል።

አስቀድመን እንደተመለከትነው፥ ኤጳፍራ ምናልባት የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ይሆናል፤ ጳውሎስን ለማገዝ ደግሞ ወደ ሮም ሄዷል። ለጳውሎስ ብሎ «በፈቃዱ የታሠረ» ይሁን ወይም በትክክል በሮማውያን ታሥሮ ይሁን አናውቅም። ለክርስቶስና ለጳውሎስ ላለው መሰጠት ልናደንቀው ይገባናል።

በመጀመሪያው የወንጌል ተልእኮ ጉዞው ከጳውሎስ ተለይቶ የነበረው (የሐዋ. 12፡12፥ 25፤ 15፡36-41) ወጣቱ ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ከጳውሎስ ጋር ነበር (ቆላ. 4፡10)። ጳውሎስ ማርቆስን ይቅር ብሎት በታመነው አገልግሎቱ ደስ ተሰኝቶ ነበር (2ኛ ጢሞ. 4፡11ን ተመልከት)።

ከተሰንሎንቄ የነበረ አርስጥሮኮስ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም፥ ከዚያም ወደ ሮም ሲሄድ አብሮት ሄዶ ነበር (የሐዋ. 19፡29፤ 27፡2)። ዴማስ በጳውሎስ ደብዳቤዎች ውስጥ ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል፡- «አብሮት የሚሠራ ዴማስ» (ፊሊሞ. 24)፥ «ዴማስ» (ቆላ. 4፡14)፥ «ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛል» (2ኛ ጢሞ. 4፡10)። ማርቆስ ወድቆ ነበር ግን ተመልሷል። ዴማስ ደህና እየሠራ ይመስል ነበር ግን በኋላ ወደቀ።

ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር የነበረ፥ ያገለገለውና በኋላም የሉቃስ ወንጌልንና የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን የጻፈ ተወዳጅ ሐኪም ነበር (ቆላ. 4፡14)።

የጳውሎስ ቡራኬ ለደብዳቤዎቹ «ሕጋዊ ፊርማው» ነበር (2ኛ ተሰ. 3፡17-18)፤ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ጸጋ ያጎላ ነበር። ከሁሉም በላይ፥ እንድንድን ያስቻለን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ነበር (ኤፌ. 2፡1-10)። «ያንን በእኔ ቁጠረው! እኔን እንደምትቀበል እነርሱን ተቀበላቸው!» ያለውም እርሱ ነበር።

በዶ/ር ዋረን ዌርዝቢ የተዘጋጁ የ«...ሁን» ተከታታይ መጻሕፍት

1. ለጌታ የተገዛህ ሁን (ማቴዎስ)
2. ርኅሩኅ ሁን (ሉቃስ 1–13)
3. የበረታህ ሁን (ሉቃስ 14–24)
4. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተመላለስ (የሐዋርያት ሥራ 1–12)
5. ደፍረህ መስክር (የሐዋርያት ሥራ 13–28)
6. ተጽናና (2ኛ ቆሮንቶስ)
7. አርነት መውጣት (ገላትያ)
8. ደስተኛ ሁን (ፊልጵስዩስ)
9. ፍጹም ሁን (ቆላስይስ)
10. ለምጽአቱ ተዘጋጅ (1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ)
11. ታማኝ ሁን (1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ፥ ቲቶ፥ ፊልሞና)
12. በብስለት ማደግ (ያዕቆብ)
13. ንቃ (2ኛ ጴጥሮስ፥ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ፥ ይሁዳ)
14. እውነተኛ ሁን (1ኛ ዮሐንስ)
15. ድል አድራጊ ሁን (ራእይ)